# መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት

## የሃይማኖትና የሥርዓት መጽሐፍ

---

ተጽሕፈ እመምህር ዶ/ር ዘበነ ለማ

ከመምህር ዶ/ር ዘበነ ለማ ተጻፈ

ሚያዝያ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

## ማስታወሻነቱ

1ኛ. ከህፃንነት ዕድሜ ጀምሮ ጥልቅ የሆነ የቤተክርስቲያንን ምሥጢር፣ ትርጓሜና ሥርዓተ ቅዳሴን ካስተማሩኝ ታላቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ ብፁዕ አቡነ ሰላማ።

2ኛ. ትርጓሜ መጻሕፍትን ካስተማሩኝ፡ በአእምሮዬ ውስጥ ለቀረጹት በልቡናዬም ካሳደሩትና የግእዝ ቋንቋን ካስተማሩኝ ለታላቁ መምህር ለመጋቤ ምሥጢር አለቃ መሠረት ተሰማ።

3ኛ. በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ካስተማሩኝ መምህራን ሁሉ ፤ በተለይም ሐዲስን ካስተማሩን ለብጹዕ አቡነ እንድርያስ (ለቀድሞ ሊቀ ሊቃውንት አባ ኅሀ ጽባሕ)፤ አሁን በሕይወተ ሥጋ ለሌሉት ለብሉዩ ሊቅ ለመምህር መጋቤ ብሉይ መዘምር ታዬ።

4ኛ. ለወላጅ እናቴ ለወ/ሮ አስገደች መኩሪያ ይሁንልኝ።

## ምስጋና

ለፈጣሪዬ ለልዑል እግዚአብሔርና ለእናቱ ለድንግል ማርያም ይህ የዘላለም ምስጋናዬ ነው።

በሥራዬ ሁሉ ላልተለየችኝ፡ ለአገልግሎት እንድፋጠን ዘወትር ለምትረዳኝ ለተከበረችው ውድ ባለቤቴ ኅሊና ታደሰ፤

በአሜሪካን አገር ለሚገኘው ለደብረ ገነት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን፤ በገንዘባቸውና በጸሎታቸው ለረዱኝ ሁሉ፤ መጽሐፍ ለምን አትጽፍም እያሉ ሲያሳስቡኝ ለነበሩ ይሁንልኝ።

# መቅድም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ዘለዓለም አዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ጽሒፈ መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት።

በአብ ስም አምኜ አብን ወካዲ ብዬ፡ በወልድ ስም አምኜ ወልድን ተወካዲ ብዬ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብዬ፡ በስም በአካል በግብር ሦስት ብዬ በመለኮት በአዘዝ በአገዛዝ አንድ አምላክ ብዬ በረድኤተ እግዚአብሔር መጽሐፈ አሚን ወሥርዓትን አጽፋለሁ።

አገራችን ኢትዮጵያ ከዓለም ሁሉ ቀድማ መጽሐፈ ኦሪትን ከነትምህርቱ፣ ክህነተ ኦሪትን ከነ ሥርዓቱ፣ ጽሌ ኦሪትን ከነመሥዋዕቱ ብኩርናን ከነትንቢቱ ከአምላክ የተቀበለች ናት።ቀጥሎም በሕገ ወንጌል ቀድማ ያመነች በክርስቶስ መሠረት ላይ የተመሠረተች ናት።

፹፩ዱን ቅዱሳት መጻሕፍት ተቀብላ ንባባቸውን ከትርጓሚያቸው አስማምታ የያዘች ብቸኛ ቤተክርስቲያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ናት። ቅዱሳን ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሊቃውንት የተነበዩትን፣ የሰበኩትን፣ የተረጎሙትን ብሉዩን፣ ሐዲሱን፣ ሊቃውንቱን፣ አዋልዱን ትውፊቱ ሳይቀር ይዛ ያለች ቤተክርስቲያን ናት።

እኔም ይህንን መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት የሚለውን መጽሐፍ በእግዚአብሔር ፈቃድ ስጽፍላችሁ የቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ሃይማኖትና ሥርዓት ብሎም ትውፊት ከመሠረቱ ጀምሮ ሲያያዝ የመጣውን አውቃችሁ እንድታሳውቁ፡ በቅን ልቡና በንጹሕ ኅሊና እየመረመራችሁ ሃይማኖታችሁን ታጸኑ ዘንድ የጠፋትን ትመልሱ ዘንድ ሃይማኖታዊ ባህላችሁን ትጠብቁ ዘንድ ሁሉንም በየዘመዱ አርጌ መጻፌን ከአንባቢያን አሳስባለሁ።

መምህር ዶ/ር ዘበነ ለማ

# ማውጫ


ሃይማኖት .......... 15
ሃይማኖትና ምግባር .......... 17
ክርስትና .......... 19
ኦርቶዶክስ .......... 20
ተዋሕዶ .......... 22
ሥነ-ፍጥረት .......... 24
ሃያ ሁለቱ (፳፪ቱ) ሥነ-ፍጥረታት .......... 25
ሰባቱ (7ቱ) ሰማያት .......... 29
ሦስቱ ሕግጋት .......... 31
ኢትዮጵያና ሕገ ልቡና .......... 31
ኢትዮጵያና ሕገ ኦሪት .......... 34
ኢትዮጵያና ሕገ ወንጌል (ክርስትና) .......... 35
የሚበሉና የማይበሉ ምግቦች .......... 38
አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት .......... 41
ምሥጢረ ሥላሴ .......... 42
ምሥጢረ ሥጋዌ .......... 46
ከማን ሰው ሆነ? .......... 46
ሰው የሆነው ማነው? .......... 47
ለምን ሰው ሆነ? .......... 47
ምሥጢረ ጥምቀት .......... 49
በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁም- .......... 50
በውኃ መጠመቅ .......... 50
በዮሐንስ መጠመቅ .......... 51
ምሥጢር መባሉ- .......... 52
ምሥጢረ ቁርባን .......... 52
ምሥጢር ለምን ተባለ? .......... 53

በምሥጢረ ቁርባን የሞቱ መታሰቢያነት ........ 54

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ........ 55

ምሥጢር የተባለበት ........ 59

ንፍሐተ ቀርን በዕለተ ትንሣኤ ........ 61

ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን . . . . . . . . 63

1. ምሥጢረ ጥምቀት፡- ........ 63

ከመጠመቅ ዕድሜያምን ያህል መሆን አለበት ከሚለው ፡- ........ 64

ማዕተብና ክታብ ........ 65

፩፡ ነጭና ቀይ ማዕተብ፡- ........ 65

፪. ጥቁር ማዕተብ ........ 66

ክታብ ........ 66

2. ምሥጢረ ሜሮን፡- ........ 67

3. ምሥጢረ ቁርባን፡- ........ 67

በመቁረብ ምን እናገኛለን? ........ 67

ሥጋና ደሙ የሚሰጠው ለማን ነው? ........ 68

4. ምሥጢረ ክህነት፡- ........ 68

ዲያቆናዊት ........ 69

ዓቃቢት ........ 69

5. ምሥጢረ ተክሊል፡- ........ 70

6. ምሥጢረ ንስሐ፡- ........ 70

ንስሐ ለማን ነው የሚገባው ? ........ 71

ንስሐ እንዴት ነው የሚገባው ? ........ 72

ራስን ለካህናት ማሳየት ........ 72

7. ምሥጢረ ቀንዲል፡- ........ 74

የጌታ በዓላት . . . . . . . . 82

ዘጠኙ ዐበይት በዓላት ........ 82

ዘጠኙ የጌታችን ንኡሳን በዓላት ........ 93

አሥራ ሦስቱ (፲፫ቱ) ሕማማተ መስቀል .......................... 99
አምስቱ ቅንዋት (ችንካሮች) .......................... 103
ሰባቱ (፯ቱ) አጽራሐ መስቀል .......................... 104
ሰባቱ (7ቱ) ተአምራት በጌታ ስቅለት .......................... 108
ሥርዓተ ግዝረት .......................... 110
ግርዛት ከማን? መቼ? .......................... 111
መጽሐፍ ቅዱስ .......................... 113
የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት .......................... 114
የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት .......................... 117
ወንጌል .......................... 122
አርባዕቱ (፬ቱ) ወንጌላውያን .......................... 122
አዋልድ መጻሕፍት .......................... 129
፩. የገድል መጻሕፍት፡- .......................... 130
፪. የድርሳን መጻሕፍት፡- .......................... 131
፫. የተአምር መጻሕፍት፡- .......................... 131
፬. የመልክአ መጻሕፍት፡- .......................... 132
ትውፊት .......................... 134
አሠርቱ ( ፲ቱ) ቃላተ ኦሪት .......................... 138
ሰንበት .......................... 142
ቅዳሜ .......................... 142
እሑድ .......................... 144
እሑድ በብሉይ ኪዳን .......................... 145
እሑድ በሐዲስ ኪዳን .......................... 147
የጽዋ ማኅበር ሰንበቴ .......................... 150
የጽዋ ማኅበር፡- .......................... 150
ሰንበቴ .......................... 152
ስድስቱ (፮ቱ) ቃላተ ወንጌል .......................... 156
ስድስቱ ጥያቄዎች በጊዜ ምጽአት .......................... 157
እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም .......................... 158

ወላዲተ አምላክ መሆኗ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 160

የጸጋና የአክብሮት ስግደትና ምስጋና ለእመቤታችን . . . . . . . . . . 161

የእመቤታችን ቅድስናና ንጽሕና . . . . . . . . . . . . . . . . . . 165

ቅድስት ........................................ 165

ድንግል ........................................ 166

የእመቤታችን ዕድሜ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 168

ርእሳነ አበው . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 169

የዕድሜ ከሺህ ማነስ ........................................ 173

የዕድሜ መጠን ........................................ 176

አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 179

ቅዱሳን ነቢያት (ነቢያን) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 184

የዐበይት ነቢያት ስማቸው ከነትርጉሙ ........................................ 185

ደቂቀ ነቢያት ስማቸው ከነትርጉሙ ........................................ 185

ቅዱሳት ነቢያት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 188

አሥራ አምስቱ ነቢያት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 189

የጌታ ቤተሰቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 190

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 191

የሐዋርያቱ ስም ትርጉም ........................................ 192

፯ቱ ሊቃነ መላእክት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 196

አርባዕቱ እንስሳት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 197

መልካቸው፦ ........................................ 198

አገልግሎታቸው፦ ........................................ 199

ስማቸው ........................................ 200

ሃያ አራቱ (፳፬ቱ) ካህናተ ሰማይ . . . . . . . . . . . . . . . . 201

ቁጥራቸው ፳፬ መሆኑ ........................................ 201

አገልግሎታቸው ........................................ 201

ቅዱሳን ሰዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 204

የሌሎችን መልክ ይመስላሉ ........................................ 204

የቅዱሳን በረከታቸው ........................................ 207

የቅዱሳን አማላጅነታቸው በዚህ ዓለም ........ 208

የቅዱሳን አማላጅነታቸው ከምድራዊው ዓለም በኋላ በዐጸደ ነፍስ ........ 211

የቅዱሳን መታሰቢያቸው ........ 214

ታቦት በቅዱሳን ስም ........ 214

ሥርዓተ ምንኩስናና ብሕትውና ........ 216

አሥርቱ መዓርጋት ........ 221

ባለሥላሳ፣ ስድሳና ባለመቶ የመዓርጋት ምሥጢር ........ 223

ሠማኒ፣ማዕከላዊና ፍጹም ........ 224

ንጽሐ ሥጋ፣ንጽሐ ነፍስና ንጽሐ ልቡና ........ 225

ቅዱስ መስቀል ........ 226

የመስቀል ምልክት በሰማይ ........ 227

የመስቀል ምልክት በዘመነ ብሉይ ........ 228

የመስቀል ምልክት በዘመነ ሐዲስ ........ 230

ስግደት ለመስቀል ........ 231

መስቀልን መሳምና መሳለም ........ 232

መስቀል ልዩ ነው ........ 234

የመስቀል ጠላቶች ........ 234

ጥምቀት ........ 236

በጥምቀት ያለ ምሥጢር ........ 236

፲፪ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስና በእንተ እግዚእትነ ማርያም ........ 238

መቅጠሪያ ........ 239

ቤተ መቅደስ ........ 241

ታቦት ........ 245

የታቦት ኃይል ........ 247

ታቦት በአዲስ ኪዳንና በሰማይ ........ 247

ስግደት ........ 249

የስግደት ዓይነት ........ 249

ሦስቱ የአሰጋገድ ዓይነቶች ........ 251

በስግደት ውስጥ ያለ ምሥጢር ........ 252

የሚሰገድበትና የማይሰገድበት ጊዜ ........ 255

አምስቱ የግዝት በዓላት በዓለ አምሳን (፶ን) ጨምሮ ........ 256

አመራረጣቸው ........ 257

ሥርዓተ ቅዳሴ ........ 261

አሥራ አራት (፲፬) ቅዳሴ ........ 262

ግእዝ ዕዝልና አራራይ የሚቀደስበት ጊዜ ........ 265

የቅዳሴ ክፍል ........ 266

ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ........ 266

የቀዳሾች ልዑካን ቁጥር ምስጢር ........ 268

ደጀ ሰላም ........ 270

የመሳለሚያ ምልክት ........ 271

የአለባበስ ሥርዓት በቤተክርስቲያን ........ 274

ልብሰ ተክህኖ ........ 274

ሀ. የካህንና የዲያቆን ልብስ፡- ........ 275

ለ. እክሊል (ቆብ)፡- ........ 275

ሐ. ሞጣሕት፡- ........ 276

ልብሰ ተክህኖ በመቅደሱና ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ........ 276

የካህናት ጥምጥም፡- ........ 277

የምእመናን አለባበስ በቤተክርስቲያን ........ 278

የልብስ ነጭ መሆኑ ወይም መታጠቡ ........ 279

የሴቶች ራሳቸውን መከናነብ ........ 281

በቅዳሴ ጊዜ ከንንብ የሚወልቅበት ጊዜ ........ 282

የነጠላ፣ ጋቢ ወይም ኩታ አለባበስ ........ 282

መጋረጃ - መንጦላዕት ........ 284

ሰባቱ ኪዳናት ........ 286

ንዋያተ ቅድሳትና ምሥጢራቸው ........ 287

መሶበ ወርቅ ........ 287

ጽዋዕ (ጽዋ) ........ 289

ዕርፈ መስቀል ........ 290

ጥላ ........ 291

ጽንሐሕ (ጥና) ........ 292

ንዋየ ቅድሳት ከሌላ አገልግሎት አይውሉም ........ 294

ቅዱሳን ሥዕላት ........ 296

ስግደት ለሥዕላት ........ 298

ቅዱሳት ሥዕላት ያድናሉ ........ 300

ጠበል (ጸበል) ........ 301

ጠበል በብሉይ ኪዳን ........ 301

ጠበል በሐዲስ ኪዳን ........ 303

ጠበል በሰማዩ መቅደስ ........ 304

ዕጣን ........ 305

ዕጣን በሰማዩ መቅደስ ........ 305

ዕጣን በሕገ ልቡና ........ 305

ዕጣን በዘመነ ብሉይ ........ 306

ዕጣን በዘመነ ሐዲስ ........ 306

የሚጠን ሥርዓት ........ 307

የዕጣን ምሳሌነት ........ 309

የቅዱሳ እምነቱ ቆቀር ዕጣን ምሳሌነት ........ 311

የዘጠኙ ዕፀው ዕጣን ስም ........ 311

ከጣዖት የሚያጥን ይጠፋል ........ 312

ሕመት ........ 314

ቅዱስ አፈር ........ 315

ዳቦ፣ ንፍሮና የንፍሮ ውኃ ........ 316

መሥዋዕት፣ እሥራት፣ በኩራትና ቀዳምያት ........ 318

መሥዋዕት ........ 318
አሥራት ........ 320
የአሥራት አሥራት ........ 321
በኵራት ........ 322
ቀዳሚት ........ 324
ዜማ ቤተክርስቲያን ........ 326
፯ቱ (7) አጽዋማት ........ 329
ዐቢይ ጾም ........ 329
ጾመ ነቢያት ........ 330
ረቡዕና ዓርብ (ጾመ ድኅነት) ........ 330
ጾመ ነነዌ ........ 330
ጾመ ገሃድ ........ 331
ጾመ ሐዋርያት ........ 331
ጾመ ፍልሰታ ለማርያም ........ 332
የንስሐና የፈቃድ ጾም ........ 333
ጸሎትና ሥርዓቱ ........ 334
ጸሎት በቀን ሰባት ጊዜ ........ 335
ከጸሎት ወደ ቤተክሰርስቲያን መሄድ ........ 338
በጸሎት የሚደረጉ ሥርዓታት ........ 340
ስእለት ........ 343
የሠርግ ሥርዐት ........ 348
ቀብርና ለቅሶ ........ 350
አቀባበር ........ 350
የለቅሶ ሥርዓት፡ ........ 352
እጅ መታጠብ፡ - ........ 352
ሚከሰት፡- ........ 353
ነጭ ክር፡- ........ 353

ሐሠሌት፡- ........ 354

ፍትሐትና ተዝካር ........ 355

የሙታን መታሰቢያ ቀናት ........ 358

ምጽዋት ........ 360

ማኅሌትና ሰዓታት ........ 363

የማኅሌት ንዋያት ........ 365

ከበሮ ........ 365

የከበሮ አሠራርና አመታት ትርጉም ........ 366

ጸናጽል ........ 368

መቋሚያ ........ 370

አክሊታ ........ 371

ጭብጨባ ........ 372

ሽብሸባ ........ 374

ምእመናን ከዝማሬ የሚጠቀሙባቸው ........ 375

መሰንቆ ........ 375

በገና ........ 376

መለከት ........ 379

ክራር ........ 381

ዋሽንት፣ እንዚራ፣ እምቢልታ ........ 382

# ሃይማኖት

ሃይማኖት በእግዚአብሔር የተሰጠ ፀጋ ነው። ሰውን እግዚአብሔር ሲፈጥር በአፍንጫውም የሀይወት እስትንፋስ እፍ ብሎ ሕያው ሲያደርገው በልቡና በአእምሮ የተሣከበትን ረቂቅ የሆነ ሐሳብ ሃይማኖትን ቀርጾበታል። ከዚሀም የተነሣ ሰው ፈጣሪውን የሚያውቅበት የሚያምንበትና የሚያመልክበት መንገድ ሃይማኖት ነው። ስለዚሀም ይሀ መንገድ አንድ ብቻ መሆኑን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲሀ ያስተምረናል።

> "አሐዱ እግዚአብሔር ወአሐቲ ሃይማኖት ወአሐቲ ጥምቀት"
>
> "እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ሃይማኖትም አንዲት ናት፤ ጥምቀት አንዲት ናት።" ኤፌሶን ፬፡፭ (4፡5)

ይሀ ቃል እውነት ነው። ዓለምን የፈጠረ አንድ እግዚአብሔር ነው። ይሀ እግዚአብሔር ተስፋ የሚደረግባት የሚታመንባት ሃይማኖትም አንዲት ናት። ይሀች ሃይማኖት በልጅነት የምትሰጥበት ጥምቀትም አንዲት ናት።

በአጠቃላይ በቁም ትርጉም ሃይማኖት የሚለው ቃል እምነት፣ማመን፣ መታመንና ተስፋ ይሆናል። ይሀ ደግሞ የሚፈጸመው እምስቱን አዕማደ ምሥጢራት በማመን ሰባቱንም ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በመቀበል ነው። ይሀን የሚያምን ሃይማኖተኛ ተብሎ ይጠራል። የሃይማኖት ቅድስትና የሃይማኖት ርትዕት እማኝ ይባላል። ይሀችውም ቅድስትና ርትዕት የተባለችው አንድ ጊዜ የተሰጠች የቅዱሳን ሃይማኖት እርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ነች፤ ስለዚሀችም የቀናች ሃይማኖት እመከራችሁ ዘንድ ግደታ አለብኝ የሚለን የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብ ወንድም ቅዱስ ይሁዳ ነው። የይሁዳ ፡፩፡፫ (1፡3)

በግእዙ "ወአስተበቍዐክሙ ከመ ትትቀነይዋ ለእንተ ተውህበት ለቅዱሳን ሃይማኖት" በቀጥታ ትርጓሜው "ለቅዱሳን የተሰጣቸውንም ሃይማኖት እንድታገለግሏት እማልዳችኋለሁ" ይላል ይሀም በምሥጢሩ ለሐዋርያት

የተነገራቸውን ሃይማኖት ትይዟት ትማሯት ዘንድ አለምናችኋለሁ የሚል ነው። እግዚአብሔር ፈጥሮ በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል የገለጠልንን የድኅነታችንን ነገር አምነት እርሱን ማምለክ ሃይማኖት ነው። ይህንን የበለጠ ትረዱ ዘንድ አንደኛ፡ "ጸሎተ ሃይማኖት" ሁለተኛ "ሃይማኖተ አበውን" መመልከት ማንበብ፣ መጠየቅና መረዳት ያስፈልጋል። እንግዲህ አንባብያን ሆይ ሃይማኖት አንዲት አንጂ ሁለት ሦስት ወይም መቶ ሺ የሚል በመጽሐፍ ቅዱስ አልተነገረምና በእውነተኛይቱ ርትዕት፣ ቅድስት በተባለች በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ አምነት እስከ ሞት ድረስ ጽኑ።

> "እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ከማነጽ አየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም አየጸለያችሁ፡ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ። ፩፡፳-፳፩ (1፡20-21)

# ሃይማኖትና ምግባር

እግዚአብሔር አምላክ በመጻሕፍቱ እንደነገረን በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ወደ መንግሥተ ሰማያት ከመግባት የሚያስፈልጉ ሁለት ዓቢይ ነገሮች ናቸው። እነዚህም ሃይማኖትና ምግባር ናቸው። ይህም እምነትና መልካም ሥራ ማለት ነው።

ሃይማኖትና ምግባር በአንድ ላይ ካልተጣመሩ መዳን አይቻልም። ሃይማኖት ብቻውን ወይም ምግባር ብቻውን አያድንም። ቅዱስ ያዕቆብ ይህን ሲገልጽ ሰይጣን ያምናል መልካም ሥራ ስለሌለው አይድንም ብሎ ሁለቱ ካልተዋሐዱ ትርጉም እንደሚያጣ ተናግሯል።

> "አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።" ያዕ ፪፡ ፲፱ (2፡19)

ስለዚህ በእምነት ብቻ እድናለሁ ብሎ ማሰብ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ነው። ስለዚህ ሐዋርያውም ጨምሮ በምሳሌ ሲያስተምረን፡-

> "ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።" ያዕ ፪፡፳፮ (2፡26)

ስለዚህም ለአንድ ክርስቲያን ምግባር ወይም በጎ ሥራ መሥራት ከሃይማኖት ጋር መንግሥተ ሰማያትን ከመውረስ የሚያበቃ ነው። በማቴዎስ ወንጌል እንደተጻፈ ጌታ ከፍርድ ሲመጣ የሚጠይቀው የምግባር ጥያቄ ነው። ማቴ ፳፭ ፥ ፴፬ (25፡34)። ጻድቃንም ሆኑ ኃጥአን በምድር የሚሠሩት ይከተላቸዋል።

> "ሥራቸውም ይከተላቸዋል" ራዕ ፲፬፡፲፫ (14፡13)

ይህን ሳንረዳ በዕምነት ብቻ ወይም በጸጋው ብቻ እንድናለን ብለን በጎ ምግባርን ሳንፈጽም ብንቀር አስደንጋጭ የሆነ የጌታ ቃል በእኛ ላይ ተቃቷል፡-

"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ

ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም.....የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።" ማቴ ፯፥፳፩-፳፫ (7፡21-23)

"አሁንስ ምሳር ደግሞ በዛፎች ሥር ተቀምጧል እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።" ሉቃ ፫፥፱ (3፡9)

ይህ ሁሉ የወንጌል ቃል የሚመክረን ሃይማኖትን ከምግባር አስተባብረን በመያዝ ከመንግሥተ ሰማያት የበቃን እንሆን ዘንድ ነው። ምክንያቱም የክብር ጌታ ከሁሉ ሳያዳላ የሚፈርደው እንደ ሥራችን መጠን ነውና።

አስረጅ፡-

> "አንተ ከእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጣለህና።" መዝ ፷፩፥፲፪ (61፡12)
>
> "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ከእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።" ራዕ ፳፪፥፲፪ (22፡12)
>
> "በጎ ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን ግን እግዚአብሔር ከመከራው ሁሉ እንደ ጠበቀው እንደ ኢዮብ ባሮቹ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር በበጎ ሥራው ሁሉ ይጠብቃቸዋል።" ፩መቃ ፴፮፥፲፮ (36፡16)

ሃይማኖትና ምግባርን ይዘን በቀኙ ከመቆም ያብቃን። አሜን!

# ክርስትና

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ሃይማኖት ክርስትና ተብላ ትጠራለች። "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም እኔን ምሰሉ" እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስትና ስንል ክርስቶስን መስሎ መኖር በቃሉ መመራት ማለት ነው። ይህንን ቃሉን የክርስቶስ ወንጌል እየሰበኩ ሕዝቡን ወደሕይወት ዘመር እንዲል ያደረጉ ደቀመዛሙርት ተብለው ይጠሩ የነበሩ የጌታ ሐዋርያትና አርድእት በአንጾኪያ ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ። ሐዋ. ፲፩፥፲፱-፳፮ (11፥19-26)፥

ደቀ መዛሙርት ወይም ክርስቲያን ስንል ደቀ መዛሙርት ከመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ይባሉ እንጂ አስቀድሞ ጌታ በማቴ. ፲፮፥፲፰ (16፥18) "ወዲበ ዛቲ ኰኲሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ" በዚህች ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን አሠራታለሁ ብሎ ገልጾታል።

ስለዚህ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ቤዛ ሆኖናል የሚል ሕጉንና ሥርዓቱን ጠብቆ የሚኖር ክርስቲያን ተብሎ ተጠራ፤ ስለዚህ እኛም በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለናል።

# ኦርቶዶክስ

ብዙዎች ይህንን ስም በተለይ በእምነት የመጀመርያነትን ከመግለጽ ይጠቀሙበታል። ኦርቶዶክስ የሚለው ቃል የግሪክ ሲሆን "ኦርቶ" (ኦርቶስ) ማለት ቀጥ ያለ ማለት ሲሆን "ዶክስ" ማለት ደግሞ እምነት ማለት ነው። ስለዚህ ኦርቶዶክስ ማለት ቀጥ ያለ፣ የጸና፣ የቀና እምነት ማለት ነው።በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን እንደተገለጸልን ቀጥ ያለ እምነት ወይም እውነተኛ ሃይማኖት ተብላ በአምላካችን የተመሠረተችው ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ናት። ቀድሞ በነቢዩ በኤርምያስ የቀደመችው መንገድ ብሎ ያናገረ ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ባስተማረን ወንጌል ጠባቢቱ በር ጠባቢቱ መንገድ ብሎ ኦርቶዶክስ የሕይወት መንገድ መሆኗን አስተምሮናል። መሥርቷታልም።

> "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ። በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ፥ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእስዋም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፥ እነርሱ ግን እንሄድባትም አሉ።" ኤር ፮፥፲፮ (6፥16)

> "በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና። የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።" ማቴ - ፯፥፲፫ - ፲፬ (7፥13 - 14)

ከሁለቱ ጥቅስ ልብ የምትሉት ነገር ብዙዎች ይህችን እውነተኛ መንገድ እንደማይቀበሏት ነው። ከሐድያን መናፍቃን የተበረዘና የነቀዘ እምነት እንዲሁም ከወንጌል ውጪ የሆነ የፍልስፍናን ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከማስገባት በሚጥሩበትም ጊዜ ቅዱሳን አባቶች 318ቱ ኪቃውንት አርዮስንና መሰሎቹን አውግዘው አኛ አሉ ጌታችን የመሠረተልንን ነቢያት ትንቢት የተናገሩላትን፣ ሐዋርያት የሰበኩላትን ፣ሰማዕታት የሞቱላትን ቀጥ ያለች እምነት ይዘን

እንሄዳለን ብለው ሥርዓት ስለደነገጉ እምነታችንም ኦርቶዶክስ ተብላ ትጠራለች።

"የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታችሁ ምሰሉአቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ" ዕብ.፲፫፡፯ (13፥7)

# ተዋሕዶ

ተዋሕዶ የቃሉ ትርጉም ግእዝ ሲሆን የሚያበሥረንም የአምላካችን የእግዚአብሔርን ሰው የመሆን ምሥጢር ነው። ይህም ገና ያኔ በኦሪት ዘፍጥረት ፫፥፳፪ (3፥22) "እግዚብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" የሚለው አምላካዊ ቃል የተፈጸመበት የሰው ልጅ የመዳን ዜና ነው።

ተዋሕዶ ስንል ማን ከማን ተዋሐደ? በዮሐንስ ወንጌል ፩፥፲፬ (1፥14) ላይ "ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ" ያ ቃል ሥጋ ሆነ ይላል ሙሉ ወንጌሉን ስናነብ ግልጽ ይሆንልናል። "ያ ቃል" የተባለው እግዚአብሔር ነው። "ሥጋ" የተባለው ደግሞ ሰው ነው።ከዚህ የወንጌል ምስጢር የተነሣ ተዋሕዶ ማለት አካላዊ ቃል የተባለ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ ከተባለ ሰው ያለመለየት፣ ያለመቀላቀል፣ ያለድማሬ አንድ ሆነ። በተዋሕዶ ከበረ ስለዚህ አምላካችን እግዚብሔር እኛን ለማዳን ሲል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ስንል የእሷን ባሕርይዋን ባሕርይ አደረገ። ሥጋም የአምላክን ባሕርይ ባሕርዩ አደረገ።ይህ ምን ማለት ነው? አካላዊ ቃል እግዚአብሔር፡- አይዳሰስም፣ አይታይም፣ አይጨበጥም፣ አይዳሰስም፣ አይበላም፣ አይጠጣም፣ አያንቀላፋም፣ አይሞትም ወዘተ ... እነዚሀ ሁሉ የሚስማሙት ለሰው (ለሥጋ) ነው። አምላካችን ከድንግል በተወለደ ጊዜ ግን በተዋሕዶ የሰውን ባሀርይ የራሱ አደረገ። በአጭሩ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ካለ አባት ከእመቤታችን ተወልዶ ሥጋን ተዋሕዶ (30) በሠላሳ ዘመኑ ተጠምቆ በቀራኒዮ ተሰቅሎ በጐልጐታ ተቀብሮ ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶ ዐረገ በተዋሐደው ሥጋ ዳግም ለፍርድ ይመጣል "ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል" ሥራ. ፩፥፲፩ (1፥11) ሥጋን ለብሶ እንዳረገ እንዲሁ ይመለሳል በመንግሥተ ሰማያት ለዘላለም ይኖራል ብሎ ማመን እውነተኛ የተዋሕዶ እምነታችን ነው።

የማይመረመር የማይከወጥ ቃል የሚከወጥ ሥጋን ተዋሐደ ሙከወጥ ይስማማው የነበረ ሥጋን የማይከወጥ አደረገው። ስለዚህም በተዋሐደው በመዋቲ አዳም ሥጋ ተገለጠ የማይከወጥ ባሕርይ ያለው ቃል የሚከወጥ ባሕርይ ባለው ሥጋ ሞተ በፍዳ የተያዙትን በወንጌሉ አዳናቸው።" ሃይማኖተ አበው።

ስለዚህም ወገኖች ሆይ፡- አምላካችን በደሙ የመሠረተልንን የነጻች እምነታችንን እስከ መጨረሻ ካፀናን የክብሩ ወራሾች የስሙ ቀዳሾች አድርጎ በክብር ያኖረናል። "ሕጉንም በቀንና በሌሊት የሚያስብ እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች ፍሬዋን በየጊዜው እንደምትሰጥ ዛፍ ይሆናል።" መዝ. ፩፡፪ (1፡2)

> የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናል" ዕብ ፫፡፲፬ (3፡14)

ይህ የቅዱስ ጳውሎስ ቃል በአምላካችን ሰው መሆን (ተዋሕዶ) ያገኘነውን የልጅነት ፀጋ ያሳያል።ከፅንሰታችን እስከ ዕለተ ሞትታችን ኋላም እስከ ዕለተ ምጽአት በዚች ተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንተን የቀደመች ልጅነታችንን ብንጠብቅ ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆናለንና።

ተዋሕዶ የእግዚአብሔር ሰው የመሆን ምሥጢር ነው። ከድንግል ሰው የሆነው ቃል የተባለ እግዚአብሔር ወልድ እርሱ አምላክ ነው። ሰው በመሆኑ ከአምላክነቱ አንዳች አልጎደለውም።

ተዋሕዶ የቃል እግዚአብሔር ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ የመንሣት (የመዋሐድ) ምሥጢር ታላቅ ነው። እርሱ የዳዊት ልጅ እንደሆነ እንዲሁ የዳዊት ፈጣሪ ነው። ከአብርሃም ዘር እንደተገኘ እንዲሁ ከአብርሃም በፊት ነበረ።

እስረጅ፡ማቴ ማቴ. ፳፡፳ ፳፪፡፵፩፡፵፭ (22፡41-45) ዮሐ ፰፡፶፰ (8፡58)

# ሥነ-ፍጥረት

የሚታየውና የማይታየውም ሁሉ በአንድ አምላክ በኩሉ እግዚአብሔር የተፈጠረ ነው። በጸሎተ ሃይማኖት እንዲህ ይላል።

> "ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ፣ ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ... ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ ... ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ..."

> "ሁሉን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ሰማይና ምድርን የፈጠረ የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ አንድ የአብ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን...... ሁሉ በእርሱ የሆነ በሰማይ ካለው በምድርም ካለው ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም.......ጌታ ማኅየዊ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን"

ይህም፡- ዓለም በጠቅላላው በሥላሴ እንደተፈጠረ የሚያስረዳ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም የሚጀምረው እግዚአብሔር ፈጣሪ መሆኑን እየገለጸ ነው። "በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ" በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ብሎ ነው። ዘፍ ፩፡፩ (1.1)። እግዚአብሔር ፈጣሪ፣ አስገኚ፣ የሁሉ ጌታ መሆኑን የምናውቀው በዚሁ በፈጠረው ፍጥረት ነው። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይገልጸዋል። "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና" ሮሜ ፩፡፳፩ (1:21)

እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን በስድስት ቀን ውስጥ ፈጥሮታል። መፍጠርም የጀመረበት ቀን በእሁድ መጋቢት ፳፱ (29) በዘመነ ዮሐንስ ነው። እግዚአብሔር በስድስቱ ዕለታት ውስጥ የፈጠረውን አንድ በአንድ ከመቁጠር ፍጡር የማይደርስበትና የማይፈጽመው ነው። በየወገኑ በየወገኑ ግን ቅድስት

ቤተክርስቲያናችን እንደምታስተምረን ፳፪(22) ነው። ከዚህም ውስጥ ሁለቱ ሰውና መላእክት ሲሆኑ እነዚህንም ስሙን ከመቀደስ ክብሩን ከመውረስ ፈጥሯቸዋል የቀሩትን ፍጥረታት ግን ከአንክሮ ከተዘከሮ ከምግበ ሥጋ ከምግበ ነፍስ ፈጥሯቸዋል። (አቡሻኽር)

ከአንክሮ ከተዘከሮ ማለት ከመማሪያ ከመመራመሪያ ከመታሰቢያ ማለት ሲሆን ይህም ከላይ እንዳየነው ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ (ከሰው) በፍጥረቱ ይታወቃል እንዳለ በዚህ በእግዚአብሔር የእጅ ፍጥረት እግዚአብሔርን እያመለኩ፣ እያደነቁና እያሰቡ ይኖሩ ዘንድ የተፈጠሩ ማለት ነው።

## ሃያ ሁለቱ (፳፪ቱ) ሥነ-ፍጥረታት

**እሑድ**፡- እሑድ የመጀመሪያ ዕለት ሲሆን በዚህ ቀን ነው እግዚአብሔር አምላክ መፍጠር የጀመረው። በዚህ ቀን የተፈጠሩትም ፍጥረታት ስምንት ናቸው በኩፋሌም እንዲህ የሚል ምስክርነት ይገኛል። "ወገብረ ፰ተ ዘመደ" ኩፋ ፪፡፰ (2.8)

በመጀመሪያይቱ ቀን በዕለተ እሁድ ስምንት ታላላቅ ፍጥረታትን ፈጥሮአል

1. ነፋስ
2. እሳት
3. ውኃ
4. መሬት
5. ጽልመት
6. ብርሃን
7. መላእክት
8. ብሩህ ሰማይ

የመጀመሪያዎቹ ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ፬ ያሉት አራቱ ባሕርያት ተብለው የሚጠሩት ናቸው።

ሰኑይ (ሰኞ)፡- ይህም ከፍጥረት ሁለተኛ ቀን ሲሆን። በዚህ ቀን እግዚአብሔር አምላክ በዕለተ እሑድ የፈጠረውን ወኃ ከሦስት ክፍል የከፈለበት ነው። በዚህም በውቅያኖስና በሐኖስ መካከል ድንበርን ይለዩ ዘንድ ነው። በዚህ ቀን ውኃ ከሦስት ሲከፈል አንደኛው ውቅያኖስ ሁለተኛው የብርሃን መመካከሻ አድርጎ ጠፈር ሦስተኛውን ከላይ ሰቅሎት ሐኖስ ብሎታል። በአጠቃላይ ግን በዚህ ቀን የተፈጠረው ፩ ፍጥረት ጠፈር ይባላል።

"ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ጠፈር ማዕከለ ማይ" ዘፍ ፩፡ ፮(1.6)

ሠሉስ (ማክሰኞ)፡- በዚህ ቀን እግዚአብሔር ሦስት ፍጥረታትን ፈጥሯል፡

በጥፍር የሚካጡና የሚለቀሙ ለምሳሌ፡- ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ካሮት፣ ድንች፣ የመሳሰሉ ወይም አትክልት

በማጭድ የሚታጨዱ ለምሳሌ፡- ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ የመሳሰሉ ወይም አዝርዕትን

በምሳር (በመጥረቢያ) የሚቆረጡትን ለምሳሌ ዋንዛ፣ ዝግባ፣ ጽድ የመሳሰሉትን

ዕፀወ ገነትን (የገነት ዕፅዋትን)፡- የእነዚህ መገኛቸው ከምድር ስለሆነ ከዚህ ተቆጥረዋል። ከሌሎች ዕፅዋት ከላይ ከተጠቀሱት የሚለዩበት ነገር እነዚህ ሁልጊዜ ብርሃን የሚይዙያቸው ስለሆኑ ነው። ኩፋ ፪፡፲፪ (2.12)

ረቡዕ፡- በዚህ በአራተኛው ቀን በረቡዕ እግዚአብሔር ቀን፣ ሌሊትን ይለዩ ዘንድ፣ ለምልክቶች፣ ለዘመናት፣ ለዕለታት ለዓመታት ይሆኑ ዘንድና ያበሩ ዘንድ ሦስት ታላላቅ ብርሃናትን ፈጠረ።

፩ .ፀሐይ

፪ .ጨረቃ

፫ .ከዋክብት

ሐሙስ፡- በዕለተ ሐሙስ በአምስተኛው ቀን እግዚአብሔር ሦስት

ፍጥረታትን ፈጥሮአል።

"ወይቤ እግዚአብሔር ለታውፅአ ማይ ዘይትሐወስ መንፈስ ሕይወት"

እግዚአብሔር አለ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ዘፍ ፩፡፳ (1፡20)

በኃያሉ ፈጣሪ ትእዛዝ መሠረት ከውኃ የተገኙ፡-

በእግራቸው የሚሽከረከሩ

በልባቸው የሚሳቡ

በክንፋቸው የሚበሩ

እነዚህን ምንም መገኘታችው ከውኃ ቢሆንም ተፈጥሮዋቸው ከአራቱ ባሕርያት ነው።

<u>ዓርብ</u>፡- ዓርብ ስድስተኛው ቀን ሲሆን ከፍጥረት የመጨረሻው መካተቻ ቀን ነው።

በዚህ ቀን አራት ፍጥረታትን ፈጥሮበታል።

፩. በልባቸው የሚሳቡ ተንቀሳቃሾች

፪. በእግራቸው የሚሽከረከሩ

፫. በክንፋቸው የሚበሩ

እነዚህ በዕለተ ሐሙስ ከተፈጠሩት የሚለዩት መገኛቸው ከየብስ (ከመሬት) ስለሆነ ነው።

፬. በዚህ ቀን ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥሯል።

"ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ" ዘፍ ፩፡፳፮ (1፡26)

እንግዲህ ከመጀመሪያው ቀን ከእሑድ ጀምረን እስከ ፍጥረት መጨረሻ ቀን ዐርብ ድረስ ያሉትን ፍጥረታት በየወገናቸው ብናይ ሃያ ሁለት ናቸው። ፳፪ቱ (22ቱ) ሥነ ፍጥረታት የተባለው በዚህ ነው።

ጠቅላላ የቁጥራቸውን ድምር በየዕለቱ ያለው ይህ ነው።

እሑድ - 8 ፍጥረታት

ሰኞ - 1 ፍጥረት

ማክሰኞ - 3 ፍጥረታት

ረቡዕ - 3 ፍጥረታት

ሐሙስ - 3 ፍጥረታት

ዓርብ - 4 ፍጥረታት

ቅዳሜ - አልቦ (0) ፍጥረት

ድምር = 22 ፍጥረታት ይሆናሉ

> "ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ። እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና" ዘፍ ፪፥፩-፫ (2፡1-3)

በዚህ ቃል የተመለከትነው

፩. ሥነ ፍጥረት በሰድስት ቀን እንደተፈጸመ

፪. የሰማይና የምድር ሠራዊት ተፈጸሙ ሲል የሰማይ ሠራዊት መላእክት ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ የምድር ሠራዊት ደግሞ ዕፅዋት፣ አዕባን (ድንጋዮች)፣ እንስሳት አራዊትና የሰው ልጆች ናቸው።

፫. የሠራውን ሥራ ሲል ደግሞ ሰማይን ከነግሡ ምድርንም ከነልብሱ ፈጥሮ የሚታየውንም የማይታየውንም ፈጥሮ ጨረሰ ፈጸመ ለማለት ነው።

፬. እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ውጪ ምንም ነገር የለም አይኖርም ከፍጥረት በኋላ ግብር አምግብር ይራባል እንጂ ፍጥረት ተፈጥሮ ተጠናቋል።

፭. በሰባተኛው ቀን ዐረፈ ሲል እግዚአብሔር ደክሞት ዐረፈ

አይደለም። በባሕርይው ድካም የለበትም ለእኛ ዕረፍት አድርጎ ልዩ የምስጋና ቀን ይሆን ዘንድ ነው።

፯. ይህችን ሰባተኛይቱ ቅዳሜን ባረካት ቀደሳት። ስለዚህም ቀዳሚት ሰንበት ተባለች ሁለተኛይቱ ታላቂቱ ሰንበት እሑድ ናት።

፯. ሌላው ዓቢይ ምሥጢር እግዚአብሔር ሰባት ዕለታትንና ጊዜን አብሮ እንደፈጠረ ማወቅ ነው።

## ሰባቱ (7ቱ) ሰማያት

ሰማይ ከ22ቱ ሥነ-ፍጥረታት አንዱ እንደሆነ ተመልክተናል። በኦሪት ዘፍጥረት እንደምናየው መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው የሰማይና የምድርን በእግዚአብሔር መፈጠር በመናገር ነው።

"በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ" ዘፍ ፩፡፩ (1፡1)

በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ይላል። ውኃንም በከፈለበት ጊዜ ጠፈሩን ሰማይ ብሎ ጠራው ይላል።

"ወሰመዮ እግዚአብሔር ለውእቱ ጠፈር ሰማየ" ዘፍ ፩፡፰ (1.8)

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ትምህርት መሠረት ይህ ሰማይ አንድ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉት ይታመናል። ለዚህም ነው ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በ ፪ (2)ኛ መልእክቱ ምዕራፍ 3 ቁጥር 10 ላይ ስለ ምፅአት ሲናገር

"እንተ ባቲ ሰማያትኒ ይትረኃዋ ወይሰሰላ" ፪ጴጥ ፫፡፲ (3፡ 10)

"በዚያም ቀን ሰማያት ይከፈታሉ በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ"

ይህን የእግዚአብሔር ቃል ስንመለከት ቅዱስ ጴጥሮስ ሰማያት ብሎ ሲጠራ አብዝቶ መናገሩ የተለያዩ የሰማይ ክፍሎች እንዳሉ

ያስገነዝባል ቅዱስ ጴጥሮስ በታላቅ ድምፅ ይከፈታሉ ያልፋሉ ይጠራሉ ያላቸውን ሰማያት ትተን የእግዚአብሔር ቁፋን ያለበትንና የመላእክት ከተማ የሚገኝበትን ሰባቱን ሰማያት እንመለከት። በቀሌምጦስ መጻሐፍ ስለ ሥነ-ፍጥረት እንደተገለጠው ከኀላፊው ጠፈር በላይ ያሉትን ፯ (ሰባት) ሰማያተ ብርሃን ይላቸዋል። እነዚህም ከዚህ እንደሚቀጥለው ያሉት ናቸው።

ኤረር

ራማ

ኢዮር

ኢየሩሳሌም ሰማያዊት

ሰማይ ውዱድ

መንበረ መንግሥት

ጽርሐ አርያም ናቸው።

ከነዚህ ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት ኤረር፣ ራማ፣ ኢዮር ዓለመ መላእክት ተብለው ይጠራሉ ። መንበረ መንግሥት መንበረ ስብሐት መንበረ ጸባዖት ጽርሐ አርያም ደግሞ ማኅደረ እግዚአብሔር ይባላል።

# ሦስቱ ሕግጋት

**ሕገ ልቡና** - ከአዳም እስከ ሙሴ

**ሕገ ኦሪት** - ከሙሴ እስከ ዮሐንስ መጥምቅ

**ሕገ ወንጌል** - ከዮሐንስ መጥምቅ እስከ ምጽአት

> "ኦሪትኒ ወነቢያትኒ እስከ መጥምቀ ዮሐንስ እምትካት ሰበኩ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር"
>
> "ኦሪትም (ሕግ) ነቢያትም ከጥንት ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ድረስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተማሩ።" ሉቃ፡፲፮፡፲፮ (16፡16)

እግዚአብሔር አምላካችን የፈጠረውን የሰውን ልጅ ወደ ሕይወት ይመልስ ዘንድ በተለያዩ ዘመናት እርሱን የሚያውቁበትን ከእርሱም የሚገዛበትን መንገድ ሰጥቶታል። እነዚህም ሕገ-ልቡና፣ ሕገ-ኦሪት እና ሕገ ወንጌል ናቸው። የሰው ልጅ ፍጥረት ሁሉ አምላኩን ለማወቅ እነዚህ ሕግጋት ይገለጹለታል ከእነዚህ የወጣ የለም ያለ ሕግ የሚሠራ ሁሉ ያለ ሕግ ይቀጣልና። የሚገርመው ነገር እነዚህን እሟላታ በዓለም ላይ ያለች ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት። በሦስቱም ሕግጋት እግዚአብሔርን እያመለከች በመኖሯ አምላኩተ እግዚአብሔርም ስላልተቋረጠባት ስለዚህም ነበር ቅዱስ ዳዊት "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር"

> "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች (ታደርሳለች)" መዝ- ፷፯፡፴፩ (67፡ 31)

## ኢትዮጵያና ሕገ ልቡና

ሕገ ልቡና ሕገ ኦሪት በሙሴ አማካኝነት እግዚአብሔር ለሕዝቡ እስከሰጠበት ጊዜ ድረስ የሰው ልጅ ይጠቀምበት የነበረ ዛሬም የሚሠራ ያልተፃፈ ሕግ ወይም የአእምሮ (ጠባይዕ) ነው።

ይህ የአእምሮ ጠባይዕ ለሰው ልጆች በእግዚአብሔር አምላክ የተሰጠው ታላቅ ፀጋ ስለሆነ ክፉንና ደጉን ጽድቅና ኩነኔውን ይለይበት ዘንድ የሚያስችለው የኅሊና ሕግ ነው። በኅሊና

መገዛት መልካም ነው።

> ይህን የልቡና ሕግ በኛ ውስጥ የቀረፀው ገና ሲፈጥረን እንደሆነ ማስተዋል ይገባናል። "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" ዘፍ፡ ፪፡፯ (2:7)

ሰው የተፈጠረው እንደመካአከት በሕገ ልቡና እንዲሠራ ነበር። ሕገ ኦሪትና ሕገ ወንጌል የተሰጡት በዚያ መኖር ስላልቻለ ነው። ከአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነ ነቢዩ ሄኖክ እንዲህ አለ። "እስመ ኢተፈጥረ ሰብእ ከዝ ከመዝ ከመ ያጽንኡ ሃይማኖቶሙ በራቅ ወበቀለም ዘእንበለ ጸእሙ ከመ መላእክተ እግዚአብሔር ይግበሩ ወይንበሩ ጻድቃነ ወንጹሐነ" ይህ ቃል እውነት ነው። ሰው ሲፈጠር እንደ መላእክት በሕገ ልቡና እንጂ በቀለም በተጻፈ ሕግ እንዲመራ አልነበረም ግን ደግ እግዚአብሔር በፀጋ ላይ ፀጋ ጨምሮ ሰጠው።

> "እንግዲህ ይህች ሕያዊት የሆነች ነፍሳችን ናት የፈጠራትን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለምትረዳ እኛም በእውነተኛ መንገድ እንድንሄድ የምትጠራን ይህም ሕገ ልቡና ነው። በአጠቃላይ እግዚአብሔር በልባችን የቀረጸው ሕግ ነው። ሐዋርያው ለዚህ ነበር እንዲህ ያስተማረው" ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ግን ባይኖራቸው እንኳ ከራሳቸው ሊመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በእርሳቸው ሊካሰሱ ወይም ሲያመካኙ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። ሮሜ፡ ፪፡፲፬ (2:14)

ክብር ምስጋና ይግባውና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኦሪትም በወንጌልም የነገረን ይህንን ነው።

> "አፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኩሉ ልብከ፡ ወበኩሉ ነፍስከ ወበኩሉ ሐይልከ፡ ወበኩሉ ሕሊናከ"
>
> "አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፡ በፍጹም

ስውነትህ፡ በፍጹም ኃይልህም፡ በሐሳብህም ሁሉ ውደደው" ዘዳ፡ ፮፡፲ (6፡10) ሉቃ ፲፡፳፯ (10፡27)

እንግዲህ ይህንን ያህል ስለ ሕገ ልቡና ካየን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ሕግ መሠረት እንደ ተጠቀመበትና አምላኩን እንዳመለከበት ብዙ ግልፅ ማስረጃዎች አሉ ስለዚህ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን የምታውቀው በኦሪት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊት ከፍጥረት ጀምሮ ነው።

ምሳሌ፡-

ሕገ ኦሪት የተሰጠው በሙሴ ነው ሙሴ ሕግን ከመቀበሉ በፊት እግዚአብሔርን አማኝ ነው የፈርዖንን ቤት ሹመት የናቀው በእምነት ነው። ዕብ. ፲፩፥፳፫-፳፰ (11፥23-28) ይህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ያገባት ሚስቱ ኢትዮጵያዊት እንደሆነች መጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘኁልቍ ፲፪፡፩ (12፥1) ይገልፃል። ይህች የሙሴ ሚስት ሲፓራ እግዚአብሔርን ከሚያምን ቤተሰብ የተወለደች ነበረች። ይልቁንም አባቷ የእግዚአብሔር ካህን ነበረ። ይህ የሙሴ አማች የሲፓራ አባት ዮቶር በሌላ ስሙ ራጉኤል የተባለው ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር የሕግ መጽሐፍ እንዲህ ይላል ዘጸ ፲፰፡፲፪ (18፡12) እግዚአብሔርንም እንዲህ አያለ ያመሰግን ነበር ዘጸ ፲፰፡፲ (18፡10) እንግዲህ ይህ የሚገልጽልን ኢትዮጵያ ከሕገ ኦሪት በፊት በሕገ ልቡና ከአምላኳ እንደ አቤል እንደ ኢዮብ መሥዋዕት የምታቀርብ የእግዚአብሔር ሀገር መሆኗን ነው። ታላቁ ሊቀ ነቢያት ሙሴም የሚታምን የካህነ ጣዖት ልጅ ያገባል ብሎ ማሰብ አላዋቂነት ከመሆኑም በላይ የሙሴን ክብር ዝቅ ማድረግ ነው።

ንግሥተ ሳባ ወይም ንግሥት አዜብ ተብላ የምትጠራው ኢትዮጵያዊት ንግሥት ማክዳን ብንመለከት እግዚአብሔርን ማመን የጀመረችው ኢየሩሳሌም ሄዳ ከመጣች በኋላ ሳይሆን ከመሄዷ በፊት አስቀድሞ በሕገ ልቡና ፈጣሪዋን የምታውቅ መሆኗን የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክርልናል። ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና ሀገረ እግዚአብሔር ስለሆነች ንግሥቲቷም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ንጉሥ ሰሎሞን የሄደችበት ምክንያት በተመሳሳይ እምነት ያለች እስራኤል

በሰሎሞን ምክንያት ያገኙትውን በረከት ከመመልከቷና እግዚአብሔርን ከማመስገን ነበር።

> “አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን” ፩ነገ ፲:፱ (10:9) በማለት ምስክርነቷን ገልጻለች። ይህን ማለቷ ንግሥቲቷ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ታውቀውና ታመልከው ስለነበር ነው። ከዚህም ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእምነት ምሳሌ አድርጎ በወንጌል ያስተማረን እንዲህ ብሎ

> “ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ አመ ዕለተ ደይን ወትትፋታሕ ምስለ ዛ ትውልድ ወታስተኀፍራ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን”

> “ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ተነሥታ ከዚህ ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፡ ታሳፍራታለች፡ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና ሲል መስክሮላታል።” ማቴ ፲፪:፵፪ (12:42) ሉቃ ፲፩:
> ፴፩ (11:31)

ንግሥተ አዜብ ወደሀገሯ በተመለሰች ጊዜ ሀገራችን ያን ጊዜ ሕገ ኦሪትን ተቀብላ ሃይማኖተ ኦሪትን ብሔራዊ እምነት አድርጋለች፤ ቀድሞ ያለውንም አጽንታለች። ይህም የሚፈጸመው በቃልኪዳኑ ታቦት ነውና ከንጉሥ ሰሎሞን በወለደችው በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ገባች።

## ኢትዮጵያና ሕገ ኦሪት

ኢትዮጵያን የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር አሞጽ ፱:፯ (9:7) ይህም ምን ይገልጽልናል ብሎ ለሚጠይቅ ነገሩ እንዲህ ነው ዛሬ እስራኤል ታቦቱ የላትም። የዚህ ምሥጢር ባለቤት ግን ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ናት።

በአጠቃላይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፍጥረት ጀምሮ የብሉይ ኪዳንን እምነትና ሥርዓት ጠብቃ አስጠብቃ እግዚአብሔርን በማምለክ የጸናች አገር ናት፡- ቅድመ ክርስትና ይህ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት እየተሠዋባት የነበረች አገር እንደነበረች በሁሉም የአገሪቷ ክፍል ያለ የሃይማኖት መገለጫ የታሪክ ማስረጃ የባህልም ምስክርነት አለ።

ለምሳሌ፡- በመካው ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ይቀርብባቸው የነበሩ የንዋየ ቅድሳት ምስክሮች አሉ። ኢትዮጵያ በዚያ ዘመን ለአምላኳ መሥዋዕተ ቁርባን ታቀርብ ነበር። ነቢዩ ሶፎንያስ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ "ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱልኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል" በግእዙ እንዲህ ይላል። "እምነ ማዕዶተ ፈለገ ኢትዮጵያ ያመጽኡ ሊተ መሥዋዕተ" የዚህም ትርጓሜ "ከኢትዮጵያ ወንዝ ጀምሮ መሥዋዕቱን ያመጡልኛል።" ሶፎ ፫፡፲ (3፡10)

እንዲህ ባለ ሁኔታ ኢትዮጵያ ለአንድ አምላክ እየሰገደች እርሱን ብቻ እያመለከች ሀገረ እግዚአብሔር ሆና አምላክ ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ተጠምቆ፣ በመስቀል ተሰቅሎ፣ ደሙን አፍስሶ፣ ሥጋውን ቆርሶ፣ ዓለምን ሁሉ ያድናል እያለች የተቆጠረው ሱባዔ የተነገረው ትንቢት ይፈጸማል አምስት ሺህ አምስት መቶ የኃጢአት የጨለማ ዘመን ያበቃል እያለች የነቢያትን ትንቢት በመጋራት በእምነት ፀንታ ስትኖር ዘመኑ ሲፈፀም በትንቢቱ መሠረት ጌታችን እኛን ለማዳን ሰው ሆነ ተዋሕዶ ሃይማኖት በዚህ ተጀመረች ኢትዮጵያም የመጀመሪያዋ ክርስቲያን ሀገር ለመሆን በቃች።

## ኢትዮጵያና ሕገ ወንጌል (ክርስትና)

ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪት ስለማመኗ የነገረን መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለ ክርስትናውም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። የሐዋርያት ሥራ ፰፡፳፮ (8፡26) የጌታም መልአክ ፊሊጶስን ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ

መንገድ ሂድ አለው። ተነሥቶም ሄደ። እነሆም ሕንደኬ በመጠሪያ ስሟ ኄርሳሞት የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር። ሲመለስም በሠረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር። ፊልጶስም አፉን ከፈተ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት ... ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም።

እንግዲህ ልብ በሉ

ጃንደረባው አማኝ ነበር

ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሊሰግድ ነበር

የኢሳይያስን ትንቢት ያነብ ነበር

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ማስረጃዎች ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነት አማኝ የነበረች ሀገር መሆኗን የሚገልጽ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ስንመለከት

ፊልጶስ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት

ጃንደረባው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አመነ

ተጠመቀ

እነዚህ ማስረጃዎች ደግሞ የክርስትናን እምነት የሚገልጹ ናቸውና ኢትዮጵያ ከ33 ዓ.ም ጌታ ከሞት ተነሥቶ ካረገ በኋላ ወዲያው ክርስትናን እንዳመነች የሚያሳይ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከዚህ ከጃንደረባው በመጠሪያ ስሙ ባኮስ ወይም አቤላክ ከተባለው ቅዱስ ሐዋርያ በፊት ኢትዮጵያውያን በሐዋርያት ሥራ ምራፍ ፪ (2) በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ጊዜ በዚያ ነበሩና እነዚህም ክርስትና ተቀብለዋል። በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል ይልቁንም ጃንደረባው ከመካው አፍሪካ ሐዋርያ ሆነ። "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" መዝ.፷፯፥፴፩ (67፥31) ተብሎ የተነገረው የነቢዩ ዳዊት ትንቢታዊ መዝሙር በዚህ እንደተፈጸመ እንገነዘባለን። ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ክርስትና በኢትዮጵያ እየተስፋፋች የወለደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ይሰበክባት ጀመር። ይልቁንም ደግሞ በ330 ዓ.ም ክርስትና

የመካው የኢትዮጵያ እምነት በመሆን ብሔራዊ እምነት ሆነ። በዓለም ላይ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ክርስቲያን ሀገር ሆነች።

# የሚበሉና የማይበሉ ምግቦች

እግዚአብሔር አምላክ የነፍስም የሥጋም አምላክ ነው። በቅዱስ መጽሐፉም ከነፍሳችንም ከሥጋችንም የሚጠቅመንን ነግሮናል። በዘፍጥረት እንዳየነው እግዚአብሔር ከምግበ ሥጋና ከምግበ ነፍስ የሚሆነውን ሁሉ ፈጥሮልናል። ስለዚህም ከእንስሳትም ወገን ሆነ ከእትክልት ወገን የሚበላ አለ የማይበላም አለ። እግዚአብሔር በነቢዩ በሕዝቅኤል እንደተናገረ ካህናት ይህንን ማስተማር አለባቸው። ምእመናንም ይህንን መረዳትና ማወቅ ይገባቸዋል።

> "በተቀደሰውና ባልተቀደሰው መካከል ይለዩ ዘንድ ሕዝቤን ያስተምሩ፥ ንጹሕና ንጹሕ ባልሆነው መካከል ይለዩ ዘንድ ያሳዩአቸው።" ሕዝ. ፵፬:፳፫ (44፡23)

የሚበላው ንጹሕ ተብሎ ሲጠራ የማይበላው ደግሞ ንጹሕ ያልሆነ ተብሎ ተገልጿል። በተለይም በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፩ (11) ዘዳግም ፲፬ (14) ላይ ተዘርዝሮ ተቀምጧል። ከዚህም የምንረዳው የሚበሉት የተሰነጠቀ ሰኮና ያላቸው ሆነው የሚያመሰኩ እንስሳት ሁሉ ናቸው። ነገር ግን ከሚያመሰኩት ሰኮናቸው ስንጥቅ ከሆነው ከነዚህ አትበሉም። ለምሳሌ ግመል ያመስኳል ነገር ግን ሰኮናው ሰካልተሰነጠቀ አይበላም። ሌሎችም እንደ ሽኮኮ፣ ጥንቸል፣ አሳማ (እርያ)፣ የነዚህ ሥጋ አይበላም። በውኃ ውስጥም ካሉት ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው አይበሉም። ከአእዋፍም እንደ ንስር፣ ጭላት፣ቁራ፣ ሰጎን፣ ጉጉት፣ አርኩም፣ ጋጋኖ፣ ጥምብ አንሣ በየወገኑ አይበላም። በዝርዝር ግን ከላይ ባሉት ሁለት ምዕራፎች መመልከት ያስፈልጋችኋል።

አንዳንድ ሰዎች ይህ ሕግ የተሰጠው በኦሪት ዘመኑ ብቻ ይመስላቸዋል። ሕጉ ግን ሰው ከተፈጠረበት ጀምሮ በሕገ ልቡና ጭምር የተገለጸ ነው። ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፯:፪-፫ (7፡2-3) ከኖኅ እንደተነገረው ከኦሪቱ በፊት የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት እንደተጠቀሱ

እንመለከታለን።

"ከንጹሕ እንስሳ ሁሉ ሰባት ሰባት ተባዕትና እንስት፥ ንጹሕ ካልሆነ እንስሳም ሁለት ሁለት ተባዕትና እንስት፥ ከሰማይ ወፍ ደግሞ ሰባት ሰባት ተባዕትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ ከዘር ይቀር ዘንድ ካንተ ትወስዳለህ"።

ይህ ሕግ የተጻፈው ከኦሪት በፊት በሕገ ልቡና ነውና የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት ከኛ ጥቅም ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘው መቼም የማይለወጥ ሕግ ነው። ስለዚህም ይህን የሚተላለፉ ፍርድ እንዳለባቸው በኢሳይያስ ፷፮፥፲፯ (66፥17) ላይ ተጽፏል።

በሐዋርያት ሥራ ፲ (10) ለጴጥሮስ የተነገረውን ይህንን ሕግ የማያውቁ አሕዛብ እንዳሻቸው ይበላሉና ጴጥሮስ ሆይ ተነሣና አርደህ ብላ እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ እታርክሰው መባሉ ጴጥሮስ አማይበሉ እንስሳትን ይበላ ዘንድ ሳይሆን የሚበሉትን ግን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲያመጣ የተገለጸ ራእይ ነበር።

እግዚአብሔር እነዚህን ከእንስሳት፣ ከአትክልት፣ ከአዝርእትም ወገን እንዳይበሉ ያዘዘበት ምክንያት በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፫፥፰፻፳፫ ሰከ ምግብ በተገለጸው እንዲህ ተነግሯል።

(እኒህንም የሚከለክሏቸው በውስጣቸው ነፍስን (ሰውነትን) የሚጎዳ ሕማም ስላለ ነው። ከጣዖታት የተሠዋውን በመብላት ጣዖትን ከሚያመልኩ ጋር አንድ መሆን በአምልኮታቸው አንድ የሚያደርጋቸው ይሆናልና። ይህም ጣዖትን ወደማምለክ ይሰበዋል። ነፍስንም ሥጋንም የሚጎዳ ሕማም በውስጡ ስላለ ነው። ይህች መፈጠርን ወደማጥፋት በሚያደርሰ ጥፋት የሥጋን ባሕሪያት ስምምነት ታጠፋለችና። ዳግመኛም አካልን ወደማትደል ታደርሳለች።

እንግዲህ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ሆኖ ያለ ሲሆን ሁሉንም ግን እንበላ ዘንድ አላሰናበተንም። እንጂ ፍጥረት ሁሉ

መልካም ነው። ሁሉ ተፈቅዶልኛል የሚል ሰው ቢኖር ግን ሰውን ሰው እንዳይበላው የሚያዘው ሕግ የት ነው። ስለዚህ የሚበሉና የማይበሉ፣ ንጹሕ የሆኑና ያልሆኑ ተብለው ተለይተው ተጽፈዋል።

# አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን እምነቷን የምትገልጽበት ከሰዎችም የምታስተምርበትና የምትመሰክርበት አምስት አዕማደ ምሥጢራት አሏት፡-

"ናሁ ኅቡዓ ነገረ እነግረከሙ" እነሆ ኅቡዕ (ምሥጢር) እነግራችኋለሁ ፩ ቆሮ፡ ፲፭፡፶፩ (15፥51) እንዳለ እነዚህ አምስቱ ምሥጢራት አምስቱ ኅቡዓት ተብለውም ይነገራሉ። አምስቱም ነገረ መለኮት ናቸው።

ሀ/ <u>አምስት</u>፡- ቁጥራቸውን ይገልፃል

ለ/ <u>አዕማድ</u>፡- ማለት ምሰሶዎች ማለት ነው። አንድ ቤት ሲሠራ ሊቆምና ጠንካራ ሊሆን የሚችለው በአዕማድ (ምሰሶዎች) ነውና። ለሃይማኖታችንም መሠረታዊ ምሰሶዎች አሏት።

ሐ/ <u>ምሥጢር</u>፡- ከወዳጅ የሚገለጽ ነገር ሲሆን ለሚያምኑ ሁሉ የሚገለጽና በእምነት ብቻ የሚረዱት በመሆኑ ምሥጢር ይባላል።

አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የሚባሉትም፡-

ምሥጢረ ሥላሴ

ምሥጢረ ሥጋዌ

ምሥጢረ ጥምቀት

ምሥጢረ ቊርባን

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው።

አንድ ክርስቲያን እነዚህን ጠንቅቆ ከተረዳ መሠረቱ ጠንካራ ዐለት ይሆናል። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. ፲፬፡፲፱ (14፥19) ላይ "ወባሕቱ በቤተ ክርስቲያን እፈቅድ ኀምስተ ቃላተ እንግር በልብየ ከመ ከባዕዳንኒ እምሃር እስመ ይኄይስ እምእእላፍ ቃል በነገረ በሐውርት" "አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ"

ብሎ የእምነቱን አዕማደ ምሥጢር በእውነት ለምእመናን ያስተምር የነበረው።

## ምሥጢረ ሥላሴ

ከእምነቱ አዕማደ ምሥጢር አንደኛው ይህ ምሥጢረ ሥላሴ ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር የአምላካችን አንድነትና ሦስትነት የሚገለጽበት ነው።

ሀ/ አንድነት፡- በመለኮት በባሕርይ በህልውና በፈቃድ በአዘዝ በአገዛዝ ይህን ዓለም በመፍጠርና በማሳለፍ ይህን በመሳሰለው ሁሉ።

ለ/ ሦስትነት፡- በስም በግብር በአካል በኩነት

በስም፡-አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ። ማቴ.፳፰፡፲፱ (28፥19)

በግብር፡- አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ ነው። ዮሐ. ፩፡፳፭ (1፥25)

በአካል፡- ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክእ አለው። ለወልድም እንዲሁ ለመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ

በኩነት፡-አብ ልብ ነው። ወልድ ቃል ነው፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር በስም በአካል በግብር በኩነት ሦስት ነው ብንልም በመለኮት በህልውና በባሕርይ በአዘዝ በአገዛዝ በመሳሰሉት አንድ ስለሆነ አንድ አምላክ ተብሎ ይታመናል ይጠራል እንጂ ሦስት አማልክት አይባልም። ከዚህም የተነሣ ሥላሴ ሦስት ሲሆኑ አንድ አንድ ሲሆኑ ሦስት በመሆናቸው ይህ ምሥጢር ተባለ ለሚያምን ብቻ የሚገለጽ ምስጢር።

ለምሳሌ አዳም አንድ ነው ሦስት ሊሆን አይችልም።

እብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ደግሞ ሦስት ናቸው አንድ ሊሆኑ እይችሉም። ስለዚህም ቅድስት ሥላሴ ስንል "ቅድስት" ልዩ "ሥላሴ" ሦስትነት ሲሆን ልዩ የሆነች ሦስትነት ብለን እናምናለን።

## በመጽሐፍ ቅዱሳውያን ማስረጃዎች

<u>አንድነት:</u> "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" የሚለው ቃል አንድነቱን ያሳያል። ዘፍ. ፩:፩ (1፥1)

<u>ሦስትነት</u>፡- "የጌታችን የኢየሱስ (ወልድ) ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም (አብ) ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።" 2ቆሮ. ፲፫፡ ፲፬ (13፥14) ይህ ቃል ሐዋርያት ሕዝቡን የሚባርኩበት ቃል ነው ይህም ስመ ሥላሴ ነው።

<u>አንድነትና ሦስትነት</u>፡- እግዚአብሔር አለ "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር።" ዘፍ. ፩፡ ፳፮ (1፥26) "እግዚአብሔር አለ" ሲል አንድነቱን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር የሚሉት ቃላት ሦስትነቱን በግልጽ ያመለክታሉ።

### ሌሎች ምሳሌዎች

<u>ፀሐይ</u>፡- ሀ/ ክበብ (ቅርፅ) አካት

ለ/ ብርሃን አካት

ሐ/ ሙቀት አካት

አንድ የሆነችው ፀሐይ ክበብ ብርሃን ሙቀት ስላላት ሦስት ፀሐዮች አትባልም አንድ ፀሐይ እንጂ። በክበቡ አብ ይመሰላል በብርሃኑ ወልድ ይመሰላል በሙቀቱ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ቢባሉም እርሱ ግን አንድ ፈጣሪ አምላክ ነው።

"አብ ፀሐይ ወልድ ፀሐይ ወመንፈስ ቅዱስ ፀሐይ ፩ዱ

ውእቱ ፀሐየ ጽድቅ ዘካዕከ ኲሉ"

"አብ ፀሐይ ነው። ወልድ ፀሐይ ነው። መንፈስ ቅዱስም ፀሐይ ነው፡ ከሁሉ በላይ የሚሆን አንድ የእውነት ፀሐይ ነው" ቅ.ማርያም

<u>ነፍስ</u>፡- ሦስትነት አካት

ሀ/ ልባዊነት

ለ/ ነባቢነት

ሐ/ ሕያዊነት

ይህ ማለት ነፍስ ለባዊት ናት (ልብ) ነባቢት ናት (ቃል) ሕያዊት ናት (እስትንፋስ) አሁን እንደምታዩት ልብ የምታደርግ የምትናገር ሕያው የሆነች ብለን ብንመለከትም ሦስት ነፍሳት ሳይሆን አንድ ነፍስ ብቻ ነች። በለባዊነት አብ ይመስላል። በነባቢት ወልድ ይመስላል በሕያዊነት ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ይመስላል።አብ ልብ ነው፡ ወልድ ቃል ነው፡ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው። ልክ እንደነፍስ ሦስትነት ሲኖራት አንድ ነፍስ እንደምንል ሥላሴም ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸውና አንድ አምላክ ብለን እናምናለን።


## <u>አስረጅ ንባባት</u>

በብሉይ ኪዳን፡- ዘፍ. ፪:፳፮ (2፥26) ዘፍ. ፪:፲፰ (2፥18) ዘፍ. ፫:፳፪ (3፥22) ዘፍ. ፻፲፯ (117) ዘፍ. ፲፰:፩ (18፥1) መዝ. ፴፪:፭ (32 (33) ፥5) ኢሳ. ፮:፫ (6፥3) ኢሳ. (፵፰:፲፪) 48፥12፣ በአዲስ ኪዳን ማቴ. ፫:፲፮ (3፥16) ማቴ. ፳፰:፲፱ (28፥19) ዮሐ. ፩:፳፮ (1፥26) ፪ቆሮ ፲፬:፲፫ (14፥13) ፩1ጴጥ.፩:፪ (1፥2) ፩ዮሐ. ፭:፯ (5፥7)።

ክብዙ በጥቂቱ ይህን ከገለጽን ሌላውን የቤተ ክርስቲያናችንን የጠራ ወንጌል በመስማት ዕውቀታችሁን ይዛችሁ በእምነት ከመጽናት ትጉ። አንድ ሲሆን ሦስት፤ ሦስት ሲሆኑ አንድ መሆኑ ምሥጢር ተባለ።

የምሥጢር ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለሁላችንም ይግለጽልን።

የአንድነትንና የሦስትነትን ምሥጢር ነቢያት ሐዋርያት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ይልቁንም ከሀዲ አርዮስን ያሳፈረ ቅዱስ አትናቴዎስና ቅዱስ አግናጢዮስ ያስተማሩንን በቀላሉ እንዲረዳችሁ ይህን አስተውላችሁ ተመልከቱ። በኮምፒውተር ላይ ብትገቡም ታገኙታላችሁ።




አብ፡- ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም፤ አይባልም።

ወልድ፡- አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም፤ አይባልም።

መንፈስቅዱስ፡- አብ ወይም ወልድ ተብሎ አይጠራም፤ አይባልም።

አብ እግዚአብሔር ነው፤ ወልድ እግዚአብሔር ነው፤ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር አብ ነው፤ እግዚአብሔር ወልድ ነው፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

"ሠለስቱ ስም ፩ዱ እግዚአብሔር" ሦስቱ ስም ግን አንድ እግዚአብሔር ።

## ምሥጢረ ሥጋዌ

ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ያለአባት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው ሆኖ ከወደቅንበት የኃጢአት ጉድጓድ (ሲዖል) አወጣን አዳነን ብለን ሰው መሆኑን የምንረዳበት እምነት ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላል።

### ከማን ሰው ሆነ?

በነቢዩ ኢሳይያስ ፯፥፲፬ (7፥14) "ናሁ ኬ በእንተ ዝንቱ ይሁበክሙ እግዚአብሔር ትእምርተ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል።" "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ብሎ እንደተናገረ ሰው የሆነው ከድንግል ነው። በሉቃስ ፩፥፳፯ (1፥27) "የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።"

ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ የወደቀውን አዳም ለማዳን ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆነ። ይህ ሰው የሆነው አምላክ ነው። የሥጋን ባሕርዩ ያደረገ የማይታየው የታየው የማይዳሰሰው የተዳሰሰው ከእመቤታችን በተዋሐደው ሥጋ ነው ብሎ ማመን ምሥጢረ ሥጋዌን መረዳት ነው። መሠረታዊ ቃሉም በዮሐ.፩፥፩-፲፬ (1፥1-14) ያለው ነው። በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ቃልም በእግዚብሔር ዘንድ ነበር። ቃልም እግዚአብሔር ነበር ብሎ "ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለውን የእግዚአብሔርን ከእመቤታችን

[illegible]ወልድ ይገለፃል።

**[illegible] የሆነው ማነው?**

እግዚአብሔር ነው፡- ዮሐ. ፩፡፩-፫ (1፡1-3)

አምላክ ነው፡- ኢሳ. ፱፡፮ (9፡6)

ጌታ መድኃኒት ነው ፡- ሉቃስ ፪፡፰-፲፬ (2፡8-14)

**ሰው** የሆነው ከድንግል የተወለደው ሰማይና ምድርን የፈጠረ ብቻውን አምላክ የሆነ ጌታ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ደገኛው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ገልጾታል።

> “ወእሙንቱ አበዊነ ወእምካዕሌሆሙ ተወልደ ክርስቶስ በሥጋ ሰብእ ዘውእቱ አምላክ ቡሩክ ለዓለመ ዓለም አሜን”...

> “አባቶችም ለእነርሱ ናቸው፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን።” ሮሜ ፱፡፭ (9፡5)

**ለምን ሰው ሆነ?**

አዳም በበደለው በደል የሰው ልጅ ሁሉ የሞት ሞት ተፈርዶበት ከአምላኩ ተለይቶ ገነት መንግሥተ ሰማያትን አጥቶ በኃጢአት ወድቆ ስለነበር ይህ የወደቀውን አዳም ለማንሳት የሰው ልጅ ሁሉ ሕይወትን ያገኝ ዘንድ የዲያብሎስ ባርያ የነበረው ደካማው የሰው ልጅ ብርቱ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን ያገኝ ዘንድ ወልድን ፍቅር ከሰማይ ስቦት የመንግሥቱ ልጆች እንሆን ዘንድ አምላክ ሰው ሆነ።

> “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና” ዮሐ ፫፡፲፮ (3፡16)

> “የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት

የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆቹ እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ" ገላ. ፬፥፬ (4፥4)

ስለዚህ የዘላለም ሕይወት እናገኝ ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በስተቀር የሰውን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ ያለመለወጥ ያለመቀላቀል ያለመለያየት ያለመከፋፈል በተዋሕዶ ሰው ሆነ።

ስለዚህም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከእመቤታችን ተወልዶ የሰው ልጅን ሁሉ አዳነ። ስለዚህ አምላክ ሰው ሆነ ሰውም አምላክ ሆነ የሚለውን ምሥጢር በእምነት የተረዳ በጠንካራው ዐለት ላይ የተመሠረተ ነው።

"በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃ አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።" ገላ. ፭፥፩ (5፥1)

ወልድ ሰው በመሆኑ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ያነሰ ወይም የበለጠ አይደለም። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ዘላለም ትክክል ነው። ብዙዎች የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው መሆን ብቻ ያዩና ኃይሉንና አምላክነቱን ይክዳሉ ፪ጢሞ ፫፥፭ (3፥5) እርሱ ግን ዳኛ ፈራጅ ዘላለማዊ አምላክ ነው። በቸርነቱ ከሁላችን ጋር ይሁን።

"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ።" ዕብ. 13፥8

ሊቁ ቅዱስ ጎርጎርዮስ የቅዱስ ባስልዮስ ወንድም፡ ከእመቤታችን ተወልዶ ስለአዳነን የአብ ልጅ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አስተምሮናል፡-

በምድራዊ ልደቱ አባት አለው አትበሉ፡ በሰማያዊ ልደቱም እናት አለችው አትበሉ፡ እርሱ በምድር አባት የሌለው ነው በሰማይም እናት የሌለችው ነው።

ትስብእትን (ስውነቱን) ከመለኮት ልዩ ነው አትበሉ ከተዋሕዶ በኋላ አይለይምና አይቀላቀልምና፡ መለኮቱን ከተዋሐደው ከትስብእት ልዩ ነው አትበሉ በእርሱ ያለ ተዋሕዶውን ዕወቁ እንጂ።

የክርስቶስን አካል ሁለት አታድርጉ ወደ ሁለት አካል ወደ ሁለት ባሕርይ ፈጽማችሁ አትለዩት ወልድን አንድ ወገን የተዋሐደውን ሥጋም አንድ ወገን አታድርጉ።

የማይለየውን ተዋሕዶውም ሊፈርስ የማይቻለውን አንዱን ትለዩ ዘንድ አትድፈሩ ሰው በሆነ በእግዚአብሔር ከመለኮቱ የተለየ ዕሩቅ ብእሲ (ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና እንዲሁ እንደ አንድ ሰው አምላክነት የሌለው) እንደሆነ አታስቡ እርሱ አንድ ብቻ እንደሆነ እመኑ እንጂ እርሱ በተዋሕዶ ሰው የሆነ አምላክ ነው።

ከዘመን አስቀድሞ በቅድምና የነበረ ዛሬ ሰው የሆነ አምላክ ይህ ነው። እርሱም መለኮቱ ከትስብእቱ ትስብእቱ ከመለኮቱ ሳይለይ ለዘለዓለም ይኖራል።

## ምሥጢረ ጥምቀት

የማይታየውና የማይመረመረው አምላክ ከእመቤታችን ሰው ሆነ በሠላሳ ዓመቱ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ አዳምና ሔዋን ያጡትን ልጅነት ከመመለስ ለሰው ልጆች ሁሉ የተጠመቀውን ጥምቀት የምናውቅና የምናምንበት ሦስተኛው አዕማድ ምሥጢረ ጥምቀት ነው።

> "ወእሜሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ኀበ ዮርዳኖስ ከመ ይጠመቅ እምዮሐንስ" ያንጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ማቴ. ፫፡፲፫ (3፥13)

በዚያን ጊዜም ዕድሜው የ30 ዘመን ጎልማሳ ነበር። በ30 ዘመኑ መጠመቁ አባታችን አዳምን ሲፈጥረው የ30 ዘመን ጎልማሳ አድርጎ ነበር። አዳምም የ30 ዘመን ሆኖ ተፈጥሮ የተሰጠውን

ልጅነት በዲያብሎስ አስነጥቆ ነበርና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ልጅነት ሊመልስለት በ30 ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በአፍላገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ።

**<u>በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁም፡-</u>**

ሀ. ትንቢቱ ይፈፀም ዘንድ ነው። "ምንተ ኮንኪ ባሕር ዘጎየይኪ ወአንተኒ ዮርዳኖስ ዘገባእከ ድኅሬከ" አንቺ ባሕር የሸሸሽ አንቺም ዮርዳኖስ ወደኋላሽ የተመለስሽ ምን ሆናችኋል መዝ. ፻፲፫:፭ (113:5)

ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ይጠይቅና መልሱንም በቁጥር ሳባት ላይ ይተነብያል ይናገራል "እምቅድመ ገጹ ለእግዚ ያዕቆም "ከያዕቆብ አምላክ ፊት"

ለ. ዲያብሎስ በአዳምና በሔዋን ላይ የዕዳ ደብዳቤ ጽፎ በዮርዳኖስ ቀብሮት ስለነበር ያንን ለመደምሰስ። ጠላት ዲያብሎስ አዳምና ሔዋንን የዘለዓለም ባሮች አድርጎ በሁለት ዕብነ ሩካም ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል ቀብሮት ነበር። በዮርዳኖስ የተቀበረውን፡ ከብር ይግባውና ጌታ ሲጠመቅ በሰውነቱ ረግጦ በአምላክነቱ አቅልጦ አጠፋው። በሲኦል የተቀበረውን በቀራንዮ ተሰቅሎ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ደመሰሰው። ቆላ- ፪:፲፬ (2:14) ፩ጴጥ ፫:፲፱ (3:19)

ሐ. በብሉይ በዮርዳኖስ ወንዝ (ጠበል) እየተጠመቁ ከሥጋ ደዌ ይፈወሱ እንደነበር የነፍሳችንን ደዌ ሊፈውስልን በዮርዳኖስ ተጠመቀ። ለምሳሌ ኢዮብ ንዕማን ፪ ነገ. ፭:፲፬ (5÷14)

**<u>በውኃ መጠመቁ</u>**

ሀ. ትንቢት ስለአለ፡- "ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ" ሕዝ. ፴፮:፳፭ (36÷25)

ለ. ጌታ ሲጠመቅ በማር ወይም በቅቤ ወይም በሌላ አላደረገውም በውኃ ተጠመቀ ምክንያቱም ውኃ ለድሀው ለሀብታሙ ለታላቁ ለታናሹ ለሁሉ ይገኛልና።

ይህን ያደረገው ከእኛ ነውና ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ ከመዳን "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሊጠመቅ ይገባዋል።" ፳፰፡፲፱ (ማቴ. 28፥19)

እንድ ሰው አምኖ በሚጠመቅበት ጊዜ ካህናት በጸሎት ውኃውን ሲባርኩት ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ማየ ገቦ ይሆናል። ዮሐ. ፲፱፡፴፬ (19፥34) በዚያን ጊዜም ከውኃና ከመንፈስ ይወለዳል። ይህችም ሁለተኛ ልደት ትባላለች። አንደኛ ልደት ከእናት ከአባት አለና - ጌታም የነገረን ይህንን ነው። እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁ አታድንቅ ብሎ ኒቆዲሞስ እንደነገረው። ዮሐ.፫፡፩-፲፭ (3፥1-15)።

## በዮሐንስ መጠመቁ

ክብር ይግባውና ጌታችን የተጠመቀው በዘካርያስና በኤልሳቤጥ ልጅ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ ነው። የዚህም ምክንያት፡-

አንደኛ፡ ጌታችን ወደዚህ ዓለም መምጣቱ ለትሕትና ነው እንጂ ለልዕልና ስላልሆነ ነው ። "ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር። ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው። ያን ጊዜ ፈቀደለት።" ማቴ ፫፡፲፬፡፲፭ (3፡ 14-15) ጽድቅም የተባለች ትሕትና ናት።

ሁለተኛ፡ ሰው ሁሉ ወደ ካህን ሄዶ መጠመቅ እንዳለበት ሲያስረዳ ነው።

ወደ ዮርዳኖስ መሄዱ በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው "ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ" ማቴ ፫፡፲፫ (3፡13) እምላክ ሆኖ ሳለ። ስለምን ዮሐንስን አንተ መጥተህ አጥምቀኝ አላለውም ለምን ጌታ እራሱ ሄደ? ይህም ለእኛ ትምህርት ነበር። ሰው ምንም ያህል የተከበረ ቢሆን ካህኑን ናና ቤቴ አጥምቀኝ እንዳይል ለአርአያና ለምሳሌ ነው። ማንም ቢሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ መጠመቅ

እንዳከበት ሲያስተምረን ነው።

ውድ አንባብያን ሆይ- ይህንን የጌታችንን ጥምቀት ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመሄዱ ምስጢር በእኛ ቤተክርስቲያን ብቻ ጥር ፲ (10) ቀን ታቦታቱ ወደ ወንዝ ወይም በተመደበ የማደሪያ ስፍራ በክብር ወጥተው ጌታ ከአገሩ ከማደሪያው ገሊላ ናዝሬት ወደ ዮርዳኖስ እንደ ሄደ ሁሉ ዛሬም በታቦቱ የሚመሰከው ጌታ ከመቅደሱ ከመንበሩ ወጥቶ ወደ ወንዝ ይወርዳል።

**ምሥጢር መባሉ፡-**

አምላካችን በተጠመቀ ጊዜ ሰማይ ተከፍቶ አብ በደመና ወልድ በዮርዳኖስ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መታየቱና "የምወደው ልጄ" ብሎ አብ የተናገረለት መንፈስ ቅዱስ የመሰከረለት ወልድ በተዋሕዶ አንድ መሆኑ ነው። ይህ አንዱ ወልድ ሁለት አይደለም አብ ልጄ ያለው ሌላ ከድንግል ማርያም የተወለደው ሌላ አይደለም። በበረት የተወለደው ሌላ ሰብአ ሰገል የሰገዱለት ሌላ አይደለም የተጠመቀው ሌላ አይደለም ጥምቀት የሚያሻውም ሌላ አይደለም። እርሱ አንድ የሆነ አምላክ በፈጠረው በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ መጠመቁ ይህ ድንቅ ምሥጢር ነው።

በጸሎት ውኃው ተለውጦ ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ውኃ ሲሆን በሥጋ ዓይን ስለማይታይ ምሥጢር ነበረ።

በመንፈስ ቅዱስ የምንወለድበት ጊዜ ልክ ከእናታችን ከአባታችን ስንወለድ እንደማናውቅ በዚያን ሰዓት ስለማንረዳ በመንፈስ የሚታወቅ በመሆኑ ምሥጢር ነው።

## ምሥጢረ ቁርባን

ይህ ዐራተኛው ምሥጢር ሲሆን ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ከሚያምኑ ሁሉ በቀራኒዮ ተራራ በመስቀል ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶና ክቡር ደሙን አፍሶ የሰጠው ምሥጢረ ቁርባን ይባላል። "ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ

እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።" ዮሐ፥ ፮፥፶፩ (6፥51)

**ቍርባን ማለት፡-** የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው ።

> "ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋውንም አንስቶ አመሰግኖ ሰጣቸው። እንዲሁም አለ። ጽዋውንም አንሥቶ አመሰግኖ ሰጣቸው። እንዲሁም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች ከኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።" ማቴ. ፳፮፥፳፮-፳፰ (26፥26-28)

## ምሥጢር ለምን ተባለ?

ኅብስቱ ተለውጦ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ትኩስ የአምላክ ሥጋ፤ ወይኑ ተቀይሮ ደመ መለኮት (የጌታን ደም) ሲሆን በሥጋ ዓይን ስለማይታይ ምሥጢር ተባለ። አንድም በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ፀጋን ይሰጣልና ምሥጢር ተባለ። ሌላው ምሥጢር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው "አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማይ" ከሰማይ የወረደ ኅብስት እኔ ነኝ እንዳለ ከዚህ ኅብስት የበሉ ሁሉ ለዘላለም ሕያው ሆነው ይኖራሉ። ዮሐ፥ ፮፥፶፩ (6፥51) በዚሁ ወንጌል ምዕራፍ ፩፥፲፬ (1፥14) እንደተጻፈው "ቃል ሥጋ ኮነ" ቃል ሥጋ ሆነ ሲል "ቃል" የተባለ መለኮት ከሰማይ ወርዶ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስን ተዋሐደ እንጂ ከሰማይ የወረደ የሕይወት ኅብስት ወይም እንጀራ ሲል ሥጋን ከሰማይ ይዞት መጣ ማለት አይደለም።

ምሥጢረ ቁርባን የሚነገረን "በእንተ ሕይወት ዘለዓለም" ለዓለም ሁሉ ሕይወት ሊሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅሎ የሰጠንን የሥጋውና የደሙን ምሥጢር ነው። በትርጓሜ ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ እንደተገለጸው ቅዱስ ኤፍሬም እንዳስተማረው አዳምና ሔዋን ትዕዛዝ ሳያፈርሱ በገነት ቢኖሩ ኖሮ ሺ ዓመት ሲሞሉ ዕፀ ሕይወትን በልተው ታድሰው ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገቡ ነበር። ግን በምክረ ዲያቢሎስ

ተታከው ራሳቸውም ለተው ዕፀ በከስን በልተው ወደቁ። ጌታ መሐሪ አምላክ አልተወንምና ከአመቤታችን በተዋሐደው ሥጋ በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በነጻ ሰጠን። በዕፀ ሕይወት ምሥጢር "ምሥጢረ ቁርባን" ወደ መንግሥተ ሰማያት እንገባ ዘንድ አደከን። ይህ ታላቅ ምሥጢር ነው።

በዘመነ ብሉይ የነበረው መስዋዕት ከጌታችን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ምሳሌ ነው። በተከይ የፋሲካው በግ ምሥጢር ክርስቶስ ነው። በዘጸአት ፲፪ (12) እስራኤል የሰውት ንጹሕ በግ የቤታቸውን በር (ጉበን) በደሙ ቀብተው ከመቅሰፍቱ የዳኑበት ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ "ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም" እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ብሎ እንደተናገረው ምሳሌነቱ ለአምላካችን ሥጋና ደም ነው። የሐ፡ ፩፡፳፱ (1፡29)። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም በዚህ ቃል ይጠቀልለዋል። እንዲህ ብሎ፡- ከሞት ወደ ሕይወት ፊልሰን የሄድንበት በፋሲካችን ፋሲካችን ክርስቶስ ተሰቅሏልና። ፭፡፭-፯ (5-7) ስለዚህ "በምሥጢረ ቁርባን" ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ይህን ታምናለች፡-

- በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን እመቤት ከቅድስት ማርያም የተዋሐደው (የነሣው) የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችንም ሥጋና ደም መሆኑን።
- ያለመቀላቀል ያለትድምርት ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋር እንደተዋሐደ መለኮቱ ከሰውነቱ አንዲት ሰከንድ (ቅጽበት) እንኳን እንዳልተለየ።

## <u>በምሥጢረ ቁርባን የሞቱ መታሰቢያነት</u>

ሁልጊዜ ቤተክርስቲያናችን ይህን የቁርባን ምሥጢር የምትፈጽመው በሥርዓተ ቅዳሴ ነው። ከቅዳሴ ውጪ ቁርባን የለም። ይህን የምናደርገው የጌታችን ሞቱን ለማሰብ ነው።

"ንዜኑ ሞተከ ወትንሣኤከ ቅድስተ" እንዲህ እንዳንድ

ሰዎች ይህን ባለመረዳት የጌታ ሥጋና ደም መታሰቢያ ይመስላቸዋል ይህ ፈጽሞ ስሕተት ነው። መታሰቢያነቱ ከሞቱ ነውና።"

"እንካችሁ ብሎ ይህ ሥጋዬ ነው... ስለ ብዙዎች ከኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ማቴ. ፳፮፥ ፳፮ (26፥26)

"...ይህን ከመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ የሁሉጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና" 1ቆሮ. ፲፩፥፫-፮ (11፥3-6)

ስለዚህ ከመታሰቢያዬ አድርጉት ሲል ከሞቱ መታሰቢያ ነው እንጂ ከሥጋና ከደሙ መታሰቢያ አይደለም። ራሱ ሥጋውና ደሙ ነውና ቅዱስ ሥጋውን በልተን ክቡር ደሙን ጠጥተን የዘላለም ሕይወት ያውርስን ዘንድ የመሐሪ አባታችን ቅዱስ ፈቃድ ከሁላችንም ይደረግ።

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

እምስተኛው አዕማደ ምሥጢር ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ነው። ይህም ምሥጢር የጌታችን የእምካካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ መነሣት የምናምንበት ምሥጢር ነው። ብዙ መጽሐፍት ቀላቅለው የእኛን ብቻ ትንሣኤ አድርገው ሲጽፉ አጋጥሞኛል። የእኛም ትንሣኤ ቢነገርበትም ይህ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን የትንሣኤያችን በኩር የሆነውን የእምካካችንን ከሞት መነሳት ምሥጢር የምንረዳበት የምናምንበት ነው። ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን በውስጡ ካሉት ምሥጢራት መካከል እነዚህን ለይቼ ጽፌላችኋለሁ፡-

1ኛ. ምሥጢረ ሕመም 2ኛ. ምሥጢረ ስቅለት 3ኛ. ምሥጢረ ዕርገት 4ኛ. ምሥጢረ ዳግም ምጽአት- እነዚህ ሁሉ የሆኑትና የሚፈጸሙት በተዋሐደው ሥጋ ነው። የጌታችን ሕመሙና መከራው፣ በቀራንዮ መስቀሉ ከሞት

በተነሣ በ40ኛው ቀን ማረጉ እንደገና በማትታወቀው ዕለት ከፍርድ መምጣቱ ከአመቤታችን በተዋሐደው ሥጋ ነውና ምሥጢር ነው። ስለዚህም አምስተኛው አዕማድ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ነው ብለው አባቶቻችን ወስነው ያስተማሩን ክብር ይግባውና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በሦስተኛው ቀን ከሞት ሲነሣ የተዋሐደውን ሥጋ በመቃብር ትቶ ወይም ሌላ ለውጦ ሳይሆን ከድንግል በነሣው ሥጋ ነውና ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ተባለ። የጌታ ከሙታን መካከል መነሣቱ በገዛ ራሱ ሥልጣን ነው። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር አብ አስነሣው ወይም መንፈስ ቅዱስ አስነሣው የሚል ቃል ሲያገኙ ወልድ በራሱ ሥልጣን የተነሣ አይመስላቸውም። ግር ይሰኛሉ። ይህም ምሥጢረትንሣኤ ሙታንን ካለመረዳት የተነሣ ነው። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት እንዳየነው እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዕዘዝ በአገዛዝ ይህን ዓለም ፈጥሮ በማሳለፍ በፈቃድና በአምላክነቱ አንድ አምላክ መሆናቸውን ነው። ስለዚህም አብ አነሣው መንፈስ ቅዱስ አነሣው ራሱ ወልድ ተነሣ ቢል አንድ ናቸውና አንድ ዓይነት ነው። ስለዚህም ጌታችን በራሱ ፈቃድ መነሣቱን ሲገልጽ፡-

> "ወበእንተዝ ያፈቅረኒ አብ እስመ አነ እሜጡ ነፍስየ ቤዛ አባግዕየ ከመካዕበ አነሥአ ወአልቦ ዘየሐይደንያ እላ ለልየ እሚጥዋ በፈቃድየ እስመ ብውሕ ሊተ አመጥዋ አንብራሂ ወእሢማ ወብውሕ ሊተ ካዕበ አነሥአ"

> "ነፍሴን ደሞ እንሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ እመራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ካኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ካነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።" ዮሐ. ፲፡፲፯-፲፰ (10፡17-18)

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ለመረዳት ወሳኝ የወንጌል ክፍል ይህ የጌታ ቃል ነው።

1. ነፍሴን እነሣት ዘንድ ሲል ትንሣኤውን

2. አኖራታለሁ ሲል አንድ በመለቀል ሁለት በመቃብር

3. ካኖራት ሥልጣን አለኝ ሲል ከሞቱና ከመቃብሩ

4. ካነሣት ሥልጣን አለኝ ሲል ከሞት ከመነሣቱ ነው።

ይህን ቃል ያላወቀ ትርጓሜውን ያልተረዳ ሰው ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን አይገባውም። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፯፥፲፰-፳፪ (27 18-22) ጌታችን ከሙታን መካከል ተለይቶ እንደሚነሣ ለአይሁድ ሲያስተምር "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀን እነሣዋለሁ አላቸው" እነሱ ግን አልገባቸውም ሲሠራ አርባ ስድስት ዓመት ስለፈጀው የሰሎሞን ቤተመቅደስ መሰላቸው። ወንጌሉ እንደሚነግረን "እርሱ ግን ስለሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበር።" ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ማለት ይህ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ቃል አሰበው ከሙታን ከተነሣ በኋላ ይህን ስለትንሣኤው ቀድሞ እንደተናገረ መጽሐፍም በትንቢት እንደተነበዩ አሰቡ ማሰብ ብቻ አይደለም አመኑ።

ትንቢት ስለ ትንሣኤ ሙታን በብሉይ ኪዳን፡-

"ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሀ እምንዋም"

"እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ" መዝ ፸፯፥፷፭ (77፥65)

ቅዱስ ዳዊት ትንሣኤውን ሲገልጽ እግዚአብሔር ተነሣ ይላል። ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሰበከው ስለ ቅዱስ ዳዊት ነቢይነት ይመሰክራል በመዝ፡ ፲፭፥፱-፲ (15፥9-10) ያለውን ትንቢት እንዲህ ይላል፡- "ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ" ሐዋ፡፪፡፴፩ (2፥31)

ሌላው በዘመ ብሉይ አስቀድሞ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን የተገለጸበት ታሪክ የነቢዩ የዮናስ በከርሠ አንበሪ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ማደሩ ነው።

"ወነበረ ዮናስ ውስተ ከርሠ አንበሪ ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ሊያልየ"

"ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ነበረ" ዮናስ ፪፡፩ (2፡1)

ይህ የምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ምሥጢር መሆኑን ራሱ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ነግሮናል፡ - "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፡ ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደነበረ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።" ማቴ፡ ፲፪፡፵-፵፩ (12፡ 40-41) አንባብያን ሆይ በዚህ የወንጌል ቃል የተጠቀሰውን አቆጣጠር እገልጽላችኋለሁ። ይህም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት የተባለው ሲሆን ሁለት ምክንያቶች እነዚህ ናቸው። ጌታችንን በሰቀሉበት ዕለት ዕለተ ዓርብ በተአምራት ሁለት ቀን ሆናለች።

ዓርብ - ከጠዋት እስከ 6ሰዓት - 1ቀን

- ከ6ሰዓት እስከ 9ሰዓት - 1ሌሊት

- ከ9ሰዐት እስከ ማታ - 1ቀን

"ከስድስት ሰዓትም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።" ማቴ- ፳፯፡፵፭ (27፡45)

ሌላው ዓለም ሁሉ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ከምሳሌ አንድ ሰው ዓርብ ቢሞት በእሑድ ቀን ጠያቂ መቼ ሞተ ስንት ቀን ሆነው ? ቢል ከትናንት ወዲያ ሞተ ሦስት ቀን ሆነው ብለን እንደምንመልሰው ነው።

ስለዚህም ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ማለት ክብር ይግባውና ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞት ቀራኝነትና ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሞት ሳይገታው መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስን አጥፍቶ ተነሣ ብለን

የምናምነው እውነት ነው።

**<u>ምሥጢር የተባለበት</u>**

ምሥጢር የተባለበት ምክንያት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናታችን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሐደው ሥጋ መከራን ተቀብሎ ሞቶ ተነሥቶ በ40ኛው ቀን እንዳረገ በዚሁ በተዋሐደው ሥጋ ሳይለወጥ ሳይቀየር ለሰው ልጆች ሕይወት ይሰጥ ዘንድ ተመልሶ ይመጣል። ስለዚህም ሙስና መቃብርን አጥፍቶ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ከፈቱልኝ ሳይል መቃብሩ እንደተቆለፈ ድል አድርጎ ተነሥቷልና ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ተባለ።

1ኛ. መቃብሩ እንደተዘጋ፤ እንደተቆለፈ መነሣቱ፣

2ኛ. በተዋሐደው ሥጋ መነሣቱ ድንቅ ምሥጢር ነውና፣

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ክርስቶስ የትንሣኤያችን በኩር ነውና የእኛ ትንሣኤ ምን እንደሚሆንና እንደሚመስል ከጌታ ትንሣኤ "ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን" እንዳይቀላቀል ጽፌላችኋለሁ።

አንድ ሰው ሞተ ስንል ነፍስና ሥጋ ሲለያዩ ነው። ሥጋ ወደ መቃብር ይወርዳል ነፍስ ደግሞ እንደሰውየው ሃይማኖትና ምግባር ወደ ገነት ወይም ወደ ሲኦል ይገባል። በትንሣኤ ዘጉባኤ ጊዜ ወደ መንግሥተ ሰማያት አልያም ወደ ገሃነመ እሳት ይገባል።

<u>ገነት</u>፡- እስከ ትንሣኤ የጻድቃን ነፍስ የሚቆይባት ስፍራ ናት።

<u>ሲኦል</u>፡- እስከ ትንሣኤ ዘጉባኤ (እስከ ዕለተ ምጽአት) የኀጥአን ነፍስ የሚቀጣባት ሥፍራ ናት።

<u>መንግሥተ ሰማያት</u>፡- በትንሣኤ ዘጉባኤ ጊዜ ለቅዱሳን የምትሰጥ የዘላለም ቤት ናት።

ገሃነመ እሳት፡- በትንሣኤ ዘጉባዔ ጊዜ የኀጥአን የመጨረሻ ፍርድና የሞት ቦታ ናት።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ በ30 ዘመኑ ተጠምቆ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን ያፈሰሰው እኛ የዘላለምን ሕይወት እንድንወርስ ነው። ያ ደግሞ የሚሆነው በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ነው። በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም።

> "... ኢየሱስም፡- ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። ሕያው የሆነም የሚያምንብኝ ሁሉ ከዘላለም አይሞትም።" ዮሐ. ፲፩፡፳፭ (11፥25)

ጌታችን ይህንን አናምን ዘንድ በትምህርቱ ብቻ ሳይሆን በተአምራት አሳይቶናል።

ሀ/ አልዓዛርን - ዮሐ. ፲፩፡፵፫ (11፥43)

ለ/ ወለተ ኢያኢሮስን ማቴ. ፱፡፳፭ (9፥25)

ሐ/ አንድ ጐበዝን ሌሎችንም ከሞት አንሥቶ ሕይወት ሰጥቷል። ሉቃ. ፯፡፲፭ (7፥15)

> "ወእመሰ ኢይትነሣኡ ምውታን ክርስቶስኒ ኢተንሥአ እሙታን"
>
> "ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ" ፩ቆሮ፲፭፡፲፮ (15፥16)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ እንደተነሣ ሁሉ ለእኛ የትንሣኤ በኵር እንደሆነልንና ብታምኑኝ እናንተም ትነሣላችሁ ብሎ እንዳስተማረን ሥጋችን ከሞተ ከበሰበሰ በኋላ መነሣታችንን ምሥጢር አስብሎታል። ይህ የሚበሰብሰው ሥጋችን ባለመበስበስ የሚደክመው ባለመድከም የሚራበው ባለመራብ የሚሞተው ባለመሞት በመሞት በድካም የሚወድቀው በኃይል የሚነሣበት ነውና

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ተባለ። ቅዱስ ጳውሎስ የምሥጢረ ትንሣኤን ነገር ቀጥሎ ባለው ንጽጽር ለቆሮንቶስ ሰዎች አስተምሯል። ፩ቆሮ፲፭ (15)

በመበስበስ ይዘራል ባለመበስበስ ይነሣል፤ በድካም ይዘራል በኃይል ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል በክብር ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል መንፈሳዊ አካል ይነሣል

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ አእላፍ አእላፋት ከሆኑ መላእክቱ ጋር ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ በቀኙ ከሚቆሙት ቅዱሳን ጋር ያቆመን ዘንድ የእርሱ ፈቃድ ይሁንልን።

## ንፍሐተ ቀርን በዕለተ ትንሣኤ

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይልና በብዙ ክብር ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ የሙታን መነሣት እንዴት እንደሚሆን በማቴዎስ ወንጌል ፳፬፥፴፩ (24፥31) እንደነገረን መላእክቱን ከመለከት ድምጽ ጋር ይልካቸዋል። ቅዱስ ጳውሎስም ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ባስተማረበት ፩ቆሮ፲፭፥፶፩ (15፥51) ከአምስቱ ምሥጢራት አንዱን ልንገራችሁ ብሎ ሙታን ብቻ ሳይሆኑ ጌታ አምላክ ሲመጣ በሕይወተ ሥጋም ያሉ በቅጽበተ ዓይን ሞትን ቀምሰው በኋለኛው መለከት ግብር አምግብር ይለወጣሉ ይላል።

የንፍሐተ ቀርኑ (የመለከቱ ዐዋጅ) በሦስት ክፍል እንደሚሆን ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ በቅዳሴው ጽፎታል።

፩. በመጀመሪያው ንፍሐተ ቀርን (መለከት) በተለያየ አሟሟት የሞተ አንዲት ቅርፊት ሳትቀር የተበተነ የሥጋ ትቢያ ሁሉ ወደ ቀደመ መገናኛ ይሰበሰባል።

፪. በሁለተኛው የመለከት ድምፅ (ዐዋጅ) አጥንቶች ከሥጋና ከደም ጋር ይያያዛሉ።

፫.በሦስተኛው የመለከት ድምፅ ሙታን እንደ ዓይን ጥቅሻ ይነሣሉ። ጻድቃንም ኃጥአንም ይነሣሉ።

"በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል.... በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነሣሉ፡ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና" ዳን፡፲፪፡፩-፪ (12፡1-2)

# ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

እነዚህ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በዓይን የሚይታይ በእጅ የሚይዳሰስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከምእመናን የሚታደሉባቸው የሚፈጸምባቸው ናቸው። ምሥጢር ከወዳጅ የሚነገር እንደሆነ ሁሉ እነዚህም ምሥጢራት መባላቸው ከእውነተኛ ክርስቲያኖች የሚፈጸሙ በመሆናቸው ነው።

አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ነገረ መለኮት የሚነገርባቸው ሲሆን እነዚህ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ምሥጢራተ ክርስቲያን ናቸው ይህም ማለት ከምእመናን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸም ነውና።

"ጥበብ ቤቷን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶዎች አቆመች" ምሳ፡ ፱፡ ፩ (9፡1)

ዝርዝራቸውም

ምሥጢረ ጥምቀት

ምሥጢረ ሜሮን

ምሥጢረ ቁርባን

ምሥጢረ ክህነት

ምሥጢረ ተክሊል

ምሥጢረ ንስሐ

ምሥጢረ ቀንዲል ሲሆን አፈጻጸማቸውም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

## 1. ምሥጢረ ጥምቀት፡-

ይህ የሚፈጸመው ካመነ ሰው ነው። ማር. ፲፮፡፲፮ (16፥16)። ሙሉ ሥርዓቱ የሚፈጸምበት "መጽሐፈ ክርስትና"በየተባለ መጽሐፍ አለ።

**ከመጠመቅ ዕድሜያችን ያህል መሆን አለበት ከሚለው ፡-**

ሀ/ ከእውነተኛይቱ እምነት ከተዋሕዶ ውጪ ከሆነ ሰው። መጀመሪያ የቤተክርስቲያኒቱ እምነትና ሥርዓት መማር አለበት። ማመንም አለበት። "ባመነም ጊዜም የሚሰጠውን ቀኖና ፈጽሞ ይጠመቃል። ያመነ የተጠመቀ ይድናል እንዲል" ማር. ፲፮፡፲፮ (16፥16)

ለ/ ከክርስቲያኖች /ከተዋሕዶ/ አማኝ ከክርስቶስ ወገን ግን ቤተክርስቲያናችን ሥርዓትን ሠርታለች። ይኸውም ወንዶች በተወለዱ በ40 ቀናቸው ሴቶች ደግሞ በ80 ቀናቸው ይጠመቁ ዘንድ። ይህም ምሳሌ አለው፡-

- አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ሔዋን ደግሞ በ80 ቀኗ ወደ ገነት መግባታቸው ኩፋሌ ፬ ፱ (4፥9)
- ሴት ልጅ ወንድ ስትወልድና ሴት ስትወልድ የመንጻት ልማዷ ወንድ ከወለደች 40 ቀን ሴት ከወለደች 80 ቀን ስለነበር። ዘሌ. ፲፪ (12)

በነዚህ ምሳሌዎች ቤተክርስቲያናችን ከክርስቲያን ልጆች እንዲህ ሥርዓትን ሠራች። ሕፃናት ሲጠመቁ የክርስትና አባት ወይም የክርስትና እናት ይደረጋል። ይህም ሕፃናቱን የሃይማኖት ትምህርት ያስተምሩ ዘንድ ነው።

ሕፃንም ይሁን ትልቅ ሰው በሚጠመቁበት ጊዜ ሦስት ጊዜ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ከሰገዱ በኋላ ይጠመቃሉ። ከዚያም ሥርዓተ ቅዳሴው ተፈጽሞ ሥጋውንና ደሙን ይቀበላሉ።

- ጥምቀት የሚደረገው በውኃ ብቻ ነው።
- ተጠማቂው ሦስት ጊዜ በውኃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ይደረጋል ወይም ካህኑ በላዩ ያፈስበታል። ምሳሌነቱ የጌታችን ሞቱ ን መቀበሩንና ከሞት መነሣቱን የሚያስረዳን ነው።
- ከተጠመቀ በኋላ ማዕተብ በአንገቱ ይታሰርለታል። ይህም ጌታን በጦር ሲወጉት ከጎኑ የፈሰሰው የደሙና የውኃው

ምሳሌ ነው።

ጥምቀቱ ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ስለሆነ አንድ ጊዜ ብቻ ነው አይደገምም። ሁለት ጥምቀት የለም ሃይማኖት አንዲት ብቻ ስለሆነች ጥምቀትም አንዲት ናት። ኤፌ ፬፥፭ (4፥5) ስለዚህ በሌላ እምነት የነበረ ሰው ሁሉ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንዲት ሃይማኖት ሲመጣ ጥምቀት ይፈጸምለታል።

## ማዕተብና ክታብ

ማዕተብ (በአንገት የሚታሰሩ ክሮች)

ማዕተብ የሚለው "ዐተበ" ባረከ ከሚል የግእዝ ቃል የወጣ ነው። ማዕተብ ስንል የተባረከ ይሆናል። በአንገታችን የምናስራቸው ክሮች ተባርከው ስለሆነ በዚሁ ማዕተብ ተብለው ይጠራሉ። አሰረ ማለት ነው የሚል ይገኛል።

## ፩፡ ነጭና ቀይ ማዕተብ፡-

ነጭና ቀይ ክር በክርስትና ጊዜ የሚታሰር ሲሆን ትርጉሙም ጥምቀት የጌታችንን ሞትና ትንሣኤ የምናስብበት ስለሆነች ይኸውም ወደ ውኃው መጥለቅ እንደ መቃብር፤ ከውኃው መውጣት እንደትንሣኤ ነውና፡

> "...ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን?"

የከብር ከብር ይግባውና ጌታቸችን በቀራንዮ በመስቀል በተሰቀለና ሞትን በቀመሰ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ እንደጻፈው ከጭፍሮቹ አንዱ ይላል ለንጊኖስ ይባላል በጦር የጌታችንን ጎኑን ወጋው በዚህ ጊዜ ደምና ውኃ ፈሰሰ።

> "፩ዱ እምሐራ ረገዞ ገቦሁ ዘየማን በኲናት ወሶቤ ወጽአ እምኔሁ ደም ወማይ"
>
> "ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው ያንጊዜ ደምና ውኃ ወጣ" የሐ ፲፱፡፴፬ (19፡34)

ከዚህም ምሥጢር የተነሣ በጥምቀት ጊዜ የሚታሰረው ቀይና ነጭ ክር የደሙና የውኃው ምሳሌ ነው።

## ፪. ጥቁር ማዕተብ

ጥቁር ማዕተብ ደግሞ በጥምቀት ያገኘናት ሃይማኖታችን በዚህ ዓለም ስንኖር ፈተናና መከራ እንዳከበባት የሚያሳይ ነው። በዚህ ሃይማኖት በወርቅ ትመስላለች ወርቅ ወርቅነቱ የሚታወቀው በእሳት ተፈትኖ ነው። ሃይማኖትም ጽኑ መከራዎችና ፈተናዎችን በማለፍ ነው።

> "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ" ዮሐ ፲፮፥፴፫ (16፥ 33)
>
> "ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ከምስጋናና ከክብር ከውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል" ፩፥፩-፮ (1፥1-6)

## ክታብ

ከዚህ በተጨማሪ በሕግ መጽሐፍ እንደተጻፈ እንዲህ ሲል ፡- "እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ ለልጆችህም አስተምረው በቤትህም ስትቀመጥ በመንገድም ስትሄድ ስትተኛም ስትነሣም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።" ዘዳ ፮፥፮-፱ (6፥6-9)

በሚለው መሠረት ብዙ ክርስቲያኖች ክታብ በአንገታቸው ያደርጋሉ።ክታብ ማለት ጽሑፍ ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው።በተለይ "ትምህርተ ኅቡዓት" በአንገት ይታሰራል። ትምህርተ ኅቡዓት ከሰባቱ ኪዳናት አንዱ ሲሆን ጌታችን ይህን አስተምሯቸዋል ሰይጣን በዚህ አፈአል ስለዚህም በተለይ ልጆች በአንገታቸው ያስሩላቸዋል። ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነ ሌላ አሸንክታብ

ሁሉ ፈጽሞ ከልክል ነው። ኃጢአትም ነው።

## 2. ምሥጢረ ሜሮን፡-

ይህ ቅዱስ ዘይት ሲሆን ማንኛውም ተጠማቂ ተጠምቆ ሲወጣ የሚቀባው ነው። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋን ያሳድር ዘንድ ተጠማቂው በዚህ ይታተማል። ልክ እንደ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ይደረጋል።

## 3. ምሥጢረ ቁርባን፡-

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የዘላለም ሕይወት ይሆን ዘንድ ያቀረበው የራሱ ሥጋና ደም ነው። ቄሱ ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ ሥርዓተ ቅዳሴው ሲያደርስ ወደ እውነተኛ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣል።

- በሥርዓተ ቁርባን ጊዜ ቄሱ ሥጋውን ያቀርባል ዲያቆን ደግሞ በዕርፈ መስቀል ደሙን
- ቁርባን ቢያንስ ከ18 ሰዓት ከምግብና መጠጥ ተከልክሎ ነው።ጾም ግድ ነው።
- ሥጋውና ደሙ (ቁርባን) ለክርስቲያኑ ሁሉ በንስሐ የተፈቀደ ነው።

**በመቁረብ ምን እናገኛለን?**

እግዚብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ ያለሕግ አልተዋቸውም። የሰጣቸውም ሕግ ክፉንና ደጉን ከምታሳውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ ነበር። በምክረ ሰይጣን ተታለው በበሉ ጊዜ ግን ወደቁ። አምላክም የሰውን ልጅ አልተወውምና ሊያድነው ከእመቤታችን ተወለደ። በቀራንዮ በመስቀል ተሰቅሎም ደሙን አፍስሶ የሞተውን አዳምን ሕይወት ሰጠው።የወደቀችውን ሔዋን አዳናት ዘፍ. ፫፡፩ (3፥1) ገላ.፬፡፬ (4፥4) ማቴ. ፳፯፡፴፪-፴፬ (27፥32-34)

ስለዚህ ሕይወትን ያገኘነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነውና። ይህን በቀራንዮ የተሰቀለልንን ቅዱስ

ሥጋ ስንበላ ክቡር ደሙን ስንጠጣ የዘላለም ሕይወት ይኖረናል። ማለትም ጌታችን ከእኛ ጋራ እኛም ከጌታችን ጋራ ለዘለዓለም እንኖራለን።

> "የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ሥጋን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወተ የላችሁም ...ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።" ዮሐ. ፮፥፶፫-፶፱ (6፥53-59)

ከዚህ የወንጌል ቃል የአምላካችን ትዕዛዝ ተነሣ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በተቀበልን (በቆረብን) ጊዜ ሦስቱ ዋና ጥቅሞች፦

የኃጢአት መደምሰሻ

የአጋንንት ድል መንሻ

የመንግሥተ ሰማያት መውረሻ ናቸው።

## ሥጋና ደሙ የሚሰጠው ለማን ነው?

ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ሕይወቱን የሰጠው ለሁሉ ነውና። በንስሐ ሕይወት በምክረ ካህን ያለ ክርስቲያን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ያገኝ ዘንድ ያለዕድሜ ገደብ ሥጋውና ደሙን ይቀበል ዘንድ ይገባዋል። ቍርባን የሚከለክለው ዝሙት ስርቆት መግደል ሐሜትና የመሳሰሉት ሲሆን ከእነዚህ ርቆ በቅድስና ሕይወት በክርስቲያን ሁሉ ሥጋ ወደሙን ተቀብሎ ሊኖር ይገባዋል። የሰው ልጅ ከኃጢአት ነጽቶ መኖር አይችልምና እግዚአብሔር ይህንን ስለሚያውቅ ለሁላችን የንስሐ ሕይወትን አዘጋጅቶልናል። እንዲም የሥጋ ወደሙ መስጠት ምክንያት ከኃጢአት መደምሰሻ ነው

## 4. ምሥጢረ ክህነት፦

በቤተክርስቲያናችን ሦስት ዓይነት የክህነት መዓርጋት አሉ።

<u>ዲቁና</u>፦ በአንብሮተ እድ በጳጳሳት አማካኝነት የሚሰጥ ነው።

**ቅስና**፡-አንድ ዲያቆን ሲያገባ ወይም ሲመነኩስ የሚሰጥ ነው።

**ጵጵስና**፡-ይህ ሹመት በአሁን ሰዓት የሚሰጠው በድንግልና ካለ መነኮሴ ነው። የሚሾመው በመካ የሲኖዶስ አባላት ፈቃድ በፓትርያሪኩ አንብሮተ እድ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሕግና በጥንት የቤተክርስቲያን ሥርዓት ጳጳሳት የአንዲት ሴት ባል የሆኑም ይሾሙ ነበር። እነዚህ ያየናቸው የክህነት ሥልጣን የሚሰጡት ለአንድ ሰው አንደ ብቻ ነው።

## **ዲያቆናዊት**

የሥልጣነ ክህነትን ነገር በተናገረበት በ ፩ጢሞ ፫፡፲፩ (3፡11) "እንዲሁም ሴቶች ጭምቶች የማያሙ ልከኞች በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል።" ይህንንም ቅዱሳን ሐዋርያት በመጽሐፋቸው ሲገልጹት "ወዓዲ ዲያቆናዊትኒ ትሠየም ወይእቲ ኅሪት ወንጽሕት እንተ አልባቲ ነውር ከተልእኮ እንስት" "ዳግመኛም ዲያቆናዊት ትሾም ይህችም ነውር የሌለባት ሴቶችን ከማገልገል የተመረጠች ንጽሕት ትሁን" ዲድስቅልያ

የዲያቆናዊት አገልግሎት የታወቀ ነው። ይህም በዲድስቅልያ ፲፮፡፴፪ (16፡32) እንደተጻፈው ለምእመናት (ለሴቶች) መልእክተኛ ናት "ወትቀብዓን ቀብዐ ወታለብሶን አልባሲሆን እምድኅረ ጥምቀት" ንዑስ ክርስቲያን ወይም ከአደጉ በኋላ ከሚጠመቁ ሴቶች የካህኑን እጅ ይዛ ከተጠመቁ በኋላ ቅብዕ ትቀባለች ልብሳቸውን ታለብሳለች።

ከዚህ ውጭ ግን በመቅደሱ መቀደስና ማስተማር፣ ማጥመቅና ማቁረብ ሌሎችንም የካህኑንም ሆነ የዲያቆኑን ሥራ አታደርግም።

## **ዓቃቢት**

ይህ ሥራ በአብዛኛው የሴት ሥራ ሲሆን ምስጋና ይግባትና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከቤተመቅደሱ አገልግሎት ማይ (ውኃ) ትቀዳ እንደነበር ሁሉ፡ በዚህ አገልግሎት ያሉ ሴቶች (ዓቃቢያት) ይህንኑ ያደርጋሉ።

ሌላው ትልቁ ሥራቸው ደግሞ ከሥጋ ወደሙ የሚሆነውን መገበሪያ ማዘጋጀት ነው።

## 5. ምሥጢረ ተክሊል፦

ምሥጢረ ተክሊል በሁለት ክርስቲያኖች በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት ፈቃድ በቤተሰቦቻቸውም መልካም ፈቃድ ከሚደረግ ጋብቻ በተክርስቲያን የምትፈጽመው ሥርዓት ነው።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ መሆን አለባቸው።

ደናግል (ካን/ካት) መሆን አለባቸው።

ከዝምድና ስባት ትውልድ የራቁ መሆን አለባቸው።

የሚፈጸመውም አንድ ጊዜ ብቻና በሥጋ ወደሙ ነው። ፍቺና ሞት ቢያጋጥምና ትዳር ቢመሠርቱ በተክሊል አይደረግም።

## 6. ምሥጢረ ንስሐ፦

አንድ ክርስቲያን በኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ ከእግዚአብሔር የሚጠይቀው ይቅርታ መጸጸት መመለስ ከኃጢአትም መንጻት መጥራት ነው።

እያንዳንዱ ክርስቲያን መምህረ ንስሓ (የንስሓ አባት) ያስፈልገዋል።

ንስሓ የሚደጋገም ነው። ኃጢአት ይደጋገማልና

ንስሓ አለ ብሎ ኃጢአትን መሥራት በእግዚአብሔር ላይ እንደመዘበት ይቆጠራል፡

ንስሐ የቃሉ ምንጭ የግእዙ ግስ ነስሐ ነው። ይህም ንስሐ ገባ ወደ እግዚአብሔር ተመለሰ ማለት ነው። ሰው የቀድሞ በደሉን ትቶ ወደ አምላኩ እግዚብሐር ሲመለስ ወይም ስትመለስ ያ ንስሓ መግባት ይባላል። "ንስሓ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋትም እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ፤ የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ከእናንተ አድርጉ የእስራኤል ቤት ሆይ ስለምን

ትሞታላችሁ የምሞቱን ሞት አልፈቅድምና ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።" ሕዝ. ፲፰፡፴-፴፪ (18፥30-32)

አምላካችን እግዚአብሔር በሕይወት እንድንኖር ይፈልጋልና። በደላችንና ኃጢአታችንን ይቅር ይል ዘንድ ንስሐን አዘጋጀልን። ይህም ያለማወቅ ጊዜ አላልፎ እግዚአብሔርን በማወቅ መኖር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው እንዲህ ብሎ "እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል" ሐዋ. ፲፯፡፴ (17፥30)። ሰው በባሕርዩ ድካመት በኃጢአት ለሚወድቅ ከወደቀበት መነሣት የሚችለው ጌታችን አምላካችን ባዘጋጀው የንስሐ መንገድ ነው። ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው እኛን በንስሐ ሕይወት ለማዳን ነው። ትእዛዙም ንስሐ ግቡ የሚል ነው።

"ንስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት"

"መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" ማቴ. ፬፡፲፯ (4፥17)

የጌታችን መንገድ አዘጋጅ የተባለው ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የሰበከውና ያስተማረው መንግሥተ ሰማያት ስለቀረበች ንስሐ ግቡ ከኃጢአታችሁ ተመለሱ እያለ ነበር። "በዚያ ወራት መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።" ማቴ. ፫፡፩፡፪ (3፡1-2)። ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባ ዘንድ አስቀድሞ ንስሐ መግባት ያስፈልገዋል። ብዙ ሰዎች ንስሐ እንዴት ነው የሚገባው? ለማን ነው የሚገባው? የሚሉ ጥያቄዎች በውስጣቸው ይፈጠርባቸዋል መልሱ በመጽሐፍ ቅዱሳችን እንዲህ ተቀምጧል።

**<u>ንስሐ ለማን ነው የሚገባው?</u>**

1. ለእግዚአብሔር

2. ከካህን

## ንስሐ እንዴት ነው የሚገባው ?

ንስሐ በሚገባበት ጊዜ ኃጢአትን መንገር ነው። ይህም ደግሞ ከአሠርቱ ትዕዛዛትና ከስድስቱ ሕገ (ቃላተ) ወንጌል ያጎደሉትን በመናዘዝ ነው ። ከ ሀ እስከ ፐ አሠራሩን ግን መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም።

## ራስን ለካህናት ማሳየት

ሰዎች ንስሐ የሚገቡት ልዑል እግዚአብሔር እንዳዘዘ ራሳቸውን ለካህን በማቅረብ ኃጢአታቸውንም በመንገር ማለትም በመናዘዝ ነው። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን አምላካችን አባታችንና ፈጣሪያችን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሰጠን ትእዛዝ ራስን ለካህን ማሳየት ነው።

### *በብሉይ ኪዳን*

በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፫ (13) እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ያዘዛቸው ሰዎች በደዌ በሚመቱበት ሰዓት ወደ ካህኑ ይቀርባሉ ካህኑም ንጹሕ ነው ያለው ንጹሕ ይሆናል ርኩስ ነው ያለውም ርኩስ ይሆናል። ይህ ለሥጋም ለነፍስም ደዌ ይሆናል።

### *በሐዲስ ኪዳን*

በማቴዎስ ወንጌል ፲፰፥፲፰ (18፥18) እንደተገለጸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የነገራቸው እንዲህ የሚል ነው። "እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።"

ይህ በሁለቱም ኪዳናት የተሰጠ ኃጢአትን በንስሐ የማንጻት ሥልጣን ነው። ይህም ሥልጣን የተሰጠው ለካህናት ነው። ስለዚህ ከኃጢአት ነጽቶ ሥርየትን ለማግኘት ግዴታ ወደ ካህን መቅረብ ያስፈልጋል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እርሱ ቀርበው "ኢየሱስ ሆይ አቤቱ ማረን"

ብለው የለመኑትን አሥሩን ለምጻሞች ያዘዛቸው ሄደው ራሳቸውን ለካህን እንዲያሳዩ ነበር።

"ሂዱ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ" ሉቃ. ፲፯፥፲፬ (17፥14)

በዚህ በፈጣሪያችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት ንስሐ በምንገባበት ጊዜ ግዴታ ወደ ካህን መቅረብ ይኖርብናል። ከዚህም ነው አንድ ክርስቲያን የነፍስ አባት ወይም የንስሐ አባት የሚያስፈልገው። ይህም መምህረ ንስሐው ወይም የነፍስ አባት ከተነሳሒው (ንስሐ ከሚገባው ወይም ከምትገባው) ማድረግ የሚገባውን ቀኖናውን ይነግረዋል። ይህም ቀኖና እንደ ኃጢአቱ የሚሰጥ ሲሆን ካህኑ በቤተክርስቲያን ሕግ መሠረት ይፈጽማል። ይህም ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የያዘ ይሆናል።

ሀ. ጾም

ለ. ጸሎት

ሐ. ለቅሶ ወይም ዕንባ

መ. ስግደት

ሠ. ምጽዋት

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዛት በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ብንመለስ እምካካችንም በረድኤት ወደእኛ እንደሚመለስ ያስተምሩናል።

"ይህ አስቡና አልቅሱ ተላላፊዎች ሆይ ንስሐ ግቡ ልባችሁንም መልሱ" ኢሳ. ፵፮፥፰ (46፥8)

"አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በለቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ" ኢዩ ፪፥፲፪

"ኃጢአትህንም በጽድቅ በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር" ዳን. ፬፥፳፯ (4፥27)

እነዚህ የተመለከትናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች የሚነግሩን በንስሐ ጊዜ ልንፈጽማቸው የሚገቡት ሕግጋት ነው። እዚህ ላይ ልብ የምንለው ነገር በየዕለቱ

ከእግዚአብሔር ይቅር ብለን አያለን ስንጸልይ፣ ስናስቀድስ፣ የእግዚአብሔር ቃል ስንማርና ስናነብ ንስሐ መሆኑን ነው። ሁልጊዜ በየሰዓቱ ይቅር በለን ልንለው ይገባል። እንደ ትእዛዙም ወደ ካህናት በመቅረብ እንናዘዛለን።

"ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች ቀሳውስት ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሠረይለታል እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ" ያዕ ፭፥፲፬-፲፮ (5፥14-16)

ይህን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቀብለን ንስሐ በምንገባበት ጊዜ ጌታችን እንደተናገረው በሰማይ ደስታ ይሆናል መላእክትም ሐሤት ያደርጋሉ። "እላችኋለሁ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።" ሉቃ. ፲፭፥፲ (15፥10) በተቃራኒው ደግሞ ሰዎች ይህን ታላቅ የእግዚአብሔር ትእዛዝ በማወቅም ባለማወቅም ባይፈጽሙና ንስሐ ባይገቡ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ድኅነትን ማግኘት ፈጽመው አይችሉም።

"ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ" ሉቃ. ፲፫፥፫ (13፥3)

"እንግዲህ ንስሐ ግባ አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፤ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ" ራዕ. ፪፥፲፮ (2፥16)

ንስሐ ገብተን ከኃጢአት ርኩሰት ነጽተን የመንግሥቱ ወራሽ ያድርገን አሜን።

## 7. ምሥጢረ ቀንዲል፡-

ይህ ሥርዓት ከሥጋም ከነፍስም ከበሽተኞች የሚደረግ ነው። ይህም የታመሙ ሰዎች ጸሎት ተደርጎላቸው ቀንዲል ይቀባሉ ከሕመማቸውም ይፈወሳሉ ከሥጋ በሽታ ብቻም ሳይሆን ከነፍስ ደዌም ይድናሉ።

በጠቅላላው እነዚህ 7ቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የሚፈጸሙበት እያንዳንዳቸው የራሳቸው የጸሎት አፈጻጸምና ሥርዓት አላቸው። እነዚህም የቤተክርስቲያኗ ሥርዓተ አምልኮ ማስፈፀሚያና የሃይማኖት መመሪያ ናቸው።ሌሎችም የተለያዩ ምሥጢራት ከምእመናን ይደረጋሉ።

ክርስቲያን የተባለ ሁሉ በግድ የሚፈጽማቸው ምሥጢራት

1. ጥምቀት 2. ሜሮን 3. ቁርባን 4. ንስሐ

በፈቃድ የሚፈጸሙ ምሥጢራት

1. ክህነት 2. ተክሊል 3. ቀንዲል

# የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ልደት

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ልደት አለው። እነዚህም አንደኛው ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ የተወለደው ነው። ከአብ በመወለዱም አብ አይበልጠውም ወልድም ልጅ ስለተባለ ከአብ አያንስም። ከባሕርይ ሕይወቱም ከመንፈስ ቅዱስም ትክክል ነው። አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው እንደተናገረው አብርሃም ይስሐቅን ፤ ይስሐቅ ደግሞ ያዕቆብን አባት በመሆን እንደሚበልጠው ከሥላሴ ግን እንዲህ አይደለም።

"አኮ ከማሁ ከመከኮት ኢይልሕቅ አብ እምወልዱ ወልድኒ ኢይልሕቅ እመንፈስ ቅዱስ ወመንፈስ ቅዱስ ኢይንእስ እም ወልድ ወወልድኒ ኢይንእስ እምአቡሁ"

"አብ ከልጁ አይበልጥም። ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም። መንፈስ ቅዱስም ከወልድ አያንስም። ወልድም ከአባቱ አያንስም"

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱ አንድ አምላክ ናቸው።

"እሐቲ መንግሥት ወእሐቲ ሥልጣን ወእሐቲ ምኩናን" በመንግሥት አንድ ፤ በሥልጣን አንድ ፤ ባገዛዝ አንድ ናቸው።

የወልድ ከአብ መወለድ ዘመን የማይቆጠርበት ነው። በቅዱስ ዳዊት የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ቅድመ ዓለም አካል ዘእምአካል ባህርይ ዘእምባህርይ ወልድ ከአብ መወለዱን ይገልጽና ከድንግልም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ተዋሕዶ በተወለደ ጊዜም ልጁ እንደሆነ ዛሬ ብሎ ይገልጸዋል።

"ወለዶ አብ ከወልዱ አልቦ ዕለት ወአልቦ ሰዓት"

"አብ ልጁን ወለደው ዕለት ግን የለም ሰዓትም የለም" ሠለስቱ ምእት

"እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ ወእነ ዮም ወለድኩከ"

"እግዚአብሔር አለኝ፡ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ" መዝ. ፪፡፳፯ (2፡27)

ይህም ቃል አብ ወልድን እንደወለደው በምሥጢረ ሥላሴም እንደተመለከትነው አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ መሆኑን ስያስረዳ ቅዱስ ጳውሎስ በሰንበት ቀን በጲስድያ ዘአንጾኪያ አስተምሮታል። የሐ ሥራ ፲፫፡፴፫ (13፡33) ። ለዕብራውያንም ጽፎላቸዋል ዕብ ፩፡፭ (1፡5) ።

ይህ የተመለከትነው የወልድ የመጀመሪያ ልደቱ ዘመን በማይቆጠርለት ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሰዎችን ልጆች ሁሉ ለማዳን ድኅረ ዓለም ከአባታችን አዳም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ያለወንድ ዘር (ያለአባት) ከድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደው ልደት ነው። የማቴዎስ ወንጌል ሲጀምር ይህ ልደቱ እንዴት እንደሆነ እንዲህ ይላል፡- "መጽሐፈ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም"

"የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ" ማቴ ፩፡፩ (1፡1)

ይህም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እመቤታችን ያለወንድ ዘር እንደወለደችው ቃል የተባለ እግዚአብሔር ሥጋ ማለትም ሰው የሆነበትን ምሥጢር የሚተርክ ነው። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አስረግጦ ይናገረዋል።

"ወአመ በጽሐ ዕድሜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት" ገላ ፬፡፬ (4፡4)

ይህም ማለት የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ከአዳም ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ያለው እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን አንድ ልጁን ላከ። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ቃሉ የጌታችንን ሁለቱን ልደቶች ገልጿቸዋል። አንደኛ "ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ" ብሎ ቀዳማዊ ልደቱን እግዚአብሔር ልጁን ላከ ይላልና። ሁለተኛ "ወተወልደ እምብእሲት" ከሴት ብቻ የተወለደው ብሎ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከእመቤታችን መወለዱን ይገልጻል።

ከእግዚአብሔር የተካከው ቅዱስ ገብርኤል ድንግልን ሲያበሥራት የተናገረው የሁለት ልደትን ነገር ነው።

"እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ። እርሱ ታላቅ ነው የልዑል ልጅም ይባላል። ሉቃ፩፡ ፴፩ (1፡31)

አባ ኤፍሬም ሶርያዊ በሐሙስ ውዳሴው ቅድመ ዓለም ከአብ ድሕረ ዓለም ከእመቤታች የመወለዱን ሁኔታ እንዲህ ተናገረ፤

"እምኀበ አብ ወጽአ ቃል ዘእንበለ ድካም ወእም ድንግል ተወልደ ዘእንበለ ሕማም"

ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ድካም ሳይሰማው ተወለደ። አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከድንግል ሕማም ሳይሰማት እርሱንም ሕፃናትን የሚሰማ ሳይሰማው በኅቱም ድንግል ተወለደ።

ሁለት ልደት ማለት ይህ ነው። ከዚህ የወጣ አስተምህሮ ትልቅ ስሕተት ነው።

"ልደት ቀዳማዊ ተዐውቀ በዳኃራዊ ልደት" ይህም ማለት ዳኃራዊ ልደቱን ከድንግል መወለዱን ከቀዳማዊ ልደቱ ከአብ ከመወለዱ እምላለ መርገፍ አድርጎታል።

የደገኛው መምህር የባስልዮስ ወንድም የኑሲስ ኤጲስቆጶስ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ስለጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት አብ ልጁ መሆኑን እንደመሰከራት በተናገረበት አንቀጽ እንዲህ አለ።

"በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ" ማቴ ፫፡ ፲፯ (3፡17)

"ኢትኃሥሥ ከተሠግዎቱ አብ በዲበ ምድር ወኢትኃሥሡ ኮቱ እመ በሰማያት ወዉእቱ እንበለ አብ በዲበ ምድር ወውእቱ እንበለ እም በሰማያት"

"በምድራዊ ልደቱ አባት አለው አትበሉ በሰማያዊ ልደቱም እናት አለችው አትበሉ እርሱ በምድር አባት የሌለው ነው በሰማይም እናት የሌለችው ነው።"

ሃይማኖተ አበው

የመለኮቱ መገኘት ከድንግል አይደለም ከአብ ከተወለደ በኋላ ለመለኮቱ ሁለተኛ ልደትን አይሻምና ከዓለም አስቀድሞ ከነበረ ከአብ ጋር በየጊዜው ሁሉ ከሚኖር ከርሱ በመለኮቱ ዳግመኛ ሊወለድ ሁለተኛ ልደትን ወደደ ተብሎ ይነገርለት ዘንድ ይህስ ክሕደት ነው ሐሰትም ነው። ቅዱስ ቄርሎስ ሃ.አ. ምዕ ፳፲

# የክርስቲያኖች ሁለት ልደት

ክርስቲያኖች ሁለት ልደት አለን። አንደኛ ከእናት ከአባታችን የተወለድነው ልደት ነው። ይኸውም ከአንድ ሕዋን ነፍስና ሥጋ የሚሆን ከአባት ዘር ይከፈልና ከእናት ደግሞ ደም ተወስዶ በሴት (በእናት) ማኅፀን ተጸንሶ በ፵(40)ኛው ቀን ተስእሎ መልክ ይቀረጻል። በእናት ማሕፀን ሰው የሚሆንበት ፵ (40)ኛው ቀን ነው። ብዙ ሰዎች የ፵ (40) ቀን ዕድሌ የሚሉት ይህንን ነው።

"የዐቁር ማየ በማኅፀን ወያረግዕ ከመ ይኩን ሥጋ የዐሥር በእሥራው ወያጸንዕ በአምትንት"

"ውኃን በማኅፀን ይቋጥራል ሥጋም ይሆን ዘንድ ያረጋዋል በሥር ያሥረዋል በጅማትም ያጸናዋል" ቅዳሴ ሠለስቱ ምዕት

ከዚህ በኋላ በዘጠኝ ወር በአምስት ቀን ከእናት ከአባት የምንወለደው የመጀመሪያ ልደት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጥምቀት የምናገኘው ነው። ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን ሴቶች ደግሞ በሰማንያ ቀን ከአብራከ መንፈስ ቅዱ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከሥካሴ ልጅነትን የምናገኝበት ሁለተኛ ልደታችን ነው። ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሁረ ኦሪት ከነበረው ከፈሪሳውያን አለቃ ከኒቆዲሞስ ይህንን ሲያስተምረው በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል እንዲህ ተጽፏል።

"ኢየሱስም መለሰ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆዲሞስም ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን አለው። ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ

አታድንቅ።" ዮሐ ፫:፫-፯ (3:3-7)

ከዚህ የወንጌል ቃል እንደምንረዳው ሁለቱ ልደቶቻችን በጌታችን ተገልጸዋል። ወደምሥጢሩ ሳንገባ "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው" ብሎ የመጀመሪያ ልደታችንን "ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው" ብሎ ሁለተኛ ልደታችንን በግልጽ ያሳየናል።

# የጌታ በዓላት

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን የማዳን ተግባር በየዕለቱ የምናስብ ስንሆን። ስለእኛ ድንቅ ነገር ያደረገባቸውን ዕለታት ደግሞ በተለየ ምስጋና እየዘከርን እናከብራቸዋለን። እነዚህም ዘጠኙ ዐቢያንና ዘጠኙ ንኡሳን በዓላት ናቸው። እኒህን በዓላት ስናከብር ለሥጋዊ ምግብና መጠጥ ሳይሆን በነዚህ ቀናት የተደረገውን ድንቅ ድንቅ ተአምራት ተመልክተን ሕይወታችንን ለአምላካችን በመስጠት የተቀደሰ ሕይወት ይኖረን ዘንድ ነው።

## ዘጠኙ ዐበይት በዓላት

1. <u>ትስብእት</u>፡- ይህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው ትንቢት በተቆጠረው ሱባዔ አማካኝነት የሰውን ልጅ ለማዳን ንጽሕት ቅድስት ከምትሆን ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ያለወንድ ዘር የተጸነሰበት ዕለት ነው። ቀኑም መጋቢት 29 ቀን ነው። "ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅ ትወልዳለች ..." ኢሳ. ፯፡፲፬ (7፥14) ሉቃ. ፩፡፴ (1፥30)

2. <u>ልደት</u>፡- ይህ የሰው ልጆች ሁሉ ደስታ የሆነ ታላቅ የመዳን በዓል ነው። "እትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ተወልዶላችኋልና" ሉቃ. ፪፡፲፩ (2፥11) ብዙዎች ነቢያት እግዚአብሔር አምላክ ክክብር ዙፋኑ ዝቅ ብሎ የደካማውን የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ እንደሚወለድ ተናግረው በነበረው ትንቢት መሠረት አምላካችን ከእመቤታችን የተወለደበት ዕለት ነው። ይህም ቀን ታሕሳስ 29 ነው። በዐራት ዓመት አንደ ታሕሳስ 28 ቀን ይከበራል። ኢሳይያስ እንዲህ የሚል ትንቢት ተናግሮ ነበር "ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶልናል አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።" ኢሳ. ፱፡፮ (9፥6) የጌታችን

መወለድ የሰው ሰላምና ደስታ ነው። ሰው ከአምላኩ የተገናኘበት ከመላእክት ጋር የዘመረበት በጎ ፈቃድ የተደረገበት ልዩ ቀን ነው። ስለዚህም ነው መልአኩ በዚያን ቀን መንጋቸውን ሲጠብቁ ከነበሩት ከእረኞቹ እንዲህ ያላቸው፡- "እነሆ ከሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና" ያላቸው ሉቃ. ፪፡፰ 2፥8

3. <u>ደብረ ታቦር</u>፡- ይህ በዓል የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮቱ የተገለጸበት የነቢያት አምላክ መሆኑ የታወቀበት የሕያዋንና የሙታን (አምላክ) መሆኑ የታወቀበት ቀን ነው። ጌታችንን ብዙዎች ማን እንደሆነ ለማወቅ አእምሮአቸው ደንዝዞ ነበርና። አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን ለመረዳት ተስኗቸው ነበር። በማቴዎስ ፲፮፡፲፫ (16፥13) ላይ ተጽፎ እንደምናገኘው በፊልጶስ ቂሳርያ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ብሎ ጠይቋቸው ነበር። "መኑ ይብልዎ ሰብእ ለወልደ እጓለ እመሕያው" ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ብሎ ደቀ መዛሙርቱም ሲመልሱ አንዳንዶች ኤልያስ ሌሎች ደግሞ ዮሐንስ መጥምቁ ግማሾቹ ኤርምያስ ሙሴ አንዳንዶቹ ከቀደሙት ነቢያት አንዱ መጥቷል ይላሉ ብለው መለሱለት። ቅዱስ ጴጥሮስ ግን ትክክለኛ መልስ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ተናገረለ። እንዲህ ብሎ "አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው" አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ።

ይህ በሆነ በሳምንቱ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ሦስቱን ጴጥሮስ ዮሐንስ ወንድሙ ያዕቆብን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ወጣ። ይህም ተራራ ደብረ ታቦር ነው። ደብረ ታቦር ማለት የታቦር ተራራ ማለት ነው። በዓሉም የተሰየመው በዚሁ ስም ነው። በተራራውም ላይ እንዲህ ሆነ የጌታችን ልብሱ ተለወጠ አብረቀረቀ ሁለት ሰዎች በደመና በሰማይ መጡ እነዚህም ሙሴና ኤልያስ ናቸው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት በመስቀል ተሰቅሎም ስለማዳኑ መስክሩ ተናገሩ። ይህን የምናስብበት ቀን የደብረ ታቦር በዓል ተብሎ ይታወቃል። ቀኑም ነሐሴ 13 ቀን ነው። ይህ በዓል ሁልጊዜ በፍልሰታ ጾም ላይ ስለሚውል በተለምዶ ቡሄ እያሉ ይጠሩታል።

4. <u>ጥምቀት</u>፡- የጥምቀት በዓል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ የተጠመቀበትን የምናስብበት በዓል ነው። እግዚአብሔር አምላክ አዳምን የ30 ዓመት ጐልማሳ አድርጎ ፈጠረው። አዳምም የፈጣሪውን ትእዛዝ በማፍረስ በምክረ ዲያብሎስ ተታሎ ልጅነቱን አስወሰደ። ዲያብሎስም አዳምና ሔዋን የእርሱ ባርያ እንደሆኑ አድርጎ በእብነ ሩካም (እንደ በረድ ድንጋይ ዐይነት ነው) ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ ቀብሮ ሌላውን በሲኦል አስቀምጦት ነበር። ስለዚህ የሁላችን አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የዕዳ ጽሕፈት ደምስሶ የልጅነትን ሥልጣን ከአዳም ይመለስለት ዘንድ በ30 ዓመቱ ተጠመቀ። ይህን በዓል ቤተክርስቲያን በየዓመቱ ጥር 11 ቀን በታላቅ ምስጋና ታከብረዋለች።

5. <u>ሆሳዕና</u>፡- ይህ በዓል የሚታሰበው የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም የገባበት ቀን ነው።

> "ከጽዮን ልጅ፡-እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሏት" ዘካ. ፱፡፱ (9፥9) ማቴ. ፳፩፡፬ (21፥4)

ብሎ ነቢዩ ዘካርያስ ትንቢት እንደተናገረ። ጌታችን ከቀደመዛሙርቱ ሁለቱን ልኮ የታሰረች አህያ ከነውርጫዋ ፈትታችሁ አምጡልኝ አለ። እነሱም ባመጡለት ጊዜ ተቀመጠባቸው። ሕዝቡም ልብሳቸውን እነጠፉ እንዲያን ካንተ ከተቀመጥከባት አህያ ክብር ይገባል ሲሉ ከዛፍ ጫፍ ጫፉን እየቆረጡ በመንገድ ላይ አነጠፉ። በርካታ ሕዝብ ተሰብስቦ ከጌታችን ፊትና ኋላ ሁሉም ይዘምር ነበር። ሲዘምሩም እንዲህ ይሉ ነበር። "ሆሣዕና ከዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ሆሣዕና በአርያም" ማቴ. ፳፩፡፱ (21፥9) ሆሣዕና የቃሉ ትርጉም መድኃኒት ማለት ሲሆን አሁን አድን የሚለውን ትርጉምም ያካትታል።

በዚህ ቀን አፍ እንኳን ያልፈቱ ሕፃናት በተአምራት ይህን ዝማሬ ዘምረዋል። ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጸሐፎች ተበሳጭተዋል። ተቆጥተዋል የሚዘምሩት ሕፃናትም ዝም እንዲሉ ለማድረግ ሞክረዋል። ጌታ ግን እንዲህ ተብሎ ትንቢት ተነግሮአል አላቸው።

"ከሕፃናትና ከሚጠቡት ልጆች አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ" መዝ. ፰፥፪ (8፥2) ማቴ. ፳፩፥፭ (21፥5)

በዚህ ታላቅ ቀን የቢታንያ ድንጋዮች ሳይቀሩ በሰው ቃል ተናግረው እንደዘመሩ በቤተክርስቲያናችን ይነገራል። በዚህ ዕለት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መቅደስ ገብቶ ድውያንን ዕውሮችንና አንካሶችን ፈወሰ። ቤተመቅደሱንም ለማርከስ ክብር ባለመስጠት ሥጋዊ ቤት ያደረጉትን ገሥጾ ለቤተመቅደሱ ክብር እንዲህ ብሏል።

"ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት" ማቴ. ፳፩፥፲፫ (21፥13)። ስለዚህም ቀድሞ በነቢያት ትንቢት ተናግሯል። ኢሳ. ፶፮፥፯ (56፥7) ኤር. ፯፥፲፩ (7፥11)

በዚህ ቀን በቤተክርስቲያናችን ከጌታችን ዐቢያን በዓላት አንዱ ይህ ስለሆነ ትንሣኤ (ፋሲካ) ከሚውልበት ቀድሞ ያለው እሑድ በታላቅ ሥነ ሥርዓት በየዓመቱ ይከበራል።

6. <u>ስቅለት</u>፡ - እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት ያድነው ዘንድ ወዷልና በቀራንዮ ተራራ በዕፀ መስቀል ላይ እጆቹን ለሕማም ዘርግቶ የተሰቀለበት የሰው ልጅ ሁሉ የዳነበት የተመረጠ ዕለት ስቅለት ተብሎ በቤተክርስቲያናችን በየዓመቱ ከትንሣኤ (እሁድ) በፊት ባለው ዐርብ ቀን በስግደት በጸሎት በልመና ይከበራል።

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ የፈጠረው በስድስተኛው ቀን በዕለተ ዓርብ ነበር።

"እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደ

ምሳሌያችን እንፍጠር ... እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን" ዘፍ. ፩፥፳፮-፴፩ 1፥26-31 በእግዚአብሔር ተባርኮ የተፈጠረ ሰው ከሰባት ዓመት የገነት ቆይታ በኋላ በሰይጣን ተታሎ እግዚአብሔርን የመሰለ ጌታ ገነትን የመሰለ ቦታ አጣ። ከገነትም ተባረረ ተሰደደ። መሐሪ ይቅር ባይ የሆነ አምላክም እንደገና ወደክብሩና ቦታው እንደሚመልሰው ቃል ኪዳን ገባለት። ቃል ኪዳኑንም ከአመቤታችን ተወልዶ በ30 ዘመኑ ተጠምቆ በዕፀ መስቀል በቀራንዮ ተሰቅሎ እንደሚያድነው ነበር። ይህ የሰው ልጆች የመዳን ነገር ተገልጦለት ነቢዩ ኢሳይያስ ይህን ትንቢት ቀድሞ ተናግሯል።

"ስለ በደላችን ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን" ኢሳ. ፶፫፥፭ (53፥5)

ነቢዩ እንደተናገረ አረኛ እንደሌላቸው በጎች ተቅበዝብዘን የነበርን የሰው ልጆችን ያድነን ዘንድ አምላካችን ስለ ሁላችን መተላለፍ በቀራንዮ ስለእኛ ተሰቀለ። የሾኽ አክሊል ደፉበት እጆቹንና እግሮቹን ቸነከሩት በሁለት ወንበዴዎች መካከል ያለአንዳች በደል ሰቀሉት ይህ ሁሉ የሆነው እኛ ሕይወት እናገኝ ዘንድ ነው።

7. <u>ትንሣኤ</u>፦ የትንሣኤ በዓል በየዓመቱ የሚከበር ሲሆን ምክንያቱም እንዲህ ነው። አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲፈጥረን ከሕይወት እንጂ ከሞት አልነበረም። አዳምና ሔዋን ግን በምክረ ሰይጣን ተታለው በራሳቸው ሞትን አመጡ ይህም ሞት በአንዱ በአዳም ምክንያት ለልጅ ልጆች ሁሉ ዕዳ ሆነ። በዚህም ምክንያት ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምሳል። አዳም አትብላ የተባለውን ትእዛዝ በማፍረስ ሞት የሚያመጣውን ዛፍ በልቷልና። ዘፍ. ፪፥፯ (2፥7) "ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ"

ዘፍ. ፫፥፲፱ (3፥19) "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ"

በዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፎች እንደምናነበው አባታችን አዳም የአምላኩን ትእዛዝ በማፍረሱ ከእግዚአብሐር ተለየ ወደቀ የብርሃን ልብሱ ተገፈፈ ልጅነቱን ተነጠቀ ፈሪ ደካማ ሆነ ከመልካም ሰፍራ ከገነትም ተባረረ ገነትም በምትገለባበጥ የኪሩቤል ሰይፍ ትጠበቅ ጀመር ተዘጋችም። ዘፍ. ፫፥፳፫ (3፥ 23)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሐር ግን ምንም እንኳን አዳም ቢበድለው ዝም ብሎ አልተወውም ከልጅ ልጅ ተወልዶ እንደሚያድነው ቃል ስለገባለት ከድንግል ማርያም ተወልዶ በተዋሐደው ሥጋ ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ሞትን በሞት ሽሮ ሕይወት እንደሚሰጠው በነቢያት ሁሉ የተነገረ ነበርና የተቆጠረው ሱባኤ ሞላ የተነገረው ትንቢትም ተፈጸመ። ቅዱስ ዳዊትም ስለ ጌታ ትንሣኤ ተንብዮ እንዲህ አለ።

> "ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እምንዋም ወከመ ኃያል ወኅዳገ ወይን ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ" መዝ. ፸፯፥፷፭ (77-65)

ወንጌልም ተጽፎ እንደምናነበው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁድ እንደሚገሉት በሦስተኛውም ቀን እንደሚነሣ ሥጋውን ቤተመቅደስ ብሎ ከሚሰሙት ነግሮአቸው ነበር። አልገባቸውም እንጂ አይሁድ ተነግሮአቸዋል። እነሱ የመሰላቸው ስለሕንፃው ነበር። ዮሐ. ፪፥፲፱ (2፥19) ኢየሱስም መልሶ ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም እነሣዋለሁ አላቸው። ስለዚህ አይሁድ ይህ ቤተመቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሰራ ነበር። አንተስ በሦስት ቀን ታነሳዋለህን አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር።

ከዚህ የወንጌል ቃል እንደምንረዳው የሁላችን አዳኝ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በሞቱ ሽሮ አዳምንና ልጆቹን ሊያድን ወድዷልና በሠስተኛው ቀን በዕለተ እሑድ መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በፍጹም ድንግልና እንደተወለደ ሁሉ ልክ እንዲሁ ሙስና መቃብር (በስብሶ ፈርሶ መቅረትን) አስወግዶ በታላቅ ኃይልና ግርማ ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ ይህም በቤተክርስቲያናችን የትንሣኤ

በዓል በየዓመቱ በዓቢይ ጾም መጨረሻ ይከበራል።

በዚህ በበዓለ ትንሣኤ ዕለት ክርስቲያኖች በቤተመቅደስ ቅዳሜ ማታውን ተሰብስበው እየዘመሩ እያመሰገኑ ያድራሉ። ከኪቱንም ሁሉ ከምስጋና ይቆማሉ። "ምድር በክርስቶስ ደም ነጽታለችና ፋሲካውንም ታደርጋለች ከእኛ ትንሣኤህን ከምናምን ወገኖችህ ከጨለማ የሚያወጣ ብርሃንህን ላክልን" እየተባለ እየተዘመረ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበትን ልዩ ቀን በልዩ ማኅሌት ምስጋና ያስባሉ።

## ከትንሣኤ በኋላ ያለው ሳምንት ስያሜ

ሰኞ፡- ከትንሣኤው ቀጥሎ ያለው ዕለተ ሰኞ "ማዕዶት" ይባላል። ይህም "ፀዓተ ነፍሳት እምሲኦል" የነፍሳት ከሲኦል መውጣትና ወደ ገነት መሻገር የሚታሰብበት ነው።

ማክሰኞ፡- ይህ ዕለት ቶማስ ተብሏል። በመጀመሪያ ትንሣኤውን ተጠራጥሮ በኋላ ግን ዳሰሶ አብሶ "ጌታዬና አምላኬ" ብሎ በመሰከረው በሐዋርያው ቶማስ ተሰይሟል።

ረቡዕ፡- አልዓዛር ተብሏል - ከትንሣኤው ቀጥሎ አራተኛ ቀን ነው። ከሞተ አራት ቀን ሆኖት የነበረውን አልዓዛርን ከሞት እንሥቶታልና በሱ ተሰይሟል።

ሐሙስ፡- አዳም ሐሙስ በሚል ይታሰባል። "በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ከዕለት . . ." ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ አድንሃለሁ ብሎ ነገረው ትንቢት ተፈጽሟልና አምስተኛው ዕለት በዚህ ተሰይሟል፡፤

ዓርብ፡- ቤተክርስቲያን ተብሏል። ቤተክርስቲያን ምእመናንን የሰው ልጆችን ሁሉ ዓርብ ፈጥሮ ዓርብ አድኖአቸዋልና። በዚህ ተሰየመ።

ቅዳሜ፡- ቅዱሳት አንስት ተብሏል- እንደሥርዓቱ ቅዳሜን አርፈው በእሑድ ገስግሰው ትንሣኤውን ባዩ በተቀደሱት ሴቶች ተሰይሟል፡፤

**እሑድ**፡- ዳግም ትንሣኤ ይባላል። ይህም ጌታ ከሞት የተነሣበት ሳምንቱ ሲሆን በዚህ ዕለት ልክ እንደትንሣኤው ቀን በተዘጋ ቤት እያሉ እንደገና ለቶማስና ለሐዋርያቱ የተገለጠበት ዕለት ነው።

8. <u>ዕርገት</u>፡- የሁላችን ቤዛ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከሞት ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ለሌሎች እየተገለጠ እስከሚያርግ ድረስ በልዩ ልዩ መንገድና ቦታ ለሁሉ ይገለጽላቸው ነበር።

ይህም እስከሚያርግበት ቀን ድረስ ሆነ። ጌታችን አምላካችን ከሞት ከተነሣ በአርባኛው ቀን ላይ እንዳረገ በመጽሐፍ ተጽፏል። ይህም ዐቢይ በዓል በቤተክርስቲያናችን በታላቅ ድምቀት ከሞት በተነሣ በአርባኛው ቀን ማለትም ትንሣኤን ባከበርን በአርባኛው ቀን ይከበራል።

> "አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው።" ዮሐ.ሥራ ፩፡፫ (1፥3) በዚህ የመጽሐፍ ቃል እንደምንመለከተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ እንደተገለጸላቸውና እንዳስተማራቸው ተጽፏል። ያስተማራቸው የነገራቸው ምን ነበር? ይህ በእኛ ቤተክርስቲያን ብቻ ተጠብቆ ያለ እውነት ነው። ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉም ጨምሮ እንደገለጸው "በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው ይላል።" ሉቃ. ፳፬፡፵፬ (21፥44)

ጌታ በአርባው ቀናት ያስተማራቸው ኪዳን ተብሎ ይታወቃል። ይህም ኪዳን ሰባት ክፍል ያለው ነው። ሰባቱ ኪዳናት ተብሎ ይነገራል።

እንዲህ ባለ ሁኔታ አርባውን ቀናትእየተገለጸ ካስተማራቸውና ትንሣኤው እውን እንደሆነ ካወቁ ከተረዱ በኋላ በመለከት ድምፅ በእልልታ በመላእክት ዝማሬ ወደ ቀደመ ክብሩ ተመልሶ ዐረገ። ቅዱስ ዳዊት ስለጌታችን

ማረግ አስቀድሞ በትንቢት እንዲህ ተናግሯል። "ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ፡ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን፡ ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ"

> "አምላክ በእልልታ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ" መዝ. ፵፮፡፭ (46፥5)

ልክ እንዲህ እንደተናገረ አምላካችንና ንጉሣችን እግዚአብሔር ከሞት ከተነሣ በአርባኛው ቀን ደቀመዛሙርቱ እያዩት በመላእክት ዝማሬ ወደ ሰማይ ዐረገ ወደ ቀደመ ክብሩ ተመለሰ። "እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሠውራ ተቀበለችው።" ሐዋ. ፩፡፱ (1፥9 ) እርሱም ሲያርግ እጆቹን አንሥቶ ባረካቸው።

> "እስከ ቢታንያም አወጣቸው እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው። ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ። እነርሱም ሰገዱለት በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌምም ተመለሱ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ።" ሉቃ. ፳፬፡፶-፶፫ (24፡ 50-53)

ይህ ድንቅ ነገር ነው ቤተክርስቲያናችንም በታላቅ ክብር በየአመቱ ከትንሣኤ በኋላ በአርባኛው ቀን የምታከብረው። ልዩ በዓል ነው።

"ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም።" ዮሐ. ፫፡፲፫ (3፥13) እኛን ከማዳን ከሰማይ የወረደው ከድንግል የተወለደው ሞቶ ተቀብሮ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው በአርባኛው ቀን ወደ ሰማይ የወጣው እርሱ የሁላችን አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስሙ ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁንና እኛንም እርሱ ወዳለበት ሊወስደን ዳግም ይመጣል።

> "ይህ ከእናንተ ወደሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው" ሥራ ፩፡፲፩ (1፡11)

9. <u>ጰራቅሊጦስ</u>፡- ይህ በዓል በቤተክርስቲያናችን የሚከበረው ጌታችን ከሞት በተነሣ በሃምሳኛው ባረገ ደግሞ በአሥረኛው ቀን ነው። በዓሉም መንፈስ ቅዱስ ከጌታ ቤተሰቦች የወረደበት ዕለት ነው።

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሎ አዟቸው ነበር።

> "ወአንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም" ሉቃ. ፳፬፡፵፬ (24፥44) እናንተስ ከሰማይ የሚወርድ ኃይል መንፈስ ቅዱስን እስከምታገኙ ድረስ ከኢየሩሳሌም ከተማ አትውጡ በዚህ ቆዩ ብሎ አዘዛቸው። በመጀመሪያ ኃይል ካላገኙ አሕዛብ ለይፍ ቢያላዩአቸው አሳት ቢያነዱባቸው ከአውሬ ቢጥሉአቸው የተቤዣቸውን ጌታ ይክዱሉና። ፍሩሃን የነበሩ ጥቡዓን ይሆኑ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እስከታገኙ በሌሎች አገሮች ከለብከተ ወንጌል እንድትፋጠኑ ብሎ የተሰፋውን ቃል ገብቶላቸው አረገ።

ጌታችን ባረገ በአሥረኛው ቀን እንደተሰፋው ቃል መንፈስ ቅዱስን ላካላቸው። በዚያን ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ጌታቸው የነገራቸውን ትእዛዝ አክብረውት በአንድ ልብ አመቤታችንን ድንግል ማርያምን በመካከላቸው አድርገው በጸሎት እየተጉ ነበር።

> "እነዚህ ሁሉ ከሴቶች ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር" ሐዋ. ፩፡፲፪-፲፬ (1፥12-14)

በሌላ በኩል ደግሞ በመካው ዓለም ያሉ አይሁድ ከበዓል በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ነበር። ይህም ቀን በዓለ ኀምሳ ተብሎ ይታወቃል። በዚህ ዕለት ነበር የነቢዩ የኢዩኤል ትንቢት የተፈጸመው። ነቢዩ እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር።

> "ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል መንፈሴንም በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ ወንዶችና ሴቶች

ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ። ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ።" ኢዩ. ፪፥፳፰ (2፥28)።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ተጽፎ እንደምናነበው በዓለ ኀምሳም የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ከጠዋቱ ፫ (3) ሰዓት ድንገት እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ። ይህም ድምፅ በመጣ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩ ከመላው ዓለም የመጡት ሕዝበ አይሁድ ወደ ጽርሐጽዮን ተሰበሰቡ። መንፈስ ቅዱስ ወደወረደበት ስፍራ። በዚህ ጊዜ በሐዋርያቱ ላይ የእሳት ካንቃዎች ወይም ልሳኖች በራሳቸው ላይ ተቀመጡባቸው ታዩአቸውም፡ በሁሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው። መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸላቸውም በተለያዩ ቋንቋዎች ወይም ልሳኖች የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ተናገሩ። ከመላው ዓለም የተሰበሰቡትም ሰዎች እጅግ ተደነቁ። የተደነቁበትም ምክንያት ደቀ መዛሙርት የሚያውቁት የዕብራይስጥ ቋንቋ ብቻ ሲሆን አሁን ግን በዓለም ሁሉ ቋንቋ ሲናገሩ ቢያዩ ተገረሙ የሚሉትንም አጡ። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ እንደተናገረ ይህ ሁሉ የሆነው እግዚብሔር አምላክ ቀድሞ በኢዩኤል ነቢይ ያናገረውን ትንቢት ይፈጽም ዘንድ ነው።

ይህ ነው ጌታችን ከሞት በተነሣ በኀምሳኛው ቀን ባረገ በአሥረኛው ቀን ከተከታዮቹ የሰጠው ኃይል ደቀመዛሙርቱም ኃይል የሚሆናቸው ሀብትን ዕውቀትን ገንዘብ አደረጉ። ይህ የሆነበት ማለትም ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ከደቀመዛሙርት የወረደበትን ቀን በየዓመቱ ቤተክርስቲያናችን ታከብረዋለች።

በዚህ ታላቅ ቀን አምላካችን እስከ 72 ቋንቋ ከደቀመዛሙርቱ ገልጸላቸዋል። በዘፍጥረት ፲፩፥፩-፱ (11፥1-9) እንደተገለጸው ዓለሙ ሁሉ በአንድ ቋንቋ ነበረ። በኃጢአቱ ምክንያት ተለያየ። በዚህን ጊዜ 72 ቋንቋ ተፈጥሮ

ነበር። ይህም በነገደ ካም፣ ሴምና ያፌት ከሦስት ተከፍሎ ነበር።

በነገደ ካም 32 ቋንቋ

በነገደ ሴም 15 ቋንቋ

በነገደ ያፌት 25 ቋንቋ

በባቢሎን የተከያየውን በአምነት አንድ ያደርገው ዘንድ እምካከችን በዕለተ ጰራቅሊጦስ ቋንቋን ገለጸላቸው። ዓለሙ ሁሉ ይድን ዘንድ በተቀደሰችው በአንዲት አምነት ይጸና ዘንድ።

"ዐረገ ውስተ አርያም ፄዊወከ ፄዋ ወወሀብከ ጸጋከ ለእጓለ አመሕያው"

"ወደ ላይ ዓረግሀ ምርኮን ማረክሀ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠሀ" መዝ፡ ፷፯፡፲፰ (67፡18)

## ዘጠኙ የጌታችን ንኡሳን በዓላት

**መስቀል**፡- ይሀ በዓል የሚከበረው መስከረም አሥራ ሰባት ቀን ነው። መጋቢት አሥር (10) ቀን ደግሞ ተቀብሮ ከነበረበት የተገኘበት ዕለት ስለሆነ ይከበራል። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ተአምራት አየሠራ ቢያስጨንቃቸው አይሁድ በምቀኝነት ተነሳስተው ቀበሩት ወደ ሦስተ መቶ (300) ዘመናት የሚጠጋ ያሀል በሁለት ተራራ መካከል ቀብረው ቆሻሻ ሲያስጥሉበት ኖሩ። በኋላም ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ቅድስት እሌኒ መስቀሉን ከሚገኝት ካሀናት ሱባኤ ገብተው ደመራ አስደምራ ዕጣን቎ ቢጤስ የዕጣኑ ጢስ መስቀሉ ያለበትን ስፍራ ስለጠቆማት ቁፍሮ አስጀመረች መጋቢት 10 ቀን ተገኘ። ቅዳሴ ቤቱም

መስከረም 17 ቀን ይውላል። ይህ በዓል በየዓመቱ በቤተክርስቲያናችን ይከበራል።

"ብዙዎች ከክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ። መጨረሻቸው ጥፋት ነው። " ፊል. ፫፡፲፰-፲፱ (3፥18-19)

<u>ስብከት</u>፡- ይህ በዓል በነቢያት ማለትም በገና ጾም ውስጥ የሚከበር ሲሆን ነቢያት ጌታ ይወለዳል ብለው እንደተነበዩ እና እንደሰበኩ ተወልዶም እንዲያድናቸው እጅህን ከአርያም ላክልን እያሉ የጸለዩበት ነው። የጌታችን መወለድ፡ የሰው ልጆች መዳን በብዙና በተለያዩ መንገዶች ቀድሞ ተሰብኮ ነበር። ከዚህም ነው ይህንን ሲያስረግጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ላይ ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ከአባቶቻችን ከነቢያት ተናገረ ብሎ የሰበከው።

<u>ብርሃን</u>፡- ይህም በዓል በነቢያት ጾም ወይም በገና ጾም የሚከበር ሲሆን ነቢያት የጌታን መወለድ እያሰቡ ከሲኦል መውጣታቸውን እየናፈቁ "ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ እማንቱ ይምርሐኒ ወይሰዳኒ ደብረ መቅደስከ ወውስተ አብያቲከ እግዚኦ" ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክልን ማለት ግለጥልን ተወልደህ አድነን ከሲኦልም አውጥተህ ወደ ገነት መልሰን እያሉ እየጸለዩ ያሰቡትን እኛም ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እንመለስ ዘንድ ከጨለማ ሲኦል ወጥተን የክብሩ ወራሽ የሰሙ ቀዳሽ እንሆን ዘንድ እናከብረዋለን። መዝ፡ ፵፪፡፫ (42፡3) ብርሃን ጌታችን ነው። እነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም" እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ዮሐ. ፰፡ ፲፪ (8፥12) እንዲል።

<u>ኖላዊ</u>፡- ይህም በዓል በገና ጾም የሚታሰብ (የሚከበር) ሲሆን በኪሩቤልና በሱራፌል ዙፋን ነግሦ የሚኖረው እግዚአብሔር ከሕዝቡ መልካም እረኛ ይሆን ዘንድ

መገለጡን የሚያሳይ ነው። ኖላዊ ማለት በግእዝ ሲሆን እረኛ ማለት ነው። እረኛችንም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። "አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር ወኖላዊሰ ኄር ይሜጡ ነፍሶ በእንተ አባግዒሁ" "መልካም (ቸር) እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።" ዮሐ፡ ፲፡፲፩ (10፡11)

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ልበ አምላክ ዳዊት ነቢዩ አሞፅ ሌሎች ሁሉ መልካም እረኛ ነበሩ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚሁ የወንጌል ክፍል እንደተጻፈ "በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል" ቁጥር ፫ (3) እንዳለ ይህ የሚያሳየው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆች ሁሉ ፈጣሪ አምላክ መሆኑን ነው። ሌላው መልካም እረኛነቱ ከሌሎቹ የሚለየው ነፍሱን ለበጎቹ የሚሰጥበት መንገድ ነው። ይህም እረኛ በጎቹን ከእውሬ ቢከላከል ቢያበላቸው ቢያጠጣቸው መጨረሻ አርዶ አወራርዶ ይመገባቸዋል። አምላካችን መልካሙ እረኛ "ናላዊ ኄር" ክርስቶስ ግን ሥጋውንና ደሙን እንመገበው ዘንድ ለእኛ ለበጎቹ በቀራንዮ አደባባይ ሰጠን። መልካሙ እረኛ ለበጎቹ ብሎ ሰውነቱን አሳርዶ ይሰጣል።

<u>ጌና (ገና)</u>፡- ይህ በዓል የሚከበረው በአራት ዓመት አንደ ታኅሣሥ 28 ቀን ነው። "በዛቲ ዕለት ኮነ በዓለ ጌና ዘውእቱ በዓለ ልደት" "በዚች ዕለት የጌና በዓል ሆነ፡ ይኸውም የልደት በዓል ነው" ቤተክርስቲያናችን የጌታችን ልደት ታኅሣሥ 28 እና 29 ብቻ ሳይሆን በየዕለቱ የምትከብረው ነው።

<u>ግዝረት</u>፡- ይህ በዓል በየዓመቱ ጥር 6 ቀን ይከበራል። በወንጌል ተጽፎ እንደምናነበው ቤተክርስቲያናችንም እንደምታስተምረው "ሊገርዙት ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ በማኅፀን ሳይረገዝ በመልአኩ እንደ ተባለ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ" ሉቃ. ፪፡፳፩ (2፥21)

ይህን በዓል በምናከብርበት ጊዜ የምናስበው ዋናው ነገር

ጌታችንን ሊገርዙት በወሰዱት ጊዜ ሊገርዘው የቀረበው በእጁ የያዘው ምላጭ (ቢላ ) እንደ ሰም ቀልጦበታል። የመድኃኒታችንም ደም የሚፈሰው በዕለተ ዐርብ ብቻ ነውና በተአምራት ተገዝሯል።

<u>ስምዖን ጌታን ያየበት</u>፡- በዓለ ስምዖን የሚከበረው የካቲት 8 ቀን ነው። ይህ ስምዖን የተባለው አረጋዊ ሰው በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 2 ከቁጥር 25 ጀምሮ ተጽፎ እንደምንመለከተው የእስራኤል መጽናናት ማለትም የጌታን መወለድ የእስራኤልን መዳን ይጠባበቅ ነበር። እስኪ እነዚህን ጥቅሶች እንመልከት።

ሀ/ "በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር"

ለ/ "ጌታ ሆይ አሁን እንደቃልህ ባሪያህን ታሰናብታለህ" ሉቃ. ፪፥፳፯-፳፱ (2፥27-29)

እነዚህን ሁለቱን ንግግሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት እንደተነገሩ አይዘረዝርም ስምዖን ጌታ እስኪሚወለድ ሞትን እንደማያይ የተነገረው አሁን እንደቃልህ ባሪያህን አሰናብተው ያለበት ምክንያት በቤተክርስቲያናችን እንዲህ ተቀምጧል። ከዚህች እምነት ውጪ ያሉ ከዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት አይችሉም። በወንጌል እንድምታችን ላይ ግን ይህ ተገልጿል።

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ በፊት በታላቁ ንጉሠ ነገሥት እስክንድር ዘመን በጥሊሞስ የሚባል ንጉሥ ነበር። በዚህም ዘመን የዓለም ቋንቋ በአብዛኛው ግሪክ ነው። በዚህ ጊዜ ነበር በዕብራይስጥ ቋንቋ ተጽፈው የነበሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወደ ግሪክ እንዲተረጐሙ ንጉሡ ትእዛዝ የሰጠው። ይህን ትርጉም ሥራ ሊያደርጉ የሚችሉ ሊቃውንት ተመረጡ እነዚህም ሰባው ሊቃናት ተብለው ይጠራሉ። ሙሉ ቁጥራቸው ሰባ ሁለት ነበር። እነዚህም ሰባው ሊቃናት ድርሻ ድርሻቸውን ሲተረጉሙ ስምዖን የኢሳይያስን ትንቢት ይተረጉም ነበር። እየተረጎመም እንዳለ ኢሳ. በምዕራፍ 7 ቁጥር 14 ላይ ካለው ይደርሳል። ይህም

ትንቢት እንዲህ ይል ነበር። "ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች።" ስምዖን በመንፈስ ቅዱስ በኢሳይያስ አድሮ የተነገረውን ይህን ትንቢት አንዳለ ለመጻፍ ፈራ። እንደኛ ድንግል በድንግልና ፀንሳ ትወልዳለች ብዬ ብጽፍ ይህ የአሕዛብ ንጉሥ ከፍ ብሎ እንገቴን ዝቅ ብሎ ባቴን ቢቆርጠኝስ ብሎ አስቦ በመፍራት "ድንግል የሚለውን ቃል ለውጦ ሴት ብሎ ተካው። የእግዚአብሔር መልአክም እየመጣ "ሴት ትፀንሳለች" የሚለውን እያጠፋ "ድንግል ትፀንሳለች" እያለ ይተካዋል። ስምዖንም እንደገና አየፋቀ ቢጽፍ በሦስተኛው የእግዚአብሔር መልአክ እጁን አፈፍ አድርጎ ይዞ "ስምዖን ሆይ ድንግል በድንግልና ፀንሳ እስክትወልድ ድረስ ይህን ሳታይ ሞትን አትሞትም" አለው። ስለዚህም ነው በወንጌሉ "ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር" ያለው። ስምዖንም ሲጸልይ "ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ።" ያለው ከዚህ የተነሣ ነው።

ይህ ስምዖን እንደተናገረው ቃል ጌታ በተወለደ በ40 ቀኑ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተመቅደስ በወጣች ጊዜ ሕፃኑን ከእጇ ተቀብሎ አቀፈው ጌታ ሆይ ብሎም ጠራው። ሕፃኑንም እናቱንም ባረካቸው ይካል አመስገናቸው ሲል። በዚህን ጊዜ ይህ ስምዖን ልክ እንደብላቴና ሰውነቱ ከእርጅና ታደሰ ትንቢትም እንዲህ ብሎ ስለጌታችንና እመቤታችን ተናገረ።

> "እነሆ የብዙዎች ልብ ሐሳብ ይገለጥ ዘንድ ይህ በእስራኤል ካሉት ከብዙዎቹ ከመውደቃቸውና ከመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት።"
> ሉቃ. ፪፥፴፭ (2፥35)

ከላይ ከተመለከትነው ታሪክ የተነሣ ነው ይህ በዓለ ስምዖን የተባለው ከጌታችን ንኡሳን በዓላት አንዱ ነው። ዋናው በዓሉን የምናስበውና የምናከብረው ጌታችን ወደ ቤተመቅደስ የገባበት ስለሆነ ነው። ይህ ስምዖን የተባለው አረጋዊ ቅዱስ ሰውና የፋኑኤል ልጅ ነቢይቱ ሐና ጌታን ያዩበት ዕለት ነው።

9. <u>ደብረ ዘይት</u>፡- የደብረ ዘይት በዓል የሚከበረው በዐቢይ ጾም አኩኤታ ላይ ነው። በዚህ ዕለት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት ለፍርድ መገለጥ ይታሰባል። በዓሉም ደብረ ዘይት የተባለበት ምክንያት የጌታ ደቀመዛሙርት ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህ የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው ብለው የጠየቁበት ቦታ የደብረ ዘይት ተራራ ስለሆነ ነው። ማቴ. ፳፬፡፫ (24፥3)

በዚህን ጊዜ ጌታችን ለጠየቁት መልስ ሲሰጥ እንዲህ ብሎ ጀመረ "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ" ማቴ. ፳፬፡፬ (24፥4) ስለዚህ በመጨረሻው ዘመን ብዙዎች ከሐድያን በክርስትና ወይም በኢየሱስ ስም መጥተው ሰተው እንደሚያስቴ በግልጥ ተናግሯል። እኛም ከዚህ አንጠበቅ ዘንድ ሁሌ ቃሉንና መምጣቴን እናሰባለን።

# አሥራ ሦስቱ (፲፫ቱ) ሕማማተ መስቀል

አስራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል የተባሉት ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከማዳን በዕለተ ዓርብ የተቀበላቸው መከራዎች ናቸው። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ተነበየ፡-

"እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። ኢሳ ፶፫፡፭ (53-5)

ነቢዩ እንደተናገረ ስለእኛ ሕግን መተላለፍ እርሱ ጌታችን መከራችንን ወስዶ በደላችንን ይደመስስ ዘንድ ሕማማትን ተቀበለ እነዚህንም ሕማማት አስራ ሦስት ናቸው ብላ ቤተክርስቲያናችን ታስተምረናለች። በዝርዝርም እንደሚከተሉት ናቸው።

1. <u>ተአስሮ ድኅሪት</u>፡- ተአስሮ ድኅሪት ማለት ወደ ኋላ መታሰር ማለት ነው። በኃጢአት ስንስለት የታሰረውን የሰው ልጅ ይፈታ ዘንድ ጌታችንን ወደ ኋላ አሰረው መከራን አበዙበት ሕማምን አጸኑበት።

"ወዲያውም ማለዳ የካህናት አለቆች ከሽማግሌዎችና ከጻፎች ከሸንጎውም ሁሉ ጋር ከተማከሩ በኋላ ኢየሱስን አሳስረው ወስዱትና ከጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት" ማር ፲፭፡፩ (15፡1)

2. <u>ተቀሥፎ ዘባን /ጎኑን ጀርባውን-መመታትና መወጋት</u>፡- በጌታችን ላይ ያካደረሱበት መከራ አልነበረም ጎኑን ወጉት ጎሰሙት፣ ደበደቡት፣ መቱት።

"በፊቱ ተፉበት ጎሰሙትም" ማቴ ፳፮፡፷፯ (26፡67)

3 <u>ተኰርዖ ርእስ /ራሱን መምታት</u>፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳች በደል ሳይገኝበት ስለእኛ ብዙ መከራን ተቀበለ። አየቀለዱበትም አሰቃዩት ራሱን በመቃ ደበደቡት።

"ራሱንም በመቃ መቱት" ማር ፲፭፡፲፱ (15፡19)

4. <u>ወሪቀ ምራቅ /ምራቅን መትፋት</u>፡- ምራቃቸውን ተፉበት።

ጌታችን ስለእኛ ብዙ ስቃይን ታግሠ ዘበቱበት ምንም አልመለሰም ምራቃቸውንም ተፉበት።

"በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት ጎሰሙትም።" ማቴ ፳፮፡፷፯ (26፡67)

5. <u>አክሊለ ሦክ /የእሾህ አክሊል</u>፡- የእሾህ አክሊል አደረጉበት። በጭንቅላቱ ውስጥ ገብቶ እንዲያሰቃየው ከእሾህ ተጎንጉኖ የተሰራ አክሊል በራሱ ላይ አደረጉ። የእሾህ አክሊሉም የብረት ምስማር ነው።እስከ ውስጥ ወጋው ደሙ ፈሰሰ።

"የእሾህ አክሊልም ጎንጉነው ደፉበት" ማር ፲፭፡፲፰ (15-18)

6. <u>ፀዊረ መስቀል/መስቀል መሸከም</u>፡- እጅግ ከባድ የሆነውን መስቀል አሸከሙት። ድርሳነ ማሕየዊ ዘዓርብ እንደሚናገረው የመስቀሉ ርዝመት ፲፯ አሥራ ሰባት (17) ክንድ ነበር።

"ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ" ዮሐ ፲፱፡፲፯ (19.17)

7. <u>ተጸፍዖ መልታሕት /ጉንጭ መመታት</u>፡- እምካካችን ክርስቶስ በኃጢአተኞችና በከፉዎች እጅ ለሁላችን በጥፊ ተመትቷል። እየደጋገሙ እየመጡ አሰቃይተውታል።

"ኢየሱስንም የያዙት ሰዎች ይዘብቱበትና ይደበድቡት ነበር፤ ሸፍነውም ፊቱን ይመቱት ነበርና፡- በጥፊ የመታህ ማን ነው ? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር። ሉቃ ፳፪፡፷፫-፷፬ (22፡63-64)

8. <u>ስትየ ሐሞት/ ሐሞት መጠጣት</u>፡- የሁላችን በዛ በመስቀል ሆኖ ተጠማሁ ባለ ጊዜ መራራ የሆነ ሐሞትን ነበር የሰጡት። እርሱም አልጠጣውም ተፋው። የዝናቡ ጌታ የውቅያኖስን የባሕራትን ፈጣሪ በሕመሙ አንድ ብርጭቆ ውኃ ከለከሉት።

"ወዲያው ከእነርሱ አንዱ ሮጠ ስፍንግም ይዞ ሆምጣጤ

ሞካበት በመቃም አድርጎ አጠጣው" ማቴ ፳፯፡፵፰ (27፡48)

ይህም የዝሆን ሐሞትና ከርቤ ደረት የሚሰነጥቅ ጉሮሮ የሚያነቃ መርዛማ ነበር።

9. <u>የቀኝ እጅ መቸንከር</u>፡-

10. <u>የግራ እጅ መቸንከር</u>፡-

የታመሙትን በእጆቹ ስለአዳናቸው ፊንታ ለምጻሞችን ስለአነፃ፣ የዕውሮችን ዓይኖች በእጆቹ ዳሶ ስለአበራቸው፣ የሞቱትን ስለ አነሳ እጆቹን ቸነከሩት።

11. <u>የቀኝ እግር መቸንከር</u>፡-

12. <u>የግራ እግር መቸንከር</u>፡-

ተመላልሶ ያስተማረበትን እግሮቹን እነዚያ በባሕር ላይ የተራመዱ፣ የጠፋውን በግ የፈለጉ፤ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ የተመላለሱ ቅዱሳን እግሮቹን አንዱን በአንዱ ላይ አድርገው ቸነከሩት።

> "ዐገቱኒ ከለባት ብዙኃን ወአኀዙኒ ማኅበሮሙ ለእኩያን ቀነውኒ እደውየ ወእገርየ ወኈለቁ ኩሎ አዕፅምትየ"
>
> "ብዙ ውሾች ከብበውኛልና የክፉዎች ጉባኤም ያዘኝ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ"

13 .<u>የደረት መቸንከር</u>፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመስቀሉ ላይ ወጥቶ ከንድ ያህል በተረፈ ችንካር ላይ በጀርባው አሰተኙት።

"ወውእቱ ሐዒን ዘውጽአ እንተ አንግድዓሁ" (ድርሳነ ማሕየዊ ዘዓርብ) ይኸውም ችንካር በደረቱ ዘልቆ ወጣ። ደረቱንም ከመስቀሉ ጋር ባንድ ችንካር በጀርባው አሰኪወጣ ቸነከሩት።

> "ወበቅንዋቲሁ ሰበረ ኲነ ቀኖተ ሞት"
>
> "በመቸንከሩም የሞት ችንካርን አጠፋልን"

ክህናት፡- በፊትቶ ጊዜ ቁጥሩ አሥራ ሦስት የሚሆነው ይህንን አሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀሉን በማሰብ ነው።

# አምስቱ ቅንዋት (ችንካሮች)

ከላይ በአሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል እንደተጻፈው እነዚህም ከተራ ቁጥር 9 ጀምሮ እስከ 13 ድረስ ያሉት አምስቱ ቅንዋት ወይም ችንካሮች ተብለው ይጠራሉ። አምስቱ ቅንዋትም ስማቸው እንዲህ ነው።

1. ሳዶር
2. አላዶር
3. ዳናት
4. አዴራ
5. ሮዳስ

በአምስቱ ቅንዋት የተቸነከረበት ምክንያት ክብር ይግባውና በራእይ የተገለጹትን አምስቱን ኀጣውእ (ኃጢአቶች) ወግቶ ድል መቶልናልና ድል እንመታበት ዘንድ ነው። እነዚህም አምስቱ ኃጣውእ የተባሉት፡- አምስቱ ከለባት (አምስቱ ውሾች) ይባላሉ።

1. አስማተኛነት
2. ሴሰኛነት
3. ነፍስ ገዳይነት
4. ጣዖት አምልኮ
5. ውሸትን መውደድ

እነዚሀ ሲሆኑ መንፈስ ቅዱስ ለቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደገለጸለት ይህንን የሚያደርጉ ሁሉ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር አይገቡም ከዚያ ውጪ ናቸው ይላል። ለሚያምኑ ሁሉ የጌታን ሕማሙን መከራውን ሞቱን እያሰብን በንስሐ ታጥበን ወደ ሕይወት ዛፍ እንደርስ ዘንድ በከተማይቱም በመንግሥተ ሰማይ እንኖር ዘንድ ልጅነትን ሰጥቶናል። ራእይ ፳፪፡፲፬-፲፭ (22፡14-15)

# ሰባቱ (፯ቱ) አጽራሐ መስቀል

ሰባቱ አጽራሐ መስቀል የተባሉት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ በነበረበት ሰዓት የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

1. <u>አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ፡</u>- ትርጉሙም አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው። ሉቃ ፳፫፡፴፬ (23፡34)

2. <u>ኤሎሄ ኤሎሄ ኤልማስ ላማ ሰበቅታኒ፡</u>- ይህም ቃሉ የአረማይክ ሲሆን ትርጉሙም አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ? ማለት ነው። ማቴ ፳፯፡፵፮ (27፡46)

> "ወጊዜ ተሰዓቱ ሰዓት ጸርሐ ኢየሱስ በዓቢይ ቃል እንዘ ይብል ኤሎሄ ኤሎሄ ኤልማስ ላማ ሰበቅታኒ።" በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፡-

ኤሎሄ ኤሎሄ ኤልማስ ላማ ሰብቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም ጩኸት ከራሱ ሳይሆን ከአዳምና ከልጆቹ ካሳ ኢሆን የመጣ ነውና ስለእኛ ነው። እንጂ ራሱ አምላክ ነው። ቀድሞ በትንቢት ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረው።

> "አምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወለምንት ኀደገኒ" "አምላኬ አምላኬ ተመልከተኝ ለምን ተውኸኝ" መዝ ፳፩፡፩ (21፡1) እንዳለ ይህን ቃል ስለእኛ በረድኤቱ ይጎበኘን ዘንድ በወደደ ጊዜ በመስቀሉ ላይ ተናገረ።

3. <u>ነዋ ወልድኪ ነያ እምኪ</u> - ትርጉሙ ልጅሽ ይኸው እናትህ ይችውልህ ማለት ሲሆን በመስቀሉ ሥር የተገኘውን ብቸኛ ሐዋርያ ከእናቱ ከድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ልጅ አድርጎ ሲሰጣት እንዲሁም ለዮሐንስ እስከ ሞት ድረስ የታመነ ሐዋርያ በመሆኑ አመቤታችን የቃል ኪዳን እናት ሆና ተሰጠችው። ይህም ለእሱ ብቻ ሳይሆን እስከ መስቀሉ ለሚተጉ ሁሉ እመቤታችን እናት ሆና ተሰጥታናለች። "ወእምይእቲ ሰዓት ነሥኣ ውእቱ ረድእ ወእእተዋ

ቤቶ" ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት። "ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ የእናቱም እኅት የቀለዮጳም ሚስት ማርያምም መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀመዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን። አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።ዮሐ ፲፱፡ ፳፭ -፳፮ (19፡25-26) የወንጌሉን ቃል ስንመከከት የምናስተውለው ወሳኝ ነገር ይህ ነው።

1ኛ. በመስቀሉ ሥር እመቤታችን ብቻ ሳትሆን ሌሎችም ሴቶች ነበሩ።

2ኛ. እናት አድርጎ ለቅዱስ ዮሐንስ የሰጣት እመቤታችንን ብቻ ነው።

3ኛ. ቅዱስ ዮሐንስ እናት ነበረችው ማቴ ፳፡፳ (20፡20)

4ኛ. እናቱን የሰጠው ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ ነው

5ኛ. ይህንንም ደቀ መዝሙር ለእመቤታችን ልጅሽ ብሎ ሰጥቷታል

6ኛ የእመቤታችን እናትነት እንደ ዮሐንስ ለሁሉም ለሚያምኑ ክርስቲያኖች ነው፡

7ኛ. እኛም ለእመቤታችን እናታችን የምንላት ስለተሰጠችን ነው "ሰው እናታችን ጽዮን ይላል በውስጧም ሰው ተወለደ" መዝ ፹፮፡፭ (86፡5)

አንዳንድ ሰው እመቤታችንን እናቴ ካለማለት ይህን ቃል እያጣመመ ለኢየሩሳሌም የተነገረ ነው ሊል ይችላል። ልብ በሉ አገርን እናቴ ካለ ብሎም አያውቅ እንጂ የአምላክ እናት የሆነች ድንግል ማርያምማ እንዴት እናቴ አትባል ትባላለች ነች።

8ኛ. ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀመዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት። ቤት በተባለ ልባችን እመቤታችን ትግባልን።

4. <u>ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት</u፡- ትርጉም - ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ። ጌታችን ይህን የተናገረው በቀኙ ተሰቅሎ ከነበረው ወንበዴ ነው። ይህም ሰው ጥጦስ ይባላል። አብሮት የነበረው ዳክርስ ይባላል በመንግሥትህ አስበኝ ብሎ ጌታን ቢለምን ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትሆናለህ ተብሎ ከአዳም አንኳን በመቅደም ወደ ገነት ገብቷል። "ኢየሱስም እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው። " ሉቃ ፳፫፡፵፫ (23:43)

ይህ ሰው ወደ ገነት የገባበት ምክንያት አንደኛ- ጌታችን ያለበደሉ የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት ስላወቀና ዋናውና ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እንደሚነሳ ዳግመኛ ከፍርድ የሚመጣ እግዚአብሔር መሆኑን ስላወቀና ስላመነ ነው። ከዚህም ነው "በመንግሥትህ አስበኝ" ብሎ የለመነው ። ጌታም መለሰለት እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።"

5. <u>አባ አመኃፅን ነፍስየ ውስተ እዴከ</u>፡- ይህም አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ አሰጣለሁ ማለት ነው። "ወሰቤሃ ጸርሐ እግዚእ ኢየሱስ በዐቢይ ቃል ወይቤ አባ ውስተ እዴከ አመኃፅን ነፍስየ" ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፡- አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ሉቃ ፳፫፡፵፮ (23:46)

6. <u>ጸማዕኩ</u>፡- ማለት ተጠማሁ። አንዱ በመስቀል ላይ ከተናገራቸው ቃላት ተጠማሁ ነው ይህም ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ነው። አነሱም ሐሞትና ከርቤ የተቀላቀለበት መራራ ጉሮሮ የሚሰነጥቅ የወይን ጠጅ በሰፍነግ አድርገው አቀረቡለት። "ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ ተጠማሁ አለ" ዮሐ ፲፱፡፳፰ (19:28)

7. <u>ተፈጸመ ኩሉ</u>፡- ትርጉም - ሁሉ ተፈጸመ። ጌታችን በመጨረሻ የተናገረው ቃል ተፈጸመ የሚል ነው። ከዚያም ነፍሱን ሰጠ።

> "ወሰሪቦ ብሒእ እግዚእ ኢየሱስ ይቤ ተፈጸመ ኩሉ ወአድነነ ርእሶ ወመጠወ ነፍሶ" ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፡- ሁሉ ተፈጸመ አለ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ

ሰጠ።" ዮሐ ፲፱፡፴ (19፡30) ይህም በመጽሐፍ ስለ እርሱ የተነገረው ሁሉ ተፈጸመ ደረሰ ማለት ሲሆን። አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም እድንኀለሁ ብሎ ለአዳም የገባው ቃል ትንቢተ ነቢያት ተፈጸመ ደረሰ። የሰው ልጆች ሁሉ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነጻ ወጡ። የዲያብሎስ ዘመኑ ተፈጸመ።

# ሰባቱ (7ቱ) ተአምራት በጌታ ስቅለት

ጌታችን እና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የለበሰውን ልብስም ገፈው በሰቀሉት ጊዜ ሰባት ተአምራት ተደረጉ። ሦስት ተአምራት በሰማይ ዐራት ተአምራት ደግሞ በምድር።

<u>ፀሐይ ጨለመች</u>፡- ምክንያቱም የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ልብሱን ገፈውት ነበርና የአምላኬን ዕርቃን አላሳይም ስትል። ዛሬ በስቅለት ሥዕል ላይ የምናየውን ጨርቅ ያደረገው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው። መከራውን አይቶ ስለነበር ሥዕሉን ሲሠራ በራሱ በጌታ ትእዛዝ አድርጎት ነው።

<u>ጨረቃ ደም መሰለች</u>፡-ፀሐይ ስትጨልም ጨረቃም ብርሃኗን ከለከለች።

<u>ከዋክብትም ረገፉ</u>፡- ፈጣሪያቸውን በመስቀል ዐይተው ኀዘናቸውን ገለጡ። ፀሐይም ከዋክብትም እኛ ብርሃን ብንሰጥ ባንተ ነው እንጂ ብለው ብርሃናቸውን ሠወሩ። የሰው ልጅ ግን ድኅነቱን አላወቀም።

<u>ምድር (መሬት) ተንቀጠቀጠች ተናወጠች</u>፡- ኀዘኗን ከፈጣሪዋ በዚህ ገለጠች።

<u>እዕባን (ድንጋዮች) ተፈተቱ (ተሰነጣጠቁ)</u> ፡- ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ዓለቶች ኀዘናቸውን በመሰነጣጠቅ ገልጸዋል። በጥምቀቱ ጊዜና በሆሳዕና ዘምረው በደስታ ዘለው የነበሩት ዛሬ ግን አዘኑ ተፈተቱ።

<u>የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ</u>፡- ይህም በምሥጢር በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው የጥል ግድግዳ በስቅለቱ በሞቱ ፈረሰ ሰውም ከእግዚአብሐር ተገናኘ ሲል ነው።

<u>መቃብራት ተከፈቱ ሙታን ተነሡ</u>፡- እነዚህ ሞተው

የነበሩ የተነሡት ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ገብተው የተሰቀለው የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን የመሰከሩ ቅዱሳን ናቸው። ይህን ከላይ የተዘረዘረው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 27 ቁጥር 54 ተጽፎአል። ይህ ሁሉ የሆነው በስቅለት ዕለት ዐርብ ነበር። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አምላክ ዐርብ የፈጠረውን ሰው ዐርብ አዳነው።

# ሥርዓተ ግዝረት

ከሕገ ልቡናና ሕገ ኦሪት ከመጡ ሥርዓቶች አንዱ ግዝረት (መገረዝ) ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ይህ ሥርዓት ምሳሌነቱ ለጥምቀት ቢሆንም እንኳ እግዚብሔር ለአብርሃም የዘላለም ሥርዓት አድርጎ ስጥቶታልና ምእመናን ይፈጽሙታል። ሊፈጸምም ይገባዋል።

"እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡- አንተ ደግሞ ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ አንተ ከአንተም በኋላ ዘርህ በትውልዳቸው። በእኔና በአንተ መካከል የምትጠብቋት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ።" ዘፍ. ፲፯፥፱ (17፥9)

እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ ለአባታችን ለአብርሃም ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መገረዝ እግዚአብሔርን የማምለክና የቅድስና ምልክት ሆነ። በሙሴ ዘመንም ወደመገናኛው ድንኳን ለመቅረብ የተቀደሰን ሰቃ ለመንካት በፋሲካውም ሕግ መሠረት የተቀደሰውን ምግብ ለመብላት መገረዝ ግድ ነው።

"... ከተገረዘ በኋላ ከእርሱ ይብላ" ዘጸ. ፲፪፥፴፬ (13፥34)

አለመገረዝ ደግሞ የአረማዊነት የኢአማኒነትና የጣዖት አምላኪነት እንዲሁም የነውር ምልክት እንደነበር ከእግዚአብሔር ቃል እንገነዘባለን። በግብፅ ባርነት ነፃ የወጡ እስራኤል በምድረ በዳ ለከሞቱ ወደ ተስፋይቱ ምድር የገቡ ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር በምድረ በዳ የተወለዱ ነበሩ። እግዚአብሔርም ኢያሱን ባዘዘው መሠረት ማርና ወተት የምታፈሰውን ከነዓን ከመውረስ መገረዝ ስለነበረባቸው ሰሙ የግርዛት ኮረብታ የተባለ ስፍራ አባታችን ኢያሱ ሸለፈታሞቹን በምድረ በዳ የተወለዱትን በባልጩት ገረዛቸው። እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው።

"ዛሬ የግብፅን ነውር ከእናንተ ላይ አንከባልያለሁ" ኢያሱ ፭፥፱ (5፥9)

የቤተልሔሙ የዕሴይ ልጅ ቅዱስ ዳዊት የጦር ሰው የነበረውን ፍልስጥኤማዊ ጎልያድን ድል እንደሚያደርገው ከንጉሥ ሳኦል በነገረው ጊዜ የጎልያድን ኢአማኒነት ሲገልጸው፡-

"እኔ ባሪያህ አንበሳና ድብ መታሁ ይህም ያልተገረዘው ፍልስጥኤማዊ የሕያውን አምላክ ጭፍሮች ተገዳድሮአልና ከእነርሱ እንደ አንዱ ይሆናል።" ፩ሳሙ ፲፯፥፴ (17፥30)

## ግርዛት ለማን? መቼ?

ግርዛት የሚፈጸመው ወንዶች ብቻ ሲሆኑ ይህም የሚሆነው ሕፃኑ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ነው።

"የስምንት ቀን ልጅ ይገረዝ" ዘፍ. ፲፯፥፲፪ (17፥12)

በዚህ ቀንም ለሕፃኑ ስም ይሰየምለታል። ጌታችንም ቀድሞ በመልአኩ እንደተተነበየና እንደተነገረ እናቱ ኢየሱስ ብላ የጠራችው በስምንተኛው ቀን ነው። የመጥምቁ ዮሐንስ ስም አወጣጥና ግዝረት በሉቃስ ወንጌል እንደተፃፈ፡- "በስምንተኛው ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት ወደዱ። እናቱ ግን መልሳ አይሆንም ዮሐንስ ይባል እንጂ አለች።" ሉቃ. ፩፥፶፱ (1፥59)

ከላይ እንደተመለከትነው ግርዛት ለአባታችን ለአብርሃም የተሰጠ ለልጅ ልጆቹ ሁሉ የሚሆን ቃል ኪዳን ነው። ከዚህ ውጪ ያልተገረዘ ሰው ሥጋው አልተገረዘምና አይድንም የሚል ትምህርት ቤተክርስቲያን የላትም በመገረዙ ግን በአብርሃም ቃል ኪዳን የሚታቀፍ ይሆናል። ይህ ብቻ ሳይሆን እራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር የሰጠውን ሕግ በመጠበቃችን ረድኤቱ በዝቶ ይሰጠናል። አባታችን አብርሃምም ከተገረዙትም ካልተገረዙትም በእምነት አባት ነው።

"ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም

የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው ለተገረዙትም አባት እንዲሆን ነው። ይኸውም ለተገረዙት ብቻ አይደለም ነገር ግን አባታችን አብርሃም ሳይገረዝ የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው። " ሮሜ. ፬፥፲፩ (4፥11)

ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና በብሉይ ኪዳን እምነት የነበረች ናትና የግርዛት ሥርዓት በዘመነ ሐዲስም ሳይለወጥ ልጅነትን ከምታሰጥ ከጥምቀት ጋር ይፈጸምባታል። ሌሎች አገሮች ግን ከእስራኤል በስተቀር ይህ የእምነት ሥርዓት ስላልነበራቸው ሳይገረዙ አይድኑም የሚል የፈሪሳውያን አስተሳሰብ የላቸውም መገረዛቸው ግን ጥቅም እንዳለው እግዚአብሔር በሰጠው ቃልኪዳን ውስጥ መግባት መመረጥ እንደሆነ ግን ሁሉም ሊያውቀው የተገባ ነገር ነው።

ግርዘት ምሳሌነቱ ለጥምቀት ነው ያልተጠመቀ ግን አይድንም። የሥጋ ሸለፈት ጉዳይ ሳይሆን ዘላለማዊ ቃል ኪዳን የመጠበቅ ሥርዓት ነው።

"ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ማር፡ ፲፮፡ ፲፮ (16፡16)

# መጽሐፍ ቅዱስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሕግ መሠረት እግዚአብሔር በነቢያቱና በቅዱሳኑ ያናገረውና ያጻፈው መጽሐፍ፤ ቅዱስ መጽሐፍ ይባላል። የቅዱሱ የእምላካችን ቃል ስለሆነ ቅዱሳን ሰዎችም በእግዚአብሔር ተልከውና ተነግረው ስለጻፉት ። ይህም መጽሐፍ በሁለት ክፍል ያለ ነው። ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን። ብሉይ ኪዳን ጌታ ከመወለዱ በፊት የተጻፈ፤ ሐዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታችን ከተወለደ በኋላ የተጻፈ ነው።

> "በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" ፪ጴጥ ፩፡፳፩ (1፥21)

ይህም መጽሐፍ ቤተክርስቲያናችን የምትመራበት፣ ምእመናንም እግዚአብሔርን የሚያውቁበት፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚመሩበት፣ ከእግዚአብሔር በጸሎት የሚገናኙበት፣ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ከሰዎች ያለውን ምሕረቱን የሚረዱበት፣ በአጠቃላይ ለእኛ ምክር፣ ትምህርት፣ ተግሳጽ፣ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር አጻፈው።

> "በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአል።" ሮሜ. ፲፭፡፬ (15፥4)

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የተጻፈው ሁሉ ሲል ማስተዋል ያለብን የእግዚአብሔር መንፈስ ቃኝቷቸው በቅዱሳን የተጻፈውን እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ነው። ከሃዲያንና መናፍቃን እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል እንደራሳቸው ፍላጐትና ዓለማዊ ስሜት እያጣመሙ ስለሚያስተምሩና ስለሚጽፉ እንለይ ዘንድ ይገባናል። በተለይ በ2ኛውና 3ኛው ክፍለ ዘመን የጌታችንን ወንጌል ከማሳበል የራሳቸውን ጽፈው የሚያሳስቱ ክፍሎች ነበሩ። እውነተኛውንም የመጽሐፍ ቃል የወንጌሉን ዜና እንደገዛ ስሜታቸው የሚተረጉሙ ነበሩ።

"እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም እርቶዶክስ ተዋሕዶ የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ።" ገላ. ፩፡፯ (1፥7)

ቤተክርስቲያናችን ትክክለኛ የሆኑትን መጻሕፍት ከብሉይና ከሐዲስ አንድ ሳይጎድል ይዛ የምትገኝ ከዓለም ብቸኛ ናት። ምክንያቱም ቤተክርስቲያናችን ሐዋርያት የተጠቀሙበትን ሙሉውን ሰማንያ አንድ (81) መጻሕፍት ለትጠቀም ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንት ከዚያ ያነሰ እንደየደረጃው ይቀበላሉ። እርግጥ ካቶሊኮች ሰማንያ አንዱን አይቀበሉ እንጂ የተወሰኑትን ጨምረው መቀበል ጀምረዋል። በፕሮቴስታንቱ ግን ስልሳ ስድስት መጻሕፍት ብቻ ይቀበላሉ። ወደፊት ግን እንደሚቀበሉ ፍንጮች አሉ፡ በአሁን ሰዓት እየጨመሩ ማተም ጀምረዋል። አንባቢዎች ማስተዋል የሚያስፈልጋችሁ ሌላው ነገር ከኦርቶዶክስ ክርስትና ውጪ ያሉትንስ ሰማንያ አንዱን መጻሕፍት አሟልተው መቀበል ብቻ ሳይሆን የጎደሉትው ከስድሳ ስድስቱም ውስጥ ብዙ ተቆርጦ የወጣ እንዳለ ነው። የጥንት ክርስቲያኖች ግን ዛሬ እኛ የምንቀበለውን ነገር ተቀብለው እግዚአብሔርን ሲያመልኩት ነው የኖሩት። እነዚህም ሰማንያ አንድ መጻሕፍት ሐዋርያት ቆጥረው ለቀሌምንጦስ ከዚያም 318ቱ ቅዱሳን አበው አውነተኛውን ቆጥረው እነሱም ተቀብለው ለክርስቲያኖች መመሪያ ይሆን ዘንድ የእነዚህም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስምና ቁጥር ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

## የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. መጽሐፈ ሄኖክ
2. መጽሐፈ ኢዮብ
3. ኦሪት ዘፍጥረት
4. ኦሪት ዘጸአት
5. ኦሪት ዘሌዋውያን

6. ኦሪት ዘኍልቍ
7. ኦሪት ዘዳግም
8. መጽሐፈ ኩፋሌ
9. መጽሐፈ ኢያሱ
10. መጽሐፈ መሳፍንት
11. መጽሐፈ ሩት
12. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ
13. መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ
14. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
15. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ
16. መጽሐፈ ዕዝራ ቀዳማዊ
17. መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ
18. መጽሐፈ አስቴር
19. መጽሐፈ ዮዲት
20. መጽሐፈ ጦቢት
21. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
22. መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ
23. መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ
24. መዝሙረ ዳዊት
25. መጽሐፈ ምሳሌ
26. መጽሐፈ ተግሣጽ
27. መጽሐጸ ጥበብ
28. መጽሐፈ መክብብ
29. መጽሐፈ መኃልይ
30. ትንቢተ ኢሳይያስ
31. ትንቢተ ኤርምያስ

32. ትንቢተ ሕዝቅኤል
33. ትንቢተ ዳንኤል
34. ትንቢተ ሆሴዕ
35. ትንቢተ አሞጽ
36. ትንቢተ ሚክያስ
37. ትንቢተ ኢዩኤል
38. ትንቢተ አብድዩ
39. ትንቢተ ዮናስ
40. ትንቢተ ናሆም
41. ትንቢተ ዕንባቆም
42. ትንቢተ ሶፎንያስ
43. ትንቢተ ሐጌ
44. ትንቢተ ዘካርያስ
45. ትንቢተ ሚልክያስ
46. መጽሐፈ ሲራክ

አርባ ስድስቱ (፵፮ቱ) የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሚባሉት እነዚህ ናቸው። በሕገ ልቡና ዘመን ከአሥሩ አበው አንዱ በሆነው በሄኖክ የተጻፈው መጽሐፈ ሄኖክና ሊቀ ነቢያት ሙሴ የጻፈው መጽሐፈ ኩፋሌ በሌላው ዓለም አይታወቅም። ኩፋሌ ማለት "ዘተከፍለ እምአሪት" ከኦሪት የተከፈለ ማለት ነው። ዘመናትንም ይከፍላልና ኩፋሌ ተብሎ ተሰይሟል።

ከነዚህ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የመጀመሪያዎቹ ስምንት መጻሕፍት ፰ቱ ብሔረ ኦሪት ተብለው ይጠራሉ። ኦሪት ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቊ፣ ዘዳግም በሙሴ የተጻፈ ሲሆን በመቀጠል ያሉት መጽሐፈ ኢያሱ፣ መሳፍንትና ሩት ደግሞ ሦስቱ ተደምረው በአጠቃላይ ስምንት ይሆናሉ። በዚህ ኩፋሌን ከኦሪቱ ጋር አንድ ያደርገዋል።

ከአሪት ቀድመው በሕገ ልቡና ዘመን የተጻፉ ሁለት መጻሕፍት ናቸው። መጽሐፈ ሄኖክና መጽሐፈ ኢዮብ ናቸው። እነዚህ የመጀመሪያ መጻሕፍት ናቸው። አንደኛ ሄኖክ ሁለተኛ መጽሐፈ ኢዮብ፤ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ ተብሎ ሲጠራ፣ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ ደግሞ መጽሐፈ ነገሥት ሣልስና ራብዕ ተብለው ይጠራሉ። በአቆጣጠሩ ግን ሁለቱን አንድ ሁለቱን አንድ አድርጎ ይቆጥራል ሄኖክና ኩፋሌ ስላሉ። "ቀዳማዊ ወካልዓዊ አሐዱ ሣልሳዊ ወራብዓዊ አሐዱ" ፍትሐ ነገሥት

መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ በቤተክርስቲያን ሕፁፃን ተብለውም ይጠራሉ። አስራ ስድስቱ ነቢያት ደግሞ አራቱ ዓበይት አሥራ ሁለቱ ደቂቀ ነቢያት ተብለው ይጠራሉ። ይሀ ስለ ነቢያት በተጻፈበት ክፍል ተመልከቱ።

መጽሐፈ መቃብያን ደግሞ ሦስት መጻሕፍት ሲሆኑ በቤተክርስቲያናችን አጠራራቸው የመጀመሪያው መቃቢስ ዘሞዓብ፣ ሁለተኛው መቃቢስ ዘብንያም፣ ሦስተኛው መቃቢስ ዘአልዓዛር ይባላል።

## የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. ወንጌል ዘማቴዎስ
2. ወንጌል ዘማርቆስ
3. ወንጌል ዘሉቃስ
4. ወንጌል ዘዮሐንስ
5. ግብረ ሐዋርያት
6. መልእክት ኀበ ሰብአ ሮሜ
7. መልእክት ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ
8. መልእክት ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ካልዕ
9. መልእክት ኀበ ሰብአ ገላትያ

10. መልእክት ኀበ ሰብአ ኤፌሶን
11. መልእክት ኀበ ሰብአ ፊልጵስዩስ
12. መልእክት ኀበ ሰብአ ቆላስይስ
13. መልእክት ኀበ ሰብአ ተሰሎንቄ ቀዳማዊ
14. መልእክት ኀበ ሰብአ ተሰሎንቄ ካልዕ
15. መልእክት ኀበ ሰብአ ጢሞቴዎስ ቀዳማዊ
16. መልእክት ኀበ ሰብአ ጢሞቴዎስ ካልዕ
17. መልእክት ኀበ ሰብአ ቲቶ
18. መልእክት ኀበ ፊልሞና
19. መልእክት ኀበ ሰብአ ዕብራውያን
20. መልእክተ ያዕቆብ
21. መልእክተ ጴጥሮስ ቀዳማዊ
22. መልእክተ ጴጥሮስ ካልዕ
23. መልእክተ ዮሐንስ ቀዳማዊ
24. መልእክተ ዮሐንስ ካልዕ
25. መልእክተ ዮሐንስ ሣልስ
26. መልእክተ ይሁዳ እኁሁ ለያዕቆብ
27. ራእየ ዮሐንስ
28. ትእዛዘ ሲኖዶስ
29. ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ
30. ግጽው ሲኖዶስ
31. አብጥሊስ ሲኖዶስ
32. መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ
33. መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ
34. መጽሐፈ ዲድስቅልያ
35. መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

እንግዲህና በዝርዝር እንደተመለከትነው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አርባ ስድስት (፵፮) ሲሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ ሠላሳ አምስት (፴፭) ይሆናሉ። በአጠቃላይ ድምራቸው ሰማንያ አንድ (፹፩) ይሆናል። እነዚህ ሰማንያ አንዱ መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ። የሰው ልጆች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንገባ ዘንድ በሕይወታችን የምንመራባቸው ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን የተባሉ መጻሕፍት እነዚህ ናቸው። አንዳንዶች ግን የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት በጠቅላላ እንደተሻሩ የሚያስቡም አሉ። እነዚህ ደግሞ ቆርጠው ከጣሉትም የባሱ ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል ግን እንዲህ ይለናል።

"መጽሐፍ ሊሻር አይችልምና" ዮሐ. ፲፥፴፬ (10፥34)

"ሙሴና ነቢያት አሏቸው እነርሱን ይስሙ" ሉቃ. ፲፮፥፳፱ (16፥29)

"በሕግ የተጻፈው ምንድን ነው እንደትስ ታነባለህ? ... ይህን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ" ሉቃ. ፲፥፳፭-፳፰ (10፥25-28)

"ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች እያሳቱና እየሳቱ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ። አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ከበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" ፪ጢሞ ፲፫፥፲፯ (2፥13-17)

ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ይህንን ቃል መሠረት አድርጋ ምእመናንን ታስተምራለች። ከቃሉ የምንመለከተው

ዓቢይ ነገር በቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ልማደ ሃይማኖት ነው።

1. አታላዮች አየሳቱና እያሳቱ እንደሚኖሩ
2. ስለዚህ በተማሩበት እውነተኛ እንዲት ሃይማኖት ጸንቶ መኖር
3. የተማርነው ከቅዱሳን ነቢያት ሐዋርያት መሆኑ
4. ይህንንም የተማርነው ደግሞ ከሕፃንነታችን መሆኑ
5. በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት አምኖ መኖር
6. ይህ ሁሉ የሚሆነው ቅዱሳት መጻሕፍትን በማወቅ መሆኑን
7. ፍጹማንና በጎ ሥራ እንሠራ ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚጠቅመን
8. ይህም ከትምህርታችንና ከተግሣጽ ልባችንንም በቀናው መንገድ ከመምራት እንደሚበጀን ይነግረናል።

ስለዚህ ክርስቲያኖች ሆይ ይህን የመንፈስ ቅዱስ ቃል ተረድተን እንደ ቅዱስ ባኮስ (አቢላክ) የኢትዮጵያ መንግሥት የገንዘብ አለቃ እንደነበረው ዕለት ዕለት መጽሐፍ ቅዱስን ልናነበው ልንጸልይበትና እምላካችንን ልናውቅበትና ልናናግርበት ይገባል።

> "ተነሥቶም ሄደ። እነሆም ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤ ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።" ሥራ ፰፡፳፯-፳፰ (8፡27-28)

ይህ የመላው አፍሪካ ሐዋርያ ቅዱስ ባኮስ ዘኢትዮጵያ እግዚአብሔር የተገናኘው ፊልጶስንም የላከለት በመንገድ ሳይቀር መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ ስለሆነ ነው። ይህ የኦርቶዶክሳውያን

ሃይማኖታዊ ልማድ ነው። ዛሬ እየጠፋ መጣ እንጂ ኦርቶዶክሳውያን ትምህርት ስንጀምር በእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆን ዛሬም ቢሆን ያለው ትምሕርት አብነት ነው። እግዚአብሔር አባታችን ያዘዘንም ይህንኑ ነው።

> "እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው በቤትህም ስትቀመጥ በመንገድም ስትሄድ ስትተኛም ስትነሣም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው፤ በዓይኖችህም መካከል እንደክታብ ይሁንልህ። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።
> ዘዳ፡፮፡፮-፱ (6:6-9)

# ወንጌል

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወተ ሥጋ በዚህ ምድር ሳለ ለሦስት ዓመታት ያስተማረው ወንጌል ይባላል። ወንጌል ማለት ብሥራት ስብከት ማለት ነው። ቃሉ የግሪክ ቃል ነው። በመቅድመ ወንጌል እንዲህ ይላል።

"ወንጌል ብሂል በልሳነ ጽርዕ ዘበትርጓሜሁ ስብከት" የወንጌል ትምህርት መሠረትም ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፋ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነገሠ ዲያብሎስ እንደተሻረ አዳምና ልጆቹ እንደዳኑ ነጻ እንደወጡ ማስተማር ነው።

## አርባዕቱ (፬ቱ) ወንጌላውያን

እግዚአብሔር አምላክ ወንጌልን ያጻፈው በአራት ቅዱሳን ሰዎች ነው። እነዚህም፡- ማቴዎስ፣ ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ ናቸው። ማቴዎስና ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የተመረጡ ሲሆን ማርቆስና ሉቃስ ደግሞ ከሰብአ ሁለቱ አርድእት ናቸው። እነዚህ አራቱ ወንጌላውያን አራት የሆኑበት በርካታ ምሳሌዎች አሉ አንዱንና ዋናውን ልግለጽላችሁ።በአራቱ እንስሳት ይመሰላሉ። "ፊተኛው እንስሳ አንበሳን ይመስላል ሁለተኛውም አንበሳ ላምን ይመስላል ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው አራተኛውም እንስሳ የሚበረውን ንስር ይመስላል። አራቱም አንበሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፤ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም። እንስሶቹም በዙፋን ላይለተቀመጠው ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ "ራእ. ፬፥፯-፱ (4፡7-9)

### ፩. ቅዱስ ማቴዎስ

ማቴዎስ ከሐዋርያነት የተጠራበት ስም ሲሆን የቀድሞ ስሙ ግን ሌዊ ይባል ነበር። የአባቱ ስም አልፍዮስ ይባላል (ማር ፪፥፲፬ (2፥14) የጥምቀት 12 ቀን ሰንክሳር የማቴዎስን አባት ዲቁ ብሎ ይጠራዋል። የእናቱ ስም ደግሞ ከሩስትያ (ክርስቲና) ይባላል።

የስሙ ትርጉም፡-ማቴዎስ የሚለው የስሙ ትርጉም ኅሩይ (የተመረጠ) ማለት ነው። ከቀራጭነት መርጦ ለዚህ ክብር አብቅቶታልና።

ሁለተኛ- ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው።

<u>በሰው መመሰሉ</u>

ማቴዎስ በገጸ ብእሲ ይመሰላል። ምክንያቱም ይህ ወንጌላዊ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም መወለዱን ከጥንት ቃል ከተገባላቸው ቅዱሳን አበው ይልቁንም አብርሃምንና ዳዊትን ጠቅሶ ወልደ አብርሃም፣ ወልደ ዳዊት እያለ ሰው መሆኑን ስለገለጸና ከሦስቱ ወንጌላውያን በበለጠ እምላካችን መድኃኒታችን ወልደ ዕጓለ እመሕያው (የሰው ልጅ) እየተባለ በወንጌሉ ስለተገለጸ ነው።

> "የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ" ማቴ. ፩፥፩ (1፥1)

## <u>፪. ቅዱስ ማርቆስ</u>

ቅዱስ ማርቆስ ከሰባ ሁለቱ አርድእት ክፍል ነው። የአባቱ ስም አርስጦሎስ የእናቱ ደግሞ ማርያም ይባላል። ቅዱስ በርናባስም አጎቱ ነው። በሌላ ስሙ ዮሐንስ ይባላል።

ቆላ ፬፥፲ (4፥10) የእናቱ ቤት የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን እየተባለ በቤተክርስቲያን ታሪክ የሚጠቀስ ነው፡ ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ ያስተምርበት ስለነበር ነው። ከሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስ የወረደላቸው በዚህ በማርቆስ እናት ቤት ነው።

> "... እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደነበረው ማርቆስ ወደተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም

ቤት ... " ሐዋ. ፲፪፥፲፪ (12፥12)

የስሙ ትርጉም፡- ማርቆስ የሚለው ስም ሦስት ትርጉሞች አሉት። አንደኛ - አንበሳ ማለት ነው። አንበሳ የካህም (የካም) ጌታው ነው እሱም ከሀገረ ሰብከቱ ከግብፅ የካም አምልኮትን አጥፍቷልና። ሁለተኛ ንህብ (ንብ) ማለት ነው። ንብ የሚይቀሰመው አበባ የከም- እሱም ከጌታም ከሐዋርያትም ወንጌልን ተምሮአል። ሦስተኛ ማርቆስ ማለት ካህን ማለት ነው።

## በአንበሳ መመሰሉ፡-

ቅዱስ ማርቆስ በአንበሳ ይመሰላል። በአንበሳ የመመሰሉ ምሥጢር በሁለት መንገድ ነው። አንደኛ የይሁዳ አንበሳ የተባለ የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በመጻፍ እና በሁለተኛ ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው በግብፅ ሀገር የነበረ የካም አምልኮት አንበሳ በተባለ በጌታችን ወንጌል ፈጽሞ ስለአጠፋ ምሳሌው አንበሳ ተብሏል ።

"እኔ አንደ አንበሳ ሆንኩባቸው" ሆሴዕ ፲፫፥፯ (13፥7)

"እነሆ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ አርሱም የዳዊት ሥር መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቷል" ራዕ. ፭፥፭ (5፥5)

## ፫. ቅዱስ ሉቃስ

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ምድቡ ከሰባ ሁለቱ አርድዕት ነው። ይህ ቅዱስ ወንጌላዊ በስሙ የተጠራውን ሦስተኛውን የጌታችንን ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ወይም የሐዋርያት ሥራ የተባሉትን መጻሕፍት የጻፈ በእግዚአብሔር የተመረጠ ወንጌላዊ ነው። ቅዱስ ሉቃስ የተወለደው በአንጾኪያ ከግሪካውያን ቤተሰቦች ነው። ቅዱስ ሉቃስ ሥራው ሕክምና ነበር።

"የተወደደው ባለ መድኃኒቱ ሉቃስ" ቆላ. ፬፥፲፬ (4፥14)

## የስሙ ትርጉም

አንደኛ ሉቃስ ማለት መበሥር ማለት ነው። ብሥራተ መልአክን ይጽፋልና። ቅዱስ ገብርኤል መልአክ እመቤታችንን ከእግዚብሔር ተልኮ እንዳበሠራት የጻፈ ቅዱስ ሉቃስ ነው።

ሁለተኛ ሉቃስ ማለት ተንሣኢ (ፈጣን) ማለት ነው። ከሌብከተ ወንጌል ይፋጠናልና።

ሦስተኛ ሉቃስ ማለት ዐቃቤ ሥራይ (ባለመድኃኒት ወይም ሐኪም) ማለት ነው። ቀድሞ ዐቃቤ ሥራይ በሥጋ ነበር። በኋላ ጌታ መርጦት ዐቃቤ ሥራይ ዘነፍስ ሆናል (የነፍስ ሐኪም)።

## በላሕም (እምቦሳ) መመሰሉ

ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ በላሕም (በፍሪዳ) ይመሰላል። በላሕም መመሰሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። አንደኛ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከእመቤታችን በከብቶች በረት መወለድ፣ የእረኞች መምጣት፣ የመላእክትን ዝማሬ ከሦስቱ ወንጌላውያን የበለጠ በጎላ በተረዳ ነገር ስለጻፈ ነው።

> "የበኩር ልጇን ወለደች በመጠቅለያም ጠቀለለችው በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።" ሉቃ. ፪፡፯ (2፡7)

## ሁለተኛ በላሕም (ላም) መመሰሉ

በሌሎች ወንጌል የማንመለከተውን ጠፍቶ ከነበረው ልጅ አባቱ የሠዋለትን እንቦሳ (ፍሪዳ) ስለጻፈ ነው። ይህም ምሳሌነቱ ሥጋውንና ደሙን ከሰጠን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

> "የሰባውን ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱት" ሉቃ. ፲፭፡ ፳፫ (15፡23)

## ፲. ቅዱስ ዮሐንስ

ቅዱስ ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሲሆን ከወንጌላውያኑ በስሙ የተጠራውን አራተኛውን የዮሐንስ ወንጌል የተባለውን የጻፈ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ከዚህ በተጨማሪ ሦስቱን በስሙ የተጠሩ መልእክቶችና ራእየ ዮሐንስ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችን የምትጠቀምበት ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድን የደረሰ ቅዱስ አባት ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ አባቱ ዘብዴዎስ እናቱ ማርያም ይባላሉ። በገሊላ አውራጃ ዮሐንስ እናት ማርያም ባውፍልያ ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ወገን ነች። ይህም በሰንከሳር ጥር 18 ቀን ተጽፏል። ማቴ. ፳፥፳ (20፥20)

## የስሙ ትርጉም

ቅዱስ ዮሐንስ የስሙ ትርጉም ከግብሩ ጭምር እንዲህ ያለ ነው።

፩. ዮሐንስ ማለት ርኅራኄ ወምህል (ይቅርታ) ፍሥሐ ወኃሤት (ደስታ) ማለት ነው። እንደ ሞክሼው እንደ ዮሐንስ መጥምቅ።

"ወትሰምዮ ስሞ ዮሐንስ። ወይከውነከ ትፍሥሕተ ወኃሤተ"

"ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ደስታና ተድላም ይሆንልሃል" ሉቃ. ፩፥፲፫ (1፥13)

፪. ዮሐንስ ማለት ነባቤ መለኮት በግሪኩ ታዖሎጎስ ተብሏል

ምክንያቱም በመለኮት ሕግ ተቃኝቶ ያንድነትን የሦስትነትን ነገር ተናግሯልና የጌታችንን እግዚአብሔር መሆን (አምላክ መሆን) ከሌሎቹ አስፍቶ የተናገረ ቅዱስ ዮሐንስ ነው። ዮሐ. ፩፥፩-፲፬ (1፥1-14)

፫፥ ዮሐንስ ማለት ወልደ ነጐድጓድ (ቦአኔርጌስ) ማለት ነው። ይህ ስም ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር ከብር ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ያወጣላቸው ስም ነው።

"የዘብደዎስንም ልጅ ያዕቆብን የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስን ቦአኔርጌስ ብሎ ስየማቸው የነጐድጓድ ልጆች ማለት ነው" ማር. ፫፡፲፯ (3፥17)

፬. ቅዱስ ዮሐንስ በሌላ ስሙ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ እየተባለ ይጠራል። አቡቀለምሲስ የግሪክ ቃል ሲሆን የተገለጠ ያልተሸፈነ የታየ ራእይ ማለት ነው።ይህም ትርጉሙ ዮሐንስ ባለ ራእይ ማለት ነው። ይህም ስም የተሰጠው በስሙ የሚጠራውን "ራእየ ዮሐንስ" ስለአየና ስለጻፈ ነው።

፭. በቅዳሴው አንድምታ መግቢያ እንደተጠቀሰው ዮሐንስ ማለት "ውሉደ መንግሥት ወክህነት" ማለት ነው። ትርጉሙም የመንግሥትና የክህነት ልጅ ማለት ነው።በትውልዱ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ነው። በወንጌሉ ስለ ራሱ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል።

"ያም ደቀመዝሙር በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀ ነበረ።" ዮሐ. ፲፰፡፭ (18፥5)

፮. ዮሐንስ ማለት "ፍቁረ እግዚእ" የጌታ ወዳጅ ጌታ የሚወደው ማለት ነው። ከሌሎቹ ደቀመዛሙርት ሁሉ ጌታችን መድኃኒታችን ቅዱስ ዮሐንስን ይወደው ነበር። በስቅለቱና በሞቱ ዕለት ሁሉም ሲበተኑ እሱ ብቻ በመስቀሉ ሥር ተገኝቶ ስለነበር ነው። ስለዚህም ቅድስት ድንግል እመቤታችንን እሷ እናት ትሆነው ዘንድ እርሱ ቅዱስ ዮሐንስ ልጅ ይሆናት ዘንድ እምላካችን በመስቀል ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ ተናገረ።

"ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀመዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን፡ እናትህ እነኋት አለው።" ዮሐ. ፲፱፥፳፮ሽ ሕ (19፥26)

<u>**በንስር መመሰሉ**</u>

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ከሦስቱ ወንጌላውያን ለየት ባለ መልኩ በንስር ተመስሏል። ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስ፡ ማርቆስና ሉቃስ የተመሰሉባቸውን ሰው፣ አንበሳና ላሕም ብንመለከታቸው ሦስቱም በምድር መራመድ ወይም መሄድ ይችላሉ በአየር ላይ ግን መብረር ወይም መሄድ አይችሉም። ዮሐንስ የተመሰለበት ንስር ግን በምድር መራመድ በሰማይ ወጥቶ መብረር ይችላል። እንደገና ከሌሎች አዕዋፍ ሁሉ በተለየ መልኩ ከላይ ከሰማይ ሆኖ በምድር ላይ ያለች ትንሽ ቅንጣት ነገርን አጥርቶ መመልከት ይችላል። በዚህ ንስር የተመሰለውም ቅዱስ ዮሐንስ እንደኛ ንስር ወደ ላይ ሽቅብ ወጥቶ እንደሚበር ቅዱስ ዮሐንስም የክብር ባለቤት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከአብ የመወለዱን ቀዳማዊ ልደቱን ተናግሮ በምሥጢረ ሥላሴ ይጀምራል - ይህም ከሦስቱ ወንጌላውያን የተለየ ያደርገዋል።

"ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል"

"በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ዮሐ. ፩፥፩ (1÷1)

ሁለተኛ ንስር በምድር መሄድ እንደሚችል። ቅዱስ ዮሐንስም ምንም በቀዳማዊ ልደቱና "ሁሉን የፈጠረ አምላክ፣ ፈጣሪ መሆኑን ጽፎ ወንጌሉን ቢጀምርም ደኃራዊ ልደቱን ይህም ከእመቤታችን በዚህች ምድር መወለዱን ይጽፍልናል።"

"ቃል ሥጋ ኮነ" ዮሐ. ፩፥፲፬ (1÷14) ያ እግዚብሔር ነው ያልኩት "ቃል ሰው ሆነ" ብሎ።

# አዋልድ መጻሕፍት

አዋልድ መጻሕፍት የሚባሉት ከስማንያ አንዱ (፹፩ዱ) የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር ያልሆኑ ነገር ግን ፍጹም መጽሐፍ ቅዱስን የመሰሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው።

አዋልድ የሚለው ቃል ትርጉም ልጆች ማለት ነው። ወልድ የሚለው የግእዝ ቃል ትርጓሜ ልጅ ማለት ሲሆን አዋልድ የወልድ ብዙ ነውና ልጆች ማለት ነው፤፤ ከዚህም የተነሣ አዋልድ መጻሕፍት ማለት የመጽሐፍ ልጆች ማለት ይሆናል። ስለዚህም በቤተክርስቲያናችን አዋልድ መጻሕፍት ስንል ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወለዱ አባታቸውና ወላጃቸው የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ መስለውና ተከትለው የተጻፉ ማለት ነው። አዋልድ መጻሕፍት የረቀቀውን አጉልተው፣ የጎደለውን አሟልተው ምሳሌውን ተርጉመው ያጠረውን አርዝመው መጽሐፍ ቅዱስ መሠረት በማድረግ መልካም ከሆነው እምልኮተ እግዚአብሔር የሚጠቅሙ፣ የሚረዱና፣ የሚመከሩ በእምነት የሚያጸኑ ፣ ኀይልን የሚሰጡ፣ ከጸሎት የሚያተጉና ሃይማኖታዊ ትጥቅን የሚያከብሱ ናቸው። በዚህም ጠላት ሰይጣንን ድል ይነሡታል። አዋልድ መጻሕፍት በርካታ ሲሆኑ በዚህ ጽሑፌ ግን የምገልጽላችሁ ስለ ገድላት፣ ድርሳናት፣ ተአምራትና መልክአ ይሆናል። ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጁ ጢሞቴዎስን የመከረው ከእኛም የተላለፈልን የእግዚአብሔር ቃል ከሁሉም አስረጅ ነው።

> "አንተ ግን በተማርክበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር ከማን እንደተማርኸው ታውቃለህና ከሕፃንነትህም ጀምረህ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ከበጎ ሥራ ሁሉ ከትምህርትና ከተግሣጽ ልብንም ከማቅናት በጽድቅም ካለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል። " ፪ጢሞ ፫፡፲፬፡፲፯ (3፡14-17)

ልክ በቃሉ እንደተገለጸው በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናችን

ከሕጻንነት ዕድሜያችን ጀምረን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ጸንተን እንድንኖር የሚያደርጉ ከክህደትም በመራቅ በተማርንበትና በተረዳንበት ነገር ጸንተን እንድንቆም የሚያደርጉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያከባቸው ብዙ መጻሕፍት በቤተክርቲያናችን አሉ። እነዚህም እባታቸው መጽሐፍ ቅዱስን የመሰሉ ናቸውና አዋልድ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ተብለው ይጠራሉ።

## ፩. የገድል መጻሕፍት፡-

የገድል መጻሕፍት የቅዱሳን ሰዎችን በተለይም የሰማእታትና የጻድቃንን የእምነት ተጋድሎ የሚዘከሩና የእግዚአብሔርን ጸጋ በእነሱ ላይ አድሮ እንዴት የሰይጣንን ኃይል ድል እንደመቱ የሚተርክ ነው። ከምሳሌም ገድለ ጊዮርጊስ፣ ገድለ ተክለሃይማኖት፣ ገድለ እስጢፋኖስ፣ ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እያለ የሁሉንም የሰማዕትነትና የጽድቅ ሥራ ለክርስቲያኖች ኃይልና ብርታት የእምነትም ጽናት ይሰጥ ዘንድ እናነበዋለን፣ እንጸልይበታለን፣ እንሳለመዋለን፣ በቅዱሳኑም ላይ ያደረ እግዚአብሔር በእኛም ያድራል እንባረካለንም።

> "ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።" ይሁዳ ፩፥፫ (1፥3)

ይህንን ከአላውያንና ከከሃድያንና ከመናፍቃን ጋር ያካቸውን ተጋድሎ የደረሰባቸውን መከራና ሰቃይ እየታገሡ እስከሞት ድረስ የተደበደቡትን፣ መዘበቻ በመሆንና በእስራትና በወኅኔ የተፈተኑትን፣ በድንጋይ ተወግረው የሞቱትን፣ በመጋዝ የተሰነጠቁትን፣ በሰይፍ ተገድለው የሞቱትን፣ ከአውሬ የተጣሉትን፣ በእሳት የተፈተኑትን ሁሉን እያጡ መከራን የተቀበሉትን፣ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ቆዳና ሌጦ ለብሰው ዓለም አልተገባቻቸውምና በምድረበዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ እየዞሩ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሠው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ጤዛ ልሰው ስለ ክርስቶስ ብለው ያደረጉትን ሁሉ ተጋድሎ የሚነገረን የቅዱሳን የገድል መጽሐፍ ነው። ዕብ. ፲፩፥፴፫-፴፰ (11፥33-38) በዚህ ሁሉ ጠላት ሰይጣንን

አሰጨንቀው በእግዚአብሔር ኃይል አሸነፋት።

**አንባቢ ሆይ፡-** የቅዱሳን የገድል መጽሐፍ ልክ እንደ ሐዋርያት ሥራ (ገድል) ነው። የሐዋርያት ሥራ ማለት የገድላቸው መጽሐፍ ነው። ያደረጉትን ተአምራት፣ ያስተማሩትን ትምህርት፣ የደረሰባቸውን መከራ ስቃይና እንግልት ይጽፋልና።

## ፪. የድርሳን መጻሕፍት፡-

ድርሳናት በአብዛኛው የሚጻፉት ለመላእክት ነው። ለምሳሌ ድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ገብርኤልና ሌሎችም በርካታ የድርሳን መጻሕፍት አሉ። በተለይ ደግሞ ረቂቅ የሆነ የሃይማኖትን ምሥጢር አጉልተው የሚተረጉሙ ድርሳናት አሉ። ለምሳሌ ድርሳን ዘዮሐንስ አፈወርቅ - ዕብራውያን እንደተረጎሙት። እንዲሁም ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት አድርገን እንድንቀበል ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ አበው ያዘጋጁልንም መጽሐፈ ቅዳሴን የብህንሳዊ ኤጲስ ቆጶስ አባ ሕርያቆስ የደረሰው፣ ቅዱስ ቄርሎስ የተናገረው እያለ ይገልጽልናል። ድርሰት ብሎ ሲናገር አንድ ሰው ከራሱ አሰተሳሰብ የሚያፈልቀው ሳይሆን በጾም በጸሎት የተጠመደ ከእግዚአብሔር ያደረ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ የሚጽፈው ነው።

## ፫.የተአምር መጻሕፍት፡-

በቤተክርስቲያናችን በርካታ የተአምር መጻሕፍት አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ተአምራትን በእግዚአብሔር በባለሟሎቹ የተሠሩ ጽፎልናል። በዚያ ያልተካተቱና መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈ በኋላ ደግሞ የተደረጉ ድንቅ ተአምራት የተጻፉበት የተአምር መጻሕፍት አሉን። ለምሳሌ ተአምረ ኢየሱስ፣ ተአምረ ማርያም፣ እያለ የመላእክትንም የቅዱሳንንም ተአምራት የያዙ በርካታ መጻሕፍት አሉን።

> "ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ" ዮሐ ፳፡፴ (20፡30)

እነዚህ ድንቅ ምልክቶች ወይም ተአምራት በእኛ ቤተ ክርስቲያን በተአምረ ኢየሱስ ተጽፈው ይገኛሉ። በሌሎችም መጻሕፍቶቻችን ላይ ተገልጸዋል። በአጠቃላይ የተአምራት መጻሕፍት ከድኅነት፣ ከዕውቀት፣ ከጸሎት ፣ ከመንፈሳዊ ብርታት የሚጠቅሙ ሆነው በእግዚአብሔር የተፈቀዱ ናቸው። ምእመናን ከሌሎች የተደረገው ድንቅ ተአምር እንዲደረግላቸው በሁሉም እግዚአብሔርን ከማመስገን በቤተክርስቲያናችን የጸሎት ሥርዓት ሰዓት ተመድቦላቸው ይነበባሉ። ክርስቲያኖች በቤትም ሊያነቧቸው የተገባ ነው።

## ፱. የመልክአ መጻሕፍት፡-

በቤተክርስቲያናችን ካሉ መጻሕፍት አንዱ የመልክአ መጻሕፍት ናቸው። እነዚህም ከጸሎትና ከምስጋና እንጠቀምባቸዋለን። የመልክአ መጻሕፍት የራሳቸው ዜማም ያላቸው ናቸው። በሚኅሌት እንደዕለቱ በዓል እንጠቀምባቸዋለን። እነዚህ መጻሕፍት መልክአ ተብለው የተሰየሙበት ምክንያት ከስሙ እንደምንረዳው። መልክአ የአንድ አካል ገላጭ ነውና። ከሥላሴ ጀምሮ የእግዚአብሔር ጻድቃን ሁሉ መላ አካላቸው እየተወሳ የሚመሰገኑበት ስለሆነ መላ መልካቸውን እየጠቀሰ የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ከምሳሌ መልክአ ሥላሴ፣ ኢየሱስ፣ ማርያም፣ ዑራኤል፣ አረጋዊ ወዘተ እየተባለ የተጻፈ ነው። ይህም የምስጋና መልክአ መጽሐፍ እግዚአብሔርንና ቅዱሳንን ከስማቸው ይጀምርና ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ያመሰግናል። እንዲህ እያለ፡-

ለኢየሱስ፡- "ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሐላ ዘኢይሔሱ"

"ለማይለወጠው ስም አጠራርህ ሰላምታ ይገባል"

ከዚህ ጀምሮ እየቀጠለ፡- "ለሥዕርተ ርዕስከ" ለራስ ፀጉርህ፣ "ለርእስከ" ለራስህ በማለት ሁሉንም ሕዋሳት ያመሰግናል። ቅዱሳንም እሱን መስለውታልና

"የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናልና" ሮሜ ፰፥፳፱ (8፡29)

"እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" ፩ቆሮ ፲፩፡፩ (11፡1)

ስለዚሀ እግዚአብሔር የመረጣቸው ጽድቃቸው የተመሰከረላቸው ቅዱሳን ይመሰገናሉ። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ብሏል "ለቅኖች ምስጋና ይገባል" መዝ ፴፪፡፩ (32፡1) በሌላም ስፍራ ቅዱስ ጳውሎስ እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ ይላል። ፩ቆሮ ፫፡፲፮ (3፡16) ሁላችንም ማደሪያው በአርያውና በአምሳሉ ብንፈጠርም እነሱ ግን በመልካም ሥራቸውና በሃይማኖታዊ ተጋድሎአቸው የተለዩ፣ የተመረጡ፣ ከዓለም የራቁ ንጹሕ፣ ቅዱስ መቅደስ ሆነዋልና ቤተ ክርስቲያናችን መለከአ ጽፋ ታመሰግናቸዋለች።

# ትውፊት

ትውፊት የሚለው ቃል ከግዕዙ "አወፈየ" አወረሰ፣ አቀበለ ከሚለው የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ውርስ ቅብብል ማለት ነው። ይህም እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ከአበውና ከእማት ከትውልድ የተካከፈና የሚተካከፍ፣ የሚቀባበል በጽሑፍ የሚገለጽ በቃልም የሚነገር ነው። ስለዚህ ትውፊት ለንል ከትውልድ ወደትውልድ የሚተካከፍ የእግዚአብሔር ሕግ፣ ትምህርት፣ ሥርዓትና ወግ ነው። የሚገልጠውም ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው። ክብር ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ወንጌሉን ካስተማራቸው በኋላ በተጨማሪ እንዴት ማስተማርና መኖር እንዳለባቸው የቀረውን መንፈስ ቅዱስ ያስተምራችኋል ይገልጽላችኋል ብሏቸዋል።

> "ከእናንተ ጋር ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል" ዮሐ ፲፬:፳፭ (14:25)

ከዚህ የአምላክ ቃል የተነሣ እንደምንማረው ትውፊት በመንፈስ ቅዱስ ከቅዱሳን የሚገለጥ የእውነት ትምህርት ነው። ስለዚህም ይህ የተሰጣቸው ቅዱሳን እኛም እነሱን መስለን እግዚአብሔርን አምልከን በክርስትና ሕይወት እንድንኖር በጽሑፍም በቃልም ነግረውናል። ከምሳሌ ሐዋርያት ከመልእክታቸው በተጨማሪ በቃላቸው የደነገጉትና ያስተካከፉት ያወረሱት ትምህርትና ሕግ በቤተ ክርስቲያናችን እየወረስነውና እያወረስነው የምንኖረው ነው።

> "የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ አደነግጋለሁ" ፩ቆር ፲፩:፴፬ (11:34)
>
> "እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወድም ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተ ልመጣ አፍ ለአፍም ልነግራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።" ፪ዮሐ ፲፪ (12)

ቅዱስ ጳውሎስና ዮሐንስ ከጽሑፋቸው በተጨማሪ በቃል ያስተማሩት ትምህርትና ሥርዓት እንዳለ ይህ የራሳቸው መልእክት ምስክር ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ቀኑን እንደገና ከተወደደው ወንድም ከጋይዮስና ከምእመናን በሦስተኛው መልእክቱ ይገልጽላቸዋል (፫ዮሐ ፲፫)

ታዲያ እነዚህ ቅዱሳን ሐዋርያት ሌሎችም ነቢያት ሐዋርያት ከጽሑፋቸውና ከመልእክታቸው በተጨማሪ ያስተማሩት የተረጎሙት ቃለ እግዚአብሔር ከወደት ደረሰ ብሎ የሚጠይቅ አስተዋይ መልሱን በቤተክርስቲያን ያገኝዋል። በመልእክትም ሆነ በቃል የተላለፈው የኦሪትም ሆነ የሐዲስ ምሥጢር ተዘጋጅቶ ከቀደሙት ነቢያትና ሐዋርያት ለሊቃውንቱ ደርሶ ዛሬ እኛም ተቀብለነው ይኖራል። ምእመናንም ያለማወላወል በዚህ እምነት ጸንተው ይኖሩ ዘንድ ግድ ይላል።

"እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ። "፪ተሰ ፪፥፲፭ (2፥15)

ብዙውን ጊዜ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ትጨምራለች፣ ወግ ታበዛለች በማለት ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚነቅፉ ሰዎች ይህን የእግዚአብሐር ቃል አላነበቡትምን? የሚል የእውነት ጥያቄ ሊነሣ ይገባዋል። በቤተክርስቲያኒቱ ያለው እምነት፣ ሥርዓትና ወግ ሁሉ ግን ከእግዚአብሐርና ከእርሱ ቅዱሳን የመነጨ የሕይወት ውኃ ቃሉ ነው። እንደውም ይህን የእውነት ትውፊት በመያዛችን እግዚአብሐር ደስ ይለዋል ቅዱሳኑም ያመሰግኑናል። የተቀበልነውና የወረስነው ከእነርሱ ነውና። በዚህም ቅዱሳን ክርስቶስን እምደመሰሉበት እኛም ቅዱሳኑን በመምሰል ክርስቶስን እንመስለዋለን።

"እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ። ወንድሞች ሆይ በሁሉ ስለምታስቡኝና እሳልፌ እንደ ሰጠኋችሁ ወግን ፈጽማችሁ ስለ ያዛችሁ

አመስግናችኋለሁ።" ፩ቆሮ ፲፩፡፩ (11፡1)

ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በቅዱሳን አድሮ ያስተካከፈልንን እምነትና ሥርዓትን የሚገልጹትን ትውፊታት ብንጠብቅ ጸጋ እንደምንወርስ በቅዱሳን መካከከት እንደበት እንደምነመስገን እንዲሀ ስንረዳ በሌላ በኩል ደግሞ የክርስትና ወግ ወይም ትውፊት ያልሆኑትን የከሀድያንና የመናፍቃንን የከሀደት ትምሀርትና የኑፋቄ ወግ ፈጽመን እንዳንቀበል እኛም የተቀበልነውን ትውፊት የማይቀበሉትንና የሚያናንቁትን እንዳንከተል ከእነርሱ ተከዩ በሚል የእግዚአብሔር ቃል ተይዘናል።

"ወንድሞቼ ሆይ ከእኛ እንደተቀበከው ወግ ሳይሆን ያከ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትከዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋከን።"

አንዳንዶች በእምነት ስም የራሳቸውን የልብ ከፋት ከመሸፈን ሌላ ወግን በመቅረጽ ጌታችንን ሲቃወሙ ይገኛሉና። በአፋቸው የሚያምኑ የሚመስሉ በልባቸው ግን የሚረግሙ አሉና።

> "ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምሀርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል።" ኢሳ ፳፱፡፲፫ (29፡13)

የክብር ባከቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይሀን የኢሳይያስ ትንቢት የተናገረባቸው ከኢየሩሳሌም ተሰብሰበው ወደርሱ ሐዋርያትን ከመክሰስ የመጡ ጸፎችና ፈሪሳውያንን ነው። (ማቴ፡ ፲፭፡፩-፱ (15፡1-9) ዛሬም ጌታን እናከብራለን የሚሉ በአፋቸው የሚጠሩ ቅዱሳን ሰዎችን የሚከሱ ምድራችንን የሞሉ አሉ። ቁም ነገሩ በአፍ መጥራት ሳይሆን በልብ ማመን መሆን አከበት ከሲኦል የሚያድን እርሱ ነውና።

> "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።" ማቴ ፯፡፳፩ (7፡21)

መንግሥተ ሰማያትን ከመውረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ይገባል ይህ ደግሞ በኦሪት፣ በነቢያት፣በወንጌል፣ በመልእክት ከዚህም በተጨማሪ በሊቃውንት ቅዱሳን ትርጓሜና ትውፊት በአጠቃላይ በጽሑፍና በቃል ተነግሮናል። ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠ እምነት ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከ ምጽአት ይተላለፋል፣ይቀባበላል፣ ይወራረሳልም። ስለዚህም በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲን ቅዳሴ ወንጌል ኪነበብ ሲል ቀጥሎ ያለውን ቃል እንሰማለን

ዋናው ቀዳሽ ካህን፡ "ነዋ ወንጌለ መንግሥት" የመንግሥት ወንጌል እነሆ ይህቺ ናት ብሎ ከንፍቀ ቄስ ይሰጠዋል ንፍቀም ካህን "መንግሥቶ ወጽድቆ ዘአወፈየኒ አወፈይኩከ" መንግሥቱንና ጽድቁን የምትናገር ቄሉ የሰጠኝን ወንጌል ስጠሁህ ብሎ ከዲያቆኑ ያቀብለዋል። ዲያቆኑም ሲቀበል "ነሰሑ ወእመኑ እስመ ቀርበት ይእቲ መንግሥተ ሰማያት" እመኑ ንሰሀ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ብሎ ከንፍቀ ቄስ ይቀበላል። በመግቢው ላይ የቃሉን ትርጉም እንደተመለከትነው ትውፊት ማለት ቅብብል ከአባት ከእናት ወደ ልጆች የሚተላለፍ የእግዚአብሔር ሕግ፣ ሥርዓትና ወግ ነው። ከዚህም ነው ካህኑ ከንፍቀ ካህን ንፍቁ ካህን ደግሞ ከኪያቆኑ ሲያቀብል የምናየው። ምሳሌውም ዋናው ካህን የጌታ ምሳሌ ሲሆን ከንፍቁ ካህን መስጠቱ ንፍቁ ካህን ደግሞ የነጴጥሮስ የሐዋርያት ይህም ወንጌልን ከጌታ ከመቀበላቸው ንፍቁ ካህን ደግሞ ከዲያቆኑ መስጠቱ ሐዋርያት ደግሞ ከእነእስጢፋኖስ የመስጠታቸው ምሳሌ አዲህ እየተቀባበለ የሰው ልጅ ሁሉ አምኖ ንሰሐ በመግባት መንግሥተ ሰማያትን ይወርስ ዘንድ ነው።

# አሠርቱ ( ፲ቱ) ቃላት ኦሪት

አሠርቱ ቃላተ ኦሪት የሚባሉት እግዚአብሔር አምላክ ለሊቀ ነቢያት ሙሴ በሲና (ኮሬብ) ተራራ ላይ የሰጠው ነው። አሠርቱ ቃላት፣ አሠርቱ ትእዛዛት አሠርቱ ሕግጋት ዘኦሪት ተብለው ይጠራሉ ሁሉም አንድ ነው።

እነዚህ ትእዛዛት ለአባታችን ሙሴ በሁለት ጽላት ተቀርጸው ተሰጡት። በኋላም ሙሴ ሌሎች ሁለት ጽላት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር ቃላቱን በጣቱ ጻፈባቸው። አባታችን ሙሴም ይህን ሕግ በሚቀበልበት ጊዜ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ እንጀራም አልበላ ውኃም አልጠጣ። እግዚአብሔርም በአሥሩ ቃላት ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አድርጓልና አሥሩ የቃል ኪዳን ቃሎች ይላቸዋል።

> "እግዚአብሔርም ሙሴን በእነዚህ ቃሎች መጠን ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው።" ዘጸ ፴፬፡፳፯ (34፡27)

እነዚህ ፲ቱ ቃላት በሁለት ቦታ ተጽፈው ይገኛሉ። በመጀመሪያ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፳ ከቁጥር ፪እስከ ፲፯ (20፡2-17) በሁለተኛ ደግሞ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፭፡ ፮-፳፩ (5፡6-21) ነው። ሦስተኛ ደረጃ ማጤን ያለብን ወንድምህን እንደራስህ ውደድ የሚለው የሚገኘው በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፱ ቁጥር ፲፰ (19፡18) ላይ መሆኑን ነው። እነዚህ ቃላት የተሰጡት በእግዚአብሔር ነው። የተጻፉትም በጽላቱ ላይ ነው። ቦታው ሲና ወይም ኮሬብ ሲሆን ለሕዝቡ ምስክር እንዲሆኑ በአባታችን ሙሴ አማካኝነት ነው።

> "እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ (ዕብነ በረድ) የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው፡ ዘጸ፡ ፴፩፡፲፰ (31፡18) ዝርዝራቸውም፡-

፩. ኢታምልክ አማልክተ ወኢምንትኒ ዘእንበሌየ፤

፩. ኢትምሐል ስመ እግዚአብሔር ፈጣሪከ በሐሰት፤

፪. ተዘከር ዕለተ ሰንበት ከመ ትቀድሳ፤

፫. አክብር አባከ ወእመከ፤

፬. አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ፤

፭. ኢትቅትል፤

፮. ኢትዘሙ፤

፯. ኢትስርቅ፤

፰. ኢትኩን ስምዐ በሐሰት በላዕለ ቢጽከ፤

፲. ኢትፍቱ (አትመኝ)፤

ክብር ይግባውና ጌታችን እንደተናገረ አሥርቱ ትእዛዛት በሁለት ክፍል ይጠቀለላሉ። አንደኛ እግዚአብሔርን ለለማምለክ ሁለተኛ ደግሞ ሰውን ለለመውደድ ነው። ስለዚህም ጌታ በወንጌሉ እንዲህ አስተማረን።

"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርስዋም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።" ማቴ.፳፪፡ ፴፯-፵ (22፡37-40)

ሁሉን አንድ አድርገን ስንመለከተው የአምላካችን ትእዛዙ ፍቅር ነው። ሁሉም ትእዛዛት በፍቅር ተጠቅለለዋል።

"እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ከማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታል። አታመንዝር አትግደል አትስረቅ፣ በውሸት አትመስክር፣ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሏል። ፍቅር ከባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።"ሮሜ.፲፫፡፰-፲ (13፡8-10)

የ፲ቱ ትእዛዛት ዘካለማዊነት፡- አሠርቱ ቃላት አሪት

ወይም ትእዛዛት እያለን ለንጠራ ያለገባቸው ሰዎች የኦሪት ነውና አይጠቅምም የሚል አስተሳሰብ ያሰባሉ። የኦሪት ሕግ ጸና እንጂ አልተሻረም። ስለዚህም ነገር ሁሉን አዋቂ ሕግን ሰጪ የሆነው ራሱ ባለቤቱ ክዑል እግዚአብሔር በወንጌሉ የነገረን ይህንኑ ነው።

"ኢይምስልክሙ ዘመጻእኩ እስአሮሙ ከኦሪት ወከነቢያት ዘእንበለ ጻዕሙ ከመ አፈጽሞሙ"

"እኔ ሕግንና ነቢያትን ከመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ከመሻር አልመጣሁም" ማቴ.፭፥፲፯ (5፥17)

ጌታችንም እንዴት ሊፈጽማቸው ወይም ሊያጸናቸው እንደመጣ በወንጌሉ በዝርዝር ተጽፏል። ዘላለማዊነታቸውም እስከ ፍጻሜ ዘመን በዚህ ምድር እንደሚኖር እንዲህ ይላል።

"እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም" በዕብራይስጥ የፊደል ገበታና ቁጥር አሥረኛዋ "ዮድ" ትባላለች አጻጻፏም እንደ ነጥብ ነው። ስለዚህም የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ያለው ከዚህ ነው። በምሥጢሩ ደግሞ አሥረኛዋ ትእዛዝ ኢትፍቱ (አትመኝ) ስትሆን ይህችን በአጻጻፍ የፊደል ቁጥር ከሌሎች ማነሷን አይቶና ንቆ ቢያስተምር እግዚአብሔር ከሕይወት መጽሐፍ ይደመስሰዋል በመንግሥተ ሰማያትም ስፍራ የለውም። "ዝኬ ፈትሐ አሐተ እምአላ ትእዛዛት እንተ ተሐፅፅ ወይሜሕር ከመዝ ከሰብእ ሕፁፀ ይከውን በመንግሥተ ሰማያት"

"ከ፲ቱ ቃላት አንዲቱ ታናሽ ናት ብሎ ከራሱ የሚሠራ ከሌላው የሚያስተምር ከመንግሥተ ሰማያት የወጣ ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህም ፲ቱ ቃላተ ኦሪት ከ፳ቱ ቃላተ ወንጌል ጋር ጸንተው የሚኖሩ ናቸው።

"ታደርጉትም ዘንድ ያዘዛችሁን ቃል ኪዳን አሥሩን ቃላት ነገራችሁ በሁለቱም በድንጋይ ጽላት ላይ ጻፋቸው።" ዘዳ፬፥፲፫ (4፥13)

# ሰንበት

ሰንበት የሚለው ጥሬ ቃሉ "ሰንበተ" የሚል የግእዝ ግስ ሲሆን ትርጉሙም ሰነበተ፣ አከበረ፣ ቆየ ሰንበት ማለትም የተከበረ የቆየ የሰንበት የዕረፍት ቀን ሰባተኛው ቀን ማለት ነው። ከዚህ በተለየ ግን በሃይማኖታዊ ምስጢር ትንተናው የተባረከ የተቀደሰ የተለየ ቀን ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ ዘላለማውያን የሆኑትን የማይለወጡ አሠርቱን ትእዛዛት የሰጠን ሲሆን ከእነዚህም አንዱ የሰንበትን ቀን እናከብረው ዘንድ ነው።

የሰንበት አከባበር ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ከሌሎች ሁሉ ልዩ ናት። አንዳንዶች መከበር ያለበት ቅዳሜ ነው ብለው ይናገራሉ ሌሎች ደግሞ ቅዳሜ ተሽራለች መከበር ያለባት እሑድ ናት በማለት ያስተምራሉ። እኛ ግን ኦርቶዶክሳውያን ከራሳችን በማፍለቅና በመፈላሰፍ ሳይሆን እግዚአብሔር በመጽሐፍ ያዘዘንን በመከተል ሁለቱንም ሰንበት (ቅዳሜና እሑድን) እናከብራለን። ልናውቀው የሚገባ ነገር ግን ከዕለታት ሁሉ እሑድ ትልቃለች ትበልጣለችም። ሁለቱንም ሰንበታት በዝርዝር እንመልከት።

## ቅዳሜ

ይህች ዕለት ቀዳሚት ሰንበት ተብላ ትጠራለች። ይህች ቅዳሜ እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ፈጥሮ ያረፈባትና እናከብራት ዘንድ ያዘዛት ቅድስት ዕለት ናት። እግዚአብሔር አምላክ የሠራውን ሥራ በዚህች ቀን ፈጸሚል ማለትም ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐርፏል። "ወባረካ እግዚአብሔር ለዕለት ሳብዕት ወቀደሳ" እግዚአብሔር ሰባተኛይቱን ቀን ባረካት ቀደሳትም" ዘፍ. ፪፥፫ (2፥3)

ስለዚህ እግዚአብሔር የባረከውንና የቀደሰውን እንደገና አይለውጠውምና፣ እኛም ዕለቱን በቅድስናው እናከብረዋለን። እናከብረውም ዘንድ ከልዑል እግዚአብሔር

ዘንድ ትእዛዝ አለ እንዲህም ይላል፡-

"ተዘከር ዕለተ ሰንበት ከመ ትቀድሳ" ሰባተኛይቱን ቀን ቅዳሜን እሰባት አከብራት ዘጸ. ፳፥፰ (20፥8) ይህ እንግዲህ ከአሥርቱ ትእዛዛት አንዱ ነው። ቅዳሜ ተሽራለች ብሎ የሚያምን የጌታ ቃሉ አይሻርምና ትእዛዛቱም ዘላለማውያን ናቸው፤ ሊያስተውል፣ ሊያምን ይገባዋል። አለዚያ ቃሉ እንደተናገረ በመንግሥተ ሰማያት ስፍራ አይኖረውም።

"እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከነዚህ ሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ከሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል" የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል"ማቴ. ፭፥፲፰-፲፱ (5፥18-19)

እርግጥ አይሁድ ይህችን ቅዳሜ ሰንበትን ሲያከብሩ ከዘረጉ ሳያጥፉ፡ ካጠፉ ሳይዘረጉ፣ ከከፈቱ ሳይዘጉ፡ ከዘጉ ሳይከፍቱ ነው። እኛ ግን በዚህች ቀን መንፈሳዊና በጎ ደግግ ሥራ እየሠራን ፈጣሪን እያመሰገንን እናከብራታለን፣ እንድንጨነቅበት ሳይሆን ሐሤት እናደርግበት ዘንድ እግዚአብሔር ሰንበትን ሠራልን።

"ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት ወአኮ ሰብእ በእንተ ሰንበት"

ሰንበት ስለ ሰው ተፈጠረች እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም። ማር. ፪፥፳፯ (2፥27)

ስለዚህ በዚህች ቀን ሰውም እንስሳም የሚያርፍባት ቀን ሆነች። እግዚአብሔር የሚሰጠን ሕግ ሁሉ የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም። ደግሞ እሱ የፍጥረት ሁሉ ጌታና ከፍጥረቱ ሁሉ የሚያዝን ነውና በዚህች በቅዳሜ ሰንበት እንስሳት እንኳ ያርፉ ዘንድ አዘዘ። በዚህች ቀን እግዚአብሔር የሥጋ ዕረፍትን ሰጠን ከነፍሳችንም ክብር እንድናመሰግነው ሰንበቱን ጠብቁ ብሎ አዘዘን።

የቅዱሳን አበው የሐዋርያት ቃል በዲድስቅልያ ሰላሣ ስምንተኛ (38ኛ) አንቀጽ ስለ ሰንበት ሲናገር እንዲህ ይላል። "ወገብረ ለነ መዋዕለ በዓላት ፍሥሐ ለነፍሳቲነ" "ለሰውነቶቻችን ደስታም የበዓላት ቀኖችን ሠራልን።"

> "ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው። አንተ እንደምታርፍ ሎሌህና ገረድህ ያርፉ ዘንድ አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ሎሌህም ገረድህም በሬህም አህያህም ከብትህም ሁሉ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ... ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ የሰንበትን ቀን ትጠብቅ ዘንድ አዘዘህ።" ዘዳ. ፭፥ ፲፬-፲፭ (5፥14-15)

ይህም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና በአዲስ ኪዳንም የሚሠራ የማይለወጥ ሕግ ነው። ለዚህም ነበር ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው። የጌታ ቤተሰቦች በቅዳሜ ዕለት ሥራ ያልሠሩት። ወደ መቃብሩም ያልሄዱት።

"በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ" ሉቃ. ፳፫፥፶፮ (23፥56)

## እሑድ

በስድስት ቀናት ውስጥ የሚታየውንም የማይታየውንም ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎ ቅዳሜን ቀድሶ አክብሩ ያለ አምላካችን እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ከሚዳን ሞትን ድል አድርጎ የተነሣባትን ዕለተ እሑድ የዕለታት በኩር አድርገን እናከብራታለን።

> "ኦ ዛቲ ዕለት ቅድስቱ ለአብ ቡርክቱ ለወልድ ልዕልቱ ለመንፈስ ቅዱስ ንትፈሣሕ ባቲ ወንትሐሠይ ባቲ ቀድሰዋ ለመ ትትቀደሱ ባቲ"

> "ወዮ ይህች ዕለት አብ የቀደሳተ ወልድ የባረካት መንፈስ ቅዱስ ከፍ ከፍ ያደረጋት ናት በርሰዋ ደስ ይበለን በርሰዋም ሐሤት እናድርግ ትከብሩባት ዘንድ አክብሩዋት"

አባታችን ቅዱስ አትናቴዎስ የእሑድ ዕለትን እንዲህ ከብሯን ከገለጸ በኋላ ሌሎቹን ስድስቱን ዕለታት በመጥራት ኑ እናከብራት ብሎ የክርስቲያኖች ሰንበት ብሎ ያወድሳታል።

> "የበዓላትን በኩር ኑ እናመስግናት ይህችውም የከበረች ሰንበተ ክርስቲያን ናት"
>
> "ንዑኬ ንወድሳ ለበኩረ (ዕለታት) በዓላት አንተ ይእቲ ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት" የዘጠኙ በዓላተ ትስብእት በኵር እሑድ ናት"።

እሑድ የሚለው ቃል የግእዝ ሲሆን "አሐደ" አንድ አደረገ ከሚለው ግሥ የወጣ ነው። ይህች ዕለተ እሑድ ከዕለታትና ከበዓላት ሁሉ የመጀመሪያ ናትና "በኵረ ዕለታት" የበዓላት ሁሉ መጀመሪያ ትባላለች። ይህች ዕለት ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ከእመቤታችን ሰው የሆነባት ወልድ ከሥጋ ጋር የተዋሐደባት በከበበ ትስብእት ዳግም ለፍርድ የሚመጣባት ይህችው ዕለት ናት። ሞትን ድል አድርጎ የተነሣባት፣ ሲኦልን የመዘበረባት፣ ገነትን የከፈተባት፣ አዳምንና ሔዋንን ከነልጆቻቸው ነፃ ያወጣባት፣ የሞት መውጊያ የደከደመባት፣ ለክርስቲያኖች የድል ቀን ናት ስለዚህ እሑድ የክርስቲያን ሰንበት ናትና ቤተክርስቲያናችን ታከብራታለች። አንዳንድ ሰዎች በዘመነ ቆስጠንጢኖስ ማክበር የተጀመረ ይመስላቸዋል። በዚያ ዘመን 318ቱ ሊቃውንት ከአባቶቻቸው ነቢያትና ሐዋርያት የወረደውን እውነተኛ የእግዚአብሔር ሕግ አጸደቁልን እንጂ አዲስ የፈጠሩትና የደነገጉት ምንም እንግዳ ነገር የለም። ከዚህም በመቀጠል የዕለተ እሑድን ክብር በብሉይና በሐዲስ ኪዳን እንመልከት።

## <u>እሑድ በብሉይ ኪዳን</u>

እሑድ በብሉይ ኪዳን ዘፍጥረትን ስንመለከት እግዚአብሔር ፍጥረትን የጀመረባት ዕለት መሆኗን እናገኛለን። ስለዚህም የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ትባላለች። ዘፍ. ፩፥፭ (1፥5) አትናቴዎስ "ዛቲ ዕለት ቀዳሚዊት ይእቲ ወአኮ ደኃራዊት"

ዮሐ. ፳፥፩ (20፥1)

> "ይህች ዕለት ቀዳሚት (የመጀመሪያ) ናት ደኃራዊት (ኋለኛይት) አይደለችም" ይላታል።

ቅድመ ክርስትና በዘመነ ብሉይ እሑድን እንዴት ያከብሯት እንደነበር በኦሪት ዘሌዋውያን ስንመለከት እግዚአብሔር አስቀድሞ ከድኅነት የሠራት መሆኗን እናገኛለን። ዘሌ. ፳፫፥ ፲፭-፳፩ (23፥15-21)

> ከቁጥር ፲፭-፲፮ "... ከሰንበት ማግስት ፍጹም ሰባት ጊዜ ሰባት ቀን ቁጠሩ እስከ ሰባተኛ ሰንበት ማግስት ድረስ አምሳ ቀን ቁጠሩ አዲሱን የእህል ቁርባን ወደ እግዚአብሔር አቅርቡ... "

ይህም ቁጥር ከሚያዝያ አስራ ስድስት ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ አራት ቀን ነው ይህ ሰባት ሱባዔ ይሆናል። አንድ ሱባዔ ማለት ሰባት ቀን ሲሆን ሰባቱ ሱባዔ አርባ ዘጠኝ ቀናት ይሆናል። አምሳኛው ቀንም እሑድ ላይ ይውላል። ልብ አድርገን ስንመለከት ቁጥሩ የሚጀምረው ከሰንበት ማግስት ስለሚል ነው። አንደኛው ቀን እሑድ ይሆናል አምሳኛውም ቀን እሑድ ዕለት ላይ ያርፋል። ይህችም ዕለት በዓለ ሠዊት ተብላ ትከብራለች። በዚህች ዕለት ከበኩራት ቁርባን የእህልና የመጠጥ ቁርባን የሚቃጠል የእሳት ቁርባንም እንዲሆን ጠቦቶች በጎቹና ወይፈን ከኃጢአት መስዋዕትና ከደኅንነት መስዋዕት ያቀርባሉ።

> ቁ. ፳፩ "በዚያን ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንላችሁ ዘንድ ታውጃላችሁ የተግባር ሥራ ሁሉ አታድርጉበት በምትቀመጡበት ሀገር ሁሉ ከልጅ ልጃችሁ የዘላለም ሥርዓት ነው"

በዚህች በዕለተ እሑድ (ሰንበት) የሰው ልጆች ሁሉ ድኅነት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የታወጀባት የፍጥረት ሁሉ የመዳን ቀን በቃሉ እንደተመለከትነው የተግባር ሥራ ሁሉ አታድርጉባት እንደተባለ ይህች ዕለት ዕረፍት ሥጋዊና ዕረፍት መንፈሳዊ ያለባት ናት። በቤተክርስቲያናችን ሕግ መሠረት በዕለተ እሑድ ሰንበት ዕረፍት ሥጋዊ የተባለ እርሻ፣

ቁፋሮ፣ ውጣ ውረድ የሌለባት፣ ዕረፍት መንፈሳዊ ጾም፣ ሰግደት፣ የሌለባት ሕሙም ድኩም፣ በሽተኛ የሚጐበኝባት፣ ደዌ ካልፀናበት በስተቀር ፍጥረት ሁሉ በመቅደሱ ከውዳሴ፣ ከዝማሬ፣ ከቅኔ፣ ከትርጓሜ ከሰባሔ፣ ከቅዳሴ የሚተጋባት ቅድስት ዕለት ናት።

ክርስቲያኖች ሆይ በዚህች ዕለት የሰው ልጅ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ እንዳለበት ይህን ቃሉን አዩና እንድትፈጽሙት እግዚአብሔር ይርዳችሁ። "ሰባት ሳምንትም ትቆጥራለህ መከሩን ማጭድ ከምትጀምርበት ቀን ጀምሮ ሰባት ሳምንት መቁጠር ትጀምራለህ"

> "ሰባት ሳምንትም ትቆጥራለህ፤ መከሩን ማጨድ ከምትጀምርበት ቀን ጀምሮ ሰባት ሳምንት መቁጠር ትጀምራለህ።አምላክህ እግዚአብሔረ በባረከህ መጠን በፈቃድህ የምታቀርበውን አምጥተህ ከአምላክህ ከእግዚአብሔር የሰባቱ ሱባዔ በዓል ታደርጋለህ። አንተ፣ ወንድ ልጅህና ሴት ልጅህ ወንድ ባሪያህና ሴት ባሪያህ በአገርህም ደጅ ውስጥ ያለው ሌዋዊ በመካከልህም ያሉት መጻተኛና ድሀ አደግ መበለትም አምላክህ እግዚአብሔር በዚያ ሰሙ ይጠራበት ዘንድ በሚመርጠው ሰፍራ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበላችሁ።" ዘዳግም ፲፮፥፱-፲፩ (16፥9-11)

በብሉይ ኪዳን እንዲህ ከሆነ ሕግ በጸናባት በሐዲስ ኪዳን ደግሞ የበለጠ መሆኑን አስተውሉ።

## እሑድ በሐዲስ ኪዳን

ከላይ እንደተመለከትነው አምላካችን እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን የሠራባት የተመረጠች ዕለት (ሰንበት) ዕለተ እሑድ ናት። ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተጸነሰው በዚህች ቅድስት ዕለት ነው። ሙስና መቃብርንም ደምስሶ አጥፍቶ ድል አድርጎ ከሞት የተነሣው በዚህች በዕለተ እሑድ ነው።

"በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ

መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ...መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፡-እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና እንደተናገረ ተነሥቷልና በዚህ የለም።" ማቴ. ፳፰፥፩-፲ (28፥1-10)

በብሉይ ዘመን የተደረገው ሁሉ በሐዲስ ኪዳን የተፈጸመ ነውና ጌታችን ክብር ይግባውና ኦሪትን ለመሻር ሳይሆን ልፈጽማት መጣሁ ብሎ በወንጌሉ እንደነገረን ማቴ. ፭፥፲፯ (5፥17) በኦሪት ዘሌዋውያንና በዘዳግም ላይ እንደተመለከትነው የእምላካችን ሕግ ከዘላለም የሚጸና ነው ብሎ እንደተናገረ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ ከሰባት ሱባኤ በኋላ ሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን የሰጠባት ዓለም ሁሉ ወንጌልን የሰማባት ዕለት ይህች የተመረጠች ዕለተ እሑድ ናት።

"በዓለ ሃምሳው የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም ባንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ... በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው" የሐዋ. ሥራ ፪ (2)

በዚህች የድኅነት ቀን ክርስቲያኖች እየተሰበሰቡ ከሌሎች ዕለታት በተለየ የምስጋና ቀን ሆነች። ቅዳሴ ይፈጸምባት ትንሣኤው ይነገርባት ዘንድ ሥርዓት ሆነ። ሥራ ፳፥፯ (20፥7)። ምእመናንም በዕለተ እሑድ ከችግረኞች የሚመጸወተውን ገንዘብ ሁሉ በዚህች ቀን እየሰበሰቡ ምንዱባንን ይረዱበት ነበር። ፩ቆሮ. ፲፮፥፪ (16፥2)። ይህ ሥርዓት ነው ዛሬም በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን የሚፈጸመው። የሐዋርያት አባቶቻችን በረከታቸው ይደርብንና ይህችን ዕለተ እሑድ

የጌታ ቀን ብለው ይጠሩዋታል ራዕይ ፩፥፲ (1፥10)

ከሌላው ዓለም በተለየ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ብቻ ሰንበታትን (ቅዳሜንና እሑድን) ታላቅ ክብር በመስጠት ያከብራሉ። የጥንት ክርስቲያኖችም ያደርጉት እንደበረው በቅዳሜና በእሑድ ዕለት ተጠብቀው ከእግዚአብሔር የምስጋና ቀንና ድሆችን ከመጎብኘት

የታመመን ለመጠየቅ በተለያየ መከራ ያለውን በማጽናናት ያሳልፉታል። ሁሉን የሥጋ ሥራቸውን በዕለተ ዐርብ ያጠቃልላሉ። ይህም ምሳሌነቱ ዕለተ እሑድ የክብር ባለቤት ዳግም ከፍርድ የሚመጣባት ቀን ተብላ የምትታመን ናትና ተሰናድቶ መጠበቅን የሚያሳይ የሚገባ ሥራ ነው።

> "ወጸልዩ ባሕቱ ከመ ኢይኩን ጉያክሙ በክረምት ወበሰንበት"
>
> "ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ" ማቴ. ፳፬፥፳ (24፥20)

ስለዚህ ይህች ቅድስት የሰንበት ዕለት ምእመናን ሁሉ በመቅደሱ በጸሎት የሚተጉባት እንጂ የሚተኙባት አይደለችም።

> "ኢይምጻእክሙ ግብተ ወኢይርከብክሙ እንዘ ትነውሙ ወናሁ እብለክሙ ለኵልክሙ ትግሁ።"
>
> "ድንገት እንዳይመጣባችሁ ተኝታችሁም እንዳያገኛችሁ፥ እነሆ ሁላችሁም ትጉ እላችኋለሁ። `ማር፥ ፲፫፥፴፮-፴፯ (13፥36፥37)

ከዚህ አምላካዊ ቃል የተነሣ ምእመናን ሁልጊዜ ይልቁንም በሰንበት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ይሰበሰባሉ፣ ይጸልያሉ፣ ይቀድሳሉ። እያንዳንዱን ሰንበት ተከፋፍለው በማኅበር ጽዋ ይጠጣሉ "ሰንበቴ" ብለውም ይጠሩታል። ስዚህ ርዕስ የተጻፈውን ተመልከቱ።

# የጽዋ ማኅበር ሰንበቴ

የጽዋ ማኅበር ሰንበቴ ክርስቲያኖች የሚፈጽሙት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ክርስቲያናዊ ምስክርነት ያለው ታላቅ የቅድስና ትሩፋት ነው። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የተጻፈከት ታላቅ ምሥጢር የሚገለጽበት ዓላማው መንፈሳዊ ሥራውም የጸድቅ ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር በረድኤት የሚገኝበት ነው።

> "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" ማቴ ፲፰፡፳ (18፡20)

## የጽዋ ማኅበር፡-

ክርስቲያኖች በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ስሞች ስም እየተሰበሰቡ በቤተክርስቲያን ወይም በየቤታቸው የሚፈጽሙት የቅድስና ሥራ ነው። ይህም እግዚአብሔር በመካከላቸው እንዳለ በማመን የሚከውኑት የመንፈሳዊ በረከት ነው፡፤ ይህንንም ከአንድ ክርስቲያን ቤት ወደሌላኛው እያዘዋወሩ ያደርጉታል። መነሻውም አንደኛ በዘመነ ብሉይ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በደጉ አባት አብርሃም ቤት ተገኝቶ ሣራ የሠራችውን ተመግቦ ቤታቸውንም ባርኮ የተዘጋውን በር ከፍቶ የሣራን ማኅፀን ከፍሬ አብቅቶ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ በመላእክቱ አድሮ በሎጥ ቤት ተገኘ፡ ሎጥንም ከታላቅ መከራ መላእክቱ እጁን ይዘው አወጡት። ዛሬም ክርስቲያኖች መሶቡንና ጽዋውን በመያዝ በየወሩ በየቤቱ እየተሰበሰቡ ይህንን ያስባሉ፡፤ (ዘፍ ፲፰ (18) የመሶበ ወርቁና የጽዋው መግባት የእግዚአብሔር መግባት ምሳሌ ነው፡ ምሥጢሩን እንመከከተዋለን። ከአብርሃምና ከሣራ እንዲሁም ከሎጥ የተደረገው የእግዚአብሔርን ቸርነት ጽዋው በገባበት ቤትም ይደረግ ዘንድ የምእመናን ምኞትና ጸሎት ነው።

ሁለተኛ በዘመነ ሐዲስ በወንጌልም ተጽፎ እንደምናገኘው የክብር ክብር ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ

ሥጋዊው በሚያምኑት ቤት እየገባ እየተመገበ ቤታቸውንም ይባርክላቸው ኃጢአታቸውንም ይደመስስላቸው ነበር። ከምሳሌ በቢታንያ ሀገር በለምጻሙ በስምዖን ቤት (ማቴ ፳፮፥፮ (26፥6) በኢያሪኮ አገር በቀራጩ በዘኬዎስ ቤት (ሉቃ ፲፱፥፩-፲ (19፥1-10) የማርያምና የማርታ ወንድም በሆነው በአልአዛር ቤት (ሉቃ ፲፥፴፰-፵፪ (10፥38-42)

ዛሬም ምእመናን ኃጢአተኞችን የማይጸየፍ ጌታ በቤታቸው ይገባ ዘንድ መሶበ ወርቁንና ጽዋውን ይዘው ባሉበት ቤት ሁሉ በረከት ይገባበታል።

> "እነሆ በደጅ ቆሜ እንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱ ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።" ራዕ ፫፥፳ (3፥20)

እንዲሀ ያለን ጌታ ምእመናን ይሀን ምሥጢር በሚገልጽ የጽዋ ማኅበር ይዘክሩታል። ዘከረ የሚለው የግእዝ ቃል አሰበ ማለት ነው። በዚህም ረቂቅ ምሥጢር የሚታሰበው ቀጥሎ ያለው ነው፤

<u>መሶበ ወርቅ</u>፡- መሶበ ወርቅ በውስጡ ኅብስት ይደረግበታል የዚህ ምሥጢሩ መሶበወርቅ የእመቤታችን ምሳሌ። መሶቡ የወርቅ መሆኑ የእመቤታችን ንጽሕናን የሚያመለክት ነው። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙር ፵፬ቁጥር ፱ (44፥9) እመቤታችንን ንግሥቲቱ ብሎ የወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና በቀኝሀ ትቆማለች ብሎ እንደመሰከረው። ክርስቲያኖች መሶባቸውን አጎናጽፈው ሸፍንፍን አድርገው ይይዙታል፤ ምክንያቱም ቅድስት የሆነች እመቤታችን ክብር ይገባታል። በመሶበ ወርቁ ውስጥ የሚደረገው ኅብስት "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ" ያለ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። (ዮሐ፥፮፥፴፭) ይህንንም አክብሮ መያዝ ብቻ ሳይሆን ይሳለሙታል ይስሙታል ከብሩ ከእግዚአብሔር ነው።

<u>ጽዋ</u>፡- የጽዋውም ምሥጢር እንደ መሶበ ወርቁ አንድ

ነው። ጽዋው የእመቤታችን ምሳሌ ነው። በውስጡ ያለው ወይን ወይም ጸበል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የደሙ ምሳሌ ነው። ክብር ይግባውና መሶበ ወርቁና ጽዋው የጎበስቱና የጸበሉ መያዣ የእመቤታችን መሆኑ ጌታችን ሥጋንም ደምንም የተዋሐደው ከእርሷ ብቻ ነውና። ምእመናንም ይህን በመረዳት በጽዋ ማኅበራችን የጌታችን መከራውን በቀራንዮ ያደረገውንም ሞቱን እያሰብን ይህን ደግ ሥራ እናደርጋለን፤ ዋና ዓላማው ይህ ሆኖ ሳለ በመሰባሰባችንም የተቸገሩ፣የተራቡ፣ የተጠሙ ነዳያን እናስባለን፤ ይህም ሊሆን እንደሚገባ ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ የሥጋ ወደሙንና የጽዋ ማኅበር መሰባሰብን እንዳስተማረን ልናደርገው ይገባል።

፩. የእግዚአብሔርን ማኅበር እንዳንንቅ፡- ማኅበሩ እግዚአብሔር የሚገኝበት መሆኑን እንድናውቅ። ስለዚህም ነው የእግራችንን ጫማ የምናወልቀው።

፪. በማኅበራችን ጊዜ ከልክ ያለፈ ድግስ እንዳናደርግ የሌላቸውንም ሰዎች እንዳናሳፍር።

፫. ከተቸገሩ ከተራቡ እንድናስብ፤

፬.ከልክ በላይ እንዳንበላና እንዳንጠጣ። በተለይ ስካር ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

ሌሎችም ብዙ መልእክቶች ያስተምረናል። የሥጋ ወደሙን መልእክት ከጽዋ ማኅበሩ በመለየት ፩ቆሮ ምዕራፍ ፲፩ ከቁጥር ፲፯ ጀምሮ እስከ ፴፬ ያለውን (1ቆሮ 11፡17-34) ጠንቅቆ ማንበብ ያስፈልጋል።

## ሰንበቴ

ሰንበቴ ከጽዋ ማኅበር ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ልዩነቱ አንደኛ እንደ ጽዋ ማኅበር በወር አይደለም ከሰሙ እንደምንረዳው በየሰንበቱ እሑድ እሑድ ነው፤ ሁለተኛ እንደ ጽዋ ማኅበር በየቤቱ ሳይሆን በቤተክርስቲያን ቅጽር ነው። ይህም ደገኛ ሥርዓት የመጣው ከሐዋርያት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ ነው። ቅዱሳን

አባቶቻችን ሐዋርያት በዘመኑ የነበሩ አባቶቻችን እያቶቻችን ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ የተነሣበትን የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን እሑድ እየተሰበሰቡበት በኅብረት እንጀራን ይቆርሱ ነበር። ጌታም በመካከላቸው ይገለጥ ነበር።

"በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ ለአሥራ አንዱ ተገለጠ" ማር ፲፮፡፲፬ (16፡14)

በማዕድ ሳሉ እንዲህ የተገለጠላቸው እምካከ በየሳምንቱ እየተሰበሰቡ በትምህርት፣ በጸሎት እያሰቡት በአንድ ላይ ይመገቡ ነበር፡፤

"ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" ሥራ ፪፡ ፵፩ (2፡41)

ይህ ሥርዓት በየሰንበቱ በሐዋርያት ይደረግ እንደነበር በሐዋርያት ሥራ (፳፡፯ (20፡7) የተጻፈው ቃል ይነግረናል፡፤ "ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብሰበን ሳለን..." ይላል። ዛሬም ይህ ሥርዓት ከነበረው ሳይጎድል በኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እየተፈጸመ ይገኛል።

አንባቢ ሆይ፡- የመሶበ ወርቁና የጽዋው ምሥጢር ከላይ ካለው ጋር አንድ ነው።

ይህ ሁሉ ምሥጢርና ሥርዓት ከኃያሉ እምካከ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን ነው። ሐዋርያው እንደተናገረው አንዳንዶች ይህን ታላቅ የድኅነት ሥራ በመተውና በመንቀፍ ከአጋንንት ጋር ማኅበርተኞች ሆኑ ይከናል።

"ከአጋንንት ጋር ማኅበርተኞች እንድትሆኑ አልወድም። የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም ከጌታ ማዕድ ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም" ፩ቆሮ፲፡፳፩ (10፡21)

ስለዚህ ይህ ቃል እንደሚነግረን በጽዋ ማኅበርም ሆነ በሰንበቴ የእግዚአብሔርን በረከቱን የምንፈልግ ምእመናን ፈጽመን ከሰይጣን ማኅበር ከከፋ ሥራውም አንርቅ ዘንድ ከእጉል እምነትም መጠበቅና መራቅ እንደሚገባ ያስተምራል። ይህ ሁሉ የጌታችንን መከራና ሞቱን በማሰብ በዕለተ እሑድ መነሣቱንም በመዘከርና በመናገር የዘላለምን ሕይወት እንወርስ ዘንድ ነው፤

"የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለ ሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነው ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና።" ፩ቆሮ ፲፡፲፮-፲፰ (10፡16-18)

የጽዋ ማኅበርና ሰንበቴ ከክርስቶስ ጋር አንድ የመሆን ምሥጢር ነው።

ሌላው ልናስተውለው የሚገባ ነገር የጽዋ ማኅበርና ሰንበቴ በቅዱሳንና በመላእክት መታሰቢያ እንደሚደረግ ነው። አንዳንዱ ሰው ለምን በቅዱሳን ስም ወይም በመላእክት ይደረጋል ብሎ ሊነቅፍ ይሞክራል። ሆኖም ግን በእምላክም ስም የሚደረገውም በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነው። ቅዱሳን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንደምናየው ታላቅ ክብርን እንደሰጣቸው እንመለከታለን። የእግዚአብሔር ስምም በእነሱ ውስጥ አለ፤

"መልአኬን በፊትህ እልካለሁ በፊቱ ተጠንቀቅ ቃሉንም አድምጥ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት።" ዘጸ ፳፫፡፳፩ (23፡21)

"በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ።" ኢሳ ፶፮፡፭ (56፡5)

ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር ቤቴ ተብሎ በተለየመበት ሁሉና በእርሱ መታሰቢያ ከመካእክቱና ከቅዱሳን ይህንን ጸጋ ሰጥቷቸዋልና በመታሰቢያ ይለየምካቸዋል።

# ስድስቱ (፮ቱ) ቃላተ ወንጌል

ኦሪትና ወንጌል እንደ ጥላና አካል የማይለያዩና የማይገነጣጠሉ ናቸው። ወንጌል ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ ወደሰው ልቡና አትገባም። ለዚህም ነው የከብር ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኦሪትን ነቢያትን ካሳልፋቸው የመጣሁ አይምሰላችሁ ፍጹማን ካደርጋቸው ነው እንጂ ብሎ የነገረን። በወንጌል ማቴዎስ ምዕራፍ አምስት ጌታችን እንዳስተማረን "ሰማዕከሙ ዘተብሀለ ለቀደምትከሙ......." ለቀደሙ ሰዎች የተባለውን ሰምታችኋል፤ "ወአንስ እብለከሙ እኔ ግን እላችኋለሁ እያለ ስድስቱን ቃላተ ወንጌል ወይም ሕገ ወንጌል ዘርዝሮ ነግሮናል። እነሱም ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው።

፩. ወንድምህን በከንቱ አትቆጣ አታሳዝን ፭፥፳፪
፪. ወደ ሴት አይተህ በልብህ አታመንዝር ፭፥፳፯
፫. አትፍታ ፭፥፴፪
፬. ፈጽማችሁ አትማሉ ፭፥፴፬
፭. ክፉን በክፉ አትመልሱ ፭፥፴፱
፮. ጠላታችሁን ውደዱ ፭፥፵፭

# ስድስቱ ጥያቄዎች በጊዜ ምጽአት

የክብር ባለቤት ጌታችን መድኃኒታችን ከፍርድ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንንም በግራው ያቆማቸዋል። በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። "በረከተ ገሪዛን ያደረባችሁ በረከተ ነፍስ ያካችሁ ዓለም ሳይፈጠር በጣዕም በመዓዛ በስን በብርሃን የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ሰማያትን ትወርሱ ዘንድ ወደኔ ኑ"። በግራው ያሉትም "መርገመ ጌባል ያደረባችሁ መርገመ ነፍስ ያከባችሁ ከሰይጣንና ከሠራዊቱ ወደተዘጋጀ ወደማያልፍ ስቃይ ሂዱ" ይላቸዋል።

ጻድቃንን "ነዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ" የአባቴ ብሩካን ወደኔ ኑ፤ ኃጥአንን ደግሞ "ሑሩ እምኔየ ውስተ እሳት ዘለዓለም" ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሂዱ፤ የሚልበት ምክንያት ሁለቱን የእግዚአብሔር ንብረቶች እምነትና ምግባርን አንድ አድርገን በመያዝ ስድስቱን ጥያቄዎች በሚገባ በመመለስና ባለመመለስ በሚመጣ ማለፍና መውደቅ የተነሣ ነው። እነሱም በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ፳፭፥፴፩-፵፮ (25፥31-46) ተጽፈው እንመክርበት ዘንድ የተገለጹት ናቸው።

፩. ከተራበ ማብላት

፪. ከተጠማ ማጠጣት

፫. እንግዳ መቀበል

፬. ከታረዘ ማልበስ

፭. የታመመ መጠየቅ

፮. የታሰረ መጠየቅ

"ብፁዕ ዘይሌቡ ላዕለ ነዳይ ወምስኪን እምዕለት እኪት ያድኅኖ እግዚአብሔር"

"ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል።" መዝ ፵፥፩ (40፥1)

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማርያም ተብለው የተጠሩ ብዙዎች ሲኖሩ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ግን የአምላክ እናት ስለሆነች ከሰው ወገን ሁሉ ልዩ ነች።

> "የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበር" ሉቃ ፩፡፳፯ (1፡27)

> "ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ" ሉቃ. ፩፡፳፰ (1፡28)

ማርያም ማለት ፀጋ ወሀብት፣ ፍጽምት፣ ልዕልት፣ ተከአኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ፣ መርሕ ከመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው።

አባቷ ቅዱስ ኢያቄም ይባላል እናቷ ቅድስት ሐና ትባላለች መካን ሆነው ሲኖሩ እግዚአብሔር አምላክ በመጨረሻ ከራሱ እናት እንድትሆነው ከአባቶች ወገብ ጀምሮ ያዘጋጃትን ሴት ልጅ ወለዱ ስሟንም ማርያም ብለው ጠሯት። ወንድምም እህትም የላትም ከወላጆቿ ብቸኛ ናት።

> "ርግቤ መደምደሚያዬም አንዲት ናት ከእናቷም አንዲት ናት ከወለደቻትም የተመረጠች ናት።" መሐ፡ ፮፡፱ (6፡9)

ኢያቄምና ሐና የወለዷት በስለት ነበር። ስለታቸውም የሚወልዱትን ልጅ በቤተመቅደስ እንዲኖር ከእግዚአብሔር መስጠት ነበር። በዚህም መሠረት ድንግል እመቤታችን የ3 ዓመት ሕፃን እንደሆነች ወደ ቤተመቅደስ አስገቧት።

> "ልጄ ሆይ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዩ ወገንሽን የአባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወድዷልና እርሱ ጌታሽ ነውና" መዝ. ፵፬፡፲ (44፡10)

እመቤታችን በቤተመቅደስ 12 ዓመት ኖረች ከዚያም ሰይጣን

በአይሁድ አድሮ ከቤተመቅደስ እንድትወጣ አደረጉ ምክንያታቸውም ድንግል ማርያም እንደ ሌላ ሴት መስላቸው ነበር። እርሷ ግን ከሴቶች ሁሉ ንጽሕት ናት። ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እርሷ ሲመጣ ያላት እንዲህ ነበር።

"ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት" ሉቃ. ፩፥፳፰ (1፥28)

ከቤተመቅደስም በወጣች ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰጠች ናትና ከሽማግሌዎች ከአንዱ በአደራ እንድትሰጥ ሆኖ ዮሴፍ የተባለ ቅዱስ ሰው ይጠብቃት ዘንድ ተሰጠች።

በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ የአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ በወጣች ጊዜ ዮሴፍ እመቤታችንን ይዞ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ ሄደ በዚያም እመቤታችን የዓለምን መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች። ሉቃ ፪፥፩-፯ (2፥1-7)

# ወላዲተ አምላክ መሆኗ

ድንግል ማርያም እመቤታችን የወለደችው ኢየሱስ እርሱ አምላክ ነው። ቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስ ትንቢት ተነግሮ ነበር።

> "ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶልናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" ኢሳ. ፱፥፮ (9፥6)

> ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሰማይ ወርዶ ከድንግል የተወለደው የሁላችን ቤዛ ኢየሱስ እኛን ከማዳን ሰው ይሁን እንጂ እርሱ ከዘላለም የተባረከ አምላክ ነው እንዲል ሮሜ ፱፥፮ (9፥6)

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቃል በመጀመሪያ ነበር ያ ቃል እግዚአብሔር ነበረ ያም ቃል የተባለ ሥጋ ሆነ ብሎ ከድንግል ማርያም የተወለደው አምላክ እግዚአብሔር እንደሆነ ተናገረ። ዮሐ. ፩፥፩-፲፬ (1፥1-14)

ስለዚህ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ (አምላክን የወለደች) ተብላ ትጠራለች። ይህ ከሌላ ከማንም አይቀጸልም። ድንግል ማርያም ብቻ እግዚአብሔርን ልጅ ትለዋለች። እግዚአብሔርም ድንግል ማርያምን ብቻ እናቴ ይላታል።

> "እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፥ ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፥ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም"

> "እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ማደርያውም ትሆን ዘንድ ወዷታልና እንዲህ ብሎ ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት" መዝ፥ ፻፴፩፥፲፫ (131፥13)

መረጣት ማደሪያውም ሆነች ጸነሰችው በዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ሲሞላ ወለደችው አቀፈችው አጠባችው ኢየሱስ አለችው አሳደገችው። እናቴ እያለ ይታዘዛት ነበር።

# የጸጋና የአክብሮት ስግደትና ምስጋና ለእመቤታችን

እውነተኛ ምእመናን የአምላክ እናት ለሆነች ለድንግል ማርያም የሚገባትን ክብር ይሰጣሉ። እመቤታችን ድንግል ማርያም የባለሟልነት፣ የመወደድ የመፈራት ልዩ ግርማ አላት። የባለሟልነት ግርማ በሥላሴ ዘንድ የመወደድ ግርማ በመላእክትና በምእመናን ዘንድ የመፈራት ግርማ በአጋንንትና በመናፍቃን ዘንድ።

በራእይ. ፲፪፥፩-፭ (12፥1-5) "ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጎናጽፋ ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት በራሷ ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።" ይህች ሴት እመቤታችን ለመሆኗ ቁጥር 5 ላይ "አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ ወለደች" ይላል።

ፀሐይ የተባለ - ኢየሱስ

ጨረቃ የተባሉ - ቅዱሳን

12 ከዋክብት የተባሉት - 12ቱ ሐዋርያት ናቸው ክብር ይህ ነው አጋንንት ግን ይጠሏታል።

"ዘንዶውም ወደምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።" ራእይ. ፲፪፥፲፫ (12፥13) ፀሐየ ጽድቅ አምላካችን ኢየሱስን ጸንሳ የወለደች ጨረቃ የተባሉ ቅዱሳን እነ ቅዱ ዮሐንስ መጥምቅ የሚሰግዱላት ነቢያት ትንቢታችን ሐዋርያት ሞገሳችን ሰማእታት እናታችን መላእክት እህታችን የሚሏት ክብርት ናት።

ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ለእመቤታችን የምትሰጠው ) ክብር በመጽሐፍ ቅዱስ በተፃፈው መሠረት ነው። ለምሳሌ መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እርሷም ገብቶ እንዲህ አላት፡- "ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ፀጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት" ሉቃ. ፩፥

፳፰ (1፥28)

እኛም ለናመስግናት ልክ ከእግዚአብሔር እንደተላከው መልአክ "ደስ ይበልሽ ከሴቶች ሁሉ ልዩ የሆንሽ" እያልን እናመስግናታለን። በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብቻ የተወሰነ ምስጋና ሳይሆን ፍጥረት ሁሉ እመቤታችንን ያመሰግናታል። ነቢያትም በትንቢታቸው ስለ እመቤታችን ሳይናገሩ አላለፉም። ቅዱስ ዳዊት በመዝ. 44 (55) ፥ 9-13 በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች። ... ከሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብሯ ነው።" ብሎ በእናት በአባቷ ቤት ሳይሆን በመቅደስ እንዳደገች። እግዚአብሔር ከተዋሕዶ እንደመረጣት እርሱ ደግሞ ጌታዋ እንደሆነ በቀኙ እንደምትቆም ትንሣኤዋን ሳይቀር ተናገረ። መዝ. ፵፬፥፱-፲፫ (44፥9-13)

በሉቃስ ወንጌልም እንደተጻፈው ራሷ እመቤታችን ከእግዚአብሔር የተወከደ መንፈሳዊ ሕይወት ያለው ትውልድ ሁሉ ከዘላለም እንደሚያመሰግናት ትናገራለች።

"ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኩሉ ትውልድ"

ከእንግዲህስ ወዲህ "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" ሉቃ. ፩፥ ፵፰ (1፥48)

እኛም ትውልድ ነንና የመጽሐፉንም ቃል እንስማለንና ቅድስት እናታችን ድንግል ማርያምን ብፅዕት ብለን ምስጋና እናቀርብላታለን። ምስጋናውም የሚገለጸው በእንደበት በመመስከርና የትሕትና ምልክት የሆነውን ስግደት በመስጠት ነው። ስግደቱም የአክብሮት ስግደት ይባላል። ፀጋ ክብር ላላቸው የሚሰጥ ስግደት።

> "ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማህፀኗ ውስጥ ዘለለ (ሰገደ) በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች፡- አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።"

> "ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች፡ ወደ ዘካርያስም ቤት ገብታ

ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት። ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፤ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንደት ይሆንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና።" ሉቃ. ፩፥፴፱-፵፬ (1፥39-44)

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናስተውላቸው፡

ሀ. የእመቤታችን ድምፅ ኃይል - ፅንስ ማዘለል

ለ. መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሰው እመቤታችንን እንደሚወዳት እንደ ኤልሳቤጥ

ሐ. ድንግል ማርያም እመቤታችን ከሰዎች (ከሴቶች) ልዩ መሆኗ

መ. ኤልሳቤጥና በማኅፀንዋ ያለው ቅዱስ ዮሐንስ ከጌታና ከድንግል መስገዳቸው

ሠ. የጌታዬ እናት ብላ ኤልሳቤጥ እመቤታችን የአምላክ እናት መሆኗን

ረ. ወደ እኔ ትመጣ ዘንደ እንዴት ይሆንልኛል ብላ ድንግል ማርያም ክብርት እንደሆነች የሚያሳይና የኤልሳቤጥ ትሕትናን በመንፈስ ቅዱስ እውቃ ሳትወልደው መናገሯ።

አንዳንዶች ከዚህ ከእግዚብሔር ቃል ውጪ በመሆን ይህንን ክብር ካለመስጠት በትእቢትና በክህደት ውስጥ ይታያሉ። ሰዓት አለ ሁሉም ከእመቤታችን የሚነበረክክበትና እግዚአብሔር የተወለደብሽ ከተማ ብሎ የሚያመሰግንበት።

"የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔርም ከተማ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል" ኢሳ. ፷፥፲፬ (60፥14)

አንዳንድ ሰዎች ይህ የተባለው ለኢየሩሳሌም ነው፡ አንዳንዶች ደግሞ

በኢየሩሳሌም ካለ ተራራ ነው ብለው ከእመቤታችን ለግደት አይገባም ይላሉ። እንደዚያ እንኳ ቢሆን ከኢየሩሳሌምም ሆነ ከተራራው ሲሰግዱ ታይተው አያውቁም በሰሙ ከዚያ ቢነገርም ምሥጢሩ የእግዚአብሔር ከተማና ማደሪያ እመቤታችን ናት። ብናከብራት እኛ እንከብራለን እንጂ ለእሷ የምንጨምርላት ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር ለዘላለም አክብሯታልና። የእግዚአብሔር እናት ከመሆን በላይ በምድርም በሰማይም ምንም የለም የብርሃን እናት ብርሃናትን ድንግል ማርያም።

# የእመቤታችን ቅድስናና ንጽሕና

እም ማለት በግእዝ እናት ማለት ሲሆን ብርሃን ደግሞ በብርሃንነቱ ጨለማን አስወገደ ማለት ዲያብሎስን አራቀ የተባለ ኢየሱስ ነው።

"ደግሞም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።" ዮሐ. ፰:፲፪ (8፥12)

ስለዚህ ነገር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብርሃን ነኝ ያለ የሆነ ኢየሱስን ወልዳልናለችና እመ ብርሃን የእግዚአብሔር ከተማ ጽዮን የብርሃን እናት ነች።

## ቅድስት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሰው ሁሉ ወገን የእግዚአብሔር ከተማ ጽዮን ቅድስት ንጽሕት ናት፡፡ የእርሷ ቅድስናና የሌሎች ፈጽሞ ግንኙነት የለውም።

"አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ" እንዲል እግዚአብሔር ሰውን በማዳን ዕቅዱ ከእርሱ ሰው መሆን ራሱ ቅድስት አድርጎ ከይቶ በአባቶች ወገብ ሲያስተካልፋት የነበረች ንጽሕት ዘር ነበረች። በዚህም ምክንያት ከጥፋት ዳንን። ሉቃ. ፩:፵፪ (1፥42)

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር።" ኢሳ. ፩:፲፱ (1፥19)

ስለዚህ እመቤታችን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ያልነካት ማለት በአዳምና በሔዋን የደረሰ ለትውልድ ሁሉ የተካለፈ ኃጢአት ፈጽሞ ያልደረሳት ቅድስት የሆነች ናት።

"ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው። ነውርም የለብሽም" መኃ. ፬፥፯ (4፥7)

## ድንግል

እመቤታችን ድንግል ማርያም - ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ድኅረ ጸኒስ ማለት ጌታን ከመጽነሷ በፊት፣ በጸነሰች ጊዜ፣ ከጸነሰችም በኋላም ድንግል ናት። ልክ እንዲሁ፡- ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ ፣ ድኅረ ወሊድ ድንግል ናት። ማለት ጌታችንን ከመውለዷ በፊት፣ በወለደችው ጊዜ ከወለደችውም በኋላ ዘላለማዊት ድንግል ናት። ነቢዩም ይህን ድንቅ ምልክት ጌታ ይሰጣችኋል አለ።

> "ናሁኬ በእንተ ዝንቱ ይሁበክሙ እግዚአብሔር ትዕምርተ፡ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል"
>
> "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፡" ኢሳ. ፯፥፲፬ (7፥14)

ታላቁ ምልክትና ድንቅ የሆነው ነገር ይህ ነው። እናትነትን ከድንግልና አስተባብራ የያዘች። ተአምሩም ይኸው ነው። በኅቱም ድንግልና ጌታ ከሷ ተወልዶ ሰው መሆኑን።

ነቢዩ ሕዝቅኤል የተነበየውም በዚህ ተፈጸመ እንዲህ ብሎ፡- "ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር ። እግዚአብሔርም፡- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።" ሕዝ. ፵፬፥፩ (44፥1)

የእመቤታችን ንጽሕናና ድንግልና በ3 ዓይነት ነው።

በኅልዮ (በሐሳብ)

በነቢብ (በመናገር)

## በገቢር (በመሥራት)

በነዚህ በሦስቱም ዐይነት እመቤታችን ኃጢአት አልሠራችም። ከምሳሌ ብዙ ሰዎች ድንግል ሆነው ለእግዚአብሔር ራሳቸውን ሰጥተው የኖሩ አሉ። በሥጋ ድንግል ይሁኑ እንጂ በአስተሳሰባቸው ወይም በንግግራቸው ኃጢአትን መሥራታቸው የማይቀር ነው። እመቤታችን ግን በሐሳብም፣ በመናገርም፣ በማድረግም ፈጽማ ኃጢአትን ያልሠራች የእግዚአብሔር ልዩ መቅደሱ ናት።

# የእመቤታችን ዕድሜ

እመቤታችን መካ ዘመንዋ በዚህ ዓለም 64 ነው።

ከተወለደችበት እስከ 3 ዓመቷ - ከ3ዓመት በእናት በአባቷ ቤት

ከ3 ዓመቷ እስከ 15 ዓመቷ - 12 ዓመት በቤተ መቅደስ

ከ15 ዓመቷ እስከ 49 ዓመቷ - 34 ዓመት በቤተ ዮሴፍና ከልጇ ጋር

ከ49 ዓመቷ እስከ 64 ዓመቷ - ከ15 ዓመት ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር።

በ 64 ዓመቷ አረፈች ሞታ ተነስታ ዓርጋ አሁን በመንግሥተ ሰማይ ያለች የሰው ዘር እመቤታችን ብቻ ናት።

# ርእሳነ አበው

| አሥሩ አበው የሚባሉት | የኖሩበት ዕድሜ |
|---|---|
| ፩. አዳም | 912 |
| ፪. ሴት | 930 |
| ፫. ሄኖስ | 905 |
| ፬. ቃይናን | 910 |
| ፭. መላልኤል | 895 |
| ፮. ያሬድ | 962 |
| ፯. ሄኖክ | 365 |
| ፰. ማቱሳላ | 969 |
| ፱. ላሜሕ | 717 |
| ፲. ኖኅ | 950 |

ናቸው።

፩. አዳም የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ ነው። የስሙ ትርጉም

ሀ. ምን ያምር ማለት ነው።

ለ. ምጥን ፍጥረት ማለት ነው።

ሐ. "እምድር ዘተሠገወ" ከመሬት ሥጋ የሆነ ማለት ነው። የሚስቱ ስም ሔዋን ሲሆን ትርጉሙም "የሕያዋን ሁሉ እናት" አንድም "ሕይወቱ ነሽ" ማለት ነው።

"ወገብሮ እግዚአብሔር ለሰብእ እመሬተ ምድር"

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው" ዘፍ. ፪፡፯ (2፥7)

"ወሰመየ አዳም ስማ ለብእሲቱ ሔዋን እስመ ይእቲ እሞሙ ለሕያዋን"

"አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ። የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና" ዘፍ. ፫፡፳ (3፥20)

፪. ሴት ቃየል አቤልን ከገደለው በኋላ አዳምና ሔዋን የወለዱት ልጅ ነው። የስሙ ትርጉም ምትክ ማለት ነው። የአቤል ምትክ ነውና። ሴትም አዙራንን አግባ ሄኖስን ወለዱ። ዘፍ. ፭፡፫ (5፥3) ኩፋሌ ፭፡፲፫-፲፯ (5፥13-17)

፫. ሄኖስ ሄኖስ ከአዳም ሦስተኛ ትውልድ ነው። ሄኖስ ማለት ጣዕም ኑዛዜ፣ መሠረት፣ መዓዛ ማለት ነው። የሚስቱ ስም ኖአም ነው። ቃይናን የተወለደው ከእሷ ነው።

"ወወለዶ ለቃይናን" ቃይናንንም ወለደ ዘፍ. ፭፡፱ (5፥9)፣ ኩፋሌ ፭፡፲፱ (5፥19)

፬. ቃይናን፡- ቃይናን አራተኛ ትውልድ ነው። ቃይናን ማለት ጥሪት፣ ተጋብኦ (ሀብትን መሰብሰብ) ማለት ነው። ቃይናን ሙአሊሊትን አግባ የመጀመሪያ ልጃቸውንም መላልኤል አሉት። ዘፍ. ፪፡፲፪ (2፥12)፣ ኩፋሌ ፭፡፳ (5፥20)

፭. መላልኤል፡- አምስተኛ ትውልድ ሲሆን መላልኤል ማለት ትርጉሙ "ስብሐተ እግዚአብሔር፣ መልአክ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ምስጋና የእግዚአብሔር መልአክ) ማለት ነው። የሚስቱ ስም ዲና ይባላል።

ዘፍ. ፭፡፲፭ (5፥15)፣ ኩፋሌ ፭፡፳፩ (5፥21)

፮. ያሬድ ከአዳም ስድስተኛ ትውልድ ነው። የስሙ ትርጉም ርደት (መውረድ) ማለት ነው። ምክንያቱም የሴት

ልጆች ከደብር ቅዱስ የወረዱት በእሱ ዘመን ነበር። ሚስቱም የአባቱ እኅት (የአክስቱ) የራፋየል ልጅ ባረካ ትባል ነበር። ሄኖክ የእነሱ ልጅ ነው። ዘፍ. ፭፥፲፰ (5፥18)፣ ኩፋሌ. ፭፥፳፪ (5፥22)

፯. ሄኖክ ሰባተኛ ትውልድ ነው። ሄኖክ ማለት ሐዲስ ተሐድሶ ማለት ነው። ሚስቱ አድኒ ትባላለች። የአባቱ እኅት የአክስቱ ልጅ ናት አባቱ ያሬድ ይባላል። የመጀመሪያ ልጃቸው ማቱሳላ ነው። ከመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍን የጻፈ ሄኖክ ነው ይህም መጽሐፍ ትንቢትን፣ በሱባዔ የሚቆጠሩ ቁጥሮችን፣ የዘመናትንም ቀን፣ የፀሐይን የጨረቃንና የከዋክብትን ነገር፣ የተደረገውንና ገና የሚደረገውን ፍርድ ሌሎችንም በመጽሐፍ ገልጾ ተናግሯል፣ ጽፏል። ይህም መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብቻ የቀናና መጽሐፍ ሆኖ ያገለግላል። ሌሎች አገሮች እንኳን የቀናና መጽሐፍ ሊያደርጉት ቀርቶ መጽሐፉም የላቸውም። ያወቁት ከእኛ ተገልብጦ ስለሄደ ነው። አሁን ግን በምርምር ተቆፍሮ ከኩምራን ተገኝቷል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሄኖክ አካሄዱ ሁሉ በእግዚአብሔር ሕግ በመመራት ስለነበር በዚህ ምድር ላይ ሞትን ሳይቀምስ እግዚአብሔር ወስዶታል።

> "ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና" ዘፍ. ፭፥፳፬ (5፥24)፣ ዕብ. ፲፩፥፭ (11፥5)
>
> "እርሱ አስቀድሞ ምስክርን ጻፈ" ኩፋሌ ፭፥፳፬ (5፥24)
>
> "ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ ... ከአእላፍ ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ከእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።" ይሁዳ ቁር፩፥፲፬-፲፮ (1፥14፥16)

፰. ማቱሳላ በትውልዱ ስምንተኛ የሆነው ማቱሳላ ከሁሉ በላይ ረጅም እድሜ የኖረ ነው። የስሙ ትርጉም "ሞት

ተፈናዊ" ሞት ተካኪ ማለት ነው። ማቱሳላ የከበረ ታላቅ ነቢይ ነው ከኖኅ መርከብ እንዲሠራ የእግዚአብሔርን ነገር ሁሉ ከልጆቹ ነግሯቸዋል። የሚስቱ ስም እድና ይባላል። ይህችውም የአባቱ እኅት (አከለት) ልጅ ናት። አባቷ ኢይዝራኤል ነው። ላሜህ የመጀመሪያ ልጃቸው ነው። ዘፍ. ፭፥፳፭ (5፥25)፣ ኩፋሌ ፭፥፴፬ (5፥34)

፱. ላሜህ ይህ ዘጠነኛ ትውልድ ነው። ላሜህ ማለት "ከምንት ኪተ ዕረፍት" "ከእኔ ዕረፍት ከምን" እንደማለት ነው። ሚስቱ ቤቴኖስ ትባላለች። ይህችም የአባቱ እኅት የአከለቱ ልጅ ናት አባቷ በራኪኤም ነው። የበኩር ልጃቸው ኖኅ ነው። ዘፍ. ፭፥፳፰ (5፥28)፣ ኩፋሌ ፭፥፴፮ (5፥36)።

፲. ኖኅ አሥረኛው አባት ኖኅ ነው። ኖኅ ማለት ዕረፍት ትፍሥሕት፣ ተረፍ ማለት ነው።

> ዕረፍት፡- ከሥራዬ ሁሉ የሚያሳርፈኝ አንድም ከኃጢአት
>
> ትፍሥሕት፡- ከኀዘኔ ሁሉ የሚያረጋጋኝ
>
> ተረፍ፡- እግዚአብሔር ከረገማት ከፈረደባት ምድር የሚተርፍ ስለሆነ ኖኅ ተባለ።

የሚስቱ ስም አምዛል ይባላል። በሌላ ስፍራ አኤስታማከ ይላታል። ከመምህሬ ሐይከል የሚልም ሰምቻለሁ። እነሱም ሦስት ልጆችን ወለዱ ካም፣ ሴም፣ ያፌትን። የሰው ልጆች ኀጢአት በዝቶ የጥፋት ውኃ የሆነው በኖኅ ዘመን ነው። የተረፉትም ስምንት ሰዎች ብቻ ናቸው። እነሱም ኖኅና ሚስቱ ሦስቱ የኖኅ ልጆች ከሚስቶቻቸው ጋር አንድ ላይ አራት ወንዶችና አራት ሴቶች ብቻ።

> "ምስክርነታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል። ዕብ. ፲፩፥፯ (11፥7)
>
> "ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል።

ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም። እግዚአብሔር ኃጢአትን ካደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ከፍርድ ኪጠበቁ አሳልፎ ከሰጣቸው ከቀደመውም ዓለም ሳይራራ ከሌሎች ሰባት ጋር ጽድቅን የሚሰብከውን ኖኅን አድኖ በኃጢአተኞች ዓለም ላይ የጥፋትን ውኃ ካወረደ" ፪ጴጥ፪፥፭

"ስሙንም፦ እግዚአብሔር በረገማት ምድር ከተግባራችንና ከእጅ ሥራችን ይህ ያሳርፋል ሲል ኖኅ ብሎ ጠራው" ዘፍ. 5፥29

"ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም" ፩ጴጥሮስ ፫፥፳ (3፥20)

## የዕድሜ ክሺህ ማነስ

የአሥሩን አበው ዕድሜ ስንመለከት አንድ ሺ የሞላ የለም። አባታችን አዳምም የሞተው በዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመቱ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳምን ትእዛዝ ሰጥቶት ነበር፣ ትእዛዙም መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ እንዳትበላ ከበላህ ግን የበላህ ቀን ትሞታለህ የሚል ነበር።

> "ወእምዕፀሰ ዘያርኢ ወያሌቡ ሠናየ ወእኩየ ኢትብላዕ እምኔሁ እስመ በዕለተ ትበልዕ እምኔሁ ሞተ ትመውት" "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና" ዘፍ. ፪፥፲፯ 2፥17

አዳም አባታችንና ሔዋን እናታችን በምክረ ዲያብሎስ ተታለው፣ ትእዛዝ ሻሩ። ከገነትም ተባረሩ፤ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከዔደን ገነት አሰወጥቶ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ዘጋው ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ ሰይፉን በዔደን ገነት ምሥራቅ

አስቀመጠ። ዘፍ. ፫፡፳፬ (3፥24) ሞት ወደ ዓለም ገባ በሰው በኩልም መጣ። ፩ቆሮ. ፲፭፡፳፩ (15፥21) ስለዚህም አዳም በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በራሱ ላይ አመጣ በሥጋ ሞት ወደ መቃብር መውረድ በነፍስ ሞት ደግሞ ወደ ሲኦል መውረድ የሰው ልጅ ዕጣ ሆነ።

ከላይ እንደተመለከትነው አዳም ከተፈረደበት በኋላ 930 ዓመት ቆይቶ ወልዶ ከብዶ ነው የሞተው። ከዚህም የተነሳ "›በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ያለው የአምላክ ቃል የተፈጸመ አይመስልም። እንዲህ ደግሞ እንዳንል እግዚአብሔር "ቃሌ ከአፌ በጽድቅ ወጥታለችና አትመለስም" ኢሳ. ፵፭፡፳፫ (45፥23) ይለልና ምሥጢሩን እንረዳ።

በእኛ ዘንድ አንድ ሺህ ዓመት የተባለው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አንድ ቀን ነው። ቅዱስ ዳዊት ይህንን ያውቃል እንዲህም ብሎ ተናገረ።

> "ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትላንት ቀን እንደ ሌሊትም ትጋት ነው" መዝ. ፹፱፡፬ (89፥4)

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም የአምላካችንን አመጣጥ የተወሰነ ቀንና ቁጥር እንዳለው በጻፈው መልእክቱ ስለአቆጣጠሩ ይህን እንዳትረሱ ይለናል።

> "እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን አንድ ሺህ ዓመት ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ" ጴጥ. ፫፡፰ (3፥
> 8)

እንባቢዎች ማስተዋል ያለብን ነገር በጌታ ዘንድ አንድ ቀን በእኛ እንደ አንድ ሺህ ዓመት፤ በእኛ አንድ ሺህ ዓመት በጌታ ዘንድ እንደ አንድ ቀን መሆኑን ነው። ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የቤተክርስቲያናችንን ምሥጢር እንደምንረዳው አባታችን አዳም እንደ ልዑል እግዚአብሔር ቃል በተባለው ቀን ሞቷል ማለት ነው። እንደውም በጌታ አንድ ቀን የተባለችው ከመፈጸም ሰባ (70) ዓመቶች ይቀሩት ነበር

ማለት ነው። የሞተው በዘጠኝ መቶ ሠላሳ (930) ዕድሜው ነበርና። ቤተክርስቲያናችን ሀብቷ ብዙ ነው፣ በሌላ ዓለም በማይታወቀው በእኛ ዘንድ ባለው በመጽሐፈ ኩፋሌ ሊቀ ነቢያት ሙሴ እንዲህ ብሎ ጽፎልናል።

"... አዳም ሞተ። ልጆቹም ሁሉ በተፈጠረበት ምድር ቀበሩት፣ እርሱም አስቀድሞ በምድር ተቀበረ። ከሺህ ዓመታትም ሰባ ዓመትም አንደለ ይህችውም በሰማይ ጽላት እንደ አንዲት ቀን ነበረች። ከእርሱ በበላችሁበት ቀን ትሞታላችሁ ተብሎአልና ስለዚህ ነገር ከፉ አውቀትን የሚያሳውቅ ዕፅን ስለ በላ ተጻፈ በእርስዋ ሞቷልና ስለዚህ ነገር የአንዲቱን ቀን ዓመቶች አልጨረሰም።" ኩፋሌ ፮፥፫ (6፥3)

ሌላው የአዳም የመዳን ተስፋ ስንመለከት ደግሞ እግዚአብሔር ከልጅ ልጁ ተወልዶ እንደሚያድነው ሲገልጽለት በቀሌምንጦስ፣ በአክሲማሮስ፣ በአቡሻኸር በሌሎችም መጻሕፍት እንደተጻፈ እንዲህ ነበር ተስፋ የሰጠው፡-

"በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ከዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኅከ ውስተ መርኅብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበሞትየ"

ይህንን ተስፋ በዘፍጥረት ፫፥፲፭ (3፥15) እናገኘዋለን። "በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ስኩናውን ትቀጠቅጣለህ" በዚህ ቃል መሠረት ከጊዜው "አንተ" የተባለ አባብ ነው፤ ሴቲቱ ደግሞ ሔዋን ስትሆን ፍጻሜው ግን አንተ የተባለ ዲያብሎስ ሴቲቱ የተባለች ድንግል ማርያም ዘርዋ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ በተቆጠረው ሱባዔ በተነገረው ትንቢት መሠረት የሕይወት ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ያለ ወንድ ዘር ከሴት ብቻ ተወልዶ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም አዳነን። ከላይ በተመለከትነው የቁጥር ምሥጢር መሠረት ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ያለው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ማለት ነው። አምስቱ ቀን

አምስት ሺህ ሲሆን ተኩል የተባለው ደግሞ የሺህ አጋማሽ አምስት መቶ ይሆናል። ስለዚህ በስድስተኛው ሺህ መዳናችንን ሲገልጽ በሉቃስ ወንጌል እንዲህ አለ።

> "በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ከሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።" ሉቃ. ፩፥፳፮ (1፥26)

የዚህ ቃል የመጀመሪያ ምሥጢር ገብርኤል መልአከ ኤልሳቤጥን እንደምትወልድ ለዘካርያስ ካበሠረው ከስድስት 6 ወር በኋላ ሲሆን በሁለተኛና በዋናው ምሥጢር ግን በስድስተኛው ወር የተባለው በስድስተኛው ሺህ የሚል ትርጉምን በወንጌል አንድምታችን እናገኛለን።

> "የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ" ገላ. ፬፥፬ (4፥4)

ስለዚህም እግዚአብሔር እንደተናገረ አዳም በበላ ቀን በሥጋም በነፍስም ሞተ። ሺህ ዓመትም ሳይሞላው ሞቶ ተቀበረ ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ምንም የጽድቅ ሥራ በአንዳንዶች ዘንድ ቢገኝም ሥጋ ወደ መቃብር ነፍስ ደግሞ ወደሲኦል ይወርድ ነበር። አምላካችን የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሞትን በሞቱ ሽሮ ሲኦልን መዘበራት ነፍሳትንም አወጣ ወደቀድሞ ቦታችንም መለሰን። ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሰጥቶ ዘላለማዊ ሕይወት አደለን። ያስጠበቁልንን ገነት ከፈተልን። ቅዱስ ኤፍሬም እንዲህ አለ "ከፈለነ ንብላዕ እምዕፀ ሕይወት" ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን።

ወደ ቀድሞ ቦታችን የመለሰን ገነትንም የከፈተልን አምላካችን ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን።

## የዕድሜ መጠን

1ኛ. እግዚአብሔር አምላክ ሲፈጥረን ሕያው አድርጎ

ከዘካከም ነበረ የሰው ልጅ በገነት ኖሮ ሺ ዓመት ሲሞላው ዕፀ ሕይወትን እየበላ እንደገና እየታደሰ እግዚአብሔር ባወቀ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊያስገባን ነበረ።

2ኛ. አዳምና ሔዋን በበደሉ ጊዜ የዕድሜ ጣሪያ 999 ሆነ። ከላይ እንደተመለከትነው የበላህ ቀን ትሞታለህ በሚለው ቃል መሠረት ሺ የሞላ የለም።

3ኛ. በኖኅ ዘመን የሰው ልጅ ዕድሜ 120 ሆነ።

4ኛ. ቅዱስ ዳዊት እንደተነበየው የሰው ልጅ ዕድሜ 70ና 80 ከዚህ በላይ ድካም ነው ይላል።

# በገነት ያሉ ሦስቱ ዛፎች

1ኛ. ዕፀ ምግብ፡- የሰው ልጅ እንዲመገበው የተፈቀደለት

2ኛ. ዕፀ በለስ፡- እንዳይበሉ የተከለከለው።

3ኛ. ዕፀ ሕይወት፡- ሺ ዓመት ቆይተው ተመግበው የሚታደሱበት

> "እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ። ወዴት ነህ አለው።" ዘፍ ፫፡፱ (3፡9)

"ወደ ሕይወት ዛፍ ከመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው። ራእይ ፳፪፡፲፬ (22፡14)

# አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል

አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አሥራ ሁለቱ ቤተ እስራኤልም ተብለው ይጠራሉ። እነዚህም ያዕቆብ የወለዳቸው ናቸው። ለብዙ ሃይማኖታዊ ምሥጢር ምሳሌ፣ አብነትና መርገፍ ሆነው ይገኛሉ። መስፍን ወነቢይ የሆነ የነዌ ልጅ ኢያሱ እስራኤልን ወደምድረ ርስት እየመራ ዮርዳኖስን ከማሻገር ወንዙ ቢሞላበት ከየነገዱ አንድ ሰው ባጠቃላይ አሥራ ሁለት ሰዎች መርጦ አሥራ ሁለት ድንጋዮችን ይዘው ታቦቱን የተሸከሙ ካህናት ባሕሩን ቢረግጡ ልክ እንደ ቀይ ባሕር በደረቅ መሬት ተሻገሩ ድንጋይንም የምስክር ሐውልት አድርገው አቆሙት።

"ወይቤሎሙ ንዑ ወእምጽኡ ቅድሜየ ወቅድመ እግዚአብሔር እማዕከለ ዮርዳኖስ ወንሥኡ እምዝየ አሐተ አሐተ እብነ ወፁሩ ውስተ መታከፍቲክሙ በከመ ትካቄሆሙ ለ፲ወ፪ቱ ነገደ እስራኤል"

ኢያሱም ኑ ከዚህ ከዮርዳኖስ መካከል አሥራሁለት ደንጊያ ወደ እግዚአብሔርና ወደኔ ፊት አምጥታችሁ በአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ቁጥር በጫንቃችሁ ተሸከሙ። አካቸው ይህም ከዘካከም ከመጨ ትውልድ ሁሉ ምልክት ሆነ።

እስረጅ፡- ኢያሱ ፫፡፲፪ (3፡12) ፬፡፩-፱ (4፡1-9)

ሌላው አሥራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል ምሳሌ አድርጎ ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔር መሠዊያ የሠራ በቴስቡ ዘገለዓድ የነበረው ቀናኢው ነቢይ ኤልያስ ነው። ይህም የተደረገው ዝናብ የሚሰጥ በዓሊም እንጂ እግዚአብሔር አይደለም ብለው አክዓብና ኤልዛቤል ሕዝቡን አስተው በነበረበት ዘመን ነው።

"ወነሥአ ኤልያስ አሠርተ ወክልኤተ እዕባነ በከመ ኍልቆሙ ለሕዝበ እስራኤል በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር እስራኤል ይኩን ስምከ"

"ኤልያስም ስምህ እስራኤል ይሆናል የሚል

የእግዚአብሔር ቃል እንደደረሰበት እንደ ያዕቆብ ልጆች ነገድ ቁጥር አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ወሰደ።" ፩ነገ.፲፰፡፴፩ (1ነገ.18፡31)

## የያዕቆብ ልጆች ዝርዝር

ከልያ የተወለዱ፡- ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ ዲና (ሴት ልጅ)

ከባላ የተወለዱ፡- ዳን፣ ንፍታሌም

ከዘለፋ የተወለዱ፡- ጋድ፣ አሴር

ከራሔል የተወለዱ፡- ዮሴፍ ፣ ብንያም

## የስማቸው ትርጓሜ

1. ሮቤል - አየኝ ወደደኝ ማለት ሲሆን እነሆ ወንድ ልጅ ማለትም ነው።

2. ስምዖን- "ርእየኒ አፍቀረኒ" እግዚአብሔር ሰማኝ

3. ሌዊ- ወትከውን ልዑቀ ከእግዚአብሔር እንዲል የተጠጋ ማለት ነው።

4. ይሁዳ- "ተአማኒ" በእግዚአብሔር የታመነ-ማመስገን ማለት ነው።

5. ዳን- "ፈትሐ እግዚአብሔር" እግዚአብሔር ፈረደ - ዳኛ ማለት ነው።

6. ንፍታሌም- ዘንባበ ማለት ሲሆን የኔ ትግል የሚል ትርጓሜም አለው።

7. ጋድ- አክሊል፣ ክብር ዕድል ሲሆን ወራሪ የሚል ትርጓሜም አለው።

8. አሴር- "ጽጉብ እክል" ባለጸጋ ማለት ሲሆን ደስተኛ ማለትም ነው።

9. ይሳኮር - ዋጋ ወይም የዋጋ ሰው ዋጋዬ ማለት ነው።

10. ዛብሎን - "መስተሳልም፣መውደድ፣ መኖሪያ ማለት ነው"።

11. ዮሴፍ - "ገበገብ" መጨመር "ይወስከኒ" ይጨምርልኝ ማለት ነው።

12. ብንያም - "ወልደ ኃይል ወልደ የማን" የኃይል ልጅ የቀኝ ልጅ ማለት ሆኖ አንበሳ፣ ናዛዚ ማለትም ይሆናል።

አስረጅ፡- ዘፍ ፳፱፡፴፪-፴፭ (29፡32-35) ፴፡፴፭-፲፰ (35፡18)

አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ወይም የያዕቆብ ልጆች እንደ አወላለዳቸው ከላይ የተዘረዘሩት ሲሆኑ ሌላው የምናስተውለው ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ነው።

## 1ኛ ዲና

ልያ የወለደቻት ዲና የምትባል ሴት ልጅ አለች ዘር በወንድ ስለሚቆጠር በነገድ አሥራ ሦስተኛ ተብላ ወይም እንደትውልዷ አሥራ አንደኛ ሆና አልተቆጠረችም። ስሟ ዲና ተብሏል ትርጓሜውም ዳኛ ማለት ሲሆን ከዳን ጋር አንድ ነው። በሌላም በኩልም ልያ የልጅ መዲና አደረገኝ ስትል ዲና ብላ ጠርታለች። ዘፍ ፴፡፳፩ (30፡21)

## 2ኛ ሌዊ

በምድረ ርስት ማርና ወተት በምታፈስ ከነዓን ከእስራኤል ነገዶች ርስት ሲከፋፈል ከያዕቆብ ሦስተኛ ልጅ ከሦስተኛው ነገድ ከሌዊ ርስት አልተሰጠውም። ምክንያቱም የሌዋውያን የካህናት አባት ካህን ነውና በአሥራት በቀዳምያት ስለሚኖር ርስቱ እግዚአብሔር ስለሆነ። ከነገድ ዝርዝር ቁጥርም አብረው አልገቡም። ዘኁ ፪፡፴፫ (2፡33) እንዲህ ይላል "ሌዋውያን ግን እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘ ከእስራኤል

ልጆች ጋር አልተቆጠሩም ርስተም አልተደከደካቸውም።

"ወበእይነ ዝንቱ አልቦሙ ለሌዋውያን ክፍል ወርስት ምስለ አኃዊሆሙ እስመ እግዚአብሔር ውእቱ ክፍሎሙ በከመ ይቤሎሙ"

አስቀድሞ እንደ ነገራቸው ዕድል ፈንታቸው እግዚአብሔር ነውና ስለዚህ ለሌዋውያን ከወንድሞቻቸው ከእስራኤል ጋር ዕፃ ርስት የላቸውም። ዘዳ ፲፥፱ (10፥9)

ይህም እግዚአብሔር ሌዊን የለየበት ምክንያቱ በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 8 ላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦቱን ይሸከሙ ዘንድ በእግዚአብሔርም ፊት ቆመው ሥራቸውን ይሠሩ ዘንድ ስሙንም ጠርተው ይጸልዩ ዘንድ በስማቸውም ሕዝቡ ይባርኩ ዘንድ ነው።

## 3ኛ. <u>ኤፍሬምና ምናሴ</u>

ኤፍሬምና ምናሴ ከአስኔት የወለዳቸው የዮሴፍ ልጆች ናቸው። ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ ነገድ ጋር በአባታቸው ተገብተው ተደምረው ተቆጥረዋል።

አስረጅ፡- ዘኁ ፪፥፲፰ (2፥18)

ይህም የሆነበት ምክንያት ያዕቆብ በስሙ እንዲጠሩ ልጁ ዮሴፍን ስለነገረው ነው።

"ወይሰመይ ስምየ ቦሙ" ስሜ በእነርሱ ይጠራ" ወስመ አበውየ አብሃም ወይስሐቅ" የአባቶቼም የአብርሃምና የይስሐው ስም በእነሱ ይጠራ። ዘፍ ፵፰፥፲፮ (48፥16)

በመጀመሪያ የተወለደው ምናሴ ሲሆን የስሙ ትርጉም "መርስዔ ኀዘን" መከራዬን ሁሉ የአባቶቼንም ወገን መከራ ሁሉ እግዚአብሔር እንድዘነጋው አደረገኝ ማለት ነው። ኤፍሬም የምናሴ ታናሽ ሲሆን የስሙ ትርጓሜም "ዕበይ፣ ፍሬ" ሲሆን መከራ በታዘዘበት ግብጽ እግዚአሔር አከበረኝ፣ አበዛኝ፣ አፈራኝ ማለት ነው። ዘፍ ፵፰፥፰-፳ (48፥8-20)

ወሳኙ ምሥጢር ልናስተውለው የሚገባው ቤተ እስራኤል ቤተ ኦሪት በአሥራ ሁለቱ ነገድ መመሥረቷ ቤተክርስትና ቤተ ወንጌል በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ከመመሥረቷ አምሳል መርገፍ ነው። ከዚህም አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ትተው የተከተሉትን ቅዱሳን ሐዋርያት "እውነት እላችኋለሁ እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ" ማቴ ፲፱፥፳፰ (19፡28)

ያኔ መንግሥተ ሰማያት በብሉይ በሐዲስ ነቢያትና ሐዋርያት ትምህርት ካመኑ ሁሉ ትሰጣለች። ደብተራ ኦሪትን ከበው በሰፈሩ 12 ነገድና በጉ በሾማቸው ሥዩማን ሐዋርያት ስም ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ተሸልማ ከሰማይ ትወርዳለች።

"... ታላቅና ረጅም ቅጥር ነበራት አሥራሁለትም ደጆች ነበሩአት በደጆቹም አሥራሁለት መላእክት ቆሙ የአሥራ ሁለቱም የእስራኤል ልጆች ነገዶች ስሞች ተጽፈውባቸው ነበር።... ለከተማይቱም ቅጥር አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩአት በእነርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽፈው ነበር።" ራእ ፳፩፥፱-፲፬ (21፡9-14)

# ቅዱሳን ነቢያት (ነቢያን)

ነቢያት ማለት እግዚአብሐር አምላክ ወደፊት የሚሠራውንና የሚፈጽመውን ሚገልጽላቸው እንዲሁም ከነሱ በፊት ያደረገውንም የሚነግራቸው ከሰው ወገን የመረጣቸው፣ የቀደሳቸው ናቸው። ነቢዩ አሞጽ እግዚአብሔር ለነቢያት ምሥጢር መግለጹን ሲጽፍ እንዲህ አለ።

> "እስመ አልቦ ዘይገብር እግዚአብሔር ዘኢከሠተ ወዘኢነገረ ለአግብርቲሁ ነቢያት" በእውነት ጌታ እግዚአብሐር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም ምን አያደርግም። አሞጽ ፫፥፯ (3፥7)

ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከፍጥረቱ ከሰው መልእክቱንና ትእዛዙን የሚልከው በመረጣቸው ነቢያት አማካኝነት ነበር። እነዚህም ነቢያት በተናገሩት ትንቢት በቆጠሩት ሱባዔ መሠረት የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከድንግል ማርያም መወለድ፣ በዮርዳኖስ መጠመቅ፣ በቀራንዮ መሰቀል፣ በአጠቃላይ ሞቱን፣ ትንሣኤውን፣ ዕርገቱንና ምጽአቱን በጉላ በተረዳ ነገር ገልጸዋል።

> "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሐር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን። ዕብ ፩/፤፩-፪ (1፥1-2)

በዘመኑ ሁሉ ነቢያት ቢኖሩም የትንቢት መጽሐፍ በመጻፍ ትንቢት የተናገሩት አሥራ ስድስት ነቢያት ናቸው እነዚህ ከአስራ አምስቱ ነቢያት የተለዩ ናቸው። እነዚህም እንደቤተክርስቲያናችን ትምህርት በሁለት ይከፈላሉ። አራቱ ዐበይት ነቢያትና አሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት በመባል ይታወቃሉ። ዝርዝራቸውም ከዚህ በታች እንዳለው ነው።

## የዐበይት ነቢያት ስማቸው ከነትርጉሙ

1. ኢሳይያስ፡- ማለት "ቅቡዕ እምቅብዐ ትንቢት" (ከትንቢት ቅባት የተቀባ) ማለት ነው። እንደገናም ኢሳይያስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው።

2. ኤርምያስ፡- ኤርምያስ ማለት ብርሃን ማለት ነው፤ እንደገናም "ዘተፈነወ እምኀበ እግዚአብሔር" ማለት ነው። ከእግዚአብሔረ ዘንድ የተላከ፤

3. ሕዝቅኤል፡- የስሙ ትርጉም ጽንዑ ጽንዐ እምላከ ማለት ነው፤

4. ዳንኤል፡- ዳንኤል ማለት ፍትሐ እግዚአብሔር ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነው።

## ደቂቀ ነቢያት ስማቸው ከነትርጉሙ

፩. ሆሴዕ፡- ሆሴዕ ማለት መድኃኒት ማለት ነው።

፪. አሞጽ፡- አሞጽ ማለት ጽኑዕ በእግዚአብሔር ማለት ነው።

፫. ሚክያስ፡- ሚክያስ ማለት መኑ ከማከ፤ ማን እንዳንተ ማን እንደ እግዚአብሔር ማለት ነው።

፬. ኢዩኤል፡- ኢዩኤል ማለት ኅሩየ እግዚአብሔር፤ በእግዚአብሔር የተመረጠ የእግዚአብሔር ምርጥ ማለት ነው።

፭. አብድዩ፡- አብድዩ ማለት ገብረ እግዚአብሔር፤ እግዚአብሔር ስራ ይስራል ማለት ነው።

፮. ዮናስ፡- ዮናስ ማለት ርግብ፣ የዋህ ማለት ነው።

፯. ናሆም፡- ናሆም ማለት ፈውስ እግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔር ማዳን (ፈውስ) ማለት ነው።

፰. ዕንባቆም፡- ዕንባቆም ማለት ማእምር፣ ከባዊ፣ ነባቢ ማለት ነው፤ አዋቂ አስተዋይ ተናጋሪ ሲል ነው።

፱. ሶፎንያስ፡- ሶፎንያስ ማለት ሰፋን (ሰፋኒ) ቀዳሲ ማለት ነው።

፲. ሐጌ፡- ሐጌ ማለት መልአከ እግዚአብሐር አንድም በዓል ማለት ነው።

፲፩. ዘካርያስ፡- ዘካርያስ ማለት ዝክረ እግዚአብሐር ማለት ነው። (የእግዚአብሐር መታሰቢያ)

፲፪. ሚልክያስ፡- ሚልክያስ ማለት መልአክ አንድም ሐዋርያ ማለት ነው።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው አራቱ ዐበይት ነቢያትና አሥራ ሁለቱ ደቂቀ ነቢያት በሁለት የተከፈሉትና ዐበይትና ደቂቅ የሚለውን ሥያሜ ያገኙት በጻፉትና በተናገሩት ትንቢት ብዛትና ማነስ እንጂ ሌላ የፀጋ ልዩነት ኖሮ አይደለም።

በዚህች በተቀደሰች እምነታችን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እነዚህንም ሆነ ሌሎቹ ቅዱሳን ነቢያትን ከእግዚአብሔር የተላኩ መሆናቸውን እምነን በጸሎታቸው (በምልጃቸው) እምነን እናስባቸዋለን፣ በጸሎታችን እንጠራቸዋለን። እነሱም በተሰጣቸው ቃል ኪዳን ይረዱናል።

"ነቢይ ነውና ስለአንተ ይጸልያል" ዘፍ ፳፡፯ (20፡7)

"ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል" ማቴ ፲፡፵፩ (10፡41)

ዛሬ ብዙ ሰዎች ከዚህ የእግዚአብሐር ቃል ውጪ ሲሆኑ ይታያሉ። እነዚህም ከእግዚአብሐር የመዐቱ ቀጣ አያመልጡም። ነቢያት በእግዚአብሐር የተላኩ ኪያከብሯቸውም የሚገቡ ናቸው።

"ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር ... እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። ማቴ ፳፫፡-፴፯፡፴፱ (23፡37-39)

በረድኤታቸው ከምንታመነው ሁሉ በረከታቸው በእኛ ላይ አድሮ ይኑር አሜን።

# ቅዱሳት ነቢያት

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው ቤተክርስቲያናችን የምታከብራቸው የተቀደሱ ሴቶች ነቢይያት አሉ። ከነዚህም ውስጥ ጥቂት ብንመለከት እነዚህን አራቱን እናገኛለን።

፩. ማርያም እህተ ሙሴ ወአሮን

"የአሮን እህት ነቢይቱ ማርያም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን በኋላዋ ወጡ" ዘጸ ፲፭፥፳ (15፡20)

"በፊትህም ሙሴና አሮንን ማርያምንም ልኬልህ ነበር" ሚክ፡ ፮፥፬ (6፡4)

፪. ዲቦራ

"በዚያን ጊዜም ነቢይቱ የለፊዶት ሚስት ዲቦራ በእስራኤል ላይ ትፈርድ ነበረች" መሣ ፬፥፬ (4፡4)

፫. ሕልዳና

"እንዲሁም ካህኑ ኬልቅያስና አኪቃም ዓክቦርም ሳፋንና ዓሳያም ወደ ልብስ ጠባቂው ወደ ሐስራ ልጅ ወደ ቴቁዋ ልጅ ወደ ሴሌም ሚስት ወደ ነቢይቱ ወደ ሕልዳና ሄዱ፤ እርሰዋም በኢየሩሳሌም በሁለተኛው ክፍል ተቀምጣ ነበር" ፪ነገ፳፪፥፲፬ (22፡14)

፬. ሐና

"ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች፤ እርሰዋም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች። እርሰዋም ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር፤ በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር። በዚያችም ሰዓት ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር ነበር።" ሉቃ ፪፥፴፮-፴፰ (2፡36-38)

# አሥራ አምስቱ ነቢያት

እነዚህ አሥራ አምስቱ (፲ወ፭) ነቢያት ከአሥራ ስድስቱ ዓበይትና ደቂቅ ነቢያት የተከዩ ናቸው። ብዙውን ጊዜ በሥርዓተ ቅዳሴና በጽሎተ ዕጣን የሚጠቀሱት ናቸው። ብዙ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ነቢያት አሥራ ስድስት የሚለውን ብቻ ያዩና ይህ በስህተት የገባ ይመስላቸዋል። መምህራኑና የተማሩት ካህናት በሚገባ ያውቋቸዋል እነዚህም፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. አዳም | 6. ያሬድ | 11. ኢዮብ |
| 2. ሴት | 7. ሄኖክ | 2. አብርሃም |
| 3. ሄኖስ | 8. ማቱሳላ | 13. ያዕቆብ |
| 4. ቃይናን | 9. ላሜህ | 14. ዮሴፍ |
| 5. መላልኤል | 10. ኖኅ | 15. ሙሴ |

እነዚህ አሥራ አምስቱ ነቢያት "ወአምኣፈ ፲ወ፭ ነቢያት" ከኃጢአት የተፈታን ንጹሐን አድርገን እየተባለ በምልጃቸው እንዲያድነን ዘወትር እንግዚአብሔርን እንማልዳለን። ቅዱስ ሙሴም "ሊቀ ነቢያት" ተብሎ ይጠራል። በዚህም የምታስተውሉት ሊቀ ነቢያት ተብሎ ተጠርቶ ቁጥሩ በዚህ ይቆጠር እንጂ በ ፲ወ፮ቱ (በ16ቱ) ነቢያት አይደመርም።

# የጌታ ቤተሰቦች

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን እንደምታስተምረን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ማለትም ከእመቤታችን ተወልዶ በዚህ ዓለም በሚያስተምርበት ጊዜ ለአገልግሎት የመረጣቸው ወንዶችና ሴቶች ቁጥር አንድ መቶ ሃያ ነበሩ። እነዚህም በአጠቃላይ የጌታ ቤተሰቦች ተብለው የሚጠሩ ሲሆኑ ፀሥራ ሁለት ሐዋርያት ሠላሳ ስድስት ቅዱሳት አንስት (ቅዱሳት ሴቶች) ሰባ ሁለት አርድእት ናቸው።

# አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

ሐዋርያ የሚለው ሐረ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን "ሐረ" ማለት ሄደ ማለት ሲሆን ሐዋርያ ደግሞ ሂያጅ ማለትነው። እንደገናም በምሥጢር ሐዋርያ ማለት "ፍንው" የተላከ መልእክተኛ ማለት ነው።

ጌታችን ዓለምን ያስተምሩ ዘንድ የመረጣቸው ከዋለበት የሚውሉ ካደረበት የሚያድሩ ሐዋርያት በቁጥር ዐሥራ ሁለት (12) ነበሩ።

"ወዝውእቱ አስማቲሆሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ሐዋርያት የ12ቱ ሐዋርያት ስማቸውም እንዲህ ነው።" ማቴ. ፲፥ ፪-፬ (10፥2-4) ማር. ፫፥፲፮ (3፥16) ሉቃ. ፮፥ ፲፫-፲፮ (6፥13-16)

ጴጥሮስ
እንድርያስ
ያዕቆብ
ዮሐንስ
ፊልጶስ
በርተሎሜዎስ
ቶማስ
ማቴዎስ
ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ
ታደዎስ (ልብድዮስ)
ስምዖን (ናትናኤል)
ይሁዳ (የአስቆሮቱ) በማትያስ ተተከቷል።

በሐዋርያት ሥራ ላይ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፲፫፥፲፬ (13፥14) በተጻፈው የ12ቱ ደቀመዛሙርት ወይም ሐዋርያት ዝርዝር ላይ ዐሥራ ሁለተኛው ሐዋርያ አስቆሮቱ ይሁዳ ጌታውን

መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በሠላሳ ብር ሸጦ ስለካደው አሳልፎም ስለሰጠው ካደረገው ኃጢአት ንስሐ ከመግባት ይልቅ ራሱን አንቆ ስለሞተ ከዐሥራ አንዱ ጋር አልተቆጠረም። ማቴ. ፳፯፡፫-፭ (27፥3-5)

ቅዱሳን ሐዋርያትም በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ በጸሎት ሌላ ሾመዋል። ይህም ማትያስ ይባላል። ሲጸልዩም እንዲህ ነበር ያሉት።

"የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ ይሁዳ ወደገዛ ራሱ ስፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህት አገልግሎትና ሐዋርያነት ስፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው አሉ። ዕጣም ተጣጣሉላቸው ዕጣውም ከማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ።" ሐዋ. ፩፡ ፳፬-፳፮ (1፥4-26)

## የሐዋርያቱ ስም ትርጉም

ስም መጠሪያ ሲሆን በአብዛኛው ትርጉም አለው። ይልቁንም የቅዱሳንና የቅዱሳት መጠሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ እንደምናገኘው ትርጉም አዘል ነው። የቅዱሳን ሐዋርያትም ስም ትርጉም ያለው ነው። በወንጌልና በቅዳሴ የአንድምታ መጽሐፋችን የተቀመጠልንን በአጭሩ ከወንጌል ማቴዎስ ምዕራፍ 10 ላይ እንዲህ ተመልከቱ።

1. ጴጥሮስ የተባለው መጀመሪያ ስሙ ስምዖን ሲሆን ጴጥሮስ ተብሏል። ጴጥሮስ ማለት መርግ (ዓለት) ማለት ነው። በዚህም ተመሳሳይ ደንጊያ ዓለት መሠረት ማለት ነው። መርግ (ዓለት) ከወደላይ ሲመጣ ያስፈራልና ቅ/ጴጥሮስም ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ (በሥጋው ሞተ በመለኮቱ ተነሣ ሕያው ሆነ) እያለ ሲያስተምር ከሐድያንን ያስፈራልና መርግ አለው። ፩ጴጥ. ፫፡፲፰ (3፥18) በዓሉ ሐምሌ 5 ቀን ነው። ይህም ዕለት ቁልቁል ተሰቅሎ ያረፈበት ነው።

2. እንድርያስ ማለት ተባዕ ከመስቀል በኲረ ሐዋርያት ማለት ነው። የሐዋርያት በኲር የተባለበት ምክንያት ጌታችን

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉ በፊት በመጀመሪያ ስለመረጠው ነው። ተባዕ ከመሰቀል ማለት ከመስቀል ከመከራ የጨከነ የደፈረ ማለት ነው። እንዲህ የተባለውም በካዕተ ስብእ (ሰው የሚበሉ) ሰዎች አገር ድረስ ሄዶ ወንጌልን ሳይፈራ ስብኮላቸዋልና ነው። በዓሉም ታሕሳስ 4 ቀን ነው።

3. ያዕቆብ የዘብዴዎስ ልጅ ነው የስሙ ትርጉም አኀዚ ማለት ነው። ይህ ስያሜ ከመጀመሪያው ከይስሐቅ ልጅ ከያዕቆብ ጋር የተያያዘ ነው። ዘፍ. ፳፭፡፳፮፡ (25፥26) የመጀመሪያው ያዕቆብ የዔሳውን ሰኰና ያዥ ማለት ሲሆን ይህ ደግሞ የወንጌልን ሰኰና ያዥ ማለት ነው። ያ ሰኰና ዔሳውን እንዳሰናከለ ይህ የመናፍቃንን ትምህርት ያሰናከላልና በዓሉ ሚያዚያ 17 ቀን ነው።

4. ዮሐንስ ይህ የያዕቆብ ወንድም የዘብዴዎስ ልጅ ነው። ዮሐንስ የሚለው የስም ትርጉም ፍሥሓ ወሐሤት ማለት ነው። ደስታ ፍስሐ ሐሤት ተድላ ማለትም ነው። ከምሳሌ ሞክሼውን የዮሐንስ መጥምቁን መወለድ መልአኩ ገብርኤል ከካህኑ ከዘካርያስ ሲነግረው እንዲህ ብሎት ነበር "ወብዙኃን ይትፌሥሑ በልደቱ" በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። ሉቃ ፩፡፲፫ (1፥13) ጌታ ወልደ ነጎድጓድ ብሎ ከወንድሙ ጋር ሰይሞታል። በዓሉም መስከረም 4 ቀን ነው።

5. ፊልጶስ፡ ማለት ረያጼ አፍራስ አኀዜ ኲይናት መፍቀሬ አኃው ማለት ነው፡ ሲተረጉም ረያጼ አፍራስ ፈረስን የሚገራ አኀዜ ኲናት የጦር መሣሪያ የሚይዝ መፍቀሬ አኃው ወንድሞችን የሚወድ ማለት ነው። ረያጼ አፍራስ አኀዜ ኲናት በቀድሞ ግብሩ (ሥራው) ሲሆን በምሥጢር ሲመከከተው እንስሳዊ ባሕርይን የሚገራ ወደ መንፈሳዊ የሚለውጥ አኀዜ ኲናት የጦር ዕቃ የተባለ የእግዚአብሔርን ቃል የታጠቀ የሚለውን ነው። ኤፌ. ፮፡፲-፲፬ (6፥10-14) በዓሉ ኅዳር 18 ቀን ነው።

6. በርተሎሜዎስ ማለት ተክል የማጠጣት ግብር ያለው ልጅ ማለት ነው። በአብራይስጥ "በር" ማለት ልጅ ማለት ነው። ይህ

ሐዋርያ በተአምር በአንድ ቀን ወይን ተክሎ ወዲያው አሳድጓል። ፍሬም እንዲያፈራ አድርጓል። በዓሉ መስከረም 1 ቀን ነው።

7. ቶማስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው።ይህ ሐዋርያ ሁለት ስሞች አሉት ቶማስ አንዱ ሲሆን ሌላ ስሙ ደግሞ ዲዲሞስ ይባላል። ቶማስ ለብዙዎች ፀሐይ (ብርሃን) ሆኗል። በማቴዎስ ወንጌል ፭፥፲፬ (5፥14) "እንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም" እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ብሎ ጌታችን ሐዋርያቱን ሾሟቸዋል። በዓሉም ግንቦት 26 ቀን ይከበራል።

8. ማቴዎስ ማለት ኅሩይ ማለት ነው። ይህ ሐዋርያ መጸብሐዊ (ቀራጭ) የነበረ ሲሆን ከዚያ ለይቶ የእርሱ አገልጋይ ስላደረገው ኅሩይ በአማርኛ የተመረጠ ተባለ። በግእዝ ኀረየ ማለት መረጠ ሲሆን ኅሩይ ማለት ምርጥ የተመረጠ ማለት ነው። በዓሉም ጥቅምት 12 ቀን ይዘከራል (ይታሰባል)

9. ያዕቆብ ይህ ያዕቆብ ደግሞ የእልፍዮስ ልጅ ነው። የስሙ ትርጉም እንደ 3ኛው ሐዋርያ ነው። በዓሉም የካቲት 10 ቀን ይውላል።

10. ታዴዎስ፡- ዘርዕ ወማዕረር ማለት ነው። ኦሪትን እንደ ዘር ወንጌልን እንደ መከር አድርጎ አስተምሯልና። ይህ ሐዋርያ ታዴዎስ በተአምር ስንዴ ዘርቶ ወዲያው ከመሥዋዕት አድርሷልና ይህ ሥያሜው ሆነ። በዓሉም ሐምሌ 2 ቀን ይከበራል።

11. ስምዖን፡- ይህ ስምዖን ቀነናዊ የተባለው ናትናኤል ነው። ናትናኤል ማለትም ውሁብ። ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው። ፀጋ እግዚአብሔር ፡የእግዚአብሔር ሀብት ማለት ነው። ቀነናዊ የተባለው በአገሩ ነው። የቃና ሰው ስለሆነ። ከእምካኑም ቀናኢ የነበረ ሐዋርያ ነው። በዓሉም ግንቦት 15 ቀን ይታሰባል።

12. ይሁዳ ማለት ተአማኒ በእግዚብሔር ማለት ነው። ስም አልጠቀመውም እንደ ስሙም አልሆነም ጌታውን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና። የአስቆሮቱ ይሁዳ እየተባለ ይታወቃል አገሩ አስቆሮት ስለሆነ ነው። በሱ ምትክ ማትያስ ተመርጧል።

ማትያስ ማለት ምትክ ማለት ነው። ፀሐይም ማለት ይሆናል። በዓሉም መጋቢት 8 ቀን ይከበራል።

# ፯ቱ ሊቃነ መላእክት

ሰባቱ (፯ቱ) ሊቃነ መላእክት ዓበይት ሊቃነ መላእክት ተብለው ይታወቃሉ። አንዳንድ መላእክት ሊቃነ መላእክት ተብለው ቢጠሩም ቁጥራቸው ከሰባቱ አይደሉም። ለምሳሌ ቅዱስ ኡራኤል፣ ራሙኤል፣ ፋኑኤልና ራጉኤል ሊቀ (ሊቃነ) መላእክት እየተባሉ ይጠራሉ ድምራቸው ግን ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አይገባም። ከዚህም የተነሳ ሰባቱ ሊቃነ መላእክት ሊቃነ ሊቃናት ይባላሉ። ስማቸውም እንዲህ ነው፡-

፩. ቅዱስ ሚካኤል፡- ኃይላት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ።

፪. ቅዱስ ገብርኤል፡- አርባብ በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ።

፫. ቅዱስ ሩፋኤል፡ መናብርት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ።

፬. ቅዱስ ሱሩያል፡- ሥልጣናት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ።

፭. ቅዱስ ሰዳኪያል፡ መኳንንት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ።

፮. ቅዱስ ሰላትያል፡- ሊቃናት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ።

፯. ቅዱስ አናንኤል፡- አቅራቢ አኮቴት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ።

እንዲህ ዓይነት መዓረግና ክፍል ስላላቸው ነው የሥሩግ ኤጲስ ቆጶስ ሊቀ ያዕቆብ በቅዳሴው እንዲህ የጻፈው፡-

"ለፍቁርከ ይሰግዱ ሎቱ መላእክት ወሊቃነ መላእክት"

"ለምትወደው ልጅህ መላእክት ሊቃነ መላእክት ይሰግዱለታል" ይልና

"ሠራዊተ ሚካኤል በበነገዶሙ" የሚካኤል ሠራዊት በየነገዳቸው

"ወሠራዊተ ገብርኤል በበማኅበሮሙ" የገብርኤል ሠራዊት በየወገናቸው። እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ይላል።

# አርባዕቱ እንስሳት

አርባዕቱ እንስሳት በአማርኛ አራቱ እንስሶች የሚባሉት መላእክት ሲሆኑ "ጸወርተ መንበር" የልዑል እግዚአብሔር ዙፋን የሚሸከሙ ናቸው።

ሠለስቱ ምዕት (318 ሊቃውንት) ስለዚህ አገልግሎታቸው እንዲህ ብለዋል።

"፬ቱ እንስሳ ከመ ዘይጸውሩ መልዕልተ ርእሶሙ መንበረ ስፉሐ (ብሩሃ ልዑክ) ዘኅብረ በረድ ፀዓዳ"

"አራቱ እንስሳ ኅብሩ እንደ በረድ ነጭ የሆነ ሰፊ መንበር በራሳቸው እንደተሸከሙ ሆነው አሉ"

ከዚህ ጋር አንድ በሆነ መልኩ በዓላቸው በሚከበርበት በኅዳር ስምንት ቀን በተጸፈው ስንክሳር እንዲህ ይገልጻቸዋል።

"እሉ እሙንቱ ሠረገላቲሁ ለእግዚአብሔር ፀዋርያነ መንበሩ"

"እኒህም መንበሩን የሚሸከሙ የእግዚአብሔር ሠረገላዎች ናቸው" በመጽሀፍ ቅዱስ ዳዊት ኪሩቤል ብሎ ሲጠራቸው ኢሳይያስ ሱራፌል ይላቸዋል።

አስረጅ፡-

"ተጽዕነ ላዕለ ኪሩቤል ወሠረረ" መዝ ፲፯፡፲ (17፤ 10) በዘባነ ኪሩብ ተቀመጠ በብርሃን በሥልጣን በቅዳሴ በረረ (ዓረገ) ይለዋል። በሌላም ስፍራ እንዲህ የሚል አለ፡-

"ዘይነብር ዲበ ኪሩቤል አድለቅለቃ ለምድር"

"በኪሩቤል አድሮ የሚኖር ምድርን እናወጣት" መዝ ፺፰፡፩ (98፡1)

"ርኢኩዎ ለእግዚአብሔር ፀባዖት እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ልዑል ወነዋኅ.... ወሱራፌል ይቀውሙ

ዓው ዶ"

"እግዚአብሔርን ከፁከና ከፍ ባለ ዙፋን ካይ ተቀምጦ አየሁት... ሱራፌልም በዙሪያው ቆመው።" ኢሳ ፮፡፩-፪ (6:1-2)

## መልካቸው፡-

"ፀወርተ መንበር" ዙፋን ተሸካሚዎች የተባሉ ፬ቱ እንስሳ ምን እንደሚመስሉ አምካካችን መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ከነቢዩ ከሕዝቅኤል በሐዲስ ኪዳን ከባለራእዩ ከቅዱስ ዮሐንስ ገልጾካቸዋል። እነሱም እንዳዩት እንዲህ ጽፈዋል።

> "ከመካከልም የአራት እንስሶች አምሳያ ወጣ። መልካቸውም እንደዚህ ነበረ ሰውም ይመስሉ ነበር... የፊታቸው አምሳያ እንደ ሰው ፊት ነበረ ከአራቱም በስተቀኛቸው እንደ አንበሳ ፊት በስተግራቸውም እንደ ካም ፊት ነበራቸው ከአራቱም ደግሞ የንስር ፊት ነበራቸው።" ሕዝ ፩፡፭-፲፩ (1:5-11)

እንባቢ ሆይ፡- በነቢዩ ራዕይ አራቱን እንስሶችና ሃያ አራቱን ኪቃነ ካህናት በአንድ ካይ እንደምናያቸው ማስተዋል አለብን። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌካዊ ግልጽ አድርጎ የጻፈውን ቀጥሎ እንዲህ እናገኘዋለን። ሕዝቅኤል ከውስጥ ያሉትንም ይቆጥራል ዮሐንስ ብቅ ብቅ ያሉትን።

> "በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙርያ በፊትና በኋካ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ። ፊተኛውም አንበሳን ይመስካል፣ ሁለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስካል ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው አራተኛውም እንስሳ የሚበረውን ንስር ይመስካል። አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው በዙሪያቸውም በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል።" ራዕ ፬፡፯-፰ (4:7-8)

## አገልግሎታቸው፡-

፩. ምስጋና፡- ፬ቱ እንስሳ በዙፋኑ ከዘለዓለም ጸንቶ የሚኖረውንና የሚመለከተውን ሕያው እግዚአብሔር በቅዳሴ፣ በሰባሔ፣ በውዳሴና በክብር ውኃ ከተፈጠረ ጀምሮ መፍለስ እንደማያቋርጥ እነሱም ቀንና ሌሊት ሳያርፉ ያመሰግኑታል፣ ይሰግዱለታል። ከእኒህ መላእክት ምስጋናቸው እረፍታቸው፣ እረፍታቸው ምስጋናቸው ነው። "እስመ እኩቴቶሙ ይእቲ ዕረፍቶሙ"

"አንዱም ለአንዱ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር" ኢሳ. ፮፡፫ (6፡3)

"ቅዱስ፣ቅዱስ፣ቅዱስ የነበረውና የሚመጣው ሁሉንም የሚገዛ ጌታ ያለው እምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት እያርፉም" ራዕ. ፬፡፰ (4፡8)

ያለማቋረጥ እንዲህ ሲያመሰግኑ "ትእምርተ መስቀል" የመስቀል ምልክት በመሥራት ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ ከላይ ባየነው ጥቅስ እንደገለጸው በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን ሸፍነው በሁለት ክንፋቸው ሲበሩ ዓለም የዳነበትን መስቀል ያሳያሉ።

፪. ለፍጥረት ሁሉ ይለምናሉ፡- እምላክ አማልክት ዘሀሎ ወይሄሉ። ያለና የሚኖር የአማልክት አምላክ እያሉ ያለማቋረጥ ከማመስገን ጋር በዙፋኑ ፊት ሁልጊዜ ለፍጥረት ሁሉ ይለምናሉ ይማልዳሉ ይጠብቃሉ። ለፍጥረት ሁሉ ሲል ለውን ብቻ እንዳልሆነ በትርጓሜ መመልከት ይቻላል።

"ገጸ ሰብእ ይሰእል በእንተ ፍጥረተ እጓለ እመሕያው"

"ገጸ አንበሳ ይሰእል በእንተ አራዊት"

"ወገጸ ላህም ይሰእል በእንተ እንስሳት"

"ወገጸ ንስር ይሰእል በእንተ አዕዋፍ"

ይህም ማለት እንደ ሰው ፊት ያለው ከሰው ልጆች እንበሳን የሚመስለው ከአራዊት የጥጃ መልክ ያለው ከእንስሳት ሁሉ የንስር ፊት ያለው አራተኛው እንስሳ ደግሞ ከአዕዋፍ ይለምናሉ። እነዚህም ከሰማይ ሠራዊት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ በባለሟልነት አጅግ የቀረቡ ናቸውና።

"እስመ እሙንቱ ቅሩባን ፈድፋደ ኀበ እግዚአብሔር እምኩሎሙ ኃይለ ሰማያት"

## ስማቸው

አርባዕቱ እንስሳ እየተባሉ የሚጠሩት መላእክት እያንዳንዳቸው ስም እንዳላቸው ቅዱስ ያሬድ በሰማይ እንደተመለከተውና እንደተገለጸለት ስለነሱ በተናገረው ክፍል መዋሥዕት በተባለው ድርሰቱ ጽፎታል።

፩. ባራማራ

፪. መሊጦን

፫. አግራማጣ

፬. ሱርትዮን ይባላሉ።

እንባቢያን ሆይ፡- ከአራቱ ወንጌላውያን ጋር ያለውን ምሳሌያዊ ዝምድና ስለወንጌላውያኑ በተጻፈው መመልከት ያስፈልጋል።

# ሃያ አራቱ (፳፬ቱ) ካህናተ ሰማይ

ሃያ አራቱ ካህናት ሃያ አራቱ ኢቃናት እንዳንደም ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ተብለው የሚጠሩ ሥጋ የሌላቸው ረቂቃን የእውነት ካህናት የሆኑ ከቅዱሳን ሁሉ በላይ የሆኑና ከሰማይ ሠራዊት ሁሉ ከፍ ከፍ ያሉ መላእክት ናቸው። ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ እንዳያቸው ሲጽፍ "በዙፋኑ ዙሪያም ሃያ አራት ዙፋኖች ነበሩ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሃያ አራት ኢቃናት ተቀምጠው ነበር።" ራዕ ፬፥፬ (4፡4)

፫፻፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት፡- ሃይማኖታቸው የቀና ሦስት መቶ አስራ ስምንቱ ሊቃውንት እንዲህ ሲመሰክሩ እናያለን፡-

"ወእምዓውዱ ለውእቱ መንበር ፳ወ፬ቱ ካህናት "

በመንበሩ ዙሪያ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ አሉ"

## ቁጥራቸው ፳፬ መሆኑ

አንደኛ በሃያ አራቱ ሰዓት ጸልየው ራሳቸውን ፍጥረትንም ጠብቀው አምላክን አመስግነው ዋጋቸውን ተቀብለው የሚኖሩ ስለሆነ ሃያ አራት አድርጓቸዋል። በሌላም በኩል ስንመለከተው ቤተ እስራኤል በአስራ ሁለቱ ነገድ ቤተክርስቲያን በአስራ ሁለቱ ሐዋርያት የተመሠረቱ በመሆናቸው ድምራቸውን ያሳያሉ"

## አገልግሎታቸው

የሃያ አራቱ ኢቃነ ካህናት አገልግሎት እንደ አራቱ እንስሶች ሲሆን በተጨማሪ እነዚያ መንበሩን ሲሸከሙ እኒህ ደግሞ ያጥናሉ። በፊታቸው ትሰብእትን በጌትነት እያዩ ሦስት ጊዜ ዞረው ይሰግዱለታል።

"ሃያ አራቱ ሊቃናት በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን

ፈጥረሃልና ስለፈቃድም ሆነዋልና ተፈጥረውማል ክብር፣ ውዳሴ፣ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ" ዕራ፡፬፡፲ (4፡10)

"ወእለ ዖድዎ ለውእቱ መንበር ይሰግዱ ፫ተ ጊዜ"

"መንበሩን ዞረው ሦስት ጊዜ ይሰግዱለታል" ሠለስቱ ምዕት

ቅዱስ ዮሐንስ ጨምሮ እንደገለጸልን ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በሰማይ ያለውን የእግዚአብሔርን መቅደስ በውስጡም ያለውን የቃል ኪዳኑን ታቦት ወድቀው እንደሚሰግዱለት ስቡሕ፣ ክቡር፣ ኃያል መባል ለአንተ ይገባል እያሉ የወርቅ ጥና ይዘው እንደሚያጥኑ በገና መሰንቆ ይዘው በዝማሬና በቅኔ እንደሚያገለግሉት እንመለከታለን።

አስረጅ፡-

"በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሃያ አራቱ ኪቃናት በግንባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ..." ራዕ ፲፩፡፲፮-፲፱ (11፡16-19)

"መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ ኪቃናት በበጉ ፊት ወደቁ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ፡... እያሉ አዲሱን ቅኔ ይዘምራሉ።" ራዕ ፭፡፰-፲፬ (5፡8-14)

ከዚህ የእግዚብሐር ቃል የምንረዳው ሌላው ነገር ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ የሰው ልጆችን ጸሎት ከዕጣኑ ጢስ ጋር እንደሚያሳርጉ ነው። በበዓላቸው በኅዳር ሃያ አራት ቀን ያለው ስንክሳር እንዲህ ይላል፡-

"ወኢየዐርግ ጽድቅ ወመጽዋት ኀበ እግዚአብሔር ዘእንበሌሆሙ"

"ያለእነርሱም አቅራቢነት ጽድቅና ምጽዋት ወደ

እግዚአብሔር አይቀርብም"

ይህን ሁሉ አገልግሎት ቀንና ሌሊት ሳያርፉ የሚያመሰግኑ እኒህ የሰማይ ካህናት በምድርና በሰማይ በባሕርና በታሕተ ምድር ያለ ፍጥረት ሁሉ ሰቡሕ፣ ክቡር፣ ኃያል፣ ቡሩክ መባል ለአንተ ይገባል ብለው በዙፋኑ ካለው ከልዑል እግዚአብሔር ሲሰግዱና ሲያመሰግኑ እግዚአብሔርም ምሕረትን ለሰው ልጆች ሲሰጥ አሜን ይሁን ይደረግ ይላሉ።

"አራቱም እንስሶች፡- አሜን አሉ ሊቃናቱም ወድቀው ሰገዱ" ራዕ ፭፡፲፬ (5፡14)

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላይ ይነግሣልና በሽማግሌዎቹም ፊት ክብር ይሆናል" አሜን! ኢሳ ፳፬፡፳፫ (24፡23)

# ቅዱሳን ሰዎች

ቅዱሳን ሰዎች የምንላቸው ከሌላው የሰው ልጅ በበለጠ ራሳቸውን ከእግዚአብሔር የሰጡ- ከሰው ወገን ሁሉ የተመረጡ የእግዚአብሔር ምርጥ እቃዎች የተለዩ አገልጋዮች ናቸው።

ዓለምን የናቁ አምላካቸውን ያወቁ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን ታላቅ ኃይሉን በእነርሱ ላይ አሳድሮ የጨለማን መጋረጃ አስወግዶ ብርሃንን ይፈነጥቅ ዘንድ የተጠቀመባቸው ከወንድም ከሴትም የተመረጡ ቅዱሳን አገልጋዮች ናቸው። እነዚህም በራሱ የተጠሩና የተዘጋጁ አስቀድሞም የወሰናቸው ናቸው።

> "ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰኗልና አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።" ሮሜ. ፰፥፳፱ (8÷29)

ቤተክርስቲያናችን ቅዱሳን ብላ የምታከብራቸው፡-

ሀ. ነቢያት
ለ. ሐዋርያት
ሐ. ሰማዕታት ።
መ. ጻድቃን

ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው አስቀድሞ ከቅድስና የወሰናቸው እግዚአብሔር፣ የጠራቸው እግዚአብሔር፣ ያጸደቃቸው እግዚአብሔር፣ ያከበራቸው እግዚአብሔር፣ እኛ ክርስቲያኖች ከቃሉ ተገዢ ነንና የጠራቸውን እንጠራቸዋለን፣ ያጸደቃቸውን ጻድቃን እንላቸዋለን፣ ያከበራቸውን እናከብራቸዋለን።

## <u>የልጁን መልክ ይመስሉ</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰነ ሲል፡- ልጁ የተባለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" ማቴ. ፫፥፯ (3÷7)። ስለዚህ ነገር ቅዱሳን የሚመስሉት ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ፡-

"ተመስሉ ኪያየ በከመ አነ አትሜሰሎ ለክርስቶስ"

"እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" ፩ቆሮ. ፲፩፥፩ (11÷1)

## ከሚመስሉበት ዋና ዋናው

የሚመስሉበት ዋናው ነገር የተሰጣቸው ሥልጣንና ጸጋ ይሆናል።

"እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" ዮሐ. ፲፬፥፲፪ (14÷12)

በማይታበለው በአምላካችን ቃል መሠረት እግዚአብሔር ከመረጣቸው ጸጋውን አብዝቶ ይሰጣል። በሚቀጥሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት የተሰጣቸውንና ይመስሉት ዘንድ ያደላቸውን ክብር እንመልከት፡-

ሀ. እግዚአብሔር አምላክ ነው ቅዱሳን ደግሞ በእርሱ የፀጋ አማልክት ተባሉ።

ዘጸ. ፳፥፪ (20÷2) "እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ"

ሆሴ. ፲፫፥፬ (13÷4) "ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ"

የፍጥረት ሁሉ ገዥና ባለቤት እግዚአብሔር የመረጣቸውን ቅዱሳን የጸጋ አማልክት ያደርጋቸዋል። ይህም በማያልቀው ጸጋው የሰጣቸው ክብር ነው።

ዘጸ. ፯፥፩ (7÷1) "ጌታ እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፡- እይ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ"

ዮሐ. ፲፥፴፬ (10÷34) "ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን?" ይህ የተጻፈው በመዝ. ፹፩፥፮

(81÷6) ሲሆን ጌታ እንደተናገረ የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸው ቅዱሳን ሰዎች አማልክት ዘበፀጋ ይባላሉ።

ከ. እግዚአብሔር ምንም አይሳነውም ቅዱሳንም አይሳናችሁም ተባሉ

በዘፍ ፲፰፥፲፬ (18÷14) "በውኑ ከእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" ምንም አይሳነውም። ይህ ምንም የማይሳነው አምላካችን ከሰው ወገን ሁሉ የመረጣቸውን ቅዱሳን በሚለምኑት ሁሉ ምንም እንዳይሳናቸው ነግሮአቸዋል። አድርጓቸዋል። ማቴ. ፲፯፥፳ (17፥20) "የሚሳናችሁ ነገር የለም"

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው። ቅዱሳንም የዓለም ብርሃን ተባሉ።

"አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም"

"እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ዮሐ. ፰፥፲፪ (8 ÷12)

አዎ! ጨለማ ሁሉ የራቀበት እውነተኛ ብርሃን ነው። ክርስቶስ ብርሃናችን ነው። እንቅፋትና እሾህ ሁሉ ይርቃል፡ አባታችን ቅዱስ ዳዊትም ሲዘምር መዝ. ፳፮፥፩ (26፥1) "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው።" ይል ነበር። ይህ የዓለም ብርሃን የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳን እርሱን ይመስሉ ዘንድ የሰጣቸው ጸጋ ብዙ ነውና አንዱ ከዚህ አልጫ ከሆነው ዓለም ጨው እንዲሆኑና በጨለማ ውስጥ ከሚመላለሱ በጸሎታቸው፣ በትምህርታቸው፣ በአማላጅነታቸው ብርሃን ይሆኑ ዘንድ ነው።

"አንትሙ ብርሃኑ ለዓለም"

"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ማቴ. ፭፥፲፬ (5÷14)

ልናስተውለው የሚገባው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ - አምላክነቱ፣ ሁሉን ቻይነቱ፣ ብርሃንነቱ ገንዘቡ የሆነ የባሕርዩ ነው። የቅዱሳን ግን የጸጋ ነው። ከእነሱ ይህንን ሥልጣንና ክብር የሰጣቸው ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እኒህ ቅዱሳንም በኑሮአቸው፣

በሞታቸው ሁሉ እርሱን የመሰሉ ጻድቃን ናቸው።

## የቅዱሳን በረከታቸው

"በረከተ እግዚአብሔር ውስተ ርዕሰ ጻድቃን" "የእግዚአብሔር በረከት በጻድቃን ራስ ላይ ነው" ምሳሌ ፲፥፮ (10፥6) በረከታቸው ከዘላለሙ በእውነት ይደርብንና የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከጻድቃን የሰጣቸው በረከት ሊቆጠርና ሊሰፈር የሚቻል አይደለም። እምላካችን እንደተናገረ።

> "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፣ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፣ እባቦችን ይይዛሉ፣ ማር. ፲፮፥፲፯ (16÷17) የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጐዳቸውም፣ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ" ይህ እንደሚሆን በእምነት የተመለከተ ነቢዩ ኢዩኤል ቀድሞ በትንቢቱ እንዲህ ብሎ ነበር። "መንፈሴን በሥጋ ከባሹ ላይ እፈሳለሁ" ኢዩ ፪፥ ፳፰ (2፥28)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን የቅዱሳን በረከት እጅግ ዋጋ አለው። የእርሱ ደቀመዛሙርት ናቸውና ቅዱሳንን የሚቀበል ጌታን የሚቀበል ነው።

«ዘተወከፈ ነቢየ በስመ ነቢይ እስበ ነቢይ ይነሥእ ወዘተወከፈ ጻድቀ እስበጻድቅ ይነሥእ»

«ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማቴ ፲፥፵፩ (10፥ 41)

ፈጣሪ አምላክ እግዚአብሔር የመረጣቸው ቅዱሳንን ከእኛ ከምናምን ሁሉ ከበረከት አድርጓቸዋል። እሱን እምኖ የመጣውን ታላቁን አባት አብርሃምን እንዲህ ነበር ያለው፦ «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ አባrkeሃለሁ፤ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ከበረከትም ሁን» ዘፍ ፲፪፥ ፪ (12፥2)። ይህንን ቃል ሰምቶ የሚያደርገው በረከታቸውን ይወርሳል፤ የማይቀበለው ግን ቅዱሳንን የሚያቃልል ቢኖር የተረገመ ይሆናል።

«የሚባርኩህንም እባርካለሁ የሚረግሁንም እረግማለሁ» ዘፍ ፲፪፥

፫ (12፡3)

## የቅዱሳን አማላጅነታቸው በዚህ ዓለም

አማላጅ ማለት ወደዋናው ባለሙሉ ሥልጣን ሊያቀርብ የሚችል ባለሟል ነው፡ አማለደ ማለት ለመነ፣ ጸለየ ማለት ነው። ዋናው ባለሥልጣን እርሱ አንድ አምላክ የሆነ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ሥልጣኑ አምላክነቱ የባሕርዩ ነው። ባለሟሎቹ ደግሞ መረጥኳችሁ፣ ጠራኋችሁ፣ አጸደኳችሁ፣ አከበርኳችሁ ያላቸው ቅዱሳን ናቸው። ይህ የባለሟልነት ሥልጣን የተሰጣቸውም በሰማይና በምድር ንጉሥ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህን እውነት በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ በጣም በሰፊው የተጻፈ ቢሆንም ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ትንሽ ጥቅሶች እንመልከት።

### በብሉይ ኪዳን

እግዚአብሔር ስለ አብርሃም ነቢይነት በጸሎቱ እንደሚያድን እንዲህ ብሎ ለአቢሜሌክ ነገረው።

"እስመ ነቢይ ውእቱ ወይጸሊ ላዕሌከ ወተሐዩ"

"ነቢይ ነውና ስለ አንተም ይጸልያል ትድናለህም" ዘፍ. ፳፡፯ (20÷7)

‹ፈርኦንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ጓጉንቸሮቹን ከኔ ከሕዝቤም እንዲያርቅ ወደ እግዚአብሐር ጸልዩልኝ" ዘጸ. ፰፡፰ (8÷8) ‹ብሏቸዋል።

እስራኤል ኃጢአትን ሠሩ ሙሴ ግን ስለነሱ ወደ እግዚአብሐር ጸለየ (አማለደ) ሊያጠፋቸው የነበረው እግዚአብሔር በሙሴ ልመና ራራ። ዘጸ. ፴፪፡፲-፲፬ (32÷10-14)

"ንጉሥ ኢዮርብዓም የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ነቢዩን በናቀ ጊዜና ሊያሲዘው እጁን በዘረጋ ጊዜ እጁ ደረቀች፡ ከዚያም ነቢዩን ተማጸነ ወደ እግዚአብሐርም ጸልይልኝ አለው። "የእግዚአብሔርም ሰው እግዚብሔርን ለመነ የንጉሥም እጅ ወደ እርሱ ተመለሰች እንደቀድሞም ሆነች።" ፩ነገ ፲፫፡፩፡፯

(13÷1-6)

"ባርያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ" የእግዚአብሔርን ሥራ ንቀው አቃለው ቅንን ነገር ያልተናገሩ ቅዱስ ኢዮብንም ወደ ክንቱ ሐሳባቸው ሊወስዱት የነበሩትን ቴማናዊው ኤልፋዝ ሹሐዊው በልዳዶ ናዕማታዊው ሶፋርን እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው፡- እነሱም ሄደው መስዋዕት አቀረቡ ጸለዩ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ ኢዮብም ስለነሱ ጸለየ እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት ማለት ጸሎቱን ምልጃውን ተቀበለ።ኢዮ ፵፪፡፰-፱ (42፡8-9)

የነቢዩ የኤርምያስ ምልጃም በተገለጠበት በኤር ፵፪፡፩-፮ (42፡1-6) ሕዝቡ ሁሉ ተሰብስበው ወደ ነቢዩ ኤርምያስ መጥተው ልመናችን በፊትህ ትድረስ አባክህአምላክህ እግዚአብሔር የምንሄድበትን መንገድና የምናደርገውን ነገር ያሳየን ዘንድ ስለእኛ ስለዚህ ቅሬታ ሁሉ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ አሉት። እርሱም ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ አላቸው። ምልጃ ማለት ይህ ነው።

<u>በሐዲስ ኪዳን</u>

ቅዱስ ያዕቆብ ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ ይልና ጻድቅ በጸሎቱ የሚጠቅም መሆኑን ሲገልጽ "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች"ብሎ ይመሰክራል። ያዕ. ፭፡ ፲፮ (5÷16)

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር የሰው ልጆችን እንደሚያማልዱ ይህንን ተናገረ። "በእኛም የሚስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን።" ፪ኛ ቆሮ ፭፡፳ (5÷20)

እዚህ ጥቅስ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ትርጉም ላይ የፊደል ለውጥ አለ። የቅዱሳንን አማላጅነት እንስርዛለን ብለው ትልቅ ስህተት ሰርተዋል ይኸውም እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ የሚለውን እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ብለው ፊደል

‹ከ›ን ወደ ‹ል› ከውጠው አምላክ እግዚአብሔርን አማላጅ ብለውታል። ክብር እጠራሩ ክብር ይግባውና እኛ ግን በእውነቱ እንሄዳለን።

ሥራ. ፱፡፴፮-፵፫ (9÷36-43) በኢዮጴ የነበሩ ክርስቲያኖች ጣቢታ የሚሏት ዶርቃ በሞተች ጊዜ ወደ ልዳ ሄደው ቅዱስ ጴጥሮስን ጣቢታን ከሞት እንዲያስነሳላቸው ሲለምኑት ተጽፎአል እርሱም ሄዶ ተንበርክኮ ጸለየ ሕያውም አድርጎ በፊታቸው አቆማት፡ ሰዎቹ ጴጥሮስን ለመኑት እርሱ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር አማለዶ ልጅቷን አስነሣት።

ከዚህ ቅዱስ ቃል ልንረዳው የሚገባ እነዚህ ቅዱስ ጴጥሮስን የለመኑትና የጠሩት ሰዎች ክርስቲያኖች ናቸው። ግን ትሑታን የእግዚአብሔር ቅዱሳን ጻድቃን ክብርና ኃይል የሚረዱ ስለሆነ ሐዋርያውን ቅዱስ ጴጥሮስ አባክህና አትዘግይ ብለው በአማላጅነቱ አምነው አስጠሩት። ልብ በሉ እነሱ ለጣቢታ ጴጥሮስን ለመኑ እሱ ደግሞ ጌታን ለመነ የሞተችው ተነሣች።

> ሥራ ፫፡፩-፲. (3÷1-10) መለካም በሚሏት በመቅደስ ደጅ የሚቀመጠውን ሽባ ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ እኛ ተመልከት ብለው ባላቸው ጸጋ ሲፈውሱት ሲፈቱት እናያለን።

ማቴ. ፲፭፡፳፩-፳፰ (15÷21-28) እንደተጻፈ ሴት ልጇ በጋኔን ትሰቃይባት የነበረች አንዲት ከነናዊት ጌታን ልጇን እንዲያድን በለመነች ጊዜ ዝም ቢላት ደቀመዛሙርቱ ናቸው ጌታ ሆይ አሰናብታት ባሉት ጊዜ ያናገራትና ልጇን የፈወሰላት። ማማለድ ማለት ይህ ነው። እንግዲህ በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን በትንሹ እንደተመለከትነው የቅዱሳን ጸሎት ወይም አማላጅነታቸው ጥርጥር የሌለው የእግዚአብሔር እውነት ነው። አንዳንድ ይህ ምስጢር ያልገባቸው ሰዎች እኔ ራሴ በቀጥታ ወደ አምላኬ እጸልያለሁ አማላጅ አያስፈልግም ሲሉ ይደመጣሉ። በመጀመሪያ ማንኛውም ሰው ቀጥታ ወደ አምላኩ ከመጸለይ ይችላል የከለከለ የለም። ዳሩ ግን አማላጅ የሚያስፈልገው፡-

> ሀ. እግዚአብሔር የሚማልድን፣ የሚስታረቅን ቃል ኪዳን ለቅዱሳን ስለሰጠ፣

ለ. ከነሱ ይልቅ እኛ በኃጢአት ስለምንወድቅ፣

ሐ. በቅድስና ሕይወት ቅዱሳን ጻድቃን ከኛ ስለሚበልጡ፣

መ. እግዚአብሔር ባለሟሎች አድርጎ ከሰው ወገን ሁሉ ለይቶ ስለመረጣቸው፣

ሠ. ሁሉን ትተው ስለተከተሉት ማማለድ ብቻ አይደለም ይፈርዱ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። ማቴ ፲፱፥፳፯-፳፱ (19፥27-29)

እነዚህ ቅዱሳን ቅዱስ ያዕቆብ የጻድቃን ጸሎት እጅግ ኃይል ታደርጋለች ብሎ እንደነገረን ከእኛ ይልቅ ባለሟሎች ስለሆኑ እግዚአብሔር ልመናቸውን ይቀበላል።

"እስመ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ኀበ ጻድቃኑ ወእዝኑሂ ኀበ ስእለቶሙ"

"የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸውና" መዝ. ፴፫፥፲፭ (33÷15)

ስለዚህም ነው ከላይ በጥቅሶቹ እንዳየነው ሁሉ ከእግዚአብሔር ምሕረትን የፈለገ ሁሉ ወደ ቅዱሳን፣ ወደ ጻድቃን፣ ወደ ነቢያት፣ ወደ ሐዋርያት፣ ወደ ሰማዕታት እየሄደ አባካችሁ ጸልዩልኝ፣ ጸልዩልን የሚለው። ራሱ መጸለይ አቅቶት አይደለም፥ ይጸልያል መጸለይም ግዴታው ነው እርዳታን ሽቶ እንጂ ያውም ከተመረጠ ባለሟል።

## የቅዱሳን አማላጅነታቸው ከምድራዊው ዓለም በኋላ በወጸደ ነፍስ

እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጠው ክብርና ኃይል ጊዜያዊ የሆነ፣ ዕድሜ የሚገድበው፣ ቦታ የሚከለክለው፣ እድሜስ የሚሸፍነው የዚህ ዓለም ሞት የሚያሸንፈው አይደለም። ይህ ግን ያልገባቸው ሰዎች ቀድሞ ፍጹም ቅዱሳን ማማለድ አይችሉም ይሉ ነበር። ኋላው ደግሞ በሕይወት እያሉ ያማልዳሉ ከሞቱ በኋላ ግን አያማልዱም የሚል ነው። ይህንንም እያሉ ያሉበት የእግዚአብሔር ምስጢር ገብቷቸው የጻድቃኑን ኃይል ተረድተው ሳይሆን ራሳችን እናማልዳለን (እንጸልያለን) ስለሚሉ ስለራሳቸው ክብር ነው።

ከመሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ምን ብሎ ነበር? "ኢየሱስም ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል" ስለዚህ ሥጋ እስከ ምጽአት በመቃብር ቢቆይም ነፍስ ግን ሕያው ናትና ወደ እግዚአብሔር ትወሰዳለች።እንደውም ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ሲለዩ ወደበለጠ ክብርና ጸጋ ይሄዳሉ እንጂ ወደ ድካም አይጓዙም። ዮሐ. ፲፩፥፳፭ (11÷25) ይህ ማለት በጠቅላላው የሰው ልጅ ተአምር አድራጊ ይሆናል ማለት ሳይሆን ከላይ እንደተመለከትነው በተመረጡት ቅዱሳን የሚሠራ የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡

በእነዚህ ቅዱሳን እኛ የምንጠቀመው በረከትን በመውረስ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የማይፈርስና የማያልፍ የዘላለም ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር አድርጓል።

"ኪዳን ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ"

"ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ" መዝ. ፹፰፥፫ (88÷3)

በእግዚብሐርና በተመረጡት መካከል ያለው ቃል ኪዳን እኛን የሚጠቅመው፡

ሀ. እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋና ኃይል በማወቅ፣

ለ. ከእኛ የተለዩ የልዑል ምርጦች መሆናቸውን በመረዳት፣

ሐ. የሚገባቸውን ክብር በመስጠት፣

መ. ዝክራቸውን (መታሰቢያቸውን) በማድረግ፣

ሠ. በስማቸው ነዳያንን በመርዳት ሌላም በብዙ መንገድ። ይህንን ደግሞ ቤተክርስቲያናችን መመሪያዋ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ ጌታችን በተናገረው ቃል መሠረት ነው። እንዲህ ብሎ፡

-

"እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል። እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፡ ጻድቃንንም በጻድቃን ስም የሚቀበል የጻድቃንን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም" ማቴ. ፲፥፵፩-

፵፪ (10፥41-42)

ይህ የኦርቶዶክስ እምነት የእውነተኛይቱ ክርስትና እምነት ነው። ዛሬ ግን ብዙዎች እንኳን ሊቀበሏቸውና በስማቸው ችግረኛ ሊረዱ ቀርቶ ሲሰድቧቸውና ሲንቋቸው ማየት የተለመደ ተግባራቸው ነው። እግዚአብሔር ልባቸውን ይመልስ። በእርግጥ ይህ ሁሉ የሚሆነው በቅዱስ መጽሐፍ እምላካችን እንደተናገረው ነው።

"ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል በምኩራቦቻቸውም ይገርፏችኋልና" ማቴ. ፲፥፲፯ (10÷17)

"ስለስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናችሁ" ማቴ. ፳፬፥፱ (24÷9 )

ጌታችን እንደተናገረ በማያምኑ በከሃድያን ቅዱሳን፣ ጻድቃን እንዲህ ሲጠሉ በሚያምኑ ክርስቲያኖች ዘንድ ግን የማያልቅ በረከትን በእነርሱ ላይ ስለሕዝቡ አድርጓልና።

"በረከት በጻድቅ ራስ ላይ ነው።" ምሳ. ፲፥፮ (10÷6)

እንባቢያን ልታስተውሉት የሚገባ ነገር እንደኛ እግዚአብሔር ቅዱሳንን የሚቃወም ሰው የገዛ ዓይኑን እንደሚወጋ ሰው መሆኑን። "የሚነካችሁ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነውና" ዘካ ፪፥፰ (2፥8) በግእዙ ደግሞ "ወኵሉ ዘገሠሥክሙ በእኩይ ይትገሠሥ በእንተ እዕይንቲሁ" ጥቂት መከራ ያመጣባችሁ ሰው ሁሉ ጽኑ መከራ ይመጣበታል ብሎ ይገልጸዋል።

ሁለተኛ ደግሞ በመዝሙር ፴፥፲፰ (30፥18) ነቢዩ እንደተናገረ የሚደርስባቸውን መከራ ነው። "በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ"

ስለዚህ ይህን በረከት ለማግኘት ከላይ እንዳየነው የቅዱሳንን መታሰቢያ እንጠብቀውና እናደርገው ዘንድ የተሰጣቸውንም ክብር በማወቅ እንወዳቸው ዘንድ ክርስቲያን ነን ከምንል ሁሉ የሚገባ ሃይማኖታዊ ሐቅ ነው።

## የቅዱሳን መታሰቢያቸው

የማይጠፋ ስምን የዘላለም መታሰቢያን ለቅዱሳን ያደረገ እግዚአብሔር እንጂ ሌላ ማንም አይደለም። በነቢዩ በኢሳይያስ መጽሐፍ ስለዚህ ነገር እንዲህ ተጽፏል፡

> "በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም አሰጣችኋለሁ።" ኢሳ. ፶፮፡፭ (56÷5)

ከዚህም ቃል የተነሣ ለቅዱሳን በእግዚአብሔር ቤት ወይም ማደሪያ ላይ የማይጠፋ ለዘላለም የሚሆን የመታሰቢያ ስም ተሰጥቷቸዋል። የእግዚአብሔር ቤት ስንል ከእዚያ ውስጥ እስቲ እነዚህን እናስብ።

ሀ/ ቤተመቅደስ (ቤተክርስቲያን) ማቴ. ፳፩፡፲፫ (21÷13) ቤቴ የጸሎት ቤት ነው።

ለ/ ታቦት ዘጸ. ፳፭፡፳፪ (25÷22) - በታቦቱ ሆኜ እነጋግርሃለሁ

ሐ/ የሰው ልጅ ፩ ቆሮ ፫፡፲፮ (3፡16) የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ።

ስለዚህ ቅዱሳን የማይጠፋ የዘላለም መታሰቢያን ስም በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ሰጧችሁ ሲል እውነታው ይህ ነው።

## ታቦት በቅዱሳን ስም

በመሠረቱ ሰው ሁሉ ሊያውቀው የሚገባ ታቦት የእግዚአብሔር ነው። ለዚህም ነው በመጽሐፍ ቅዱስ እየደጋገመ "የእግዚአብሔር ታቦት" "የእግዚአብሔር ታቦት" የሚለው።

**አስረጅ፡**- ዘጸ. ፴፪፡፲፮ (32÷16) ፩ሳሙ ፮፡፩. (1÷6)

ታዲያ በቤተክርስቲያናችን ስለምን የእመቤታችን የሚካኤል፣ የተክለሃይማኖት፣ የዮሐንስ የመሳሰሉት ታቦት ነገሥ፣ ወጣ ተከበረ የምንለው። ነገሩ እንዲህ ነው፡ የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ስለሱ የኖሩትን፣ ዓለምን ንቀው የተከተሉትን፣ ስለሱ መከራ የተቀበሉትን፣ ቃል ኪዳኑን ስለጠበቁት የተመረጡ ሰዎች የተናገረውና ቃል የገባው

ኪዳን አለ። ይህም በራሱ ቤት ላይ የዘላለም የማይጠፋ ስምን እንደሚሰጣቸው አንዱ ማደሪያው ቤቱ የቃል ኪዳኑ ታቦት ነውና በዚያ ላይ ስምን ሰጥቷቸዋል። ሌላው ማስተዋል የሚገባን ነገር በታቦቱ ላይ ብቻ ሳይሆን ልክ እንደ ታቦቱ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሆኖ ሳለ እያንዳንዱ መጽሐፍ በጸፉት ነቢያት ወይም ሐዋርያት ስም እንደተሰየመ ነው። ምሳሌ የኢሳይያስ ትንቢት፣ የኤርምያስ ትንቢት፣ የማቴዎስ ወንጌል የማርቆስ፣ የሉቃስ የዮሐንስ ተብሎ እንደሚጠራ። የማይጠፋ የዘላለም ስም።

ሀ. ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ናት ቅዱሳን ደግሞ በቤተክርስቲያን በዚህ ስም ተሰጥቶአቸዋል - ምሳሌ፡- የቅዱስ ዮሐንስ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ወዘተርፈ እየተባለ፣

ለ. ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው። ለመታሰቢያ ቅዱሳንም በታቦት ላይ ስም ተሰጥቶአቸዋል - ምሳሌ፡- የቅዱስ እስጢፋኖስ ታቦት፣ የተክለሃይማኖት ታቦት፣ የአቡየ ታቦት ነገስ ወዘተርፈ እየተባለ፣

ሐ. በክርስቲያን (የሰው ልጆች) ላይ እንዲሁ ቅዱሳን የመታሰቢያ ስም አላቸው- ኃይለ ማርያም ፣ ክንፈ ሚካኤል ሰይፈ ገብርኤል ወልደ ጊዮርጊስ፣. . . . እየተባለ።

የማይጠፋ መታሰቢያ የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ የተባለው በዚህ ልክ አሁን ከላይ እንዳየነው ነው። ቅዱሳን ከዘላለም በገነት በመንግሥተ ሰማያት ነግሠው ከንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ጋር የሚኖሩም ናቸው።

ራእ. ፳፭፡፭ (25÷5) "ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ"

መዝ. ፻፲፩፡፮ (111፡6) "የጻድቃን መታሰቢያ ከዘላለም ይኖራል"

ምሳ. ፲፡፯ (10÷7) "የጻድቃን መታሰቢያ ከበረከት ነው የኀጥአን ስም ግን ይጠፋል"

# ሥርዓተ ምንኩስናና ብሕትውና

<u>ምንኩስና</u>፡- የራሱ ሥርዓትና ሕግ ያለው በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ቀድሞም በሕገ ልቡና የተፈቀደ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። ቃሉም መንኮስ ከሚለው የግእዝ ቃል የተወሰደ ሲሆን ለዓለም መሞትን የሚያሳይ ነው። ፍትሐ ነገሥት በአሥረኛው አንቀጽ ስለምንኩስና እንዲህ ይገልጻል፡-

"ምንኩስናሰ ጥበበ ሕግ መዊሐዊት ይእቲ ወመነኮሳትኒ መላእክት ምድራውያን ወሰብአ ሰማያውያን እሙንቱ ተላውያኒሁ ለክርስቶስ በከመ ከሂሎቶሙ ወበኩሉ ምግባራቲሆሙ ተመሳልያን በሐዋርያቲሁ"

"ምንኩስናሰ የመዊሐዊት ሕግ ጥበብ ናት። መነኮሳትም ምድራውያን መላእክት ሰማያውያን ሰዎች ናቸው። እንደችሎታቸው መጠን የክርስቶስ ተከታዮች በሥራቸውም ሁሉ ሐዋርያትን የሚመስሉ ናቸው።"

ይህ ከዓለም ርቆ ንጽሕናውን ጠብቆ የዓለም የሆነውን ሁሉ በመተው ማግባት መውለድን፣ መነገድ ማትረፍን፣ የጣፈጠ የላመን ምግብን መጠጥንም በመተው ፍጹም ክርስቶስ እምላክን መከተል ነው። ምንኩስና በሦስቱም ሕግጋት የነበረ ነው። ለምሳሌ በሕገልቡና መልከጼዴቅን በሕገ ኦሪት ኤልያስን በሕገ ወንጌል ዮሐንስ መጥምቅንና ጳውሎስ ሐዋርያን ማግኘት ይቻላል፤ እነዚህም ከአብነት ጠቀስሁ እንጂ በርካታ አበውና እማት አሉ። እንዲህ ባለ መልኩ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የምንኩስና ሕይወት ሥርዓት የሠራለት አባታችን አባ እንጦንስ ነው። ስለዚህ ሦስት ዓይነት የመነኮሳት ገዳም አለ።

፩. የወንዶች ብቻ ገዳም- በዚህ ወንድ መነኮሳት ብቻ ይኖራሉ።

፪. የሴቶች ብቻ ገዳም- በዚህ ሴቶች ብቻ መነኮሳይት ይኖራሉ።

፫. የአንድነት ገዳም- በእንደዚህ ዓይነት ገዳም ቦታ ይወሰንና ወንዶችም ሴቶችም በአንድነት ይኖሩበታል።

መነኰሳት ጾም ጸሎትና ስግደትን ቅዱሳት መጻሕፍትንም ማንበብ የሚያዘወትሩ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ከሕዝባውያን ጌጥ ከልማዳቸውም እንዲርቁ የትሩፋትና የበጎ ሥራን ከቀደሙ አባቶች በእውነትም መነኰሳት ከሆኑት በመቀበል ምውታን እንደሆኑ በልባቸው ያስቡ ዘንድ ሕጉ ያዛል። ከመንግሥተ ሰማያት የተዘጋጁ ጃንደረቦች ናቸውና። ማቴ ፲፱፥፲-፲፪ (19፥10-1)

ምንኩስና ሁሉን ትቶ መስቀል የተባለ መከራንና ፈተናን ተሸክሞ ክርስቶስን መስሎ መውጣት ነው። ይህም ከተሰጣቸው ነው፤

"ስለስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል። ማቴ ፲፱፥፳፱ (19፥29)

መቶ እጥፍ ያገኛል ማለት መቶ ቤቶች መቶ ወንድሞች ወይም መቶ አባቶችና እናቶች ወይም ሚስቶችና ልጆች ያገኛል ማለት አይደለም ይህ ማለት እግዚአብሔር በዚህ ዓለም የሚያሳጣው የለም ያባትነት፣ የናትነት፣ የወንድምነት የመሰለውን ይሠራለታል ሲል ነው። በወዲያኛውም ዓለም የዘላለም ሕይወት መንግሥተ ሰማያትን አወርሰዋለሁ ሲል ነው። ይህም የሚሆነው ሁሉን ትቶ በመመነን ነው፤ መነነ ማለት ናቀ ማለት ሲሆን መመነን የዓለም የሆነውን ሁሉ መናቅ ነው።

ይህንን የወንጌል ቃል ከመፈጸም የማይችል መመንኮስ እንደሌለበት የቤተክርስቲያናችን ሕግና መጻሕፍት ያስተምራሉ። ስለመነኰሳትና ብሕትውና የሚገልጡ ሦስት መጻሕፍት አሉ እነዚህም፡-

፩. ማር ይስሐቅ፡- ጾራቸውንና ግብራቸውን የሚናገር

፪. ፊልክስዮስ (ገብረክርስቶስ)፡- ዜናቸውንና ታሪካቸውን የሚናገር

፫. አረጋዊ መንፈሳዊ፡- ጸጋቸውንና መዓርጋቸውን የሚናገር

ብሕትውና፡- በጾም በጸሎትና በስግደት በመንፈሳዊ ተጋድሎ ተጠምዶ በብቸኝነት መኖር ማለት ነው። ባሕታዊ ማት ልዩ የሚል ትርጓሜም አለው። ከባሕታውያን ምሳሌአቸው በብሉይ ኤልያስ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ዮሐንስ መጥምቅና ሌሎችም ቅዱሳን ሲሆኑ ራሱ የክብር አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ አርባ ቀንና ሌሊት ከአራዊት ጋር እየኖረ በሦስቱ አርዕስተ ኃጣውእ የተፈተነበት ከሁሉም አርአያ ከመሆን ሲሆን ዋናው ከባሕታውያን አብነት ነው።

> "በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ መላእክቱም አገለገሉት።" ማር. ፩፡ ፲፫ (1፡13)

ይህን ምሳሌ በማድረግ ሥርዓተ ብሕትውናን የጀመረው አባ ጳውሎስ (ጳውሊ) ነው። ይህ አባት ዓለምን ንቆ በመተው አናብስት፣ አናምርት፣ አክይስት፣ አቃርብት ካሉበት ነቅዐ ማይ ልምላሜ ዕፀ ከሌለበት ዘር ተክል ከማይገኝበት ከጽኑ በረሃ ገብቶ በተጋድሎ ከሰይጣን የሚመጣበትን ፈተና እየተቃወመ ኖረ። እንዲህ ያለውን የባሕታውያን ሕይወት ቅዱስ ጳውሎስ ከዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ምዕራፍ ፲፩፡፴፯ (11፡37) ገልጾታል።

> "...ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ።"
>
> ብሕትውና ከናዝራዊነት ጋር ይመሳሰላል። የሚለያዩበት ብሕትውና ለዘለለም ሲሆን ናዝራዊነት የሚያበቃበት ጊዜ አለው። ዘኁ ፮፡፲፫ (6፡13) ። ብሕትውና እንደ ዮሐንስ መጥምቅ ነው።
>
> "ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው

በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር።" ማቴ ፫፥፬ (3፥4)

መነኮሳትና ባሕታውያን መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ በጸሎት በጾምና በስግደት በመጠመድ በተለይ መጻሕፍተ መነኮሳትን፡-

- በርድና ጊዜ ፊልክስዮስን
- በተባሕትዎ ጊዜ ማር ይስሐቅን
- ጣዕም ከቀመሱ በኋላ ግን አረጋዊ መንፈሳዊን ማንበብ ይገባቸዋል፤

ማጠቃለያ፡- ጌታችን ዘማቴዎስ ወንጌል እንዳስተማረን የሰው ልጅ ሁለት ዕድል አለው። አንደኛ ማግባት ሁለተኛ መመንኰስ። ምዕ ፲፱፥፲፩ (19፥11)። ቅዱስ ጳውሎስም በመልእክቱ ይህንኑ ይደግመዋል።

> "ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ከራሱ የጸጋ ስጦታ አለው አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ።" ፩ቆሮ ፯፥፯ (7፤7)

<u>አለባበስ</u>፡-

ሀ. ቆብ፡- ጌታችን በቀራኒዮ መስቀል የደፋው የሾሕ አክሊል

ለ. ቅናት፡- ይህ መነኰሳት ሲመነኩሱ የሚታጠቁት ሰቅ፣ ገመድ ሲሆን ዮሐንስ መጥምቅ የታጠቀው ጌታ የታሠረበት ገመድ ምሳሌ ነው።

ሐ. ቀሚስ፡- የከለሜዳ ምሳሌ

መ. አስኬማ፡- የሰውነት ምሳሌ "ወተመስለ በአስኬማሁ"

መመንኩስ ከዚህ ዓለም መሞት ነውና በዚህ አምሳል ደግሞ ስናየው ቆቡ የሰበን፣ ቀሚሱ የመገናጸፊያ፤ ቅናት የመግነዝ፤ አስኬማ፤ የትንሳኤ ሙታን ምሳሌ ነው።

የአኪባበሉም ደረጃ ቅናትና ቀሚሰን በንጽሐ ሥጋ፤ ቆብን በንጽሐ ነፍስ፤ አስኬማን በንጽሐ ልቡና መአርግ ሆነው ይቀበሉታል። መቅድመ ፊልክስዩስ

# አሥርቱ መዓርጋት

**፩. ጽማዌ**፡- የዚህ ቃል መሠረት ጸመወ የሚለው የግእዙ ግስ ነው። ትርጓሜው (ፍችው) ጸጥ አለ ዝም አለ ማለት ነው።ይህ የልብ ዝምታ ነው። ከዚህ ቀድሞ የአፍ ዝምታ አለ። ይህም አርምሞ ይባላል። አርምሞ የአፍ ጽማዌ የልብ ዝምታ ነው።

የመጀመሪያው የቅዱሳን መዓርግ ጽማዌ ተብሎ ይጠራል። ቅዱሳን ከዚህ ደረጃ ሲደርሱ ከኃጢአት ይርቃሉ የዓለምን ነገር ይረሳሉ ቅዱሳን መላእክትን እስከማየት ደረጃ ይደርሳሉ። ሲወጡ ሲወርዱም ይመለከታሉ ከምን እንደሆነ ግን በዚህ ደረጃ አይረዱም።

**፪. ልባዌ**፡- ይህ ሁለተኛው የቅዱሳን መዓርግ ደረጃ ሲሆን በዚህ ደረጃ ቅዱሳን ለብዙ ጊዜ ከምግብና ከውኃ ተለይተው በመንፈስ ቅዱስ መግቦት የሚኖሩበት ነው። ቅዱሳን መላእክትንም እስከመለየት የሚደርሱበት ደረጃ ነው። ይህ ሚካኤል ነው ይህ ገብርኤል ነው ብለው ያውቋቸዋል።

**፫. ጣዕመ ዝማሬ**፡- ይህ ሦስተኛው መዓርግ ሲሆን ቅዱሳን ከዚህ ደረጃ በሚበቁበት ጊዜ አምላካቸውን ከማመስገን አይጠግቡም እንደመላእክት ያለማቋረጥ ያመሰግናሉ። የዝማሬያቸውም ድምፅ ኃይል ይኖረዋል።

> "ወቦ ዘትወዲ ውስተ ልቡ ዝማሬ" እግዚአብሔርን ማሰብ እግዚአብሔርን ማመስገን በልቡ የምታሳድርበት ጊዜ አለ። አረጋዊ መንፈሳዊ።

**፬. አንብዕ**፡- (ዕንባ) በፊልክስዩስ ተስእሎ 77 እንደተገለጸው ሀብተ አንብዕ አራተኛ የቅዱሳን ፀጋ ደረጃ ነው። ቅዱሳን ከዚህ ደረጃ በሚደርሱበት ሰዓት የጌታቸውን የመስቀል መከራና ሞቱን እያሰቡ ያለቅሳሉ። የገሃነመ እሳትን መከራም እያሰቡ የሚያነቡት በዚህ በአራተኛው መዓርግ ነው። ይህ የቅዱሳን የማዕረግ ደረጃ "አንብዐ ንስሐ" "የንስሐ ዕንባ" ተብሎም ይጠራል። ምክንያቱም ዕንባቸው ሳያቋርጥ ይፈሳልና።

"ቦ ዘትወዲ ውስተ ልቡ ሐልዮተ ሕማማተ እግዚእ" የጌታችንን ሕማም ማሰብ በልቡናው የምታሳድርበት አለ።

"ወይከው እምቀራንብቲሁ አንብዐ ውዑየ ዘእንበለ መስፈርት በተዘክሮ ሕማማቲሁ" "እንዲህ ቸነከሩህ እንዲህ ሰቀሉህ እያሉ አብዝተው ያለቅሳሉ።"

የክርስቶስን መከራ እያሰበ ሰው ሁሉ ማልቀስ አለበት። ደረጃው ግን ይለያያል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ብሎ ያዘናል ያስተምረናል

"ብከይዎ ወላህውዎ አከ ታፈቅርዎ"

"የምትወዱት ሰዎች አልቅሱለት"

<u>፭. ኩነኔ</u>፡- ቃሉ ኮነነ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ነው። ፍችውም ትርጓሜውም ገዛ ማለት ነው። ቅዱሳን ሰዎች ከአምስተኛው ደረጃ ከኩነኔ ሲደርሱ ሥጋቸውን ፍጹም ከነፍስ ያስገዛሉ። ስለዚህም መዐርግ ኩነኔ ተብሎ ተጠራ። በዚህ ደረጃ ቅዱሳን ሥጋቸውን ከነፍሳቸው ማስገዛት ብቻ ሳይሆን በዚያው እንደፀኑም መኖር ነው።

<u>፮. ንጻሬ</u>፡- ስድስተኛው የቅዱሳን መዓርግ ንጻሬ ወይንም ንጻሬ መላእክት ተብሎ ይጠራል። ከዚህ ደረጃ የበቁ ቅዱሳን የእግዚብሔር ሰዎች ባሉበተ ቦታ ሆነው ቅዱሳን መላእክትን በከተማቸው ማየት ይችላሉ። መላእክትን በአሥሩ ከተማ በመቶ ነገድ ፈጥሯቸዋልና ይህን ከመመልከት ይበቃሉ።

<u>፯. ሑሰት</u>፡ በዚህ ደረጃ ቅዱሳን እንደ ፀሐይ ብርሃን (እንደ አግረ ፀሐይ) ከሁሉም ቦታ ይደርሳሉ። እንደውም ፀሐይ ወጥታ ብርሃኗ ምድር ከመድረስ ስምንት (8) ደቂቃ ከሃያ (20) ሰከንድ ያህል ይፈጅባታል። ከሑሰት የደረሱ ቅዱሳን በዚህ ይመስሉ እንጂ ከነሱ አንድ ሰከንድም አይፈጅባቸውም

<u>፰. ተሠጥሞ</u>፡- ከዚህ ደረጃ የበቁ ቅዱሳን በባሕረ ብርሃን (በብርሃን ባሕር) ይቃኛሉ። "ወኀሊናየ ምሡጥ በተደሞ ዘርእየ እግዚብሐር" ሲጸልዩም መልክዐ እግዚአብሔርን

በማየት፡ በተመሥጦ ሳለ "ይመጽአኒ ዲበ ሥጋየ ህድመት" በሥጋዬም ህድመት (ተመሥጦ) ይመጣብኛል ይላል።

፱. ፍቅር፡- ቅዱሳን ከዚህ በደረሱ ጊዜ አማኒ መናፍቅ ኀጥእ ጻድቅ ባዕድ ዘመድ ሳይሉ ሁሉን እስተካከለው ይወዳሉ።

፲. ከዊነ እሳት፡- ከዊነ እሳት በሌላ አጠራር ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ ይባላል። ይህ የቅዱሳን የመጨረሻ ደረጃ ነው። ከዚህ ደረጃ ሲደርሱ ቅድስት ሥላሴ ን በኪሩቤል ዘባን ዙፋናቸው እንዳሉ ይመለከታሉ።

> "ናሁኬ አርአዮሙ ገጾ" ፊቱን ከማየት አብቅቷቸዋልና። እንደ ባስልዮስ ዘቂሣርያ። ቅዱስ ኤፍሬም እንዳየው አባ ባስልዮስ ከከዊነ እሳት ደርሶ ነበር።

## ባለሠላሳ፣ ስድሳና ባለመቶ የመዓርጋት ምሥጢር

የቅዱሳን የብቃት ደረጃ እንደተጋድኢቸው የተወሰነ ነው። ጌታችን በወንጌሉ በምሳሌ እንደነገረን ባለሠላሳ፣ ባለስድሳ ባለመቶ ፍሬ የሚያፈሩ በሦስት ወገን የተከፈሉ የቅዱሳን የጽድቅ ደረጃን እንመለከታለን።

> "ቦ ዘምዕት ወቦ ዘስሳ ወቦ ዘሠላሳ" መቶ፣ ስድሳ፣ ሠላሳ የሚያፈራ አለ ማቴ. ፲፫፥፳፫ (13፥23) ቅዱሳን ሰዎች የብቃት ደረጃ ለመድረስ የዓለም የሆነውን ነገር ሁሉ በመተው መስቀሉን ብቻ ተሸክመው ከዚህ ዓለም የጣዕም ኑሮ ይሰደዳሉ። ኃላፊ በሆነውም በዚህ ከንቱ ዓለም እንደመጻተኛ ማለትም እንደ ቋሚ ፀላለማዊ ሳይሆን እንደ እንግዳ ይኖራሉ።

"እንግዶች እንደሚሆኑ በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ...እንደመጻተኛ በእምነት ተቀመጠ" ዕብ. ፲፩፥፱ (11፥9) ሥጋቸውን ከነፍሳቸው ነፍሳቸውንም ከፈጣሪያቸው አስገዝተው ጸዋሚ፣ ተሐራሚ፣ ዝጉሐዊ፣ ባሕታዊ በመሆን በጸሎት በመጠመድ በበረሃ በገዳም ይኖራሉ። እርዓያቸውም ጌታችን

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጾዋሚ ማለት ጾመኛ፣ ተሐራሚ ማለት ከሐጢአት ሥራ የራቀ ከዓለም ነገር የተከለከለ፣ ዝጉሐዊ ማለት ራሱን ለይቶ በዐቱን ዘግቶ ወደ ዓለም ሳይወጣ የሚኖር፣ ባሕታዊ ማለት ራሱን ለይቶ በገዳም፣ በበረሃ፣ ለብቻ መኖር ነው።

> "ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ" ዕብ. ፲፩፥፴፯ (11፥37)

ቅዱሳን ሰዎች በዚህ ዓይነት ሕይወት ሲገኙ። የንጽሕና ደረጃቸው ከዝቅተኛነት ወደ ልዕልና ከፍ እያለ ይሄዳል። ደረጃቸውም ባለ ሠላሳ ባለ ስልሳ እና ባለ መቶ እንዳለው እንዲሁ ይሆናል። ይህም ወጣኒ፣ ማዕከላዊና ፍጹማዊ ደረጃ ይባላል።

## ወጣኒ፣ማዕከላዊና ፍጹም

አንደኛ ደረጃ ወጣንያን፡- ይህ የጀማርያን ደረጃ ነው። ጀማሪነታቸው ከእምነቱ ሳይሆን የብቃትና የቅድስና ነው። ይህም ፍጹም ከኃጢአት በመራቅ ነው። በዚህ ደረጃ ያሉ ወጣንያን ተብለው ይጠራሉ።

ሁለተኛው ደረጃ፡- ማእከላውያን፡- በዚህ ጊዜ ቅዱሳን የወጣኒነት የመጀመሪያውን ደረጃ አልፈው የበለጠ ጸጋና ክብር የሚይዙበት ደረጀ ነው። ወደ ሦስተኛው ደረጃ የሚቀርቡበት ስለሆነ መካከለኛው ደረጃ ተብሎ ይጠራል።

ሦስተኛው ደረጃ፡- የፍጹማን፡- የመጨረሻው የቅዱሳን ደረጃ የፍጹማን ደረጃ ነው። እነዚህ ሦስት የቅዱሳን የብቃት ደረጃ ሲሆኑ ይህም የሚሰጣቸው እንደተጋድሏቸው ብዛትና እንደሃይማኖታቸው ጽናት እንዲሁም እንደእእምሮ ስፋት ነው። እነዚህም በሦስቱ የንጽሕና ደረጃዎች ይገኛሉ። ይህም እንዲህ ነው፡-

## ንጽሐ ሥጋ፣ንጽሐ ነፍስና ንጽሐ ልቡና

፩. ንጽሐ ሥጋ፡- ይህ የሥጋ ንጽሕና ተብሎ የሚጠራው ሲሆን በዚህ ውስጥ ሦስት የቅዱሳን የማዕረግ ጸጋዎች አሉ። ንጽሐ ሥጋ ቀዳማዊ(ት) ተብሎ ይጠራል።

፪. ንጽሐ ነፍስ፡- ይህ ማለት የነፍስ ንጽሕና ነው። ቅዱሳን ንጽሐ ሥጋ ሲኖራቸው ይህ ንጽሐ ነፍስ ይጨመርላቸዋል። ይህም ማእከላዊ(ት) ይባላል። በዚህ በንጽሐ ነፍስ ሦስት የማዕረግ ደረጃዎች አሉ።

፫. ንጽሐ ልቡና፡- ሦስተኛው የቅዱሳን የንጽሕና ደረጃ ንጽሐ ልቡና የልብ ንጽሕና ነው። ይህ የመጨረሻው የፍጹማን ደረጃ ስለሆነ ፍጻሜ ተብሎ ይጠራል። ቅዱሳን በዚህ ደረጃ ውስጥ በአንደኛው ደረጃ በንጽሐ ሥጋና በሁለተኛው ደረጃ በንጽሐ ነፍስ ያሉትን ስድስቱን መዓርጋት እንደያዙ ሌላ አራት መዐርጋት ይሰጣቸዋል።

1. ባለሠላሳ= ወጣንያን= ንጽሐ ሥጋ= መዓርጋት ከ1-3

2. ባለስድሳ=ማዕከላውን=ንጽሐ ነፍስ = መዓርጋት ከ4-6

3. ባለመቶ=ፍጹማውያን=ንጽሐ ልቡና=መዓርጋት ከ7-10

ስለዚህ በነዚህ የንጽሕና ደረጃዎች ውስጥ ቅዱሳን የሚያገኙአቸው የመዓርጋት ደረጃዎች ዐሥር ይሆናሉ። እነዚህም ዐሥሩ መዓርጋት ተብለው ይጠራሉ።

# ቅዱስ መስቀል

መስቀልን ቅዱስ ብለን እንጠራዋለን ጌታችን በርሱ ተሰቅሎ ከስድስት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት በመቆየት ደሙን አፍሶ አድኖናልና። ጌታችን ክብር ይግባውና በመስቀል ስለኛ ተቸንክሮ ተሰቅሏል በስቅላቱም ዲያብሎስ አፍሯል፣ ሞተ ነፍስ ተሽሯል፣ ሲኦል ተመዝብሯል፣ ነፍሳት ከጨለማ ወጥተዋል፣ ገነት ተከፍቷል፣ ሥጋውና ደሙ ተሰጥቷል፣ ድንግል ማርያም በእናትነት ተሰጥታለች። ከዚህም የተነሣ መስቀል ለክርስቲያኖች ቅዱስ ነው፣ መድኃኒት ነው፣ ቤዛ ነው፣ ኃይል ነው፣ መመኪያ ነው፣ የነፍስ መዳኛ ነው፣ የማንነትና የእምነት መገለጫ ነው፡ ሐዋርያው እንዲህ ይገልጸዋል።

> "ወአንሰ ሐሰ ሊተ ኢይዜኀር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ወበኀቤየሰ ምዉት ዓለም ወአነሂ ምዉት በኀበ ዓለም"
>
> "ነገር ግን ዓለም ለኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከኔ ይራቅ" ገላ. ፮፥፲፬ (6፥ 14)

የክብር ባለቤት አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ እኛን ሊያድን ከሰማይ ወረደ ፍጹም ሰው ሆነ ፍጹም አምላክ ሲሆን ራሱን ዝቅ አድርጎ በትሕትና መጣ ባለፀጋ አምላክ ሲሆን ራሱን ስለእኛ ደኃ አደረገ ፪ ቆሮ ፰፥፱ (8፥9) ሲወለድ በከብቶች በረት ሲሰቀልም የመስቀል ሞት ተፈረደበት እንደ ወንጀለኛም ተቆጠረ። በሕግም በእንጨት የተሰቀለ የተረገመ ነው፡ እንዳለ ንጹሐ ባሕርይ የሆነውን እንደ ወንበደ ቆጥረው በመስቀል ሰቀሉት ዘዳ. ፳፩፥፳፫ (21፥23)። ጌታን ስለሰቀሉት ስለዘመዶቹ፡ ኢሳይያስ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር።

> "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሟል እኛ ግን እንደተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው ። እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቈሰለ"

ኢሳ. ፶፫፥፬ (53፥4)

ነቢዩ የሆነውን ሁሉ በእምነት ተመልክቶ ከመስቀሉ ከስባት መቶ ዓመታት በፊት ግፍን ሳያደርግ በአፉም ተንኮል ሳይገኝበት በግፍ እንደተሰቀለ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ እንደሰጠ የሰው ልጆችን ኃጢአት ተሸክሞ ከዓመፀኞች ከወንበደዎች ጋር እንደተሰቀለ ትንቢቱን ጽፏል። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ስለመስቀሉ ሞት ሲናገር ኢየሱስ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ ራሱን ግን ዝቅ አድርጎ ለሞትም እንደተሰጠ ለሞትም ደግሞ ያውም የመስቀልን ሞት እንደተቀበለ ገልጿል።

> "ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ። በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ" ፊል. ፪፥፯ (2፥7)

## የመስቀል ምልክት በሰማይ

እግዚአብሔር አምላክ ወደፊት የሚሠራውን የሚያውቅ አምላክ ነውና የወደቀውን አዳም በመስቀሉ እንደሚያድነው ሰይጣንንም በመስቀሉ ድል እንደሚመታው ያውቃል። በቤተክርስቲያናችን ትምህርት መሠረት ሚካኤልና ቅዱሳን መላእክት የሰይጣንን ኃይል ድል መትተው ከሰማይ የጣሉት በመስቀል ምልክት ነበር።

> "በሰማይም ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውምም" ራዕ. ፲፪፥፯ (12፥7)

በሰማይ ያሉ ቅዱሳን መላእክት ክብርና ስግደት የሚገባውን ልዑል እግዚአብሔር ያለአረፍት ያመሰግኑታል። ሲያመሰግኑም ክንፎቻቸውን በትአምርተ መስቀል (በመስቀል ምልክት) አድርገው ነው። ይህንንም መንፈስ ቅዱስ ከነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ገልጾለታል።

> "ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን

ይሸፍን ነበር በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር።" ኢሳ. ፮፥
፪ (6፥2)

በዚህ የኢሳይያስ ትንቢት ለንመለከት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የሚያመሰግኑት ቅዱሳን መላእክት ሱራፌልን ክንፎቻቸውን የሸፈኑበትና የሚበሩበት ቅርጽ የመስቀል ነው። ይህንን በትርጓሜው ትእምርተ መስቀል ይለዋል። የመስቀል ምልክት ማለት ነው፡

ገባሬ ተአምራት ወመንከራት ቅዱስ ጎርጎርዮስ እኛ ባሮችህ በዚህ አምሳል እናመሰግንሃለን ብሏል።

"ወንህነ አግበርቲከ ትሑታን ከማሆሙ በስፍሐተ እድ እንዘ ናነሥእ እደዊነ ወእንዘ ናስተማስል በአርአያ መስቀል ንሴብሐከ ወንዌድስከ።"

"እኛም ትሑታን ባሮችህ እንደነርሱ እጅን በመዘርጋት እጃችንን አንስተን መስቀልን አስመስለን እናከብርሃለን እናመሰግንሃለንም፡

## የመስቀል ምልክት በዘመነ ብሉይ

በሰማይ የታተመው በብሉይ በምሳሌ ተገልጿል በሐዲስ ደግሞ ተፈጽሟል። ይህም ማለት በግልጽ ፍጹም ሆኖ ታይቷል። በዘመነ ብሉይ የመስቀልን ነገር በተለያየ ምሳሌ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑና ከሕዝቡ ገልጾ አስታውቋል። አስቀድሞ እግዚአብሔር በብዙ ኅብርና ምሳሌ ከአባቶቻችን አስታውቆ ነበር ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደነገረን ዕብ. ፩፥፩ (1፥1) ከነዚህም መካከል እነዚህ ይገኛሉ።

፩. የቅዱስ ያዕቆብ ዘንግ አባታችን ያዕቆብ ልጆቹን ሁሉ ከባረከ በኋላ በዘንጉ ጫፍ ተጠግቶ ከእግዚአብሔር ሰገደ ይላል። ዘፍ. ፵፯፥፴፩ (47፥31) ዕብ. ፲፩፥፳፩ (11፥21) በዚህን ጊዜ ያዕቆብ ከግብፅ አ'ነደሚወጣ በአገሩም እንዲቀብረው ከዮሴፍ አምሎት ነበር። ይህም ጌታችን በግብፅ በባርነት የነበረችን ነፍስ ማለትም በሲኦል በዲያብሎስ አገዛዝ የተያዘችን ነፍስ በመስቀሉ

እንደሚያድን ያዕቆብ ያይና ያውቅ ስለነበር ነው። በዚህ ዓይነት የመስቀል መስተብቊዕ፡- "ጸልዩ ቅድመ መስቀል ኲልክሙ መሃይምናን እንዘ ትእኅዝዎ በየማን ወትክሕድዎ ለሰይጣን እስመ ተቀደሰ በደመ ክርስቶስ መድኅን"

> "ሁላችሁ ምእመናን ሆይ ሰይጣንን እየካዳችሁ መስቀልን በቀኝ እጃችሁ እየያዛችሁ በመስቀል ፊት ጸልዩ በመድኅን ክርስቶስ ደም ተቀድሷልና" ብሎ በዲያቆኑ ያዛል።

፪. እስራኤልና አማሌቃውያን በራፊዲም ምድረ በዳ በተዋጉ ጊዜ ሙሴ ከአሮንና ሖር ጋር ወደተራራ የእግዚአብሔርን በትር ይዞ ወጣ ይላል። ኢያሱም ጎልማሶችን መርጦ ከአማሌቅ ጋር ተዋጋ በዚህን ጊዜ ሙሴ እጆቹን ዘረጋ እስራኤልም አሸነፈ። ሙሴም የያዘው የእግዚአብሔር በትርና እጆቹን የዘረጋበት የቅርጽ ሁኔታ የመስቀል ምሳሌ ነበር። ጌታችን በቀራንዮ ተራራ በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ እጆቹንም ዘርግቶ ከሞት በደሙ ፍስት እንዳዳነን የሚገልጽ ነው። ዘጸ. ፲፯፥፰-፲፮ (17፥8-16)

> "ሰፍሐ እደዊሁ ዲበ ዕፀ መስቀል ከሕማም ከመ ይፈውስ ቊስለ ሕሙማን በንዝኃተ ደሙ"

> "በዕፀ መስቀል ላይ እጁን ዘረጋ በደሙ መረጨት የሕሙማንን ቊስል ያድን ዘንድ" ኤጲፋንዮስ

ከዚህ በተጨማሪ ሙሴ ቀይ ባሕርን የከፈለበት እንጨት (በትረ ሙሴ) ክርስቶስ እምላካችን ቀይ ባሕርን የተመሰለችባት ሲኦልን በመስቀሉ ትርከዛ እንዳሻገረን የሚያሳይ ነው።

፫፥ በትረ አሮን፡- በዘመነ ብሉይ በቤተመቅደሱ ወይም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የነበረች የአሮን በትር ዛሬ በመቅደሳችን ካለው መስቀል ምሳሌ ነበረች።

> "ወሊሉየ መልክዕ ወእምሳል እመልክዐ በትሩ ለአሮን ካህን ጽላሎት ወእምሳል።" መስተብቊዕ ዘመስቀል"

> "… የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ" ዕብ. ፱፥፬

(9፥4)

## የመስቀል ምልክት በዘመነ ሐዲስ

"እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በርሱ እንዲኖር በርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ከራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና" ቆላ. ፩፥፳ (1፥20)

ከገነት ተባሮ የነበረ የሰው ልጅ ወደቤቱ የተመለሰው በመስቀል ላይ በፈሰሰ ደም ነው። ደሙም የዕሩቅ ብእሲ (የተራ ሰው) ሳይሆን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። በኦሪት ዘፍጥረት ፫፥፳፫ (3፥23) እንደተጻፈው እግዚአብሔር አዳምን ከዔደን ገነት አስወጥቶ በኪሩቤልና በምትገለባበጥ ሰይፍ እንደዘጋት እናያለን። ይህች የተዘጋች ገነት የተከፈተችው ጌታችን በመስቀሉ ላይ ባደረገው የማዳን ተግባር ነው። ጌታችን በመስቀሉ ላይ በነበረ ሰዓት በቀኙ ተሰቅሎ የነበረው ጥጦስ የተባለው ወንበዴ በዚያች ቅጽበት ባገኘው ንስሐ አቤቱ በመንግሥትህ አስበኝ ባለ ጊዜ ጌታችንም ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ ብሎታል። በዚህን ጊዜ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው የጥል ግድግዳ ፈረሰ ገነትም ተከፈተች። ሉቃ. ፳፫፥፵፫ (23፥43)

"በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንን በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽህፈት ደመሰሰው እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል" ቆላ. ፪፥ ፲፬ (2፥14)

በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት በምሳሌ ሲገለጽ የነበረው የመዳናችን ጉዳይ የመስቀሉ ምሥጢር ጌታችን በቀራንዮ ስለእኛ ሲሰቀል ድኅነትና ኃይል እንደሆነ በጉልህ ታወቀ።

"ቀራንዮም ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ በዚያ እርሱን ከፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ" ሉቃ. ፳፫፥፴፫ (23፥33)

አምላካችን በዕለተ ዓርብ በተሰቀለ ጊዜ ሰዓቱ ስድስት ሰዓት ነበረ ከመስቀሉም ባወረዱት ጊዜ አሰራ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበረ። ነፍሱን አሳልፎ የሰጠውም ልክ በዘጠኝ ሰዓት ላይ ነበር። ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ሰባት ቃላትን ተናግሯል። እነዚህም ለምናምን ኃይል ለማያምኑት ግን ሞኝነት ሆኖአል። ፩ቆሮ. ፩፥፲፰ (1፥18)። በዚያን ጊዜ የተከሰቱትም ተአምራት ሰባት ነበሩ። ይህ ሁሉ ለከመዳናችን ለለእኛ የሆነ ነበር።

"በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን" ኢሳ. ፶፫፥፭ (53፥5)

## ስግደት ለመስቀል

መስቀልን አክብረን እንሰግድለታለን። ምክንያቱም ጌታችን ያዳነን በእርሱ ላይ ተሰቅሎ ስለሆነ ቅዱስ ደሙ ስለፈሰሰበትና ስለተቀደሰ፡ የተቀደሱ እጆቹና እግሮቹ ስላረፉበት ሰይጣንና አሠራሩ በመስቀል ስለተደመሰሱ።

"ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ"

"እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን" መዝ. ፻፴፩፥፯ (131፥7)

ጌታችን የተሸከመበትን ሰዓት ትተን እግሮቹ በመስቀሉ ላይ ስድስት ሰዓት እንደቆሙ እናውቃለንና እንሰግድ ለታለን። በምንሰግድበትም ጊዜ በርሱ ተሰቅሎ ያዳነንን የመድኃኒታችንን መከራውን እናስባለን። በመስቀሉም አንፃር የመድኃኒታችንን መከራውን እናስባለን። በመስቀሉም አንፃር ለፈጣሪያችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንሰግድለታለን። ያዕቆብ በዘንጉ ለአምላክ እንደሰገደ ምሳሌነቱ ለመስቀል ነውና።

"በዘንጉም ጫፍ ተጠግቶ ሰገደ" ዕብ. ፲፩፥፳፩ (11፥21)

ከዚህም የተነሳ በዘወትር ጸሎታችን እንዲህ እንላለን፡-

"እሰግድ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተቀደሰ በደሙ ክቡር መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ"

"በክቡር ደሙ ለተቀደሰው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እሰግዳለሁ። መስቀል ኃይላችን ነው። መስቀል ጽንዐችን (መጽናኛችን) ነው። መስቀል ቤዛችን ነው። መስቀል የነፍሳችን መዳኛ (መድኃኒታችን) ነው። ምስጋና እንደሚገባውም ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ነግሮናል፡-

"ስብሐት ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ"

"ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ምስጋና ይገባል"

ቅዱስ ዳዊት እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን ካለ ፡ለስገደ አባታችን ያዕቆብ በዘንጉ አምሳል ለእግዚአብሔር ከሰገደ የመድኃኒታችን ደም ለፈሰሰበት ለተፈወስንበት ለቅዱስ መስቀል አብልጠን ልንሰግድ ይገባናል እንሰግዳለንም።

## መስቀልን መሳምና መሳለም

መስቀልን በእጃቸው ይዘው ማሳለም የሚችሉ ካህናት ብቻ ናቸው። ዲያቆን ቅስና እስከሚያመጣ መስቀል ማሳለም አይችልም። መስቀልን ተሳልመን የምንስመው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት ስላለን ነው። በምንሳለ ምበትና በምንተሻሸበት ጊዜ ቅዱስ ነውና እንቀደሳለን መድኃኒት ነውና እንፈወሳለን የአጋንንትም ኃይል ከኛ ይርቃል። መስቀል የሁላችን ቤዛ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሠዋበት መሠዊያው ነውና።

"መሠዊያውም ቅድስተ ቅዱሳን ይሆናልመሠዊያዉንም የሚነካ ሁሉ ቅዱስ ይሆናል" ዘጸ. ፳፱፥፴፯ (29፥37)

ጌታችን መድኃኒታችን የነካው ሁሉ የተቀደሰ ነው። ይህንን ሥልጣኑንም ከካህናት ለሌለ ካህናት በሰሙ የሚባርኩት ሁሉ የቤተመቅደስ ዕቃ ቅዱስ ነው። መስቀሉን ስንሳለመው ድኅነት ይሰማናል። በወንጌል እንደተፃፈው ጌታችን የለበሰውን ልብስ ጫፍ ብትነካ ከሕመሟ እንደተፈወሰችው ሴት ነው።

"ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደሆነ እድናለሁ ትል ነበረችና" ማቴ.፱፥፳ (9፥20)

ስንነካው የምንፈወስ ስንሳለመው የምንቀደስ ስለሆነ መስቀሉን ቅዱስ ብለን እናከብረዋለን። ይልቁንም በምንስመው በምንሰግድለት ሰዓት ሁሉ ተሰቅሎ ያዳነንን መድኃኒታችንን እናስበዋለን።

መሳም ፍቅርን ለመግለጽ መውደድን ለማሳየት የሚፈጸም ነው። የዳንበትን መስቀል በምንስምበት ጊዜ እንደ ማርያም ባለሽቶዋ ኃጢአታችን እያመንን ከንስሐ ሕይወት ራሳችንን አቅርበን ከመፈወስ ነው።

"እግሩንም ትስመው ሽቱም ትቀባው ነበረች"ሉቃ. ፯፥፴፰ (7፥38)

አዳምንና ሔዋንን በገነት የፈለጉ በባለሽቱዋ ማርያም የተቀቡ ቅዱስ እግሮቹ ነበሩ በዕፀ መስቀል በክፉዎች የተቸነከሩትና የተሰቀሉት።

"እጆቹንና እግሮቹን ቸነከሩኝ አጥንቶቹ ሁሉ ተቆጠሩ" መዝ. ፳፩፥፲፯ (21፥17)

# መስቀል ልዩ ነው

በቤተመቅደስ ያለው መስቀልና በካህናት እጅ የሚገኘው መስቀል ሁሉ በተለየ ጸሎትና ቅብዕ ተባርኮ ይቀደሳል። ዝም ብሎ እንደተገኘ አይያዝም። ሌላ ቀርቶ ምእመናን ባንገታቸው የሚያደርጉትን መስቀል በካህናት አስባርከው ማድረግ አለባቸው። የተመሰቀለ እንጨት ሁሉ መስቀል ሊሆን አይችልም መስቀል የአሮን በትር ምሳሌ ናት እንዳልን። የአሮን በትር ደግሞ ከሌሎች በትሮችና እንጨቶች ሁሉ የተለየች ነበረች። ሊቀ ነቢያት በየነገዱ የሰበሰበውን በትሮች ወደ መቅደሱ ባስገባ ጊዜ የአሮን በትር ግን ከሌሎች በትሮች ይልቅ አቆጠቆጠች ለመለመች አበበች አፈራችም በምስክሩም ፊት ምልክት ሆና ተቀመጠች። የሌሎችም በትሮች እንዳልተመረጡ እግዚአብሔር በዚህ ተአምር ለሕዝቡ ገለጸ። ዛሬም መስቀላችን ልዩ ተአምር የተሠራበት ከሌሎች ከተመሳቀሉ ነገሮች ሁሉ የተለየ በጸሎትና በቅብዕ የከበረ ነው። ሌሎች ንዋያተ ቤተመቅደስ ሁሉ የሚባረኩት በመስቀል ነው። ዘኁ. ፲፯፥፩-፲፩ (17፥1-11)

## የመስቀል ጠላቶች

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን መስቀልና የመስቀሉ ቃላት ለእኛ ኃይልና መዳኛ ሲሆኑ ለማያምኑት ግን የሞኝነት ነገር እንደመሰላቸው ይኖራል።

> "እስመ ነገረ መስቀሉስ ዕበድ ውእቱ በኀበ ሕጉላን ወበኀቤነሰ ለእለ ድኅነ ኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ"
>
> "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና" ፩ቆሮ. ፩፥፲፰ (1፥18)

ኃይል ሆኖናልና እንሳለመዋለን፣ እንሰግድለታለን፣ እንስመዋለን፣ የሚገባውን ክብር እንሰጠዋለን።ጌታችን በርሱ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ አድኖናልና። ሐዋርያው እንደተናገረ ትምክሕታችን ነውና። ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆኑ ሰዎች እኛ ለመስቀል የምንሰጠውን ክብርና

ስግደት እንደሞኝነት ከማየት ባሻገር ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነዋል ቅዱስ ጳውሎስ መጨረሻቸውን ስለሚያውቅ እያለቀሰላቸው በመልእክቱ ጽፎ እናገኘዋለን።

> "ብዙዎች ከክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና ብዙጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ። መጨረሻቸው ጥፋት ነው ሆዳቸው አምላካቸው ነው ክብራቸው በነውራቸው ነው …" ፊልጵ. ፫፥፲፰-፳ (3፥18-20) ለእኛ ግን ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረ መስቀል ጠላት ዲያቢሎስን ድል የምናደርግበት ልዩ ምልክታችን ነው።

> "ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ፡ ከመ ያምስጡ እምገጸቅስት ወይድኅኑ ፍቁራኒከ"

> ለሚፈሩህ ምልክት ሰጠሃቸው፡ ከመከራ (ከጦር) ፊት ያመልጡ ዘንድ ወዳጆችህ እንዲድኑ።" መዝ. ፶፱፡፬ (59፡4)

በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ከራሱ፣ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያስታረቀን ኃያሉ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ተመክተን እንድንኖር ጸጋውን ያድለን።

# ማማተብ

ጸሎት በምንጀምርበት ጊዜና በምንፈጽምበት፣ በምንሰግድበትና በምንሳለምበት፣ እንዲሁም መስቀልን የሚያነሳ ቃልን በምንጸልይበት ጊዜ የሚያስደነግጥ ነገርን በምንሰማበትና በምናይበት ጊዜ በመስቀል አምሳል ገጻችንን እናማትባለን። ጸሎት በምንጀምርበት ጊዜ በማማተብ ይህንን ቃል እንላለን፡-

"አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል"

"ፊቴንና መላ ሰውነቴን በመስቀል ምልክት አማትባለሁ"

ይህን በምንልበት ጊዜ ፊታችንን ከግንባራችን ጀምረን ወደታች ወደ ደረት እንወርድና ከዚያ ወደ ግራ ሔደን ወደ ቀኝ እንመለሳለን። በዚህ ጊዜ መስቀል እንሠራለን። ይህም በጣታችን የመስቀል ምልክት በመሥራት ነው። በዚህ ጊዜ የሰይጣን መንፈስ ይርቃል መንፈስ ቅዱስ ይቀርባል። በጣታችንም የምናማትብበት ምሥጢሩ ይህ ነው።

"ወእመሰ አነ በአጽባዕተ እግዚአብሔር አወጽኦሙ ከአጋንንተ የጊ በጽሐት እንከሰ ኀቤከሙ መንግሥተ እግዚአብሔር"

"እኔ ግን በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንኩ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።" ሉቃ. ፲፩፥፳ (11፥20)

## በማማተብ ያለ ምሥጢር

በመጀመሪያ በቀኝ እጅ ጣቶች የመስቀል ምልክት እንሠራለን። ይህም መስቀል ምልክታችንና ዓርማችን እንደሆነ እንመሰክራለን። ከዚያም ገጻችንን እናማትባለን። በዚህም ጊዜ የምናስበውና የምንመሰክረው ምሥጢር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ኃይል ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገራችንን ነው።

ከግንባር ጀምረን ከላይ ወደ ደረት ወደታች በምንወርድበት ጊዜ አምላካችን እኛን ከማዳን ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን በእጥር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ለክእኛ በዚህ ምድር ሞትን ቀምሶ እኛን የማዳኑን ነገር እናስባለን።

በመቀጠልም ወደ ግራ አድርገን ወደቀኝ ተመልሰን ማማተባችን፡- በኃጢአታችን ምክንያት ያመጣነውን ሞት አጥፍቶ ከግራ ቁመት ከነፍስ ሰደት አውጥቶ ወደ ቀኝ ቁመት ገነት መንግሥተ ሰማያት እንደመለሰንና እንዳስገባን አምነን የምናስብበት ነው። እንደገናም በኃጢአት ብንወድቅ በንስሐ አጥቦ ከፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ከቀኝ ከሚቆሙት ቅዱሳን ጋር እንዲቆጥረን እንማጸናለን።

«ወያቀውም አባግዐ በየማኑ ወአጣሌ በፀጋሙ»

«በጎቹን በቀኙ ፍየሎቹንም በግራው ያቆማቸዋል» ማቴ. ፳፭፥፴፫ (25፥33)

ድካነታችንን ሁልጊዜ ከማሰብ ጋራ በምናማትብበት ጊዜ የሰይጣንን መንፈስ የምናርቅበት ኃይላችን የሆነ መስቀልን እንደምንመካበት እንገልጻለን። ለክዚህም ሁልጊዜ ማማተብ እንደሚገባ በፊልክስዮስ (ገብረ ክርስቶስ) ተስእሎ 29 በምሳሌ ተቀምጧል።

# ፲፪ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስና በእንተ እግዝእትነ ማርያም

በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ሁል ጊዜ ካህኑ እግዚአብሔር ከታሰራችሁበት የኃጢአት ማሠሪያ ይፍታችሁ ሲል ፲፪ (12) ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስና ፲፪ (12) ጊዜ ደግሞ በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ ያሰብካል። ካህናትና ምእመናን በሙሉ በጣቶቻችን እየቆጠርን ይህንኑ ፲፪ (12) ጊዜ እንላለን።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ማለት- አቤቱ ክርስቶስ ማረን ሲሆን በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ ደግሞ ስለ እመቤታችን ማርያም ብለህ ክርስቶስ ሆይ ማረን ማለት ነው።

አስራ ሁለት ጊዜ እግዚኦ መሐረነ መባሉ ለቀኑ 12 ሰዓት፤ በእንተ እግዝእትነ ማርያም ደግሞ ለሌሊቱ 12 ሰዓት ሲሆን በአጠቃላይ በየሰዓቱ ለሠራነው ኃጢአት ለሃያአራቱ (24ቱ) ሰዓት ምሕረትን እናገኝ ዘንድ ነው።

ሌላው አሥራ ሁለት ጊዜ የሆነበት ምክንያት፡-

1ኛ. በስመ ሥላሴ ነው። በእያንዳንዱ ፊደል

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ብ | ወ | ል | ድ | መ | ን | ፈ | ስ | ቅ | ዱ | ስ |
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ | ፲፩ | ፲፪ |

2ኛ. የድኅነታችን ምክንያት በሆነችው በእመቤታችን ስም ፊደል

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅ | ድ | ስ | ት | ድ | ን | ግ | ል | ማ | ር | ያ | ም |
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ | ፲፩ | ፲፪ |

አቆጣጠሩም እግዚኦ መሐረነ ሲባል በእውራጣት እየቆጠሩ ከጠቋሚ ጣት ወደታች፡ ቀጥሎ በመሐል ጣት ወደላይ፡ ከዚያም በቀለበት ጣት ወደ ታች፡ ተደርጎ በማርያም ጣት (በትንሿ) ጣት ወደላይ ነው።

ከጠቋሚ ጣት ወደታች፡- አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት መውረዱን በዚህ ምድር መመላለሱን ሕማሙንና ሞቱን እናስባለን።

መሐል ጣት ወደላይ፡- ማረጉን፡ ወደ ሰማይ መውጣቱን፡ በቀለበት ጣት ወደታች ስንቆጥር፡- ለፍርድ መምጣቱን፡

በትንሿ ጣት ወደላይ ስንወጣ ፡- ደግሞ ሁላችንን በትንሳኤ ዘጉባኤ ይዞን ወደሰማይ እንደሚያወጣን እያሰብን ነው።

በእንተ እግዝእትነ ማርያም ስንል አቆጣጠሩ፡- ከትንሽ ጣት ወደታች ይጀመርና በጠቋሚ ጣት ወደላይ ይፈጸማል። ይህም እመቤታችን ድንግል ማርያም ከትሕትና ወደልዕልና ከፍ ማለቷን የሚያሳይ ምሥጢር ነው።

## መቁጠሪያ

በአብዘኛው መቁጠሪያ የሚይዙት መነኮሳት እንዲሁም በዕድሜ የገፉ ምእመናን ናቸው። ጥቅሙም በጸሎት ጊዜ በተለይ እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ፡ ኪሪያራይሶን 41 ጊዜ ሲደገም በመቁጠሪያው እየቆጠሩ በተመሰጦ ለመድገም ነው።

ቁጥሩ፡- በአብዛኛው ጊዜ 41 ነው። ከዚያም በላይ በተለያየ ምሳሌ መቁጠሪያን የሚይዙ አሉ። 41 የሆነበት ምሥጢር በጌታችን ግርፋት አምሳል ነው። ጌታችንን 40 ጊዜ እንዲገረፍ በፈረዱበት ጊዜ አነሱ ግን እያተረፉ ገርፈውታል ስለዚህ መቁጠሪያው አትርፈው የገረፉትን ለማሰብ 41 ይሆናል። 41 ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እየተዜመ በቅዳሴው የሚባለውም ምሥጢሩ ከዚህ ጋር አንድ ነው።

የመቁጠሪያ ምሳሌነት፡- ይህም ጌታችን የተገረፈበት ጅራፍ ምሳሌ ነው።

# ቤተ መቅደስ

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሰማይ ዙፋኑ ምድር የእግሩ መረገጫ ቢባልም እርሱ ግን ሰማይና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት የነበረ በሁሉ የመላ አምላክ ነው።ይህ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ፍጥረቱ የሆነው የሰው ልጅ እርሱን ያመልክበት ዘንድ ማደሪያዬ ብሎ ቤተ መቅደስ ይሠሩለት ዘንድ የሰው ልጆችን አዝዟል።

"በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ" ዘጸ. ፳፭፡፰ (25÷8)

"ማደሪያዬንም በእናንተ መካከል አደርጋለሁ ነፍሴም አትጸየፋችሁም" ዘሌ. ፳፮፡፲፩ (26÷11)

ይህንን የእግዚአብሔር ቃል የሰሙና የፈፀሙ ቅዱሳንና የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ትእዛዙን አክብረው የእግዚአብሔርን ማደሪያና መሰዊያ ሠርተዋል፡- ለምሳሌ፡-

አብርሃም ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ ዘፍ ፲፫፡፬ (13፡4)

በሙሴ የመገናኛው ድንኳን ዘጸ ፴፫፡፯ (33፡7)

ዳዊት በኦርና አውድማ መሠውያ ሠራ የበለጠ መቅደስ ለመሥራት ተመኘ ፩ዜና ፳፩፡ ፳፮ (21፡26) መዝ. ፻፴፩፡፩-፭ (131፡1-5)

በሰሎሞን የቤተ መቅደሱ ሕንፃ ፩ነገ ፮፡፱ (6፡9)

እነ ዘሩባቤል፡ ነህምያ፡ ዕዝራ ሌሎችም ሁሉ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሠራት የተጉ ነበሩ። ዕዝ ፮፡፲፮ (6፡16)

ይህ ሁሉ ደግሞ በሰማይ ባለው አምሳል ነበር፤ ነው።

"እኔ እንደማሳይህ ሁሉ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት" ዘጸ. ፳፭፡፱ (25÷9)

ልዑል እግዚአብሔር ቤተመቅደስ በሰው ልጅ ከመገለጫው

ለማደሪያው ይሠራለት ዘንድ የፈቀደው እርሱ ነውና በዚህ ቤት የሚለምኑትን ሁሉ እሰማለሁ፤ ቤቱ የጸሎት ቤት ነው፤ ለዘላለም በዚህ እድራለሁ ብሏል። ለሰሎሞንም የነገረው ይህንን ቃል ኪዳን ነበር።

"እግዚአብሔር አለው... ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ።" ፩ነገ.(4-1፡9) ፬-፱፡፩

በእግዚአብሔር ቤት ሰዎች ሁሉ ክብርን በመስጠት፣ በመፍራት፣ ጫማን በማውለቅ ይገቡ ዘንድ በዚያም ከጸሎት ከልመና በስተቀር ከሌላ ከዓለማዊ ነገር ሁሉ እንርቅ ዘንድ እግዚአብሔር ያዛል።

"ኢየሱስ ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል" ማቴ. ፳፩፡፲፪ (21÷12)

"መቅደሴንም ፍሩ እኔ እግዚአብሔር ነኝ" ዘሌ. ፳፮፡፪ (26÷2)

መቅደሴንም ፍሩ ማለት ስገዱ አክብሩ ማለት ነው።

"ስግዱ ለእግዚአብሔር በዐፀደ መቅደሱ"

"በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ" መዝ ፺፭፡፱ (95፡9)

አንባቢዎች ሆይ እግዚአብሔር እሷልና ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ስንገባ በጥንቃቄ ይሆን ዘንድ ይገባል። ጥንቃቄውም እንዲህ ነው።

"በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው።" ፩ጢሞ ፫፡፲፭ (3፡15)

ሀ. ጫማ አድርጎ መግባት አይፈቀድም

ለ. ሴቶች በልማደ ሐዋን ጊዜ (በወር አበባ) መግባት

አይፈቀድም

ሐ. ወንዶች ሕልመ ሌሊት ሲያጋጥማቸው መግባት አይፈቀድም

መ. ከሐጩን መቆጣጠር የማይችል ሕመምተኛ (መዝረብረብ) ያለበት አስኪሚድን መግባት አይፈቀድለትም

ሠ. ባልና ሚስት ዕለቱን ግንኙነት አድርገው መግባት አይፈቀድም።

ረ. ይህን የመሳሰሉ ሁሉ ሲሆኑ ወደ ቤተመቅደስ ሲኬድ ዋናው ስግደት ነው።

በተረፈ ግን ምእመናን መባዕን በመያዝ ወደቤተመቅደስ ይሄዱ ዘንድ ይገባል። መዝ ፺፭፡፯ (95፡7)

ዛሬ መቅደስ የሌላቸው ታቦቱም የቀረ የሚመስላቸው ሰዎች ምክንያት የሚያደርጉት በሐዲስ ኪዳን ይህ የለለ እየመሰላቸው ነው። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት የእግዚአብሔር ቃላት የሚነግሩን የማደሪያው መቅደሱ ወይም ቤተክርስቲያን ይልቁንም አማናዊው የጌታ ሥጋና ደም እየተፈተተበት ከብሉይ በላይ ክብሮ እንዳለ ነው።

"ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና። ቤቱ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው። በመቅደስም ዕውሮችና አንካሶች ወደ እርሱ ቀረቡና ፈወሳቸው።" ማቴ ፳፩፡፲፪-፲፬ (21፡12-14)

በዚህ ቃል መሠረት ቤተመቅደሱ እንደተከበረ እንደሚኖር ራሱ ጌታ ተናገረ። መቅደሱ ባያስፈልግ ኖሮ የተሻረ ቢሆን ሰዎቹን ከምን ያባርራል። እንደውም በርቱ ተሽሮአል አልፎአል ይል ነበር። ግን አላለም እንደውም ሌቦቹን አባርሮ ቤቱ የጸሎት ቤት ናት አለ እንጂ።

ይህንን የሚያውቁ ያመኑና የተረዱ ቅዱሳን የጌታ ቤተሰቦች ሁል ጊዜ በመቅደሱ ይተጉ ነበር።

"በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም

እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር።" ሥራ ፪፥፵፮ (2፡46)

"ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር።" ሥራ ፫፥፩ 3፡1

እንባቢያን ሆይ በቅዱስ መቅደሱ ቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ቅዱሳን ነቢያት ቅዱሳን ሐዋርያት ዕለት ዕለት እየተጉ ከጸለዩ ከቀደሱ ከአመሰገኑ እኛ ማን ነን ትእዛዙን ጠብቀን ሁል ጊዜ በመቅደሱ የተተከልን ሆነን ፍሬ አፍርተን የለማያዊውን መቅደስም ዜጎች ያድርገን አሜን!

"እግርህ በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል። በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፤ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ። በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ፤ ስሜንም አውቆአልና አጋርደዋለሁ። ይጠራኛል እመልስለትማለሁ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ፤ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ።" መዝ ፺፩፥፲፪-፲፭

"ኦ አንትሙ ሕዝበ ክርስቲያን በከመ ተጋባእክሙ በዛቲ ዕለት ከማሁ ያስተጋብእክሙ በደብረ ጽዮን ቅድስት ወበኢያሩሳሌም እግዚእት እንተ በሰማያት" "እናንተ የክርስቲያን ወገኖች ሆይ በዚህች ቀን እንደተሰበሰባችሁ እንደዚሁ ክብርት በምትሆን በደብረ ጽዮንና በሰማይ ባለች ነጻ በምታወጣ በኢየሩሳሌም ይሰብሰባችሁ።" ሕርያቆስ ቅዳሴ ማርያም።

እግዚአብሔር እምካካችን የሰጠንን ትእዛዝ በምንጠብቅበት ጊዜ በረከቱና ጸጋው ከሁላችን ነውና ቤተክርስቲያን ጸጋ የምንከብስባት ከኀጢአት አሰራት ነፃ የምንወጣባት ናት። በቤተመቅደስ ቤተክርስቲያን ጌታችን አለ፤ ቅዱሳን አሉ፤ መላእክት አሉ - ይህም የመገናኛ ድንኳን ይባላል።

አሰረጅ፡- ዘጸ. 29÷42 ሐዋ. 2÷46 ሐዋ. 3÷1 ራዕ. 21÷3

በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ እግዚአብሔር የሚገለጥበት ታቦቱ ስለአለ ነው ከሌላም አዳራሽ የሚለየው የቃል ኪዳኑ ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያው በመቅደሱ ስላለ ነው።

# ታቦት

ቤተመቅደስን ቤተመቅደስ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሚያሰኘው የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው። በሰው ፈቃድ የተደረገ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሰው ልጅ ያደርገው ዘንድና እሱን ያመልክበት ዘንድ የተሰጠ ነው። ይህም ሰውና እግዚአብሔር ይገናኙበት ዘንድ ነው።

ትርጉም፡- ታቦት የጽላት መያዣ ሲሆን

ጽላት - ደግሞ ሕጉ የተቀረጸበት ታቦቱ ውስጥ የሚኖር ነው።

ይህ በእግዚአብሔር ከዘላለም ቃል ኪዳን ይሆን ዘንድ ከሕዝቡ ማምለኪያ በሙሴ አማካኝነት የተሰጠ ነው።

"ወሶበ ፈጸመ ተናገሮ ምስሌሁ በደብረ ሲና ወሀቦ ለሙሴ ፪ተ ጽላተ ዘትእዛዝ፡ ጽላት ዘዕብን ጽሑፋት በአጽባዕተ እግዚአብሔር"

"እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው።" ዘጸ. ፴፩፡፲፰ (31÷18) ጽላት የሚለው ቃል ሁለት መሆናቸውን የሚገልጽ ሲሆን አንዱ ግን ጽሌ ተብሎ ይጠራል።

ይህን የእግዚአብሔር ቃል ስንመለከት ስለ እግዚአብሔር ታቦት ሙሉ እውቀት ይኖረናል፡- ይህም

1. ታቦቱ (ጽላቱ) የተሰጠበት ቦታ ደብረ ሲና
2. ታቦቱን (ጽላቱን) የሰጠ እግዚአብሔር አምላክ
3. የተሰጠው ለሚያምኑ ሁሉ
4. የተቀበለው የእግዚአብሔር ሰው ሊቀ ነቢያት ሙሴ
5. ብዛት ሁለት ጽላት
6. የተሰራው ከዕብን

7. ባዶ ሳይሆን ጽሑፍ ያለበት

8. የጻፈው ራሱ እግዚአብሔር በጣቶቹ

9. ጽሑፉም አሥርቱ ትእዛዛት መሆናቸውን

ይህ በዚህች አንድ ጥቅስ ውስጥ የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

እግዚአብሔር ማደሪያው የሆነውን ይህንን ጽላት ከሙሴ የሰጠበት ምክንያት፡-

ሀ. ሙሴ በጣም ትሑት በመሆኑ - ዘፍ. ፲፪፡፫ 12÷3

ለ. ጾመኛና ጸሎተኛ በመሆኑ ዘጸ. ፱፡፱ 9÷9

<u>ሁለት ጽላት መሆኑ</u>

ሀ. በላዩ የተጻፈበት አሥርቱ ትእዛዛት በሁለት ስለሚከፈሉ እግዚአብሔርን መውደድና ሰውን መውደድ።

ለ. ከሙሴ በሁለቱም እጆቹ እንዲቀበል አድርጎታል ይህም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በሙሉ ልባችን መቀበል እንዳለብን የሚያሳዩ ነው።

ሊቀ ነቢያት ሙሴ በመጀመሪያ የተቀበለው የምስክር ጽላት በእስራኤል ኃጢአት ምክንያት ቢሰበርም በምትኩ ሌላ ይሰራ ዘንድ እግዚአብሔር አዝዟል። ይህም ታቦትን ቅዱሳን ሰዎች ሊቀርጹት እንደሚችሉ የእግዚአብሔር መልእክት መሆኑን ያሳያል።

በዚህ በምናየው ዘጸ ፴፬፡፲፬ (34፡14) ሙሴ ጽላቱን ይሥራ ዘንድ ታዘዘ እግዚአብሔርም ቃሉን እንደሚጽፍ ነገረው። ሙሴም እንደበፊቱ አድርጎ ጠረበ በሲና ተራራ ይዞ ቆመ እግዚአብሔርም በደመና ውስጥ ሆኖ ወረደ።

"እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፡- ሁለት ጽላቶችን እንደፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ በሰበርኻቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ ነገም የተዘጋጀህ ሁን በማለዳም ወደ ሲና ተራራ ወጥህ በዚያ በተራራው ራስ ላይ በፊቴ ቁም። ከአንተም ጋር ማንም ሰው አይውጣ

በተራራውም ሁሉ ማንም አይታይ፤ መንጎችና ከብቶችም በዚያ ተራራ ፊት አይሰማሩ። ሙሴም እንደ ፊተኞቹ አድርጎ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠረበ፤ በነጋውም ማልዶ እግዚብሔር እንዳዘዘው ወደ ሲና ተራራ ወጣ ሁለቱንም የድንጋይ ጽላቶች በእጁ ወሰደ፤" ዘጸ ፴፬፡፲-፬ (34፡1-4)

## የታቦት ኃይል

በኢያሱ ፫፡፲፭ (3÷15) እንደተጻፈ እስራኤል የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶባቸው መሻገር ባቃታቸው ጊዜ እንዲህ ሆነ። "ታቦቶቹንም የተሸከሙት የካህናቱ እግሮች በውኃው ዳር ሲጠልቁ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ"

በኢያሱ ፮ (6) ካህናት ታቦቱን ይዘው 7 ጊዜ ሲዞሩ ጠንካራ የነበረው በጦር ኃይል ሊፈርስ የማይችለው የኢያሪኮ ግንብ በእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦት የተነሳ ወደቀ።

መ. ሳሙ. ፭ (5) ፍልስጥዔማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ንቀው አቃለው ከጣዖት ጋር አንድ ነው ብለው ዳጎን ቤት ቢያስገቡት ታቦቱ ጣዖቱን ሰባበረው አደቀቀው።

፪ ሳሙ ፮፡፮-፱ (6÷6-9) ዖዛ ሥልጣነ ክህነት ሳይኖረው ታቦቱን በድፍረት ቢነካ ተቀጣ፣ ተሰበረ። ታቦት የሚሸከመው (የሚያከብረው) ካህን ብቻ ነው። ዲያቆንም ቢሆን፡ እንኳን ታቦት፡ ታቦቱ የሚቀመጥበት መንበሩን መንካት አይችልም።

፪ ሳሙ. ፮፡፳-፳፫ (6÷20-23) ቅዱስ ዳዊት ከታቦት ቢዘምር ሚስቱ ሚልኮል ብትንቀው እግዚአብሔር የሜልኮልን ማኅፀን ዘጋ። ይህ ከታቦት ዝማሬ እንደሚገባ ይገልጽልናል።

## ታቦት በአዲስ ኪዳንና በሰማይ

እግዚአብሔር አምላክ ይህንን ቅዱስ ማደሪያውንና መገለጫውን ከሙሴ ሲሰጥ ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ቃል ኪዳን አድርጎ ነው። ምክንያቱም በላዩ የሚገለጠው አልፋና ዖሜጋ የዘላለም አምላክ ስለሆነ የማያምኑ ሰዎች ታቦት በብሉይ ኪዳን እንጂ በአዲስ ኪዳን

ተሽሯል ይላሉ። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ግን ምን ይላል?

> ማቴ. ፭፥፲፯ (5÷17) "ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ እሥዓሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ እፈጽሞሙ" "እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም"

ስለዚሁም የቃል ኪዳኑ ታቦት የተሻረ ነው ብሎ የሚያስብ ከወንጌሉ ውጪ የሆነና የእግዚአብሔርን ሕግ የሚቃለፍ ነው። እኛ ግን እናከብረዋለን የሚገርመው የእግዚአብሔር የቃልኪዳኑ ታቦት እንኳን በምድር በሰማይ ቤተመቅደስ አለ። የዘላለም፣ የማያልፍ፣ የማይሻር እውነት ኪዳን ነውና።

> "በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ" ራእ. ፲፩፥፲፱ (11÷19)

## ቀጥሎ ያለውን ንጽጽር አስተውሉ

| | | በመጻሐፍ ቅዱስ | | |
|---|---|---|---|---|
| | በሰማይ | በብሉይ ኪዳን | በሐዲስ ኪዳን | በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ |
| መቅደስ | አለ - ራእ ፲፭፥፭ (15፡-5) | አለ - ፩ነገ ፱፥፫ (9÷3) | አለ - ማቴ ፳፩፡-፲፫ (21፡-13) | አለ |
| ታቦት | አለ - ራእ ፲፩፥፲፱ (11፡-19) | አለ - ዘጸ ፴፩፡-፲፰ (31፡-18) | አለ - ፪ቆሮ ፮፡-፲፮ (6÷16) | አለ |
| ካህን | አለ - ራእ ፬፥፲-፲፩ (4÷10-11) | አለ- ዘጸ ፳፰፥፩ (28÷1) | አለ - ማቴ ፲፰፡-፲፰ (18፡-18) | አለ |
| ጻና (መሰውያ) | አለ - ኢሳ ፮፥፮ (6፡-6) | አለ - ዘጸ ፴፥፩ (30፡-1) | አለ - ሉቃ ፩፡-፱ (1፡-9) | አለ |
| ዕጣን | አለ - ራእ ፰፥፫ (8፡-3) | አለ - ዘጸ ፴፥፴፭ (30-35) | አለ - ሉቃ ፩፥፲ (1-10) | አለ |
| ቅዳሴና ማሕሌት | አለ - ኢሳ ፮፥፫ (6፡-3) | አለ - ነህ ፲፪፡-፵፮ (12÷46) | አለ - ኤፌ ፭፥፲፱ (5÷19) | አለ |
| ሰግደት | አለ - ራእ ፲፱፥፬ (19÷4) | አለ - መዝ ፺፭፡-፱ (95፡-9 | አለ - ማቴ ፪፡-፲፩ (2÷11) | አለ |
| | | | | |

ስለዚህ ነበረ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰማይን መቅደስ ምሥጢር ገልጾ የምድሩን በዚያ አምሳል እንዲሰራ ያዘዘው።

> ዘጸ ፳፭፥፱ (25፥9) "እኔ እንደማሳይህ ሁሉ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት"

አንባቢያን ሆይ ይህንን ስንመለከት ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን እግዚአብሔራዊ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ እውነተኛ መሆኗን በግልጽ ያሳየናል። ይህንን ስንጠረዥ በሌላ እምነት ብትሞክሩት "አለ" የሚለው መልስ "የለም" እንደሚሆን ልብ በሉ። "ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ" ዕብ ፲፫፥፱ (13፥9)

# ስግደት

ስግደት የተገዢነት፣ የትሕትና የአክብሮት መገለጫ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት መሠረት ከአምላካችን ከእግዚአብሔር የአምልኮት (የባሕርይ) ስግደት ከቅዱሳንና ከመስቀል የአክብሮት የጸጋ ስግደት መስገድ ይገባል። ስለዚህ ስግደት በሁለት ይከፈላል።

## የስግደት ዓይነት

### ፩. የአምልኮት ስግደት (የባሕርይ ስግደት)

ይህ ከአንዱ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር የምንሰግደው ስግደት ነው። የምንሰግድለትም ፈጣሪያችን፣ አምላካችን ንጉሣችንና ጌታችን ስለሆነ ፈጥሮ የሚገዛ ብቸኛ አምላክ ስለሆነ ነው። ይህም ስግደት የባሕርይ ስግደት ነው።

> "ንዑ ንስግድ ወንግነይ ሎቱ፣ ወንብኪ ቅድመ እግዚአብሔር ዘውእቱ ፈጠረነ፣ እስመ ውእቱ አምላክነ፥ንሕነሰ ሕዝቡ ወአባግዐ መርዔቱ"
>
> "ኑ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ ከእርሱ ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት እንበርከክ እርሱ አምላካችን ነውና እኛ የማሰማሪያው ሕዝብ የእጁም በጎች ነንና።" መዝ. ፺፬፥፮-፯ (94፥6-7)

እግዚአብሔር በቅዱስ ዳዊት በተናገረው በዚህ ቃል መሠረት "ኑ" ብሎ ይጣራል። እኛ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ነንና እሱ ደግሞ አምላካችን፣ ፈጣሪያችን፣ ገዢያችን ነውና

እንሰግድለትና እንገዛለት ዘንድ ይናገራል። ስለዚህ ቤተክርስቲያናችን ይህን ትእዛዝ ተቀብላ እንደ ሥርዓቱ ለፈጣሪዋ ሰግደትን ታቀርባለች። ድንገት ያልተረዳ ሰው ወይም መስገድ ያልፈለገ ትእዛዙንም በብሉይ የነበረ ነው የሚል ግን ክርስቲያን ተብሎ የሚጠራ ቢኖር ለቦ ዳዊት ቃል የከብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ከአርሱ ከዳዊት ከጠቀሰ በኋላ እንዲህ ነበር ያለው፡-

"መጽሐፍ ሊሻር አይቻልምና" ዮሐ. ፲፡፴፭ (10፥35)

እንግዲህ ቃሉ ካልተሻረ ሁልጊዜ እንሰግድለት ዘንድ በመቅደሱም እንንበረከክለት ዘንድ ዛሬም እግዚአብሔር ይጠራናል። እንቢ ብንል ግን በምድረ በዳ እንዳለመረፉትና እንዳሰቆጡት። በትእዛዙም ላይ እንዳመጹት እንዳንጠፋ ያስጠነቅቃል። ቅዱስ ዳዊት "ኑ እንስገድ" ካለ በኋላ ቀጥሎ እንዲህ ነበር ያለው ።

"ዮም እመ ሰማዕክሙ ቃሎ ኢታፅንዑ ልበክሙ"

"ዛሬም ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ" መዝ. ፺፬፡፰ (94፥8)

" ምስጋና ውበት በፊቱ ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው ... ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ ቁርባን ያዙ ወደ አደባባዮችም ግቡ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ" መዝ. ፺፭፡፮-፱ (95፥6-9)

"... እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት ... ወደ ምድርም ሰገደ" ዘፍ. ፲፰፡፩-፫ (18፥1-3)

"ከመ ለስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሰግድ ኵሉ ብርክ ዘበሰማያት ወዘበምድር ወበቀላያት ወእለ ታሕተ ምድር"

"በሰማይ በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ" ፊል. ፪፡፲ (2፥10)

ይህ የአምልኮት ሰግደት ለእግዚአብሔር ውጪ ለሌላ አካል

አይሰጥም። ብቻውን የሆነ አምላክ እግዚአብሔር ነውና።

"ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ... አትስገድላቸው አታምልካቸውም" ዘጸ. ፳፥፫-፮ (20፥3-6)

__፪. የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት__፡- የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት የሚሰገደው ለእመቤታችን፣ ለመስቀል፣ ለቅዱሳን መላእክት፣ ለነቢያት፣ ለሐዋርያት፣ ለሰማዕታትና ለጻድቃን ነው።

"ነዑ ንስግድ ወንግነይ ሎቱ ወንብኪ ቅድመ እግዚአብሔር ዘውእቱ ፈጠረነ እስመ ውእቱ አምላክነ ንሕነሰ ሕዝቡ ወአባግዐ መርዔቱ"

## __ሦስቱ የአሰጋገድ ዓይነቶች__

ስግደት በሚገባ በአምላካችን በእግዚአብሔር የታዘዘ መሆኑን ካወቅንና ከተረዳን ዘንድ እንዴት መስገድ እንዳለብን ማወቅም ይገባናል። በተለያየ የአምልኮትና የጸሎት ጊዜያት የሚፈጸሙ ስግደቶች ሦስት ዓይነት መልክ አላቸው። እነዚህም አድንኖ፣ አስተብርኮና ሰጊድ ናቸው።

### __፩. አድንኖ (አትሕቶ)__

ከአሰጋገድ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን አድንኖ ማለት ትርጉሙም ራስን ዝቅ አድርጎ መስገድ ነው። በተለያዩ የቤተክርስቲያናችን መጻሕፍት አንዳንደ አምኃ (እጅ መንሳት) ተብሎ ይነገራል።

በአድንኖ ጊዜ መሬት ወድቆ አይሰገድም። ከቃሉ እንደምንረዳው ራስን ዝቅ፣ ጎንበስ አድርጎ መስገድ ነው። ለምሳሌ በቅዳሴ የጸሎት ሥነ-ሥርዓት ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ በመጨረሻ ካህኑ ሕዝቡን "እ እግዚእ አድኅን ሕዝበከ ወባርከ ርስተከ" "አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ" ብሎ ከመባረኩ በፊት ዲያቆኑ እንዲህ ብሎ ያዛል፡-

"አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር

አምካከነ በአደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርከሙ" ትርጉም፡
- በአምላካችን በእግዚብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ አገልጋዩ በሚሆን በካህኑ እጅ ይባርካችሁ ዘንድ"

በዚህ ትእዛዝ መሠረት የሚፈጸመው ስግደት ከሦስቱ ዓይነት ይህ አድንኖ የተባለው ነው። አድንኖ የሚለው ቃል አትሕቶ በሚለው በሌላ ስፍራ ሲገኝ ትርጉሙ ያው ነው።ከምሳሌ በቅዳሴ ጊዜ "እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰከሙ" "የቆማችሁ ሰዎች ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ" እንደሚለው ዓይነት ማለት ነው።

**፪. አስተብርኮ**፡- አስተብርኮ ማለተ ወደ መሬት ወርዶ መስገድ መንበርከክ ነው። ይህ ሁለተኛ ዓይነት አስጋገድ ሲሆን በዚህ ጊዜ ከራሳችን ዝቅ ማለት ብቻ ሳይሆን ከምድር ወድቀን በጉልበታችን በመንበርከክ የምንሰግደው ስግደት ነው። ብዙውን ጊዜ በጸሎት ሥነ-ሥርዓት ላይ ይፈጸማል። ከምሳሌ፡- በግል ጸሎት ጊዜም ተንበርክኮ ስግዶ እግዚብሔርን የሚለምኑበት ጊዜ ያስፈልጋል። ክርስቲያን ሁሉ ሊኖረው ይገባል።

**፫. ሰጊድ**፡- ሰጊድ ትርጉሙ መስገድ ማለት ሲሆን ይህም ሦስተኛው የአስጋገድ ዓይነት ነው። ይህ የአስጋገድ ዓይነት ወደምድር ወድቆ፣ ተደፍቶ ግምባርን መሬት እያስነኩ መስገድ ነው። ከምሳሌ በቅዳሴ ሥርዓት ጊዜ ውስጥ ዲያቆኑ ሁለት ጊዜ "ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት" በፍርሃት ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ስገዱ ይላል። በዚህን ጊዜ ሕዝቡ "ቅድሜከ እግዚኦ ንስግድ ወንሴብሐከ" አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን እናመሰግናለን ብለው በታላቁ መቅደስ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ወድቀው ይሰግዳሉ። በዚህ ጊዜ ግንባር መሬት ይነካል።

## በስግደት ውስጥ ያለ ምሥጢር

ከአምላካችን ከልዑል እግዚአብሔር በምንሰግድበት ጊዜ በማስተዋል፣ በመረዳት በፊቱ ልንንበረከክ ይገባናል። ጉልበታችን ሲሰግድ ውሳጣዊ (ውስጣዊ) መንፈሳችንና ልባችን

አብሮ በታላቁ የእግዚአብሔር መቅደስ በሰማይም ካለው ዙፋን ሊወድቅ ዝቅ ሊል ይገባዋል። ታላቁ ንጉሥ ምናሴ ስለኃጢአቱ ሲጸልይ እንደተናገረው "ወይእዜኒ እሰግድ በብረከ ልብየ እንዘ እስእል ምሕረተ ዚአከ" "አሁንም ቸርነትህን እየለመንኹ በልቤ ጉልበት እሰግዳለሁ" ጸሎተ ምናሴ ቁጥር ፱ (9)

እኛም ከዚህ የሚቀጥሉትን ምሥጢራት እያሰብን በስጋችን ጉልበትና በልባችን ጉልበት እንስግድለታለን። በሥጋም በነፍስም ፈጣሪያችን፣ አምላካችን መድኃኒታችን እርሱ እግዚአብሔር ነውና።

፩. በምንሰግድበት ጊዜ አምላካችን ከምድር አፈር እንደፈጠረን እኛም በበደላችን ምክንያት ሞትን በላያችን እንዳመጣን አፈር ነንና ወደ አፈር መመለሳችንን ምንም በሞተ ሥጋ ወደመቃብር ብንወርድም በነፍስ ወደ ሲኦል ብንጣልም ጌታችን ይቅርባይ ቸር፣ መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የበዛ ነውና፣ ከሞት አውጥቶ ትንሣኤን እንደሚሰጠን እያሰብን በማመን እንሰግዳለን ይህም በአሰጋገድ ሲገለጽ እንዲህ ነው -

ሀ. በመጀመሪያ ከመሬት ሰግደን በምንነሳ ጊዜ እንዴት እንደተፈጠርን እናስባለን። አምላካችን እግዚአብሔር ከምድር አፈር ፈጥሮ የሕይወት እስትንፋስ ሰጥቶናልና።

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" ዘፍ. ፪፡፯ (2፥7)

ለ. እንደገና ተመልሰን ስንሰግድ በበደላችን ምክንያት ሞትን በላያችን እንዳመጣን ከአፈር ሰርቶናልና ተመልሰን ወደ አፈር እንደምንመለስ።

"አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ" ዘፍ. ፫፡፲፱ (3፥19)

ሐ. ወድቀን እንደሰገድን በዚያው እንቀርም ተነሥተን እንቆማለን በዚህም ትንሣኤ እንዳለን እንገልጻለን።

ምንም አፈር ሆነን ወደአፈር ብንመለስ በክብር ባለቤት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ተነሥተን በቀኙ እንደምንቆም እናምናለን።

"ሙታን ሕያዋን ይሆናሉ፤ ሬሳዎችም ይነሣሉ" ኢሳ ፳፮፥፲፱ (26፥19)

"ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ" ፩ቆሮ ፲፭፥፶፪ (15፥52)

፪. ሌላው ምሥጢርእየወደቅን እየተነሣን በምንሰግድበት ጊዜ ሁሉ ክብር ምስጋና ይግባውና የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀሉን መከራ ስለእኛ ኃጢአት የደረሰበትን ሥቃይ እናስባለን ከመከራውም እንካፈላለን። በዚህን ጊዜ መስቀሉን ተሸክሞ መውደቁን እያሰብን ድኅነታችንን እናየዋለን።

፫. ሦስተኛውበስግደታችን ጊዜ ምንም ኃጢአተኛና በደለኛ ብንሆንም ይቅር ባይ የሆነ አምላካችን እግዚአብሔር ከወደቅንበት ኃጢአት እንደቶና ቀድሶ በንስሐ ውኃ አጥቦ ከሕይወት እንደሚያቆመንና እንደሚያጸናን እየተረዳን በፊቱ እንወድቃለን። "በየስፍራቸውም ቆመው የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን የሕግ መጽሐፍ የቀን ሩብ ያህል አነበቡ። ሦስት የቀን ሩብም ያህል ተናዘዙ ለአምላካቸውም ሰገዱ።" ነህምያ ፱፥፫ (9፥3)

"እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ" ፩ጴጥ ፭፥፮ (5፥6)

፬. እየሰገዱ ወድቆ መነሳት ምሥጢር አራተኛው ክብር ይግባህና በትንሣኤ ዘጉባኤ ታስነሳናለህ ብሎ ማመን ነው።

ከዚህ የምንረዳው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስግደት ሥርዓት ዝም ብሎ መውደቅ መነሳት ሳይሆን ረቂቅ ምሥጢር ያለው መሆኑን ነው። በዓለማችን ላይ በክርስትና ስምም ሆነ ከክርስትና ውጪ ባሉ እምነቶች ስግደት ያላቸው ቢሰግዱም ይህ ምሥጢር ግን የላቸውም። እኛ ግን ከላይ እንደተገለጸው በምንሰግድበት ጊዜ እነዚህን አራት ነገሮች እያሰብን ከባሕርይ ምስጋና ጋር የአምልኮት ወይም የባሕርይ ስግደት እንሰግድለታለን።

"ዘውእቱ አምላክነ መድኃኔ ኩሉ ይርአየነ እስከ ከዓለም ንሰግድ ኰቱ ወንሰብሖ። እስመ ውእቱ ፈጠረነ።"

"ይኸውም አምላካችን (ፈጣሪያችን) መድኃኒታችን ነው። ለዘለዓለሙ ይጠብቀናል። እንሰግድለት እናመሰግነው ዘንድ። " ቅዱስ ኤፍሬም

## የሚሰገድበትና የማይሰገድበት ጊዜ

ስግደት የሚፈጸምባቸው ጊዜያት አሉ። አንድ ክርስቲያን ጸሎት ከመጀመሩ በፊት ገጹን በሰመ ሥላሴ አማትቦ ሦስት ጊዜ መስገድ አለበት በጸሎቱ መካከልም ስግደትን በሚያነሣበት ቦታ ሁሉ ይሰግዳል፣ እንዲሁም ጸሎቱን በስግደት ይፈጽማል። ወደ ቤተክርስቲያን በሚሄድበት ጊዜ ከውጭ አጥር ጀምሮ ሰግዶ ተሳልሞ ከገባ በኋላ እንደ ሥርዓቱ ስግደት በሚያዝበት ሁሉ ይሰግድ ዘንድ ይገባል። ቤተክርስቲያናችንን ከርቀት እንኳ ቢመለከት አማትቦ ይሰግዳል ወይም ይሳለማል። በነፍስ አባትም የታዘዘ ሲኖር በቤቱም ወይም በቤተክርስቲያን ስግደቱን ይፈጽማል። ሌላው በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት በዓመት ጌታችን የተሰቀለበት ዓርብና ሰሙነ ሕማማት የስግደት ቀናት ተብለው ይታወቃሉ  በዚህ ቀን በብዙ በጾም በጸሎት በእንባ እንሰግዳለን ጌታችን ስለእኛ የደረሰበትን በማሰብ። ስግደታችን በግዝት በዓላት ዕለት ሲውል ሦስተኛው ዓይነት ስግደት ማለትም ስጊድ አይፈጸምም እንጂ ሌላው ዓይነት ስግደት አይቀርም ይፈጸማል። በነዚህ ቀናት ከሌላው በተለየ የመዳንን ነገር እናስብበታለን። በበዓለ ሃምሳም ስግደት የለም። አጠቃላይ ከፋሲካ እሑድ በፊት ያለውን ሳምንት ክርስቲያኖች ሁሉ የጌታን ሕማም እያሰቡ ለእርሱ ይሰግዳሉ። ክብር ይግባውና ጌታችን በጌቴሴማኒ በሚጸልይበት ጊዜ እየሰገደ እንዳስተማረን እኛም ይህንኑ እንፈጽማለን። ጸሎት ከስግደት ጋር ነውና። ከእርሱ ጋር እንጸና ዘንድ ቤተክርስቲያናችን ይህንንም ታስተምረናለች። ጌታ ከእርሱ ጋር በጸሎትና በስግደት ያልጸኑትን እንዲህ ብሏቸዋል።

"ወደ ደቀመዛሙርቱም መጣ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ

አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።" ማቴ. ፳፮፥፵፡፵፩ (26፥40-41)

የሕይወት ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ይህን ሦስት ጊዜ ያደረገው ለእኛ እንጂ ለእ እራሱ እንዳልነበረ ሁሉም የሚያውቀው ሐቅና እውነታ ነው። እኛም ይህንን ቃል በተግባር ልንፈጽመው የተገባ ነው። ዳሩ ግን ሥጋ ደካማ ነው፤ ከመንበርከክ ይሰንፋል። እውነተኛይቱ የእኛ ሃይማኖት ምእመናን ይሰግዱ ዘንድ በፊታቸውም ከእምካካቸው ወድቀው እንዲጸልዩ የምታዘው የተመሠረተችው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ነው።

> "ከእድንዋና ከእሰተብርኮ በቀር እስከ ምድር መስገድን የሚተውባቸውም የታወቁ ጊዜያቶች እነዚህ ናቸው። በዕለተ እሑድና በበዓለ ሃምሳ ወራት በጌታችን በዓላትና በእመቤታችን በዓላት ሥጋውንና ደሙን ከተቀበሉ በኋላ" ፍ፡ነገ፡ አንቀጽ ፲፬፡፭፻፴፯ (14፡ 537)፤ ኒቅያ ፳ (20) ፴፪ (32)

## እምስቱ የግዝት በዓላት በዓለ አምሳን (፶ን) ጨምሮ

እምስቱ የግዝት በዓላት ተብለው በቤተክርስቲያናችን የተደነገጉትና ስጊድ የማይሰገድባቸው

፩፥ ቅዱስ ሚካኤል ወር በገባ በአሥራ ሁለተኛው (፲፪) ዕለት

፪፥ እመቤታችን ወር በገባ በሃያ አንደኛው (፳፩) ዕለት

፫፥ እግዚአብሔር ወልድ (በዓለወልድ) ወር በገባ በሃያ ዘጠኝ (፳፱) ዕለት

፬፥ ቀዳሚት ሰንበት

፭፥ እሑድ ሰንበትእና በዓለ ሃምሳ ናቸው። በዓለ ሃምሳ

እንደ አንድ አሑድ ይታያል። ቀኖናና ስጊድ አይሰጥበትም"

## አመራረጣቸው

እነዚህን አምስት የበዓላት ቀኖች የተመረጡበት ብዙ ምሥጢር ያለው ሲሆን አባቶቻችን ካስቀመጡልን እውነት ስንመለከት ጥቂቱ እንዲህ ነው።

፩. ቅዱስ ሚካኤል (12)፡- ቅዱስ ሚካኤል የተመረጠው ከመላእክት ወገን ነው። እሱም የመላእክት አለቃ ነው። ቅዱስ ሚካኤልን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን እየመራ ከነዓን ያገባቸው ዘንድ የመረጠውና የላከው ነው።

"ወናሁ አፌኑ መልአኪየ ቅድመ ገጽከ ከመ ይዕቀብከ በፍኖትከ ወከመ ያብዕከ ውስጥ ምድር ዘአስተዳሎኩ ለከ"

"በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአኬን በፊትህ እሰዳለሁ" ዘጸ. ፳፫፥፳ (23፥20)

ስለዚህም በመልአኩ በመጋቤ ብሉይ ቅዱስ ሚካኤል መሪነት እስራኤል ከግብጽ ቀንበር ተላቀው ቀይ ባሕርን ተሻግረው ምድረ ርስት ማርና ወተት የምታፈሰውን ከነዓንን ወርሰዋል። ይህ ምሥጢር ከእኛ ድኅነት ምሳሌ ነው። ከነበርንበት በግብጽ የተመሰለ የስደትና የኃጢአት ሕይወት "መኑ ከማከ" "እንደአንተ ያለ ማነው" በተባለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀይ ባሕር ሲኦልን ተሻግረን ያዘጋጀልንን ከነዓን ገነትን የመውረሳችን ምሥጢር የተንጸባረቀበት የተተነበየበት የአምላክ ድንቅ ሥራ ነው። ስለዚህ ይህ ቀን ከሌሎች ሁሉ ተመርጧል። የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ጥበቃው አይለየን።

፪. የእመቤታችን ዕለት ፳፩ (21)፡- ከመላእክት ቅዱስ ሚካኤል እንደተመረጠ ከሰው ሁሉ ወገን ደግሞ የተመረጠች እመቤታችን ናት። የግዝት በዓል እንዲሆን

የእመቤታችን ዕለት መመረጡ የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሁሉ ለማዳን ሰው የሆነው ከእሷ ብቻ ስለሆነ ነው።

> "እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፣ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወዷታልና" መዝ. ፻፴፩፥፲፫ (131፥13)

> "እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ" ሉቃ. ፩፥፴፩ (1፥31)

ስለዚህ የድኅነታችን ምክንያት የእመቤታችን ቀን ተመረጠ

## ፫. በዓለ እግዚአብሔር ወልድ ፳፱ (29)፥-

ከሥላሴ ከአብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ለግዝት በዓለ ወልድ ተመርጧል።ይህ የጌታችን የመወለድ ቀን ከግዝት በዓላት የመመረጡ ምክንያት፥- አሁንም ከመዳናችን፣ ከሞት ወደ ሕይወት የመሸጋገራችን ምሥጢርን ቤተክርስቲያን ስለተረዳች ነው። እዚህ ላይ የሚገለጸው ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ከሰማይ መውረዱንና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን መዋሐዱን መወለዱን ነው።

> "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ሉቃ. ፩፥፴፭ (1፥35)

> "እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምስራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና " ሉቃ. ፪፥፲ (2፥10)

ከእመቤታችን ሥጋን የተዋሐደው ወልድ ብቻ ነው። 33 ዓመት በዚህ ምድር ተመላልሶ ያስተማረን ኋላም በቀራኒዮ ተሰቅሎ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ እግዚአብሔርወልድ ነው። ይህ የግዝት በዓል ሆኗል ስጊድ የለውም።

**፬. ቀዳሚት ሰንበት፥-** ከዕለታት መካከል ቀዳሜ የግዝት በዓል

ተብሎ የተመረጠበት ምክንያት የሁሉ ባለቤት የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዓለማትን ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ በሰባተኛው ቀን አረፈ ይህችንም ቀን ቀደሳት ለሰው ልጆችም በዓል አድርጎ ሰጠን። ስለዚህም የእምላካችንን ትእዛዝ እንጠብቅ ዘንድ ቤተክርስቲያን ታስተምራለች።

"በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ" ሉቃ. ፳፫፥፶፮ (23፡56)

<u>፮. እሑድ ሰንበት</u>፡- ከእምስቱ የግዝት በዓላት እሑድ ሰንበት የተመረጠችበት ምክንያት የሕይወት ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት የወረደበትን የማዳን ተግባሩን ፈጽሞ አዳምንና ልጆቹን ከሲኦል ነጻ አውጥቶ የዲያብሎስን እሥራር እጥፍቶ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣበት ዕለት በመሆኗ ነው።

"... ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ። ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት ገብተውም የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም። እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ እነሆ ሁለት ሰዎች የሚያንፀባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ... እንዲህ አላቸው፡- ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም።" ሉቃ.፳፬፥፩-፮

<u>በዓለ ሃምሳ (፶)</u>፡- በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፪ (2) እንደተጻፈው ጌታችን ከሞት በተነሣ በእምሳኛው ዕለት በዕለተ እሑድ ከጠዋቱ በሦስት ሰዓት መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ለደቀመዛሙርቱ ወርዶላቸዋል። ይህም በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ቀኖና አይለጥበትም ስጊድም የለበትም። ዓለም ሁሉ በእምነት አንድ የሆነበት ስለሆነ ከትንሳኤ እስከዚህ ሃምሳኛው ቀን ድረስ እንደ አንድ እሑድ ትንሣኤው ይታሰብበታል።

"ወበ፫ ዕለት ፈነወ ሎሙ መንፈስ ቅዱስ ከመ ዘእሳት ወተናገሩ በነገረ ኩሉ በሐውርት"

"በአምላኛውም ቀን በአላት አምላክ መንፈስ ቅዱስን ሰደደላቸው በአገሩ ሁሉ ቋንቋም ተናገሩ።" ቅዱስ ዲዮስቆሮስ

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት የበዓላት መኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። የሰው ልጅ ኃላፊ ከሆነው ከዓለም ነገር ብቻ ሲሮጥ ከሥጋው ሲደክም የነፍሱን ነገር እንዳይረሳና እንዳይዘነጋ ከማድረግ ነው። አምላካችን እግዚአብሔር ይህን ሥርዓት የሰጠን በነዚህ የበዓል ቀናት ሰው እርስ በእርሱ እንዲጠያየቅ፣ የታመመ እንዲጎበኝ፣ ከተከያዩ ማሕበራዊ አገልግሎቶች ጊዜ እንዲሰጥ ሌላ ቀርቶ ከሥራ የምንጠቀምባቸው እንስሳት እንኳ እንዲያርፉ ነው። በተጨማሪ ከናውቀው የሚገባን በዓመት ውስጥ ያሉት ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ቀናት ሁሉ አንድ ብቻ እንኳ ሳይሆን ተደራራቢ በዓላት እንዳሏቸው ነው።

በነዚህም ቀናት ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በበዓላቱ እናስበዋለን። በነዚህም ቀናት ሁሉ እንጸልያለን፣ መቅደሱን እንሳለማለን፣ ከድሆች እጆቻችንን እንዘረጋለን እንጂ እጣጥፈን የምንቀመጥበት አይደለም። ይህም በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን በየዕለቱ የሚከወን ነው።

ይህንን ያልተረዱ ሰዎች የተቀደሰውን የአምላካችንን ፈቃድና እሱን የምናስብበትና ከእሱ የምንገናኝባቸው የእሱንና የቅዱሳኑን በዓሎች ይቃወማሉ።

"ወይቤሉ በልቦሙ ኅቢሮሙ በበ ሕዘቢሆሙ"

"ንዑ ንስዓር ኵሎ በዓላቲሁ ለእግዚአብሔር እምድር ወትእምርቶሂ ኢነአምር ወአልቦ እንከ ነቢይ"

" አንድ ሆነው በልባቸው በየሕዝባቸው ኑ የእግዚአብሔርን በዓሎች ከምድር እንሻር አሉ፣ ምልክታችንን እናይም ከእንግዲህ ወዲህም ነቢይ የለም" መዝ. ፸፫፡፰-፱ (73፥ 8-9)

# ሥርዓተ ቅዳሴ

ቅዳሴ ማለት ምስጋና ማለት ነው። ቀደሰ አመሰገነ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የወጣ ቃል ነው። እግዚአብሔር መላእክትንና ሰውን የፈጠራቸው ለምስጋና ነው። ይልቁንም ቅዱሳን መላእክት ያለማቋረጥ ሥላሴን ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ በቅዳሴያቸው ያመሰግናሉ።

> "አንዱም ላንዱ፦ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያሉ ይጮኹ ነበር" ኢሳ. ፮፥፫ (6፥3)

ከዚህ እንደምንማረው የቅዳሴያችን ምንጩ የሰማይ መቅደስ የመላእክት ቅዳሴ ነው። አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ከውድቀት በፊት በገነት ሳሉ መላእክት ጸሎት ሲያደርጉ ሰምተው እምላካቸውን በቅዳሴ በውዳሴ ያመሰግኑት ያመልኩት ነበረ። ከወደቁም በኋላ አላቋረጡም በደብር ቅዱስ ያመሰግኑት ነበር። ይህም በልጆቹ አልፎ እስከ ዛሬ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያች በምሴተ ሐሙስ ምሥጢረ ቁርባንን ሠርቶ ለደቀመዛሙርቱ ሥርዓቱን አስተማራቸው ማቴ. ፳፮፥፳፮ (26፥26)። ከትንሣኤውም በኋላ እስካረገባት ቀን ድረስ በብዙ መንገድ እየተገለጸ ያስተምራቸውና ይባርካቸው በነበረበት በዓርባው ቀን ኪዳንን ሲያስተምራቸው አንዱ ቅዳሴ ነበር። በኋላም በፊልጵስዩስ ሰብስቧቸው ስለ ሕንፃ ቤተክርስቲያንና ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ገለጸላቸው። በዚህች ቀንም አመቤታችንን ታቦት አድርጎ ሐዋርያትን ልኡካን አድርጎ ራሱ ጌታ ዐቢይ (ሠራዒ) ካህን ሆኖ ቀድሶ ካቆረባቸው በኋላ እንዲህ የሚል ትእዛዝ ሰጣቸው፦

> "እምይእዜሰ አንትሙኒ ከመዝ ግበሩ"
>
> "ከንግዲህ እናንተም እንደዚህ አድርጉ"

ይህንን ያምላካችንን ትእዛዝ ሐዋርያት ተቀብለው ከሱ

የተማሩትን ከደቀመዛሙርቶቻቸው እያስተካከሉ እዚህ ደርሶ እኛም በዚህ ቅዱስ ሥርዓት ዘወትር ከመላእክት ጋር በዝማሬ እናመሰግናለን። እንዲህም እያለን እንለምነዋለን።

"ወከማሆሙ ለነኒ ረስየነ ድልዋነ"

"እኛንም እንደነሱ የበቃን አድርገን።"

በቤተክርስቲያናችን እግዚአብሔርን የምናመሰግንባቸው ሥጋውና ደሙ ተለውጦ አማናዊ ሆኖ የምንቀበልባቸው ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርገን አክብረን ለውጠን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደመ ወልደ እግዚአብሔር የምናደርግባቸው ቅዳሴያት በአባታችን በአባ ጊዮርጊስ ከተደረሰው ከቅዳሴ መዓዛ ውጪ አስራ አራት (፲፬) ቅዳሴያት ናቸው። እነዚህም እንደቅዳሴው መጽሐፍ ተራ ቀጥሎ ያሉት ናቸው።

## አሥራ አራት (፲፬) ቅዳሴ

<u>፩. ቅዳሴ ሐዋርያት</u>፡- ይህን ቅዳሴ አባቶቻችን ሐዋርያት ባንድነት የተናገሩት ነው።

<u>፪. ቅዳሴ እግዚእ</u>፡- ይህ ቅዳሴ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ ከሞት ከተነሣ በኋላ ያስተማራቸው ነው። ከሰባቱ ኪዳናት አንዱ ይህ ቅዳሴ እግዚእ ነው።

<u>፫. ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደነጐድጓድ</u>፡- የዚህ ቅዳሴ ደራሲ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ነው። ወልደ ነጐድጓድ ማለት የነጎድጓድ ልጅ ማለት ነው። ስለሰሙ ትርጉም የበለጠ ስለሐዋርያት በተጻፈው መረዳት ይቻላል።

<u>፬. ቅዳሴ ማርያም</u>፡- የእመቤታችን ቅዳሴ በብሕንሳው ኤጲስ ቆጶስ በአባ ሕርያቆስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተደረሰ ነው።

_፭. ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምዕት (ዘ፫፻፲፰)_፡- ሠለስቱ ምዕት ማለት ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ማለት ነው። በቁጥራቸው የተጠራውን ይህንን ቅዳሴ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ባንድነት የተናገሩት አርዮስንና ተከታዮቹን አውግዘው ሃይማኖትን አቅንተው ያባቶች ሐዋርያትን ሥርዓት አጽንተው ከወሰኑ በኋላ ነው።

_፮. ቅዳሴ ዘአትናቴዎስ_፡- ይህን በስሙ የሚጠራውን ቅዳሴ የደረሰው ቅዱስ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ የነበረ ነው። እሱም በኒቅያ ጉባዔ ከሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ቅዱሳን አበው ጋር አርዮስን ያሳፈረው ነው።

_፯. ቅዳሴ ዘባስልዮስ_፡- አባታችን ቅዱስ ባስልዮስ በቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ የነበረ ነው። የጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ወንድም ነው። በስሙ የሚጠራውን ቅዳሴ የደረሰው እርሱ ነው።

_፰. ቅዳሴ ዘጎርጎርዮስ (ሰኑሲስ)_፡- ቅዱስ ጎርጎርዮስ የቅዱስ ባስልዮስ ወንድም ነው። የኑሲስ ኤጲስ ቆጶስ የነበረ ነው። በጉባዔ ቁስጥንጥንያ ከመቶ አምሳው አንዱ ይህ አባት ቅዱስ ጐርጐርዮስ ነው። የቅዳሴው ደራሲ እርሱ ነው።

_፱. ቅዳሴ ዘኤጲፋንዮስ_፡- ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የቆጵሮስ ደሴት ሊቀ ጳጳስ ነው። በስሙ የተጠራው ቅዳሴ ደራሲ ይህ አባታችን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ነው።

_፲. ቅዳሴ ዘዮሐንስ አፈወርቅ_፡- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቁስጥንጥንያ ኤጲስ ቆጶስ ነው። ብዙ ድርሰት የጻፈ ቅዱስ አባት ነው። ከዚያ ውስጥም ይህ በስሙ የተጠራውን ቅዳሴ ድርሳንና ተግሣጽም ጽፏል።

_፲፩. ቅዳሴ ዘቄርሎስ_፡- ቅዱስ ቄርሎስ ንስጥሮስ በተወገዘበት የኤፌሶን ጉባዔ ከሁለት መቶው ቅዱሳን አበው አንዱ ነው። የጉባዔው አፈ ጉባዔ ይህ ቅዱስ አባት ነበር። በስሙ የተጠራው ቅዳሴ ደራሲ እርሱ ነው።

_፲፪. ቅዳሴ ዘቅዱስ ያዕቆብ (ዘሥሩግ)_፡- አባታችን

ቅዱስ ያዕቆብ ሥሩግ በሚባል አገር ኤጲስ ቆጶስ ነበር። ሥሩግ በጤግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች መሃከል ያለች አገር ናት። የቅዳሴው ደራሲ ይህ ያዕቆብ ነው።

፲፫. ቅዳሴ ዘዲዮስቆሮስ፡- አባታችን ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በእስክንድርያ አገር ኤጲስ ቆጶስ የነበረ ነው። በስሙ የሚጠራውን ቅዳሴውን የደረሰው እርሱ ነው።

፲፬. ቅዳሴ ዘጎርጎርዮስ ካልዕ፡-የዚህ ቅዳሴ ደራሲ አባታችን ቅዱስ ጎርጎርዮስ የተባለው ነው። በቅዳሴ መጽሐፍ ቅዳሴ ዘጎርጎርዮስ ካልዕ ተብሎ ይጠራል። ከመጀመሪያው ጎርጎርዮስ ሲለየው ነው። ይህም ቅዱስ አባት ጎርጎርዮስ ገባሬ ተአምራት ወመንከራት ተብሎ ይታወቃል።

ይህ በሥርዓተ ቅዳሴው የተጻፈ አቀማመጥ ሲሆን የተጻፈበት የመጻሕፍቱ ዘመን በትክክል አልተቀመጠም። ከዚህ ቀጥሎ ዘርዝሬ እንደየ ደራሲዎቹ ዘመን ጽፌላችኋለሁ።

1. ቅዳሴ እግዚእ (የጌታ ቅዳሴ)
2. ቅዳሴ ሐዋርያት
3. ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ
4. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ
5. ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምዕት
6. ቅዳሴ አትናቴዎስ
7. ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ
8. ቅዳሴ ባስልዮስ
9. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ
10. ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ
11. ቅዳሴ ቄርሎስ
12. ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ
13. ቅዳሴ ያዕቆብ ዘስሩግ
14. ቅዳሴ ማርያም

## ግእዝ ዕዝልና አራራይ የሚቀደስበት ጊዜ

ቅዳሴ ግእዝና ዕዝል የሚቀደስባቸው ዕለታት ተከይተው የታወቁ ናቸው። በአብዛኛው ጾም የሚሆንበት ወራት በዓል ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው ግእዝ ይቀደሳል። በበዓላት ጊዜ ደግሞ ዕዝል ይቀደሳል። ዕዝል ወይም ግእዝ መሆኑ የሚለየው ወንጌል ከተነበበ በኋላ በሚባለው መርገፍ ነው። ወይንም ከወንጌሉ ንባብ በፊት "በወንጌል መራሕከነ" የሚለው ከተዘመረ ቅዳሴው ግእዝ ነው። "ተፈሥሑ" በእግዚአብሔር ከተባለ ደግሞ ዕዝል ነው። አንዳንድ ጊዜ በእሑድ ዕለት "ተፈሥሑ" ተብሎ ግዕዝ ይቀደሳል። ከመቼ እስከመቼ ግእዝና ዕዝል እንደሚቀደስ ጊዜያቱ እነዚህ ናቸው፡-

ከስብከት እስከ ዓቢይ ጾም ዋዜማ - ዕዝል

ከዓቢይ ጾም ዋዜማ እስከ ሆሣዕና - ግእዝ

ከሆሣዕና እስከ ሠኔ ፲፮ (16) - ዕዝል

ከሠኔ ፲፯ (17) እስከ መስከረም ፳፭ (25) - ግእዝ

ከመስከረም ፳፮(26) እስከ ኅዳር ፮ (6) - ዕዝል

ከኅዳር ፯ (7) እስከ ስብከት - ግእዝ ይቀደሳል።

ከግእዝና ከዕዝል በተጨማሪ አራራይ የሚባል ዜማ እንዳለ ይታወቃል። ይህ ዜማ የሚቀደስበት የተወሰነ ጊዜ የለውም። ነገር ግን በግእዝም በዕዝልም ዜማ ጣልቃ ይዜማል።

ግእዝ በሚቀደስባቸው ወቅቶች በዓለ ንግሥ ሲሆን ዕዝል ይቀደሳል። ማኅሌት በተቆመ ጊዜ ምንጊዜም ቅዳሴው ዕዝል ነው።

## የቅዳሴ ክፍል

እያንዳንዱ ቅዳሴ በየዕለቱ የሚቀደስ ሁለት ታላላቅ ክፍሎች አሉት እነዚህም፡- ሥርዓተ ቅዳሴና ፍሬ ቅዳሴ ናቸው። ዋና ካህን እኰቴተ ቍርባን ዘ … ብሎ እስከሚጀመርበት ያለው ሥርዓተ ቅዳሴ ሲሆን ሁልጊዜ አይለወጥም አንድ ዓይነት ነው። ከዚያ በኋላ ግን ፍሬ ቅዳሴው ከላይ እንደተመለከትነው ከቅዳሴያት የዕለቱ በግጸዌው መሠረትና እንደበዓሉ ይቀደሳል። አንድን ቅዳሴ በዝርዝር ስንመለከተው ደግሞ ሦስት ክፍሎች እናገኛለን።

**፩. የዝግጅት ክፍል**፡- ይህ ክፍል ቀዳሹ ዋና ካህን ቅዳሴውን ከመጀመሩ በፊት በንዋያት ላይ የሚጸልየው ወደ መንጦላዕት ከመግባት አስቀድሞ የሚጸልየው እንዲሁም ወደ መንጦላዕቱ ገብቶ የሚጸልየው የጸሎት ጊዜ ነው። በሥርዓቱ የተደነገገውን ጸሎት ከፈጸመ በኋላ ሁሉም ዝግጁ መሆናቸውን ካየ በኋላ ወደ ቅዳሴው ይገባል፤

**፪. የትምህርት ክፍል**፡- ሁለተኛው የትምህርት ክፍል ሲሆን ይህም ካህኑ "ሚ መጠን ግርምት ዛቲ ዕለት" ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት ብሎ ከሚጀመርበት አንስቶ ዲያቆኑ "ጸልዩ በእንተ ሰላም" ስለ ሰላም ጸልዩ እስከሚልበት ጊዜ ያለው የትምህርት ጊዜ ነው።

**፫. የፍሬ ቅዳሴ ክፍል**፡- የፍሬ ቅዳሴ ክፍል ሠራዒው (ዋናው) ቀዳሽ ካህን "እኰቴተ ቁርባን ዘ …" ብሎ ጀምሮ ሠራዒው (ዋናው) ቀዳሽ ዲያቆን "እትው በሰላም (በሰላም ግቡ) ብሎ ሕዝቡን እስኪያሰናብትበት ያለው የቅዳሴ ሰዓት ነው።"

## ከቤተልሔም ወደ መቅደስ

ቅዳሴ በሚገባበት ጊዜ ቀዳሽ ልኡካኑ ከቤተልሔም ተነሥተው ወደ መቅደሱ ኅብስቱን በመሶበ ወርቅ ወይኑን በጽዋዕ አድርገው ይገባሉ። ይህም ምሳሌነቱ ከድኅነታችን ጋር የተያያዘ ታላቅ ምሥጢር ነው። ቤተልሔም ማለት ከሁለት

ቃላት ጥምረት የተገኘ ቃል ነው። "ቤተ" ማለት ቤት ማለት ሲሆን "ልሔም" ማለት ኅብስት (እንጀራ) ማለት ነው። የግእዙና የዕብራይስጡ ትርጉም አንድ ነው። ስለዚህም ቤተልሔም የሚለው ቃል ትርጉም የኅብስት ቤት ወይንም የእንጀራ ቤት ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁላችንን ለማዳን ከእመቤታችን የተወለደው በኤፍራታ ምድር በቤተልሔም ነው።

"...ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው። እነርሱም፡- አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሺም ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፏልና በይሁዳ ቤተልሔም ነው አሉት" ማቴ. ፪፥፭ (2፥5) ሚክ. ፭፥፪ (5፥2) ነቢያት በመሰከሩላት ቅድስት ቤተልሔም ከእመቤታችን የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ኅብስት የሕይወት እንጀራ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚሰጥ ከሰማይ የወረደ ነው።

> "እነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት" የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።" ዮሐ. ፮፥፴፭ (6፥35)

የቤተልሔም አሠራር ሁልጊዜ ከቤተመቅደሱ በስተ ምሥራቅ ነው። ምሳሌነቱም ፀሐይ ከምሥራቅ እንደምትወጣ "ፀኀየ ጽድቅ" እውነተኛ ፀኀይ ኢየሱስ ክርስቶስ በምሥራቅ በተመሰለች ቤተልሔም ተወልዷልና። በምሥጢርም ቤተልሔም የምትባል እመቤታችን ናት ከርሷ መድኃኒታችን ተወልዷልና።

ይህን ከተመለከትን ቅዳሴ ሲገባ ከቤተልሔም ተነሥቶ ወደ መቅደሱ የመምጣት ምሥጢሩ ክብር ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ተወልዶ በቀራንዮ የመሰቀሉ ነገር ነው፤ በቤተመቅደስ በመንበሩና በታቦቱ ላይ የሚፈተተው ሥጋውና ደሙ ለሁላችን ቤዛ ለሕይወትና ለመድኃኒት ለኃጢአትም ማስተሥረያ ሲሆን በቀራንዮ ተራራ በመስቀል ላይ የመሠዋቱ ምሥጢር ነው።

"ይእቤኒ እግዚኦ እንዘ ንቤለር ሞተከ ወትንሣኤከ"

## የቀዳሾች ልዑካን ቁጥር ምስጢር

በቅዳሴ ጊዜ የሚቀድሱት ልዑካን (አገልጋዮች) ቁጥር መደቡ አምስት ነው። ይህም በሁሉ የተለመደ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በበዓላት ጊዜና በአንዳንድ ገዳማትና አድባራት ለቅዳሴ የሚሠየሙት የልዑካን ቁጥር ሰባት አሥራ ሁለት ሃያ አራትም የሚሆንበት አለ። ምሳሌነትም አለው።

ሰባት ልዑካን ቀዳስያን የሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አሥራ ሁለት ልዑካን ቀዳስያን የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሃያ አራቱ ልዑካን ቀዳስያን የሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ምሳሌ ናቸው። በሰማይ ባለው የእግዚአብሔር መቅደስ የሚያገለግሉት ኪቃነ ካህናት ቁጥራቸው ሃያ አራት (24) ነው። ራዕ. ፬፥፲፩ (4፥11)

በሁሉም ቤተክርስቲያን የሚታየው የቀዳስያን ቁጥር ከላይ እንዳየነው አምስት ልኡካን ናቸው። ይህም በወንጌል ተጽፎ ከምናገኘው ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን ከገለጸባት የደብረ ታቦር ምሥጢር ጋር የተገናኘ ነው። ደብረ ታቦር የቤተክርስቲያን ምሳሌ ከብሉይ ነቢያት ሙሴና ኤልያስ ከሐዋርያት ጴጥሮስ ዮሐንስና ያዕቆብ በተራራው መገኘታቸው ቤተክርስቲያን ብሉይም ሐዲስም የሚነገርባት ከመሆኗ ነው። የደብረ ታቦር ተራራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነቢያትና የሐዋርያት የሕያዋንና የሙታን አምላክ መሆኑን የገለጸበት ነው። ከሙታን ሙሴን ከሕያዋን ኤልያስን ማምጣቱ ከዚህ ነው። ዛሬም በቅድስት ቤተክርስቲያን ቅዳሴ ሥርዓት የጌታችን አምላክነቱ ለቅለቱ ሞቱና ትንሣኤው ያደረጋቸው ድንቅ ተአምራት ሁሉ የሚገለጽበት ነውና ደብረ ታቦር ይህ ሁሉ የተነገረባት ስለሆነች የመቅደሱ ምሥጢር ምሳሌ ናት። በደብረ ታቦር ጌታችን አለ፡ በመቅደሱ በዘካለም የቃል ኪዳኑ ታቦት አድሮ አለ። እንደ ሙሴና ኤልያስ ሁለቱ ቀሳውስት አሉ። እንደ ሦስቱ ሐዋርያት ጴጥሮስ ዮሐንስና ያዕቆብ ሦስቱ ዲያቆናት አሉ። አምስቱ ልኡካን የሚባሉትም ቀዳስያን እነዚህ ናቸው።

<u>፩. ሠራዒ ካህን</u>፡- ቅዳሴውን የሚመራው የሚባርከው

የሚያቆርበው ይህ ነው። ገባሬ ሠናይ ተብሎም ይጠራል።

<u>፪. ንፍቅ ካህን</u>፡- ዋናውን ካህን ይረዳል ከእርሱ የተመደበውን ሥርዓት ያከናውናል።

<u>፫. ሠራዒ ዲያቆን</u>፡- በዲቁናው ዋና ሆኖ የሚያገለግለው ነው። ደሙን የሚያቀብለው ይህ ዲያቆን ነው። ገባሬ ሰናይ ዲያቆን ይባላል።

<u>፬. ንፍቅ ዲያቆን</u>፡- ይህ ሁለተኛው ዲያቆን ነው። የእርሱን ምድብ ያገለግላል።

<u>፭. አብሪ ዲያቆን</u>፡- ይህ ሦስተኛ ሆኖ የሚገባው ሲሆን "ፍሬ ስሞን" ተብሎ ይጠራል። መብራት ያበራል ጧፍ ይይዛል መጽሐፍ ይገልጻል።

# ደጀ ሰላም

በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ ከሚሠሩት አንዱ ደጀ ሰላም ነው። ይህም በገነት ሲመሰል ቤተ መቅደሱ ደግሞ በመንግሥተ ሰማያት ይመሰላል። ስለዚህም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድ ሰው ቤተልሔምንም ደጀ ሰላምንም ከሩቅ ሰላምታ ይሰጣል።

# ደጀ ሰላም

በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ ከሚሠሩት አንዱ ደጀ ሰላም ነው። ይህም በገነት ሲመሰል ቤተ መቅደሱ ደግሞ በመንግሥተ ሰማያት ይመሰላል። ስለዚህም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድ ሰው ቤተልሔምንም ደጀ ሰላምንም ከሩቅ ሰላምታ ይሰጣል።

# የመሳለሚያ ምልክት

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በታነጸችበት ስፍራ ሁሉ። በአጠገቡ ባለ መንገድ መሳለሚያ አለ። ይህም የተቆለለ ድንጋይ ይሆንና በአናቱ የመስቀል ምልክት አለው። በዚህ መንገድ የሚጓዙ ክርስቲያኖች

1. ድንጋይ አንስተው በተከማቸው ድንጋይ ላይ ያስቀምጣሉ
2. አማትበው ሦስት ጊዜ ይሳለማሉ (ይሰግዳሉ)
3. ለካም ከኪ ቅድስት ቤተክርስቲያን አምላክ ኢየሩሳሌም ለማያዊት ብለው ይጸልያሉ።

ይህም የሚደረገው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ውስጥ መግባት ባለመቻል ሲሆን፣ መሳለሚያውም በዚያ ሥፍራ ቤተ ክርስቲያን እንዳለች ከመጠቆም ነው። መንገደኞች ናቸውና ከሩቅ ተሳልመው ይሄዳሉ።

የዚህ ድንቅ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ምሥጢር እንዲህ ነው።

አንደኛ መሳለሚያ የሚሠራበት ምክንያት በዚያ ቤተመቅደስ እንዳለ ታቦተ ሕጉና በላዩ ከዘላለም አድሮ የሚኖር እግዚአብሔር እንዳለ ከመጠቆም ሲሆን ይህም ከአባታችን ከያዕቆብ ታሪክ የተወሰደ ነው። በኦሪት ዘፍጥረት ፳፰፥፲-፳፪ (28፥10-22) እንደተጻፈው ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን ሲሄድ በሎዛ መንገድ ስከመሸ ድንጋይ ተንተርሶ በዚያ አደረ። ሌሊት በሕልሙም ከሰማይ እስከ ምድር የተተከለ መሰላል በበላዩ እግዚአብሔር ቆሞበት መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት አየ። እግዚአእብሔርም ተገልጦ የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ ነኝ ይህችን ምድር ከአንተና ከዘርህ እሰጣለሁ አለው። ያዕቆብም እንዲህ አለ "በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር አለ። ፈራ እንዲህም አለ ይህ ስፍራ እንደት ያስፈራል ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም

የሰማይ ደጅ ነው።"

ከዚያም ያዕቆብ ድንጋዩን ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው ዘይትም አፈሰሰበት።

እንደ አባታችን ያዕቆብ ምእመናን፡-

1. በዚያ ስፍራ እግዚአብሔር ማደሪያ እንዳለው እናውቃለን።
2. ከእግዚአብሔር ስግደት እንሰጣለን የሚያስፈራ የእግዚአብሔር ግርማ በመቅደሱ ስላለ።
3. ያም መቅደስ የእግዚአብሔር ቤት እንጂ ተራ አይደለምና
4. መቅደሱም የሰማይ ደጅ ነው።
5. ድንጋይም አንስተን በመሳለሚያው እናኖራለን

ሁለተኛው ድንቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሥጢር ከላይ እንደገለጽሁት ክርስቲያኖች በመሳለሚያው ከሩቅ ከእግዚአብሔር የሚሰግዱትና የሚሳለሙት ተጓዦች ናቸውና መግባት ስላልቻሉ ነው። በዚህም የምናስበው ሊቀ ነቢያት ሙሴና እስራኤል ወደ ቅድስቲቱ ከተማ መግባት ስላልቻሉ በሩቅ ሆነው እንደተሳለሟት ነው።

አስረጅ፡-

ዘዳ ፩፡፴፯ (1፡37) ፫፡፳፯ (3፡27)

"እግዚአብሔርም ከዘርህ እሰጣታለሁ ብዬ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የማልሁላቸው ምድር ይህች ናት በዐይንህ እንድታያት አደርግሁህ ነገር ግን ወደዚያች አትሻገርም አለው። " ዘዳ ፴፫፡፬ (33፡4)

"ወባሕቱ አምርኁቅሰ ርእይዋ ወተአምኅዋ"

"ነገር ግን ከሩቅ አይተው ተሳለሟት" ዕብ ፲፩፡፲፫

(11፥13)

ሦስተኛው ግሩም ምሥጢር ደግሞ "ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም" ለሰማያዊት ኢየሩሳሌም መንግሥተ ሰማያት አምሳል መርገፍ የሆንሽ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሰላም ለአንቺ ይሁን ብለን ስንሳለም። ቅዱስ ጳውሎስም እንደገለጸው፡-

"አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ.... ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና" ዕብ ፲፩፡፲፮ (11፥16)

የሚለውን የተስፋ ቃልና ከያዕቆብም እግዚአብሔር እንደነገረው ይህችን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ እንዳለ ለጊዜው ምድረ ርስት ከነዓንን ሲሆን ፍጻሜው ግን ዘላለማዊ ርስታችን መንግሥተ ሰማያትን ነው። ከዚህም የተስፋ ቃል የተነሳ የመሳለሚያ ምልክት ባለበት ስፍራ በምንሳለምበት ጊዜ ለጊዜው ወደ ቅጥረ ቤተ ክርስቲያን መግባት ባንችልም ኋላ ግን በመቅደሱ ገብተን ሰግደን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እንቀበላለን። በፍጻሜ ዘመንም መንግሥተ ሰማያትን እንደምንወርስ የሚያመለክት ፍጹም ሃይማኖታዊ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ነው።

የመሳለሚያው ድንጋይም ያለው ሌላ ጥቅም ቤተመቅደስ ይታደስበታል ይሠራበታል፡፤ ይህም ከላይ እንዳየነው ልማደ ያዕቆብ ነው።

"ወዛቲ ዕብን እንተ ዐቀምኩ ትኩውነኒ ቤተ እግዚአብሔር" ዘፍ ፳፰፡፳፪ (28፥22)

ያዕቆብም እንዲህ አለ፡- ይህችም ያቆምኩዋት ድንጋይ ቤተ እግዚአብሔር ትሆንልኛለች ማለት ቤተ እግዚአብሔር እሠራባታለሁ ሲል ነው።

"ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል"

"አሜን በቤትህ ለዘላለም እኑረኝ"

# የአለባበስ ሥርዓት በቤተክርስቲያን

ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሔድበት ጊዜ ሊደረጉ ከሚገባቸው ጥንቃቄዎች አንዱ አለባበስ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ካህናትና ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከጸሎት በሚሄዱበት ጊዜ ሁሉ ሕጉን በመጠበቅ እንዲጸኑም የእግዚአብሔር ቃል ያዛል። ይህንን አውቀንና ተረድተን እንፈጽመው ዘንድ ቀጥሎ እነደ ሕጉ አጽፋለሁ።

## ልብሰ ተክህኖ

የእግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናት በቤተመቅደሱ የተለየ ልብስ በመልበስ እንዲያገለግሉት እግዚአብሔር ይወዳል ስለዚህም የአለባበስን ሕግ አዟል። ለሊቀ ነቢያት ሙሴ እንደነገረው አሮንና ልጆቹን ናዳብን፣ አብዩድ፣ አልዓዛርንና ኢታምርን ከክህነት ከመረጣቸው በኋላ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦

> "የተቀደሰውንም ልብስ ለክብርና ለጌጥ እንዲሆን ለወንድምህ ለአሮን ሥራለት። አንተም ካህን ሆኖ እንዲያገለግለኝ አሮን ቅዱስ ይሆን ዘንድ ልብስ እንዲሠሩለት የጥበብ መንፈስ ከሞላባቸው በልባቸው ጥበበኞች ከሆኑት ሁሉ ተናገር።" ዘጸ ፳፰፡፪-፬ (28፡2-4)

በመቀጠልም እግዚአብሔር የሚሠሩአቸው ልብሶች ምን ምን እንደሆኑ የዘረዘራል። አሠራሩም በሞላው ምዕራፍ በሌሎችም ስፍራዎች ተገልጧል። ስለዚህ በክህነት አገልግሎት ያሉ እንደ ትእዛዙ ዓይነት ይለብሳሉ።

> "ለአሮን ልጆች ሸሚዞችን መታጠቂያዎችን ቆቦችንም ለክብርና ለጌጥ ታደርግላቸዋለህ። ይህንም ሁሉ ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ታለብሳቸዋለህ በክህነት እንዲያገለግሉኝ ትቀባቸዋለህ ትክናቸዋለህ ትቀድሳቸውማለህ።" ዘጸ ፳፰፡፵ (28፡ 40)

እግዚአብሔር ይህንን ሕግ ከሰጠ በኋላ እንዳዘዝኳችሁ አድርጉ ብሏል።

አሰረጅ፡- ዘጸ ፴፩፡፲፩ (31፡11)፤ ፵፡፲፪ (40፡12)

በመቅደሱ አገልግሎት ካህናት የሚለብሱት ልብስ ተከህኖ የብሉይንና የሐዲስን ምሥጢር አዋሕደው የያዙ ናቸው። ከዚያ ውስጥ የተወሰኑትን እንመልከት።

## ሀ. የክህነና የዲያቆን ልብስ፡-

ካህንና ዲያቆን የሚለብሰው ልብስ ተከህኖ ልዩነት አለው። የካህኑ ካባ ሲኖረው የዲያቆኑ ካባ አይጨምርም። ግን በሁለቱም ልብስ ላይ አምስት ዘርፎች ወይም ካንቃዎች አሉት። ይህም የአምስቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አምሳል ነው። ካንቃም የሌለው ልሙጥ የሆነ ካባም ይለበሳል። የተለያዩ ቀለሞች ያላቸው ልብሶች ቢለበሱም በዋናነት ነጭ ልብስ ይታዘዛል። የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ግን ጥቁር ልብስ ተከህኖ እንዲለበስ ያዛል። ይህም በግብረ ሕማማቱ ሥርዓት ተጽፏል።

## ለ. አክሊል (ቆብ)፡-

ካህናት በቅዳሴ አክሊል በማድረግ ያገለግላሉ። "... ክብር፣ ውዳሴ፣ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።" ራእ ፬፡፲፩ (4፡11)

ይህ ቃል በሰማይ ስለሚያገለግሉት ካህናት የተነገረ ነው። የምድሩ የሰማይ አምሳል ነውና አሮን ወደ መገናኛው ድንኳን ለአገልግሎት ሲገባ በራሱ ላይ አክሊል ያደርግ ነበር ይህም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።

> "በፊቱ በኩል የተቀደሰውን አክሊል ቅጠል የሚመስለውን የወርቅ ምልክት አደረገ።" ዘሌ ፰፡፱ (8፡9)

ምሳሌነቱም እንደኛ በኤፌሶን ፮፡፲፯ (6፡17) እንደተጻፈ "ንሥኡ ጌራ መድኃኒት ካዕለ ርእስከሙ" የመዳንን ራስ ቁር አድርጉ ይላልና ጌታችን የጸፈው የእሾህ አክሊል

የድኅነታችንም ምልክት ነው። ሁለተኛ ወደ ፊት የሚጠብቀን የድኅነት ክብር ምሳሌ ነው።

"ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል" ፪ጢሞ፬፥፰ (2፥4-8)

ከቅዳሴ ውጭ ካህናት የሚያደርጉት ቆብ ተብሎ ይጠራል እንጂ አክሊል አይባልም ምሳሌነቱ ከላይ እንደተጠቀሰው ነው። የጌታን የእሾህ አክሊል መድፋቱን የሚገልጽ ነው።

"አሮንንና ልጆቹንም በመታጠቂያ ታስታጥቃቸዋለህ ቆብንም ታለብሳቸዋለህ ለዘላለም ሥርዓትም ክህነት ይሆንላቸዋል።" ፳፱፥፱ (29፥9)

## ሐ. ሞጣሕት፡-

ካህናት በቀሚስና በካባው ላይ የሚደርቡት ሞጣሕት ተብሎ ይጠራል። በብሉይ እንደነበረው ኤፉድ ነው። አሮን በልብሰ ተክህኖው ላይ ኤፉዱን ይደርብ ነበር።

"ኤፉዱንም በብልሃት የተሠራ በወርቅና በሰማያዊ በሐምራዊም በቀይም ግምጃ ከተፈተለ ከጥሩ በፍታም ብልሀ ሠራተኛ እንደሚሠራ ያድርጉ።" ዘጸ ፳፰፥፮ (28፥6)

በዘመነ ክርስትና ሞጣሕት ከሃይማኖት ረዥም ጉዞ ምሳሌ እንደሆነ ይነገራል። ከላይ ከትከሻ እስከ እግር ጫፍ ይደርሳልና የረዥም መንገድ ቅርጽ አለው። የሚያደርገው ካህን ብቻ ነው ዲያቆናት ሞጣሕት አይለብሱም።

## ልብሰ ተክህኖ በመቅደሱና ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቻ

ካህናት የተቀደሰውን ልብሰ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ይለብሳሉ። እንደ ሌላ ልብስ ከአገልግሎት ውጪ አይለበስም። ብልጣሶር የተባለ የናቡከደነፆር ልጅ በትዕቢት ተነስቶ የቤተ መቅደሱን የተቀደሱ ንዋያት ለሌላ ቢጠቀምባቸው የወገቡ ጅማቶች ተፈትተው ወዲያው ተቀስፏል። ይህም በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ፭ (5) ተመዝግቦ ይገኛል። ስለዚህ ካህናት የቀደሱባቸውንና

ያገለገሉባቸውን ልብሶች አውልቀው ሌላ እንዲለብሱ የእግዚአብሐር ቃል የቤተክርስቲያን ሕግ ያዛል።

"ወደ ውጭውም አደባባይ ወደ ሕዝብ በወጡ ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውስጥ ያኑሩት" ሕዝ ፵፬፡፲፱ (44፡19)

**የካህናት ጥምጥም፡-**

ካህናት በራሳቸው ላይ ጥምጥም ያደርጋሉ። ይህም በእግዚአብሔር አምላክ የታዘዘና የተፈቀደ ነው። እምላካችን ካህናትን ከራሱ ሲመርጥ ከአሮንና ከልጆቹ የካህናት አለባበስ ከሙሴ ሲያዘው እንዲህ ብሎታል።

"እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው እንደ ሸማኔ ሥራ ከጥሩ በፍታ ከአሮንና ከልጆቹ ሸሚዞችን ከጥሩ በፍታም መጠምጠሚያውን ከጥሩ በፍታም መልካሞቹን ቆቦች... አድርጉ።" ዘጸ ፴፱፡፳፯-፳፱ (39፡27-29)

በሌላም ስፍራ ተጽፎ እንደምናገኘው መጠምጠሚያ ከሚሠሩ በእግዚአብሔር ከታዘዙ የካህናት ልብሶች አንዱ ነው። ይህም የተቀደሰ ነው።

"የሚሠሩአቸውም ልብሶች እነዚህ ናቸው። የደረት ኪስ ኤፉድም ቀሚስም ዝንጉርጉር ሸሚዝም መጠምጠሚያም..." ዘጸ ፳፰፡፫ (28፡3)

"...የበፍታውንም መጠምጠሚያ ይጠምጥም እነዚህ የተቀደሱ ልብሶች ናቸው" ዘሌ ፲፮፡፬ (16፡4)

"በማኅተም መልክ አምሳል በተሠራ የተሠራ የወርቅ ቀጸላ በዝግራ መጠምጠሚያው ላይ አደረገለት የተከየ የክብሩ መመኪያ የሚሆን ታምራት የሚያደርግበት ሥራ የሚሆን ጌጡ ከዐይን የተወደደ የሆነ ጌጡ ፈጽሞ ያማረ የሆነ የወርቅ መጠምጠሚያን በዝግራ መጠምጠሚያው ላይ አደረገለት" ሲራክ ፵፭፡፲፪ (45፡12)

ጥምጥም ሁል ጊዜ ነጭ ነው። ይህም የቅድስናና የንጽሕና ምሳሌ ስለሆነ ነው። በራስም መደረጉ የክብር አክሊል ምሳሌ ነው።

"ቅድስና ለእግዚአብሔር የሚል ጸፉበት። በመጠምጠሚያውም ላይ ያንጠለጥሉት ዘንድ ሰማያዊውን ፈትል አሰሩበት።"

ዘጸ፡ ፴፱፡፴፩ (39፤31)

ካህናት ጥምጥምም ሆነ ቆብ ማድረጋቸው ለሕዝቡም ሆነ ለራሳቸው የቅድስና ሕይወትን ለማውረስና ለመውረስ ነው። እንዲህ ካልሆነ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።

"አንተም ቀንህ የደረሰብህ የኃጢአትህ ቀጠሮ ጊዜ የደረሰብህ ርኩስ ኃጢአተኛ የእስራኤል አለቃ ሆይ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል መጠምጠሚያውን አውልቅ ዘውዱንም አርቅ" ሕዝ ፳፩፡፳፭-፳፮ (21፡25-26)

በቅድስና በምናገለግለው ዘንድ ሰይጣን በከሰሰው ጊዜ ለታላቁ ካህን የሰጠውን ክብር አምላክ ያድለናል። "ንጹሕ ጥምጥም በራሱ ላይ አድርጉ አለ። እነርሱም በራሳቸው ላይ ንጹሕ ጥምጥም አደረጉ።" ዘካ ፫፡፩-፭ (3፡1-5)

አንባቢ ሆይ ፡- ብዙ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የዚህን ካህን ስም ኢሳሰቶ ኢያሱ ብሎ ይጽፋል ስህተት ነው።

## የምእመናን አለባበስ በቤተክርስቲያን

ምእመናን በቅዳሴ፣ በጸሎት በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዴት መልበስ እንዳለባቸው ሕግና ሥርዓት አለው። ይህም ነጭ የሆነ መሆን አለበት። ጋቢ ወይም ነጠላ ይሆናል። ሁልጊዜ ንጹሕና የታጠበ መሆን አለበት። ጌታችን መድኃኒታችን በወንጌሉ መንግሥተ ሰማያትን በሠርግ ቤት መስሎ ሲናገር ከአንድ ሰው በቀር ሁሉም ልብሳቸውን አጥበው እንደገቡ

ያስተምርና። ልብሱን ካላጠበው "ወዳጄ ሆይ የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንደት ወደዚህ ገባህ አለው" እርሱም ዝም አለ ወደ ጨለማም ተጣለ።" ማቴ ፳፪፡፩-፲፬ (22፡1-14)

"ወደ ሕይወት ዛፍ ከመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆቿም ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው።" ራዕ ፳፪፡፲፬ (22፡14) እነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር ቃላት በስሙ ከልብስ ያውሩ እንጂ ምሥጢሩ በንስሐ የታጠቡ ሰዎች ልባቸውን ከኃጢአት እድፈት ያነጹ ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገቡ የሚገልጽ መሆኑ የታወቀ ነው። የሰማይ መቅደስ ሥርዓት በምድር እንደተሠራ በተደጋጋሚ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፳፭ ቁጥር ፰ (25፡8) ያለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ መመልከት ያስፈልጋል። ስለዚህም ምእመናን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ስንሄድ አለባበሳችን ሕግ ያለው ነው። ታላቁ አባት ያዕቆብ ከተገለጠለት ከእግዚአብሔር በቤቴል መሠውያውን በሠራ ጊዜ እንዳደረገው ዛሬም እኛ የያዕቆብ ልጆች ከዘላለም እናደርገዋለን። ያዕቆብ ምን ነበር ያደረገው፡-

"ያዕቆብም ከቤተሰቡና ከእርሱ ጋር ካሉት ሁሉ እንዲህ አለ፡- እንግዶችን አማልክት ከመካከላችሁ አስወግዱ ንጹሐንም ሁሉ ልብሳችሁንም ለውጡ ተነሥተንም ወደ ቤቴል እንውጣ በዚያም በመከራዩ ጊዜ ለሰማኝ በሄድሁበትም መንገድ ከእኔ ጋር ለነበረው ለእግዚአብሔር መሠውያን አደርጋለሁ።" ዘፍ ፴፭፡፩-፬ (35፡1-4)

## የልብስ ነጭ መሆኑ ወይም መታጠቡ

የካህናትም ሆነ የምእመናን ልብስ ነጭ መሆኑና መታጠቡ

፩. ቅድስናና ንጽሕናን በመቅደሱ በቆምንበት ጊዜ ሁሉ ከኃጢአት እድፍነት ነጽተን ከማምለካችን ምሳሌ ነው።

፪. በሰማይ መቅደስ ያሉ የተቀደሱ ሰዎች ልብስ ነጭ ስለሆነ።

"ከእያንዳንዳቸው ነጭ ልብስ ተሰጣቸው" ራእ ፮፥፲፩ 96፥11)

"... እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ። እኔም ጌታ ሆይ አንተ ታውቃለህ አልሁት። አለኝም እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል። በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።..." ራእ ፯፥፲፫-፲፯ (7፥13-17)

፫. በትንሣኤውና በዕርገቱ በተገለጡ መላእክት አምሳል።

"ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በግርጌ ተቀምጠው አየች።" ዮሐ ፳፥፲፪ (20፥12)

"እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ።" የሐ ፩፥፲ (1፥10)

፬ኛ. ልጅነታችን ለመመለሱ፡- በኦሪት ዘፍጥረት ፫ ቁጥር ፲ (3፥10) እንደምንመለከተው አዳም ትእዛዝ በማፍረሱ ሕገ እግዚአብሔር በመጣሱ የብርሃን ልብሱ ተገፈፈ። የእርሱ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ምክንያት የሰው ልጆች ሁሉ በኋላም በክርስቶስ አዳኝነት ልብስ የተባለ ልጅነታችን ለመመለሱ ምሳሌ ተጎናጽፈን በመቅደሱ እንቆማለን።

"ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል" ገላ ፫፥፳፯ (3፥27)

በሥርዓተ ቅዳሴ መቅድም የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጸሎት ላይ ክርስቶስን እንዲህ ይለዋል፡- "እስመ አንተ ልብስነ" "አንተ ልብሳችን ነህ።" ተዋሕጃችን አንተ ነህና ሲል ነው። ይህም የልጅነት ጸጋ ልብሳችን እንዳይገፈፍ በእምነትና በምግባር ልንጸና የተገባ ነው፡፤

"...በእሳት የነጠረውን ወርቅ ተጎናጽፊህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን እንድታይም

ዐይኖችህን የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ።" ራዕ ፫፥፲፰ (3፥18)

## የሴቶች ራሳቸውን መከናነብ

"እንዲሁም ደግሞ ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ" ፩ጢ. ፪-፲ (1፥ 2-10)

ይህ የእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ልብስ እንዲሸለሙ ወይም እንዲያጌጡ ሲናገር የማይገባ ልብስ እንዳለ እናስተውላለን። በሕግ መጽሐፍ በእሪት እንዲህ የሚል አለና።

"ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና" ዘዳ ፳፪፥፭ (22፥5)

ይልቁንም ደግሞ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ከጸሎት በሚቆሙበት ጊዜ ሴቶች ራሳቸውን ተከናንበው ጸጉራቸውን ሸፍነው እንዲሆን ቃሉ እንዲህ ይላል፡- ፩ቆሮ ፲፩፥፫-፲፮ (11፥3-16)

"ራስዋን ሳትሸፍን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች" በተቃራኒው ወንድ ደግሞ ቢከናነብ ራሱን ያዋርዳል። ሐዋርያው ለምን እንዲህ ተናገረ ብንል

"ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም። ሴት ግን የወንድ ክብር ናት" የዚህ ቃል ምሥጢር ረቂቅ ነው። ወንዱ የእግዘአብሔር ምሳሌ የተባለው ጌታችንን በሰቀሉት ጊዜ ልብሱን ገፈው ሰቅለውታልና ወንድ የማይከናነበው ከዚያ ምሳሌና ክብር ነው። ሴት ግን የወንድ ክብር ናት ብሎ በተለይ በቁጥር ፲፰ ላይ "ተፈጥሮ እንኳ አያስተምራችሁምን" ይላል ይህም ማለት ሴትን ከወንድ የግራ ጎን አጥንት ነሥቶ (ወስዶ) የፈጠራት ሲሆን። እሷም ከተሸፈነ ሥፍራ ከተደበቀ በከንድም ከተከለለ ቦታ ተገኘታለችና ይህም ተፈጥሮዋን

በጸሎት ጊዜ ራሱዋን ጭምር በመሸፈን ትገልጣለች። በተጨማሪ ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ሥርዓት ውጭ በመሆን መከራከርን የሚሹ ቢኖሩ እንዲህ ይላል፡-

> "ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ እኛ ወይም የእግዚአሐር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም።" ፩፡፲፩-፲፮ (11፡16)

## በቅዳሴ ጊዜ ከንንብ የሚወልቅበት ጊዜ

ሴቶች በቅዳሴና በጸሎቱ በመቅደሱ እያሉ ከንንባቸውን የሚያወልቁበት ጊዜ አለ። ይኸውም አንደኛ ቅዱስ ወንጌል ሲነበብና ሲሳለሙ ነው። ሁለተኛ ሥጋውንና ደሙን ሲቀበሉ ነው። ይኸም ስለ ክብረ ወንጌልና ሥጋ ወደሙ ነው። ስለዚህ በነዚህ ጊዜያት ሴቶች ስርመዲያቸውን (ከንንባቸውን) ያወልቁና መልሰው ያደርጋሉ። ይህንንም ሥርዓት መስቀልና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲሳለሙ ይፈጽሙታል።

በዚህ አጋጣሚ ታውቂት ዘንድ የምገልጽላችሁ የአመቤታችን ተአምሯ ሲነበብ ግን ከንንብ አይወልቅም።

## የነጠላ፣ ጋቢ ወይም ኩታ አለባበስ

በቤተክርስቲያን በማንኛውም የጸሎት ሥርዓት በምን ቆምበት ጊዜ አለባበሳችን ከግራ ወደ ቀኝ የተመሳቀለ በትአምርተ መስቀል መሆን አለበት ትአምርት ማለት ምልክት ማለት ነው "አመረ" "አመለከተ" ከሚለው ግሥ የወጣ ነው። ትአምርተ መስቀል ማለትም የመስቀል ምልክት ማለት ነው፡፤ ከዚህም የተነሳ በጸሎት፣ በቅዳሴ በማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት ልብሳችንን በመስቀል አምሳል እንለብሳለን ምክንያቱም ይህን በምናደርግበት ጊዜ፡-

፩. የጌታችንን የመስቀል መከራ እናስባለን።

፪. የቆምነው ምሕረትን እየለመን ስለሆነ ድኅነትና ምሕረት የተደረገልን ደግሞ በመስቀሉ ነውና መዳናችንን እያሰብን እናመስግናለን።

፰. ሊቁ አትናቴዎስ በቅዳሴው እንደተናገረው ይህ የመስቀል ምልክት ሰይጣንን ስለሚያስፈራው ነው።

፱. በሰማይ መቅደስ የሚያገለግሉት ቀዳስያን ሱራፌል ሰድሰት ሰድሰት የሆኑ ክንፎቻቸውን በትእምርተ መስቀል አድርገው በዙፋኑ ያለውን ንጉሥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ይቀድሱታል ይሠልሱታልና እኛም በሰማይ ሥርዓት መሠረት በመስቀል አምሳል አጣፍተን እንቀድሳለን እንጸልያለን።

አንባቢ ሆይ፡- በጸሎት ጊዜያት እጆቻችንንም በመስቀል ምልክት በደረታችን የምናጣፋው ወይም የምንዘረጋቸው እነዚህን ከላይ የዘረዘርናቸውን እያሰብን እንደሆነ እናስተውል።

# መጋረጃ - መንጦላዕት

መጋረጃ በግእዙ መንጦላዕት ተብሎ ይጠራል። በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን መጋረጃዎች እናያለን ለምን? የመገናኛው ድንኳን በሙሴ ቤተ መቅደሱም በሰሎሞን በተሠራ ጊዜ እግዚአብሔር በሰማይ መቅደስ አምሳል መጋረጃ እንዲያደርጉ ስለ አዘዘ ነው። ይህም ሕግ ዛሬ በቤተክርስቲያናችን ሲሠራ ይታያል። መጋረጃውም ቅድስቱን ከቅድስተ ቅዱሳኑ ይለያል ለታቦቱም ክብር ይደረጋል። ስለ አሠራሩ ስለ ቀለሙ ዓይነት ሁሉ በመጽሐፍ ተዘርዝሯል።

> ዘጸ ፳፮ (26) ፴፰፥፲፮ (38፥16) ከዚህ ሕግ የተነሳ ታቦቱም የሚቀመጥበት ሥፍራ በመጋረጃ የተከለለ ነው።
>
> "መጋረጃውንም ከመያዣዎቹ በታች ታንጠለጥለዋለህ በመጋረጃውም ውስጥ የምስክርን ታቦት አግባው መጋረጃውም በቅድስቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መለያ ይሁናችሁ።" ዘጸ ፳፮፥፴፫ (26፥33)

እግዚአብሔር ራሱ እንዲህ ያዘዘና ዛሬ በቤተክርስቲያናችን ይህ ሥርዓት ተከብሮና ተጠብቆ መቅደሱ ባማሩ በጥሩ በተሠሩ መጋረጃዎች ያጌጣል። በዚሁ ከላይ ባየነው ምዕራፍ በቁጥር ፴፮ እንደተጻፈው በጥልፍ አሠራር ያጌጡ መጋረጃዎች ለታቦቱ ክብር ይደረጋሉ።

አንዳንድ ከእግዚአብሔር ሕግ የወጡ ሰዎች ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ከተደረጉት ሰባት ተአምራት አንዱ የሆነውን የቤተመቅደስ መጋረጃ ለሁለት መቀደዱን ጠቅሰው መጋረጃ ያለፈ ሥርዓት ነው በማለት በአምነት ቤቶቻቸው የላቸውም አያደርጉም። በመጀመሪያ የምስክሩ ታቦት ስለሌላቸው መጋረጃው ባይኖራቸው አያስደንቅም። ነገር ግን በስቅለቱ ጊዜ የመጋረጃው መቀደድ ምሥጢሩ እንዲህ ነው፡-

> "ወተሠጠ መንጦላዕተ ቤተ መቅደስ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ ወኮነ ክልኤ ክፍለ"

ትርጉሙም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ ከሁለት ክፍልም ሆነ ማለት ነው፤ ማቴ ፳፯:፶፩ (27:51) ማር ፲፭:፴፰ (15:38) ሉቃ ፳፫:፵፭ (23:45) ይህ የሆነው መልአኩ ሰይፉን በወረወረ ጊዜ ነው። ይህም በሰሙ የተሰቀለው አምላክ ለመሆኑ ከሰባት ምልክቶች አንዱ ሲሆን በምሥጢሩ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው የጥል ግድግዳ እግዚአብሔርን እንዳናይ የከለከለን ወደቀ፤ ፈረሰ ማለት ነው። እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት ተቀዷል በቃ መጋረጃ አያስፈልግም ማለት አይደለም። እንዳልሆነም ከመጋረጃው መቀደድ ጋር የተከሰቱትን ሌሎቹን ስድስት ተአምራት ማየት ነው። ለምሳሌ ምድር ተናወጠች ይላል በምሥጢሩ መርገመ ሥጋ ጠፋ ሲል ታዲያ ምድር እንደ ተንቀጠቀጠች እንደተናወጠች ቀረች ማለት ነውን? አይደለም። መጋረጃውም አብቅቷል አልቆለታል አይባልም ዛሬም በእውነተኛው መቅደስ ይኖራል።

# ሰባቱ ኪዳናት

ክብር ይግባውና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ እስከ ዕረገበት 40ኛው ቀን ድረስ ከደቀመዛሙርቱ ብዙ አስተምሮአቸዋል። ከዚህም ውስጥ ሰባቱ ኪዳናት አሉ። እነዚህም

ትምህርተ ኅቡአት

ዘጠኙ ኪዳናት -

ሀ. ሦስቱ የሌሊት

ለ. ሦስቱ የነግህ (የጠዋት)

ሐ. ሦስቱ የሠርክ (የማታ)

እግዚአብሔር ዘብርሃናት

በእንተ ቅድሳት

በሰማይ (በቅዳሴ እግዚእ) ዲያቆኑ የሚለው

ቅዳሴ እግዚእ

ቅዱስ ሥሉስ - በቅዳሴ ጊዜ ሥጋውን ደሙን እየተቀበሉ ካህናትና ምእመናን በአንድነት የሚቀድሱት የሚጸልዩት ነው።

# ንዋያተ ቅድሳትና ምሥጢራቸው

ንዋየ ቅድሳት ማለት የተቀቡ ወይንም የተለዩ (የተባረኩ) ዕቃዎች ማለት ነው። እነዚህም በቤተክርስቲያን የምንገለገልባቸው ናቸው። ንዋየ ቅድሳት በአገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት በአያንዳንዳቸው ላይ ይቀደሱ ዘንድ የተመደበላቸው ጸሎት ይጸለይባቸውና ይባረካሉ። ይህም ጸሎት በሥርዓተ ቅዳሴ መጽሐፍ "ጸሎት ላዕለ ንዋያት ሐዲሳት" በአዲሶች ንዋያተ ቅድሳት ላይ የሚጸለይ ጸሎት ተብሎ የተወሰነ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት ካህኑ በቤተመቅደሱ ባሉ ንዋያተ ቅድሳት ላይ ሁልጊዜ ጸሎት ያደርጋል ይህም "ጸሎት ላዕለ ኲሉ ንዋየ ቤተክርስቲያን" በቤተክርስቲያን ባሉ በንዋየ ቅድሳት ሁሉ ላይ የሚጸለይ ጸሎት ይባላል። ከዋና ዋናዎቹ ንዋያተ ቅድሳት (ቅድስና ዕቃዎች) የተወሰኑት ከነምሥጢራቸው እነዚህ ናቸው።

## መሶበ ወርቅ

መሶበ ወርቅ ለቤተመቅደስ አገልግሎት እግዚአብሔር ካዘዘበት ጊዜ ጀምሮ በቤተክርስቲያናችን ካሉ ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ነው። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር መናን ለእስራኤል በምድረ በዳ ባወረደ ጊዜ እሱ እንዳዘዛቸው ከልጅ ልጅ ሁሉ ምስክር ይሆን ዘንድ በደብተራ ኦሪት በእግዚአብሔር ፊት በመሶብ አድርገው አስቀምጠዋል። ዘጸ. ፲፮፥፴፩-፴፮ (16፥31-36)

> "...ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በርሷም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ።" ዕብ. ፱፥፩-፭ (9፥1-5)

የዚህም ቃል ምሥጢሩ ከሰማይ የወረደው መና፡- ስለሁላችን ቤዛ

የሆነ ከሰማየ ሰማያት የወረደው የሕይወት እንጀራ ነኝ ያለ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ። መሶብ፡- እምካከን በማኅፀንዋ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የተሸከመች የእመቤታችን ድንግል ማርያም ምሳሌ። ወርቅ፡- የንጽሕናዋ የቅድስናዋ ምሳሌ ነው። ቅዳሴ ሲገባ ከቤተልሔም ልዑካኑ ሲመጡ ዲያቆኑ መሶበ ወርቅ በራሱ ተሸክሞ ወደ መቅደስ ይገባል። በብሉይ ኪዳን የተደረገው ለሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ነውና ኅብስቱን በመሶበ ወርቅ በራሱ ተሸክሞ የሚገባው ዲያቆን የነቢያት ትንቢት ምሳሌ ነው። ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ኅብስቱ መግባቱ ነቢያት በተናገሩት ትንቢት መሠረት በቤተልሔም ተወልዶ በቀራንዮ የመሠዋቱ ምሳሌ ነው። በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ ፲፱፥፭-፰ (19፥5-8) ያለውን ታሪክ ስንመለከት ምሥጢሩ አንድ ነው።

አባታችን አባ ሕርያቆስ በደረሰው በእመቤታችን ቅዳሴ ድንግል ማርያምን በኤልያስ መሶበወርቅ ይመስላታል። እንዲህ ብሎ፡-

"መሶበ ወርቅ አንተ ኤልያስ" የኤልያስ መሶበ ወርቅ አንቺ ነሽ። የሰዓታት ደራሲም አባ ጊዮርጊስ ዘኢትዮጵያ (ዘጋሥጫ) በሰዓታቱ እስራኤል የወረደላቸውን የሰማይ እንጀራ ወይም መና ምስክር እንዲሆን ያስቀመጡበትን ጎሞር መሶበ ወርቅ የእመቤታችን ምሳሌ እንደሆነ ተናግሯል።

"ጻሙስ አንቲ ዘእስተርአይኪ በደብረ ሲና"

ጎሞረ ወርቅየ መስፈርቱ ለመና" ይህም ሙሴ በሲና ተራራ ያያት ጻጦስ የተባለች ዕፀ እንዲሁም መናው ምስክር የተቀመጠባትን ጎሞር (መሶብ) የእመቤታችን ምሳሌ መሆኑን ያሳያል። ከዚህ ነው አባታችን ቅዱስ ጊዮርጊስ መሶበ ወርቅ ብሎ የጻፈው። በውስጧ ያለው ኅብስተ መና የሁላችን ቤዛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህም ሁልጊዜ ቅዳሴ ሲገባ ሁሉም ይህንን ቃል እንዲህ እያለ ያዜማል፡-

> "አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡእ ኅብስት ዘወረደ እምሰማያት ወሃቤ ሕይወት ለኵሉ ዓለም"

"ንጹሕ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ በውስጧ የተሰወረ መና የነበረባት ከሰማይ የወረደ ኅብስት ለዓለም ሁሉ ድኅነትን የሚሰጥ"

ይህንን ቃል የውዳሴ ማርያም ደራሲ አባታችን ቅዱስ ኤፍሬምም በእሑዱ ውዳሴ ማርያም ላይ ተናግሮታል። ዋና ድርሰቱ የቅዱስ ኤፍሬም ነው። በቅዳሴው ላይ ያለው ከድርሰቱ ተወስዶ ነው።

## ጽዋዕ (ጽዋ)

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ቁርባንን በሠራበት ዕለት ለሐዲስ ኪዳን የኃጢአት ሥርየት የሚፈስውን ደሙን ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው በጽዋዕ ነው። ሁለተኛው በማግሥቱ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ደሙ ፈሰሰ። አንድ የመቶ አለቃም መጥቶ ጎኑን በጦር ወጋው በዚህን ጊዜ ደሙ ሲፈስ ቅዱሳን መላእክት በብርሃን ጽዋዕ (ጽዋ) እንደተቀበሉት ቤተክርስቲያናችን ታምናለች። በዚህ ታላቅ ሥርዓት መሠረት በቅዳሴ ጊዜ ክቡር ደሙ በጽዋዕ ተደርጎ ሥርዓቱ ይፈጸማል።

"ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።" ማቴ. ፳፮፥፳፯ (26፥27)

ይህ የወንጌል ቃል የሚፈጸምባት እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ ይህን የአምላክ ትእዛዝ አያከናወነች ትኖራለች። ይህም የጌታችን ትእዛዝ ዘወትር በቅዳሴው ይፈጸማል። በእመቤታችን ቅዳሴ አባታችን አባ ሕርያቆስም እንዲህ ተናግሮታል።

"ወከማሁ ጽዋዐኒ እምድኅረ ተደሩ አንጸረ ወይቤ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ያነቅዖ ኩይናት"

እንዲሁም ጽዋውን ከተመገቡ በኋላ አመለከተ ይህ ጽዋ ስለናንተ ጦር የሚያፈስው ደሜ ነው ንሡ ጠጡ አለ።

ጽዋ ምሳሌነት አለው። ይህም እንዲህ ነው፡-በብሉይ ኪዳን ዘመን ካህኑ የመሥዋዕቱን ደም ከመርጨት ደሙን የሚያደርግበት ጽዋዕ (ዕቃ) ከአሁኑ የጌታችን ደም መያዣ ጽዋዕ ምሳሌ ነው። ሌላው ደግሞ ጽዋዕ የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን ደሙ የጌታችን ምሳሌ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን እኛን በሚጸን ነፍስን ሥጋንና ደምን የተዋሐደው ከእመቤታችን ነውና። ሌላው ከላይ እንደተመለከትነው በስቅለቱ ጊዜ ለንጊኖስ የተባለ መኰንን በጦር ሲወጋው ደሙን እንዳፈሰሰው ያንን መከራውን አናስብ ዘንድ ዲያቆኑ በዕርፈ መስቀል ጽዋውን ጠልቆ ደሙን ማቀበሉ የዚያ ምሳሌ ነው። ጽዋው የተወጋው የጌታ ጎን፣ ዕርፈ መስቀሉ የጦሩ ምሳሌ ነው።

> "ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ" ዮሐ. ፲፱፥፴፬ (19፥34)

## ዕርፈ መስቀል

ዕርፈ መስቀል ዲያቆኑ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ከቆራቢዎች የሚያቀብልበት የተለየ ንዋይ ነው። የዚህም ምሳሌነቱ በሦስት ወገን ይህንን ይመስላል። የመጀመሪያው በዘመነ ብሉይ ከኃጢአት ማስተሥረያ እንዲሆን የሚቀርበው የመሥዋዕቱ ደም የሚረጭበትና የሚቀባበት የዕርፈ መስቀል ምሳሌ ነው። በብሉይ ካህኑ በጣቱና በመርጫ ደሙን ይረጭ ነበር።

> "ካህኑም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ባለው በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ደሙን ይረጨዋል።" ዘሌ. ፲፯፥፮ (17፥6)

ሁለተኛውም ነቢዩ ኢሳይያስ ንጉሥ ዖዝያንን መቅደሱን ሲደፍር ባለመገሠጹ ትንቢት ተነስቶት በነበረ ጊዜ መሐሪ እግዚአብሔር በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋኑ ተቀምጦ ሱራፌል ቅዱስ፣ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር እያሉ ሲያመስግኑት

የስማይ መቅደስ ተገለጠለት። ከሱራፌልም አንዱ ከመሠዊያው በጉጠት ፍም ወስዶ የኢሳይያስን ከንፈር ሲያስነካለት የኢሳይያስ በደል ተወገደለት። ኢሳይያስ ፮፥፮ (6፥6)። ሱራፌል ፍሙን የያዘበት ጉጠት ዲያቆኑ ደሙን ይዞ የሚያቀብልበት የዕርፈ መስቀሉ ምሳሌ ነው።

ሦስተኛም፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጎኑን የተወጋበት የጦሩ ምሳሌ ነው። ዮሐ. ፲፱፥፴፬ (19፥34)

## ጥላ

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከታቦት ከወንጌል፣ ከመስቀል፣ ከሥጋ ወደሙ፣ እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ሥርዓቱ ጥላ (ጃንጥላ) ይዘረጋል። ይህም ስለ ክብር ነው። ምሳሌነቱም እስራኤል በምድረ በዳ በተጓዙ ጊዜ የጋረዳቸው የክብር ደመናና ሊቀ ነቢያት ሙሴ በደብረ ሲና ታቦቱን በተቀበለ ጊዜ የጋረደው የክብር ደመና ነው። ሌላው ጥላ በሚዘረጋበት ጊዜ የምናስበው የእግዚአብሔር ረድኤት ሁልጊዜ በእኛ ላይ ረብቦ እንደሚኖር ነው።

"የደመናውም ዓምድ ከፊታቸው ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ" ዘጸ. ፲፬፥፲፱ (14፥19)

"ሙሴም ወደ ድንኳኑ በገባ ጊዜ የደመና ዓምድ ይወርድ ነበር በድንኳኑም ደጃፍ ይቆም ነበር። እግዚአብሔር ሙሴን ይናገረው ነበር። ሕዝቡም ሁሉ የደመናው ዓምድ በድንኳኑ ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር ሕዝቡም ሁሉ ተነሥቶ እያንዳንዱ ደጃፍ ይሰግዱ ነበር።" ዘጸ. ፴፫፥፱ (33፥9)

በዚህ ቃል መሠረት ቤተክርስቲያናችንን ስንመለከት፡- ሙሴ የካህናቱ ምሳሌ ነው። ሕዝቡ የምእመናን ምሳሌ፡ የደመናው ዓምድ የጥላው (የጃንጥላው) ምሳሌ ሕዝቡ በዚያን ጊዜ መስገዳቸው ዛሬም ለታቦት፣ ለሥጋ ወደሙ፣ ለወንጌል፣ ምእመናን የመስገዳቸው ምሳሌ ነው።

## ጽንሐሕ (ጥና)

እግዚአብሔር በሰማይ ያለውን የመቅደሰ ምሥጢር ለሙሴ ባሳየው መሠረት ካህኑ አሮን በመገናኛው ድንኳን ከእግዚብሔር በጽንሐሕ ዕጣንን ያቀርብ ነበር። ጽንሐሕ በግእዝ ሲሆን በዐማርኛ ጥና ይባላል - በግእዙ ማዕጠንት ብሎም ይጠራዋል።

"በእግዚብሔርም ፊት ካለው መሠዊያ ላይ የእሳት ፍም አምጥቶ ጥናውን ይሞላል። ከተወቀጠውም ከጣፋጭ ዕጣን እጁን ሙሉ ይወስዳል።" ዘሌ. ፲፮፥ ፲፪ (16፥12)

ከዚሀ ቃል እንደምንረዳው ጥና (ማዕጠንት) ከቤተመቅደሱ ንዋየ ቅድሳት አንዱ ነው።

"በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ" ዕብ. ፱፥፬ (9፥4) ይህ ሥርዓት እግዚብሔር ከዘካከም የሰጠው ሕግ ነውና ዛሬም በመቅደሳችን ይደረጋል። ምንጩ ከሰማይ መቅደሰ ነው። ምድራዊ አይደለም። ዘጸ ፳፭፥ ፱ (25፡9)

"ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ" ራዕ. ፰፥፮ (8፥6)

በእግዚብሔር መቅደሰ ይህ በሚደረግበት ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ እንደተመለከተውና በዚሁ ምዕራፍ እንደጻፈው ከማዕጠንቱ በሚወጣው ከዕጣን ጢስ ጋር የሰው ልጆች ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያርጋል። ሌላው በጥናው አሠራርና ሥርዓት ልዩ የቤተክርስቲያናችን ምሥጢር ይገለጽበታል። ይኸውም፣ - ጽንሐሕ ከእመቤታችን ምሳሌነት አለው። በሥርዓተ ቅዳሴ እንዲህ ይላል፡- "አንቲ ውእቱ ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት ቡሩክ ዘነሥአ እመቅደሰ" (ዋና ድርሰቱ የቅዱስ ኤፍሬም ነው። የእሑዱ ውዳሴ ማርያም ላይ ይገኛል)

"ቡሩክ ከቤተመቅደሰ የተቀበላት የእሳትን ፍሕም

የተሸከምሽ የወርቅ ጥና አንቺ ነሽ"

ምሳሌነቱም እንዲህ ነው፡- አሳቱን ይዞ የሚሸከመው የጥናው ክፍል የእመቤታችን ማኅፀን ምሳሌ ነው። አሳቱ የመለኮት (የቃል) ዕጣኑም የትስብዕት (የሥጋ) ምሳሌ ነው። አሳቱ ጥናውን እንደማያቃጥለው እመቤታችንም እሳት የተባለ መለኮትን በማኅፀኗ በተሸከመች ጊዜ እሳተ መለኮትነቱ እንዳላቃጠላት የሚገልጽ ነው። የወርቅ ጥና ብሎ መግለጹም ወርቅ የተባለ የእመቤታችን ንጽሕናዋ ነው። ጥና የሚያያዝበት አራት ዘንጎች አሉ። አንዱ በመሐከል ሆኖ ሦስቱ ደግሞ ሻኩራዎችን ተሸክመው ይሠራሉ። ይህም የሚያስተምረን ሦስቱ ዘንጎች በስም በአካል በግብር ሦስት የሆነ የእግዚአብሔር መሐከል ያለው አንዱ ደግሞ በመለኮት በአዘዝ በአገዛዝ ይህን ዓለም በመፍጠርና በማሳለፍ አንድ መሆኑን የሚገልጽ ምሳሌ ነው። ይህም በጐላ በተረዳ ነገር የተገለጸው መድኃኒታችን ከእመቤታችን በተወለደ ጊዜ ስለሆነ በጥናው አሠራር ተገልጾ እናየዋለን።

> "መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ሉቃ. ፩፥፴፭ (1፥35)

በተጨማሪ የመሐከለኛውን ዘንግ ስንመለከት የምንረዳው ሌላ ዐቢይ ምሥጢር ዘንጉ የማኅፀኗ ምሳሌ ከላይ ወደታችኛው የማኅፀኗ ምሳሌ ወደሆነው ክፍል መውረዱ ቃል የተባለ እግዚአብሔር ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በድንግል ማኅፀን የመፀነሱና ከእርሷ የመወለዱ ምሳሌ ነው። ሦስቱ ዘንጎች ደግሞ እመቤታችን በሦስት ወገን ያላትን ንጽሕና የሚገልጽ ነው እነዚህም ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስና ንጽሐ ልቡና ናቸው።

እንደገናም ከሰው ዘር ሁሉ ልዩ የሆነች እመቤታችን በሦስት ወገን ድንግል መሆኗን የሚያመለክት ነው ይህም በኃልዮ (በሐሳብ) በነቢብ (በመናገር) በገቢር (በመሥራት) ከሚመጣ ኃጢአት እመቤታችን ንጽሕት መሆኗን ነው። "አሳትነት ያለውን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ማዕጠንት አንቺ ነሽ" ቅዱስ አባ ኤፍሬም ውዳሴ ዘሰንበተ ክርስቲያን (ዘእሑድ)

በሦስቱ ዘንጎች ላይ ያሉ ድምፅ የሚሰጡ ሻኩራዎች የሚመስሉት እንደየቀጥራቸው ነው። ቀጥራቸውም አሥራ ሁለትና ሃያ አራት ነው። አሥራ ሁለት ሲሆን የአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤልና የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፡ ሃያ አራት ሲሆን ደግሞ የሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ምሳሌ ነው። የሚሰጠውም ድምፅ የነቢያት ትንቢት የሐዋርያቱ የቃላቸው ነገርና የሃያ አራቱ ካህናተ የሰማይ ቅዳሴ ነው።

"ውስተ ኩሉ ምድር ወፅአ ነገሮሙ"

"ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ"

"ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ

ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ" መዝ. ፲፰፥፬ (18፥4)

"ሃያ አራቱም ሽማግሌዎችና አራቱ እንስሶች በፊታቸው ተደፍተው በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለእግዚአብሔር አሜን ሃሌ ሉያ" እያሉ ሰገዱለት። ድምፅም፡- ... ከዙፋኑ ወጣ። እንደ ብዙ ሕዝብም እንደ ብዙ ውኃዎችም ድምፅ እንደብርቱም ነጎድጓድ ድምፅ ያለ ድምፅ ሰማሁ።" ራዕ. ፲፱፥፬-፰ (19፥4-8)

ጽናውን ይዘው እያጠኑ በመቅደሱ የሚያገለግሉም ካህናት በሰማይ ካህናት፡ በአሮንና በልጆቹ፡ በነዘካርያስ የክህነት ሥልጣን ያሉና በእግዚብሔር የተሾሙ ናቸው።

## ንዋየ ቅድሳት ለሌላ አገልግሎት አይውሉም

እነዚህ የተመለከትናቸው የተባረኩ የቤተመቅደስ ንዋያትና አጠቃላይ የቤተክርስቲያን የውስጥ መገልገያዎች በፍጹም ከቤተመቅደስ ወጥተው ከዓለማዊ ግብር አይደረጉም። ከዚህም የባቢሎንን የአጭር ጊዜ ንጉሥ የነበረ በድፍረቱ የተቀሰፈ ብልጣሶርን በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 5 የተጻፈውን መመልከት ትልቅ ማትረፊያ ነው።

"የዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበረው ከእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የመጡትን የወርቁን ዕቃዎች አመጡ ንጉሡና መኳንንቶቹም ሚስቶቹና ቁባቶቹም ጠጡባቸው።" ዳን ፭፡፫ (5፡3)

በትንቢቱ እንደተጻፈው እግዚአብሔር በዚያች ሌሊት ብልጣሶርን ቀሰፈ። ዛሬም ይህ የመቅደሱን ዕቃ ከዓለማዊ ግብር ሊያደርጉ የሚሞክሩትና የሚያቃልሉትን ሁሉ በማኔ ቴቄል ፋሬስ እየመዘ ሲገስጽ ይኖራል። ከዚህም የተነሳ ሰዎች በዚህ ድፍረት እንዳይጠፉ አባቶቻችን ሕግን ሠርተውልናል።

"ከቤተክርስቲያን ከተባረከ ዕቃ ወገን የሆነውን ሁሉ የወርቅና የብር ዕቃም ቢሆን ሰው በቤቱ ውስጥ ሊሠራባቸው አይገባውም። ይህ ሕግን ማፍረስ ነውና። ይህን ያደረገ እንደሆነም ከተፈረደበት በኋላ ከቤተክርስቲያን ይከይ" ረስጣ ፳፰ (28)

# ቅዱሳን ሥዕላት

በቅድስት ቤተክርስቲያን የሚፈጸመውና የሚደረገው የቅዱሳን ሥዕላት ነገር በቅዱስ መጽሐፍ መሠረትነት የተደገፈና በእግዚአብሔር የተፈቀደ ከመሆኑ ከሚያምን ምንም ጥርጥር የሌለው ነው። በብሉይም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ሥዕል እንደነበረ የሰው ልጆችም ከፈጣሪያቸው የሚገናኙበት አንዱ የድኅነት መንገድ እንደነበር እንመለከታለን።

በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ሃያ አምስት ቁጥር አሥራ ዘጠኝ ስንመለከት (25፥19) የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሙሴን መላእክትን እንዲሠራ (እንዲሥል) እንዳዘዘው እንመለከታለን።

> "ከሥርየት መክደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሠራዋለህ"

ኪቀ ነቢያት ሙሴም ይህንን የአምላክ ትእዛዝ ተቀብሎ የመላእክቱን ምስላት በመቅደሱ አድርጓቸዋል። እግዚአብሔርም በእነሱ ሆኖ ያነጋግረው ነበር።

> "በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል በሥርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋግርሃለሁ" ዘጸ. ፳፭፥፳፪ (25፥22)

ይህ ትእዛዝ ከሙሴና በዘመኑ ካሉ ሰዎች ብቻ ተሰጥቶ የሚያበቃ አይደለም። ይህንንም ጠቢቡ ሰሎሞን ከእግዚአብሔር መቅደሱን ሲሠራ መላእክቱን የዘንባባ ምስል ሌሎችንም ሠርቶ ነበር። መቅደሱ ዛሬም ስላለ ሥዕላቱም አብረው አሉ።

> ፩ ነገ ፮፥፳፫-፴ (6፥23-30) በዚሁ ቃል ላይ ስንመለከት ሰሎሞን የሠራቸውን ሁለት ኪሩቤል በቁጥር ሃያ ስምንት (28) እንደምናየው በወርቅ ለበጣቸው ይላል። ይህ ክብር ዛሬም በቤተክርስቲያናችን ይደረጋል።

አንዳንድ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀት ማነስ የተነሳ የእግዚአብሔርን አሠራር ከአጋንንትና ከጣዖት አሠራር ጋር እያቀላቀሉ የሥዕላትን ነገር ከመቀበል ሲፈተኑ እናያለን። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን የመቅደሱ አሠራር ከጠቅላላ ጓዙ ጋር ትእዛዘ እግዚአብሔር መሆኑን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ልብ አድርጎ መገንዘብ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር የሚያዝንና የሚነግረን ሁሉ የሚጠቅምና ቅዱስ ነው።

ከምሳሌ እስራኤል በምድረ በዳ በነዘር እባብ በተነደፉ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ አዞት ነበር።

> "እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል አለው።" ዘኁ. ፳፩፥፰ (21፥8) ቃሉ በቀጥር ዘጠኝ እንደሚነግረን "ሙሴም የነሐሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈችውን ሰው ሁሉ የነሐሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ"

እንባቢ ሆይ የምናስተውለው ነገር ቢኖር ይህ የነሐስ እባብ ተስቅሎ ተሠርቶ ያዩትን ካዳነ ዛሬ ያሉን በአምላክና በቅዱሳን ስም የሚሠሩ ቅዱሳን ሥዕላት ማዳን እንደሚችሉ ማረጋገጥ ነው። የዚህም የሙሴ የነሐስ እባብ ምሳሌውና ምሥጢሩም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ ተራራ መስቀል ነው።

> "ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል" ዮሐ. ፫፥፲፬ (3፥14)

ትርጓሜ፡- እስራኤል የነፍሳት ምሳሌ፡ የነደፋቸው እባብ የሰይጣን ምሳሌ፡ ሙሴ የሠራውና የሰቀለው የነሐስ እባብ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፡ የነሐሱ እባብ የተሰቀለበት ዓላማ የመስቀል ምሳሌ፡ እስራኤልን የነደፋቸው እባብ በውስጡ ክፉ መርዝ እንዳለው ሁሉ ሰይጣን ሰዎችን የሚገድል ክፉ ምክር ያለው ከመሆኑ ምሳሌ፡ ሙሴ የሰቀለው የነሐስ እባብ ግን መርዝ የለውም የነሐስ ነው ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ በነበሩ ሰዎች እንደኃጢአተኛ

ቢታይም እርሱ ግን ክብር ይግባውና ንጹሐ ባሕርይ መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

ይህ የሙሴ ሥራ ጣዖት አይባልም በእግዚአብሔር የታዘዘ ነውና። ከዚህም በተገኘ ትምህርት የጌታችንን ሥዕል ብናደርግ የምንድንበት ከተያዝንበት የዲያብሎስ ሽንገላ የምንፈወስበት ከመሆኑ የሚያሳምን ነው።

> "ኦ አብዳን ሰብአ ገላትያ መኑ አሕመመክሙ ከመ ኢትእመኑ በጽድቅ ዘያስተርኢ ከዐይን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአቅደመ ተጽሕፎ በእንቲአሁ ከመዝ ይሰቀል"
>
> "የሚታለተሙሉ የገላተያ ሰዎች ሆይ በዐይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ (ተጽፎ) ነበር ከእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማነው?" ገላ. ፫፥፩ (3፥1)

ይህ አዚም ብዙዎችን የያዘ ነው ስለዚህም የእግዚአብሔር የሆነውን እንኳ ከይተው ከማየት አልቻሉም። ይህን ቃል የጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚገልጸው ከገላትያ ሰዎች ጌታችን ልክ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተጽፎ ማለትም ተሥሎ ነበር። ሐዋርያትና ቅዱሳን ሥዕልን ይጠቀሙ እንደነበረ በሮማ ምድር ሥር የሚገኘው ግበበ-ምድር (ካተኮም) የያዛቸው በነሱ የተሣሉ ሥዕሎች ከሚያስተውል ይመሰክራሉ።

በቤተክርስቲያናችንና በታሪክ እንደሚታመነው የጌታችን የስቅለት ሥዕል በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ የእናቱ የድንግል ማርያም ተወዳጅ ልጁን እንዳቀፈች በቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ የተሣሉ ናቸው። ይህንንም ብዙ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አባ ጊዮርጊስን ጨምሮ መስክረውልናል።

## ስግደት ለሥዕላት

ለእምላክ ሥዕል የአምልኮት ለቅዱሳን ሥዕላት የአክብሮት ስግደት ይሰገዳል። በቤተክርስቲያናችን "መልክአ ሥዕል" የሚባል ጸሎት አለ። ዘወትር በነግህ ከሚደርሱ ምስጋናዎች

ውስጥ አንዱ ነው። በዚህም ጸሎት እግዚአብሔር በአምላክነቱ አመቤታችንና ቅዱሳንም እንደየማዕረጋቸው ይወሳሉ፡" ይመስገናሉ።

ስለ ታቦትና ስለ መስቀል በተጻፈው እንዳየነው ከሥዕል በሚሰገድበት ጊዜ ለተሠራበት ቀለ ሳይሆን በጸሎት በከበረው ሥዕል ስግደቱ የሚቀርበው ከባለቤቱ ነው። ያዕቆብ አባታችን በዘንጉ ከእግዚአብሔር ስገደ ብሎ መጽሐፍ እንደሚነግረን ያለ ነው ዕብ. ፲፩፥፳፩ (11፥21) መስገዳችንና መሳማችን የሚገልጸው ያለንን ትሕትናና ፍቅራችንን ነው ዛሬ የምንወዳቸውንና የዘመዶቻችንን ምስል (ፎቶግራፍ) ቢኖሩም ቢሞቱም አክብረን እንደምንይዘው ያለ ነው። የእግዚአብሔርና የቅዱሳኑ ደግሞ በክብር የተለየ ነው። በሥዕሉ ፊት በምንጸልይበት ጊዜ በብዙ እንደተገለጸ እግዚአብሔር መልስ ይሰጠናል።

> "በሁለት ኪሩቤል መካከል በሥርየት መክደኛው ላይ ሆኜ እነጋግርሃለሁ" ዘጸ. ፳፭፥፳፪ (25፥22)

ጥበበኛው ሰሎሞንም መቅደሱን ሠርቶ ሥዕሉን አስጊጦ የቃል ኪዳኑን ታቦት አስገብቶ በፊቱ ተንበርክኮ ስግዶ ቢለምነው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ነበር ያለው፡
-

"... ከዘላለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ዐይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ" ፩ነገ. ፱፥፫ (9፥3) ከላይ እንደተመለከትነው ሰሎሞን ቅዱስ መቅደሱን ሲሠራ አብሮ ሥዕላትን ሠርቷል በታቦቱ ፊትም በሚሰግድ ጊዜ ከሠራቸውም ኪሩቤል መካከት ይሰግድ ነበር። እግዚአብሔርም ተቀበለው እንደውም ዐይኖቼና ልቤም በዚህ ናቸው አለው። ሥዕሎቹን አውጣና ጣል ጣዖታት ናቸው አይገቡም አላለውም ዛሬም እኛን አይለንም ያዘዘን እርሱ አምላካችን ነውና። ይልቁንም ደስ ይለዋል።

## ቅዱሳት ሥዕላት ያድናሉ

የማዳኑ ነገር የማይለፈረውና የማይቆጠረው እግዚአብሔር መንፈሱን በሥዕላቱ ላይ ስለሚያሳድር የሰዎች ልጆች ልመናን ሰምቶ በነርሱ ያድናል ይጠብቃል። ቅዱሳንም ወደነርሱ የቀረበውን ምልጃ ፈጥነው ይፈጽማሉ ይህ ሁሉ የሚሆነው ለሚያምን ነው። ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና። ማር. ፱፥፳፫ (9፥23)

ቅዱሳን ስንኳን ሥዕላቸው የለበሱት ልብስና ጥላቸው እንደሚፈውስ የረገጡት በረከት እንደሚሆን ቅዱስ ቃሉ ነግሮናል።

አስረጅ፡-

ቅ/ጴጥሮስ በጥላው ይፈውስ ነበር ሐዋ. ፭፥፲፭ (5፥15)

ቅ/ጳውሎስ በቀሚሱ ጫፍ እንደ ጌታ ይፈውስ ነበር ሐዋ. ፲፱፥፲፩ (19፥11) ማቴ. ፱፥፳ (9፥20)

ቅ/ኤልሳዕ የረገጠው የመሬት አፈር እንኳ በረከት እንደሆነ ፪ነገ ፭፥፲፯ (5፥17)

በግርማ መለኮቱ በክብረ መንግሥቱ የማይታይ አምላክ ከድንግል ተወልዶ በተዋሐደው ሥጋ ከዓለም የተገለጠ ሕያው እግዚአብሔር ያዘዘንን ፈጽመን ደግሞ ሲመጣ በቀኙ ያቆመን ዘንድ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን!

"ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአብ"

"እኔን ያየ አብን አየ" ዮሐ. ፲፬፥፱ (14፥9)

# ጠበል (ጸበል)

ጠበል የሚለው ቃል ምንጩ ከግእዙ ጠበለ ከሚለው ቃል ነው። ትርጉሙም ጠበለ፣ ተጠበለ ዘፈቀ ተዘፈቀ ጠመቀ ተጠመቀ ማለት ነው። ይህ ቃል በቤተክርስቲያን የተቀደሰን ውኃ ያመለክታል። በቤተመቀደሱ የሚጸለይበት ማይ (ውኃ) ጠበል ተብሎ ይጠራል። እንዲሁም ድውያን ይፈወሱበት ዘንድ በተለያዩ ስፍራዎች እግዚአብሔር የመረጠው ውኃ ጠበል ተብሎ ይጠራል። ካህናት የሚጸልዩበት ውኃ የተለየ ውኃ የተቀደሰ ይሆናል ጠበልም ተብሎ ይጠራል። ብዙውን ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ጠበልን ጸበል ብለው ይጠራሉ ይህም ጠበለ ከሚለው ግሥ በተለየ ደግሞ ጸበለ የሚልም አለ። የዚህ ትርጉም ደግሞ አፈር ማለት ነው። ይህም ከጠበል ጋር የተገናኘው ምእመናንም ጸበል እያሉ የሚጠሩበት ከጌታ ተአምር የተነሣ ነው።

> "ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዐይኖች ቀባና። ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፤ ትርጓሜው የተላከ ነው። ስለዚህ ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ።" ዮሐ ፱፡፮- ፯ (9፡6-7)

ጠበል ቢባል ጸበልም ቢባል በምሥጢር ይገናኛል አንድ ነው።

## ጠበል በብሉይ ኪዳን

የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ ፩(1) ቁጥር ፪(2) እንዲህ ይላል ... "መንፈስ እግዝእብሐር ይጼልል መልዕልተ ማይ" የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃው ላይ ይሰፍፍ ነበር። ይህ ምሥጢር በጥምቀት የሚሰጥ የህብተ መንፈስ ቅዱስ ምሳሌና በሃይማኖተ አበው ክፍል ዘጠኝ(9) ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ እንደተገለጸው ከእመቤታችን ድንግልናን የከፈለ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል የምንረዳው ሌላው በውኃ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያድርበት

ነው። ከዚህም ነው ቅዱስ ውኃ ወይም ጠበል አጋንንትን የሚያርቅ፣ መንፈስ ቅዱስን የሚያቀርብ፣ ዕውራንን የሚያበራ፣ ለምጻሙን የሚያነጻ፣ ጎባጣውን የሚያቀና፣ ሽባውን የሚተረትር፣ የልቡናን ጭንቀት የሚያስወግድ ፍርሃትን የሚያርቅና ሰላምና ጤናን የሚያድል።

> "በዚያን ጊዜ የዕውሮች ዐይን ይገለጣል፤ የደንቆሮችም ጆሮ ይከፈታል። በዚያን ጊዜ አንካሳ እንደሚዳቋ ይዘላል፣ የድዳም ምላስ ይዘምራል በምድረ በዳ ውኃ በበረሀ ፈሳሽ ይፈልቃልና። " ኢሳ. ፴፭፡፭ (35፥5)

ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረው በጠበል አስደናቂና አስገራሚ ተአምራት ይፈጸማሉ ከዚህም መካከል የሶሪያ ሰው የጦር አዛዥ የንዕማን ታሪክ አንዱ ነው። ንዕማን የሶሪያ ሰው ሲሆን በሽታውም ለምጽ ነበር። በቤቱ ያለች አንዲት እስራኤላዊት የነገረችውን ምክር በመስማት ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። በሰማርያ የነበረውም የእግዚአብሔር ሰው ነቢዩ ኤልሳዕ በዮርዳኖስ እንዲጠመቅ ወይም እንዲታጠብ ነገረው። ንዕማንም ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ ሰባት ጊዜ ቢነከር ከሕመሙ ተፈወሰ የቀድሞ ጤንነቱ ተመለሰ እግዚአብሔርንም አመስግኖ አመከከ። ፪ነገ ፭፡ ፩-፲፱ (1፥19)

በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቀው ከዳኑትም መካከል ታላቁ ሰው ኢዮብ ይገኛል። በመጽሐፈ ኢዮብ እንድምታ እንደተገለጸው

> "ወተሰአሎ እግዚአብሔር ለኢዮብ በደመና ወበዓውሎ" መ. ኢዮብ ፴፰፡፪ (38፥2)። እግዚአብሔር ኢዮብን በደመናና በዓውሎ እንዳነጋገረው በዮርዳኖስም ተጠመቅ ብሎ አዝዞት እንደተፈወሰ ተጽፎአል።

## ጠበል በሐዲስ ኪዳን

ስለ ጸበል ከብሉይ ኪዳን የበለጠ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ እንመለከታለን። ለብዙ ዘመናት ታሞ ተኝቶ የነበረባት በዕብራይስጥ ቤተሳይዳ በግእዙ ቤተ ሣህል በአማርኛው የምሕረት ቤት የተባለችውን የጸበል ስፍራ በዮሐንስ ወንጌል ፭፥፪-፱ (5፡2-9) የእግዚአብሐር መልአክ ውኃውን ሲባርከውና ከማናቸውም ደዌ ሰዎች ሲፈወሱ እናያለን። " ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት። በእነዚህ ውስጥ የውኃውን መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውኃውን ያናውጥ ነበርና፤ እንግዲህ ከውኃው መናወጥ በኋላ በመጀመሪያ የገባ ከማናቸው ካለበት ደዌ ጤናማ ይሆን ነበር። በዚያም ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ። ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ እስከ አሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ አውቆ። ልትድን ትወዳለህን? አለው። ድውዩም ጌታ ሆይ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት። ኢየሱስ። ተነሣና አልጋህን ተሸከመህ ሂድ አለው። ወዲያውም ሰውዬው ዳነ አልጋውንም ተሸከሞ ሄደ። " ዮሐ ፭፥፩-፱ (5፡1-9) በዚህ የእግዚአብሐር ቃል ልብ የምንለው፡-

፩ኛ. ቤተሳይዳ የምትባል መጠመቂያ ነበረች

፪ኛ. ብዙ ሕሙማን በመጠመቂያ ከመፈወስ ይሰበሰቡ በዚያም ተኝተው መዳናቸውን ይጠባበቃሉ።

፫ኛ- የእግዚአብሐር መልአክ ውኃውን ይባርከዋል።

ዛሬም በቤተክርስቲያናችንና በጠበል ስፍራዎች ሕሙማን

መዳናቸውን ይጠባበቃሉ፣ ሲጠመቁም ይድናሉ፤ በእግዚአብሔር መልአከም ይባረካሉ።

በጠበል መጠመቅ በጌታችን የተወደደና የተፈቀደ መሆኑን የሚገልጽልን መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በወንጌለ ዮሐንስ ምዕራፍ ፱፥፯ (ዮሐ. 9፥7) መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው በሰሊሆም የጠበል ቦታ እንዲጠመቅ ያዘዘው። ያም ሰው ወደ ሰሊሆም ሄዶ ታጠበ ተጠመቀ እያየም መጣ ይላል። አምላካችን ምስጋና ይግባውና መዳናችንን በብዙ መንገድ አደረገልን።

## ጠበል በሰማይ መቅደስ

በቤተክርስቲያናችን የምንጠቀመውና የምንፈጽመው ሥርዓት ሁሉ ምንጩ የሰማይ መቅደስ ነው። ይህም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሕግና ሥርዓት ነው። ሙሴ የእግዚአብሔር አምላክ ማደሪያን ሲሠራ በሰማይ ማደሪያ አምሳል እንዲሠራ ያዘዘው ራሱ እግዚአብሔር አምላክ ነው።

> "እኔ እንደማሳይህ ሁሉ እንደማደሪያው ምሳሌ እንደ እቃም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት" ዘጸ. ፳፭፥፰ (25፥8)

የተቀደሰው ማይ ወይም ጸበል በሰማይ መቅደስ ካለው በሕይወት ውኃ አምሳል ነው። ይህም ከበጉ ዙፋን የሚወጣው እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀው የሕይወት ውኃ ወንዝ አሥራ ሁለት ፍሬ ያለባትን የሕይወት ዛፍ የሚያጠጣና የሚያከመልም ሲሆን ቅጠሎቹም የሕዝብ መፈወሻ ነበሩ። ራእ. ፳፪፥፩-፪ (22፥1-2)

"ነቢዩ ሕዝቅኤል እንደተናገረው ይህ ውኃ የረከሱ ውኆችን ሁሉ የሚፈውስ ቅዱስ ውኃ ነው።" ሕዝ. ፵፯፥፰ (47፥8)

# ዕጣን

ከእግዚብሔር አምላክ ከሚቀርቡ ኃጢአትን ከሚያስተስርዩ ስጦታዎች አንዱ ዕጣን ነው። በብዙ ስፍራዎች በምድር መቅደስ የምናቀርበው አገልግሎትና በሰማይ መቅደስ ያለው ተመሳሳይ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ዕጣንም እንደዚሁ ነው። በሰማይ መቅደስ የተገለጸ እንደሆነ እንዲሁ በምድር ባለ የእግዚአብሔር መቅደስ እንዲኖር ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር አዘዘ። ዘጸአት ፳፭፥፩-፱ (25፥1-9)

## ዕጣን በሰማይ መቅደስ

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲያዘዘው የመገናኛውንና የማደሪያውን ድንኳን ሲሠራ በሰማይ መቅደስ አምላክ ነውና በሰማይ መቅደስ ሃያ አራቱ ካህናት በጥና ዕጣንን እንደሚያቀርቡ ቅዱስ ዮሐንስ በራዕዩ ተመልክቷል።

> "...አራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ ኪቃናት በበጉ ፊት ወደቁ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።" ራእ. ፭፥፰ (5፥8)

> "ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ከቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው" ራዕ. ፰፥፫ (8፥3)

## ዕጣን በሕገ ልቡና

በቤተርስቲያናችን ትምህርት መሠረት ዕጣን በሕገ ልቡናም ዘመን ከእግዚአብሔር ይቀርብ እንደነበር መጻሕፍት ይገልጹልናል። ከምሳሌ የሳሌም ንጉሥ የተባለ መልከ ጼዴቅ አጽመ አዳምን በቀራንዮ ያጥን እንደነበረ መሥዋዕትን

ያቀርብ እንደነበረ ካህንም ተብሎ እንደተጠራ ይመሰክሩልናል። ለዚህ ነው ቅ/ጳውሎስ መልከጼደቅንና አሮንን አንድ ላይ የሚገልጻቸው። ዕብ. ፭፥፩-፮ (5፥1-6)

## ዕጣን በዘመነ ብሉይ

በሰማይ ያለው ሥርዓት በምድር ስለተሠራ የዕጣኑ ዓይነት፥ አሠራሩ፣ የዕጣኑ መሠዊያ አጠቃላይ ሥርዓቱ ምን መሆን እንደሚገባው እግዚአብሔር ለሙሴ ነግሮታል።

"የዕጣን መሠዊያ ከግራር እንጨት ሠራ" ዘጸ. ፴፯፥ ፳፭ (37፥25)

"የተቀደሰውንም የቅብዓቱን ዘይት ጥሩውንም የጣፋጭ ሽቱ ዕጣን በቀማሚ ብልሃት እንደተሠራ አደረገ።" ዘጸ. ፴፯፥፳፱ (37፥29)

"በእግዚአብሔር ፊት ዕጣኑን በእሳቱ ላይ ያደርጋል" ዘሌ. ፲፯፥፲፫ (17፥13)

## ዕጣን በዘመነ ሐዲስ

ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ የጻፈውን በምዕራፍ አምስት ቁጥር ስምንትና በምዕራፍ ስምንት ቁጥር ሦስት ያለውን ጨምረን የአምነታችን መሥራች ቤተክርስቲያንን በደሙ የዋጀ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ጥበብና ምሥጢር የተገለጸላቸው የጥበብ ሰዎች ካቀረቡት እጅ መንሻ ከወርቁ ጋር ዕጣንና ከርቤ ነበር።

"ወበዊአሙ ውስተ ቤት ርእይዎ ለሕፃን ምስለ ማርያም እሙ ወወድቁ ወሰገዱ ሎቱ ወአርኃው መዛግብቲሆሙ ወአብኡ ሎቱ አምኃ ወርቀ ከርቤ ወስኂነ።"

"ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት ወድቀውም ሰገዱለት ሣጥኖቻቸውን ከፍተው

እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት" ማቴ. ፪፥፲፩ (2፥11)

ዕጣንን ጨምሮ እዚህ ንባብ ላይ የምንመለከታቸው ስጦታዎች ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ይፈጸማሉ። ሰብአሰገል ሕፃኑን ኢየሱስን ከእናቱ ጋር አገኙት ሰገዱ እንዳለ እኛም እናትና ልጁ አሉን። ሰግደትም አለን። እጅ መንሻና መባዕ እንደሰጡ እንዲሁ በመቅደሳችን ይደረጋል። ከሦስቱ ስጦታዎች ዕጣንና ከርቤ ተመሳሳይ ናቸው። ከርቤ የዕጣን ዘር ነው።

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ መልአኩ ቅ/ገብርኤል ዘካርያስን እንደት እንዳበሠረው ሲጽፍ ካህኑ ዘካርያስ በካህናት ተራ መሠረት በመቅደሱ ዕጣንን ያቀረበ ነበር።

"እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ከማጠን ዕጣ ደረሰበት" ሉቃ. ፩፥፰ (1፥8)

እነዚህ የወንጌል ንባባት የሚገልጹልን ዕጣን ከዘላለም ሥርዓት ይሆን ዘንድ የታዘዘ የእግዚአብሔር ሕግ መሆኑን ነው። በአንድ ዘመን ተደርጎ የሚቢቃ አይደለምና። ስለዚህም ነበር እግዚአብሔር እምላከ ሙሴን ስለሥርዓቱ በነገረው ጊዜ ይህን ጣፋጭ ሽቱ ዕጣን ሁልጊዜ መብራት አብርቶ እንዲያጥን ይህም ከልጅ ልጅ ሁሉ የዘወትር ዕጣን ተብሎ የታዘዘው። ዘጸ. ፴፥፯-፱ (30፥7-9) ። ይህ ደገኛ ሥርዓት በኢየሩሳሌም መቅደስ ብቻ ወይም በዘመነ ብሉይ ብቻ እንዳልሆነ እግዚአብሔር በነቢዩ ሚልክያስ አድሮ ነገረን፡-

"ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" ሚል. ፩፥፲፩ (1፥11)

## የማጠን ሥርዓት

በቤተክርስቲያን ዕጣን ከእግዚአብሔር በሚታጠንበት ጊዜ

የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው። በዕጣኑ ላይ የሚጸለየውም ጸሎት "ጸሎተ ዕጣን" ተብሎ ይታወቃል። በፍጹም ያለ ሥርዓት ያለ ጸሎትና ቡራኬ ዝም ብሎ አይደረግም። ይህም ሥርዓት በካህናት ቀሳውስት የሚደረግ ነው። ዲያቆንም ቢሆን ይህን ማድረግና ዕጣን በመቅደሱ ማጠን አይችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደታዘዘ ትልቅ ጥንቃቄ ይደረጋል። ካህናት ብቻ ሥርዓቱን ይፈጽማሉ። ይህንን ትእዛዝ ስለሻሩ ነበር እግዚአብሔር ዳታንና አቤሮንን የቆሬን ቤተሰቦች ከነሕይወታቸው ወደ ጥልቀ ያወረዳቸውና በእሳትም ያጠፋቸው።

> "በቆሬና በወገኑ የደረሰው እንዳይደርስበት ከአሮን ልጆች ያልሆነ ሌላ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ዕጣን ያጥን ዘንድ እንዳይቀርብ እግዚአብሔር በሙሴ እንደተናገረው ከእስራኤል ልጆች መታሰቢያ አደረጋቸው።" ዘኁ. ፲፮፥፵ (16፥40)

ይህን የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚተላለፍ ጥሉ ከሕገ ባለቤት ከእግዚአብሔር ጋር ነው። ንጉሥ ዖዝያን ክህነት ሳይኖረው በእናቱ በኩል ከካህን እወለዳለሁ ብሎ ጥናውን ይዞ ከማጠን ወደ መቅደስ ቢገባ በእግዚአብሔር መቅሠፍት በንዳድ እንደተመታ እንማርበት ዘንድ በመጽሐፍ ተገልጧል። እንደተጻፈውም ዖዝያን በበረታና ልቡ በታበየ ጊዜ በድፍረት በዕጣን መሠዊያ ላይ ሊያጥን ሲገባ ካህኑ አዛርያስና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰማኒያ ካህናት እየተቃወሙ እንዲህ አሉት፡- "ዖዝያን ሆይ ዕጣን ማጠን የተቀደሱት የአሮን ልጆች የካህናቱ ሹመት ነው እንጂ ከእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ ለአንተ አይገባህም በድለሃልና ከመቅደሱ ውጣ ከአምላክም ከእግዚአብሔር ዘንድ ክብር አይሆንልህም አሉት። " ፪ዜና ፳፮፥፲፯ (26፥17)። ዖዝያን ግን አልሰማም የተመካበትን ሥልጣን አጥቶ ፍፃሜው ሞት ሆኗል።

እንኳን ክህነት የሌለው ሰው ካህናትም ዕጣንን ከማጠን ወደ መቅደሱ በሚገቡ ሰዓት ከኃያሉ ከእግዚአብሔር ነውና መጠንቀቅ ይገባቸዋል። በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ አሥር ቁጥር አንድ እንደተጻፈ የካህኑ የአሮን ልጆች እንደ

አባታቸው ካህናት ነበሩ። በአገልግሎታቸውም እግዚአብሔር ያላዘዘውን እሳትና ዕጣን ቢያቀርቡ እሳት ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው። በታላቅ ፍርሃትና ንጽሕና ካልሆነ እግዚአብሔር አይቀበለውም እንደውም በቃሉ እንደተናገረ አጸያፊ ነው።

ምእመናን ከእግዚአብሔር የሚያመጡት ካህናትም ከሰሙ የሚያጥኑት በንስሐ ሕይወት በታላቅ ፍርሃት ካልሆነ፡ ሁሉ የእርሱ የሆነ እግዚአብሔር አይቀበለውም። በንጽሕና ይሆን ዘንድ በንስሐ ታጥበን ካልሆነ ቃሉ ይገሥፀናል።

"ምናምንቴውን ቁርባን ጨምራችሁ አታምጡ ዕጣን በእኔ ዘንድ አስጸያፊ ነው።" ኢሳ. ፩፥፲፫ (1፥13) ኤር. ፮፥፲፱-፳፩ (6፥19-21)

በዚህ ምዕራፍ ስንመለከት በንስሐ ሕይወት ካልኖርን መሥዋዕቴን፣ ቁርባኑን ዕጣኑን መባቻውን፣ በዓሉን፣ ጉባኤውን ሁሉ ጠልቼዋለሁ ሸክምም ሆኖብኛል ይላል። እርሱ በሚወደው መንገድ ከተጓዝን ግን የጥበብ ሰዎችንም ዕጣን እንደተቀበለ የአሮንንም እንደወደደ የእኛንም ወድዶ ይቀበልናል። የሚጸየፈው መስዋዕቱን ወይም ዕጣኑን ሳይሆን ክፉ ሥራችንን ነውና። ከዚህ ነው ልበ አምላክ ዳዊት እንዲህ ያለው፡-

"ተወከፈኒ ጸሎትየ ከመ ዕጣን በቅድሜከ"

"ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ"

መዝ. ፻፵፥፪ (140፥2)

## የዕጣን ምሳሌነት

፩. ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዕጣን ምዑዝ ነው ጌታችን መድኃኒታችንም ምዑዘ ባሕርይ ነውና። ዕጣን በሚታጠንበት ጊዜ ኃጢአታችን እንደሚወገድ ጌታችን በመስቀል ላይ ራሱ ካህን ሠዊ ራሱ መሥዋዕት ሆኖ ኃጢአታችን ተሠርዮልናል። ኤፌ. ፭፥፪ (5፥2) ይጸፋል። "ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ከእግዚአብሔርም

የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ"

ከዚያም "አንተ ውእቱ ዕጣን ኦ መድኃኒነ እስመ መጻእከ ወአድኃንከነ ተሠሃከነ" ዕጣን የተስፋ ምሳሌ ነው። ዕጣኑ ከሩቅ እንዲሸት ተስፋችን ኢየሱስ ክርስቶስን በተስፋ የመንግሥቱ ወራሽ እንዲያደርገን እንጠብቃለንና።

__፪. ከእመቤታችን፡-__ ዕጣን መልካም መዓዛ እንዳለው ሁሉ እመቤታችንም መልካም የቅድስና መዓዛ ያላት መልካም መዓዛ ያለው ክርስቶስን የወለደች ናትና። ንጉሥ ሰሎሞንና አባ ጊዮርጊስ እንዳመሰገኗት። አባ ጊዮርጊስ መዓዛ የተባለ ቅዳሴ ደርሶላታል ሰሎሞንም እንዲህ ብሏል።

> "ወደ ከርቤው ተራራ ወደ ዕጣኑም ኮረብታ እሄዳለሁ። ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም" መኃ. ፬፥፮ (4፥6)

በሥርዓተ ቅዳሴያችን በተመረጠ ዕጣን የተመሰሉ የሚመሰገንበት የዕጣን ጊዜ በተባለው ክፍለ ዘመትር እንዲህ በሚል ቃል እንቀድሳለን፡-

"ዕጣን ይእቲ ማርያም ዕጣን ውእቱ እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትሜዐዝ እምኵሉ ዕጣን ዘወለደቶ መጽአ ወአድኃነነ"

ትርጉም "ማርያም ዕጣን ናት። ዕጣን እርሱ ነው። በማኅፀኗም ያደረው ከተመረጠ ዕጣን ሁሉ የሚሸት ነውና የወለደችው መጥቶ አዳነን"

__፫. የቅዱሳን ምሳሌ ነው፡-__ ዕጣን በእሳት ከእግዚአብሔር መሥዋዕት እንደሚሆነው ቅዱሳንም በብዙ መከራና ሥቃይ ራሳቸውን ከእግዚአብሔር አቅርበዋል። በዚህም ተጋድሏቸው ከክርስቲያኖች በረከትና የሕይወት መዓዛ ሆነዋል። በዕጣኑ ኃጢአት እንደሚሠረይ በቅዱሳንም ምልጃ የሰው ልጆች የኃጢአትን ሥርየት ያገኛሉ፡ እናገኛለን።

"በሚድኑትና በሚጠፉት ዘንድ ከእግዚአብሔር

የክርስቶስ መዓዛ ነንና ከእነዚሀ ከሞት የሚሆን የሞት ሽታ ከእነዚያም ከሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን።" ፪ቆሮ ፪፥፲፭ (2፥15)።

## የቅዳሴ አምስቱ ቀቀር ዕጣን ምሳሌነት

በቅዳሴ ጊዜ ካሁኑ አምስት ቀቀር ዕጣን ከብቻ መርጦ ያደርጋል። እነዚሀም "ንስግድ" በሚል ጊዜ ሦስቱን በወንጌል ጊዜ አንዱን "ተዘከረነ" ሲባል አንዱን በጥናው ጨምሮ ያጥናል። ሌላም ንጹሕ ዕጣን ጨምሮ ያጥናል። ምሳሌነታቸውም፦ አምስቱ ቀቀር ዕጣን የአምስቱ ኪዳናት እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ የሰጠው ነው።

እነዚሀ አምስቱ ኪዳናት የሚባሉት፦

፩. ቁርባነ አቤል

፪. መሥዋዕተ ኖኅ

፫. የኂሩተ አብርሃምና የመባአ ይስሐቅ

፬. የተልእኮተ ሙሴ ወአሮን

፭. የክህነተ መልከጼዴቅ ናቸው።ሌላው በብዛት የሚጨመረው ዕጣን የአልፍ አእላፋት መላእክት ምሳሌ ነው።

## የዘጠኙ ዕፀው ዕጣን ስም

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የዕፀው ዕጣን ዓይነቶች በየስማቸው ተለይተው ይታወቃሉ። እነዚሀም፦

፩፥ ሚዓ

፪፥ ዶሪራ

፫፥ ሁድ

፬፥ ስሒክ

፭፥ መስተከ

፮፥ ስኂን

፯፥ ሰንድሮስ

፰፥ አበሜ

፱፥ ቀናንሞ

ከላይ እንደገለጽኩላችሁ በቤተክርስቲያናችን "ጸሎተ ዕጣን" የሚባል መጽሐፍ አለን። ይህም መጽሐፍ በየዕለቱ ሳይቋረጥ ተጸልዮ ነው ማዕጠንት የሚደረገው። ሙሉ ጸሎቱ በየዕለቱ ከቅዳሴ በፊት ይጸለያል። እንዲሁም በቅዳሴው መሐል በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ከውስጡ የሚደገም (የሚጸለይ) አለ። ይህም ከአምስቱ ቆቀርና በሙዳዩ ባለው ዕጣን ላይ ነው። ይህም ከቡራኬ ጋር ነው። ካህኑም ከአምስቱ ሦስቱ ዕጣኖች ወደ ጽናው ሲሆን ገባ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት በግእዝ እየደገመ ነው። "በጊደር አምላክ ዕጣኑን አቀርብልሃለሁ ከርቤና ቀንዓት ሰሊሆትም ከልብሶችህ ይገኛሉ። ጸሎቴን እንደ ዕጣን በፊትህ ተቀበል። ዳግመኛም ይህን (በዚህ ጊዜ ወደ ዕጣኑ ያመለክታል) ንጹሑን ዕጣን አቀርብልሃለሁ የኃጢአቴና የበደሌ የሕዝቡም ኃጢአት ማስተሥረያ ኪሆን። አብ ወልድ መንፈስቅዱስ የቅዱስ ስምህ ምስጋና ቡሩክ፤ ምኩዕ ነውና ዛሬም ዘወትርም ከዘላለሙ አሜን። "

## ከጣዖት የሚያጥን ይጠፋል

በመጽሐፍ ቅዱስ በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት እንደተመለከትነው ዕጣን ማጠን ከእግዚአብሔር የአምልኮት መግለጫ ነው። ዕጣንና ሽታውን በተለያየ መልክ ከመጠቀም ውጪ በአምልኮት መልክ ግን ከእግዚአብሔር ከታቦቱና ከመቅደሱ ከሥዕላቱ ካልሆነ በስተቀር ከሌሎች አማልክት ከተባሉና ከጣዖታት የሚደረገውን እግዚአብሔር አምላክ ይጸየፋል። እንዲህ የሚያደርጉም ካልተመለሱ ንስሐ ካልገቡ ፍፃሜያቸው አስፈሪ ነው።

> "ይህ ሕዝብ ዘወትር የሚያስቆጡኝ ናቸው እነርሱ በአትክልት ውስጥ የሚሠዉ፥- በጡብም ላይ የሚያጥኑ በመቃብርም መካከል የሚቀመጡ

በስውርም ስፍራ የሚያድሩ የእርያ ሥጋም የሚበሉ ናቸው" ኢሳ. ፷፭፥፫ (65፥3)

ኢሳይያስ በትንቢቱ እንደገለጸው ዛሬም ከጣዖታት የሚሠዉ በአትክልት ውስጥ አድባር አያሉ፡- የሚሰዉ በጡብም የሚያጥኑ፣ በመቃብር መካከል መናፍስት አንጠራለን አናናግራለን የሚሉ፣ በስውር ስፍራ ባለው ከሰው እየተደበቁ በማይገባ ስፍራ የሚያድሩ፣ እግዚአብሔር ንጹሕ አይደለም አትብሉ ያለውን ሕግ የሚሽሩ ዘወትር አምላካቸውን እንዳስቀየሙ ይኖራሉ። ስለዚህም ነገር ነበር፡የንጉሥ ኢዮርብዓም ትውልድ ሁሉ በኢዮአስ በእሳት የነደደው። ይህ የሚያሳየው ሰዎች ከጣዖት ከመሠዋትና ከማጠን ተመልሰው ንስሐ ካልገቡ ዘራቸውን ሁሉ ከሲኦል እንደሚዳርጉ ነውና።

አስረኛ ፲ነገ ፲፫ (13) ያንብቡ

"በእጃቸው ሥራ ሁሉ ኪያስቆጡኝ ትተውኛልና ከሌሎችም አማልክት ዐጥነዋልና ቁጣዬ በዚህ ስፍራ ላይ ይነድዳል" ፪ ዜና ፴፬፥፳፭ (34፥25)

# ሕመት

እንደ ጠበል ሁሉ ሕመት ለሕሙማን ፈውስ የሆነ በእምነት ቢደባበሱት ወይም ቢቀቡት ደዌን የሚያርቅ ነው። ሕመትን በተለምዶ ክርስቲያኖች እምነት እያሉ የሚጠሩ አሉ። በቅዳሴና በጸሎት ሰዓት በቤተመቅደሱ ከተደረገው ማዕጠንት በጽናው የሚቀረውን ቅሪት ያንን ነው የሚያምን ሰው ከጸበል ጋር ደባልቆ አንዳንደም እንዲሁ ተቀብቶ፣ ተዳብሶ የሚፈወስበት። የዚህም ምንጩ የእምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር ነው። እነዚህን ቀጥሎ ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃሎች ስንመለከት የበለጠ እንረዳዋለን።

> "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ። ይህንንም ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው።" ዮሐ. ፱፥፭ (9፥5)

በዚህ የጌታችን ተአምር መሠረት ዛሬ ክርስቲያኖች ሕመትን ከጠበል ጋር ደባልቀው የሚደባብሱት የሚፈወሱበትም።

የእግዚአብሔር ቃል ለሙሴ እንደተነገረ አጠቃላይ የመቅደሱን ሥርዓት እንደነገረው የተቀደሰውን ሁሉ የሚነካ ቅዱስ ይሆናል። ዘጸ ፴፥፳፱ (30፥29)

# ቅዱስ አፈር

ቅዱስ አፈር ከሕመት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ምእመናን ወደ አንድ የተቀደሰ ሥፍራ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን፣ ወይንም ወደ ገዳም ሲሄዱ ይዘው የሚመጡት ነው። ይህንንም የሚያደርጉት የቦታውን ቅድስና በመረዳት ነው። በዚህም የተቀደሰ አፈር ብዙ ድንቅ ተአምራት በአምላካችን በእግዚአብሔርና በባለሟሎቹ በቅዱሳን ተደርጓል። ይደረጋልም። አንዳንድ ጊዜ የዚህ ምሥጢር ያልገባቸው ሰዎች ይህን ሲመለከቱ እንደ ሞኝነት ሊያዩት ይችሉ ይሆናል። ዳሩ ግን ምሥጢሩ ረቂቅ ነው። ከእምነትም የሚመነጭ ነው። መሠረቱም ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ከለምጽ ንዳድ በዮርዳኖስ ጠበል የተፈወሰው የሶሪያው የጦር ጀግና ንዕማን ከዳነ በኋላ ከእግዚብሐር ውጪ ሌላ አምላክ፣ አዳኝ እንደሌለ ተረድቷል፤ አምኗልም። እንዲህም ብሎ መስክሯል "እነሆ ከእስራኤል ዘንድ በምድር ሁሉ አምላክ እንደሌለ አወቅሁ።" ይህ ንዕማን ቀድሞ በእግዚአብሔር የማያምን አሕዛብ ነበር። የሚያመልከውም በወርቅና በብር የተሠራ ጣዖትን ነበር። የሚጸልየውና መሥዋዕት የሚያቀርበው "ሬሞን" ለተባለ ከንቱ ጣዖት ነበር። በእግዚአብሔር ሰው በነቢዩ ኤልሳዕ አማካኝነት ከተፈወሰ በኋላ እግዚአብሔርን አመለከ ኤልሳዕም ቅዱስ መሆኑን ተረዳ። ስለዚህም ኤልሳዕ የረገጠውን አፈር ለምኖ በበቅሎ ጭኖ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ፪ነገ ፭፥፲፭-፲፱ (5፥15-19)

ዛሬም እግዚአብሔር አምላክን ያመኑ በቅዱሳን ተራዳኢነትና አማላጅነት የሚታመኑ ምእመናንና ምእመናት ከእምነታቸው ጽናት የተነሣ በእምነት በተቀደሰው አፈር ፍጹም ፈውስን የሚያገኙት። እዚህ ላይ የምንመለከተው ሌላው ክርስቲያኖች ወደ ገዳም ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ደርሰው በረከት አግኝተው የሚመለሱበት የንፍሮ ውኃ ወይም የዳቤ በረከት ነው።

# ዳቤ፣ ንፍሮና የንፍሮ ውኃ

ዳቤ በገዳም የሚገኝ ኅብስት ወይም እንጀራ ማለት ነው። ይህንን ዳቤ በመቅመስ፣ እንዲሁም የተጸለየበትን ንፍሮ በመቅመስ ውኃውንም በመጠጣት ከሕመማቸው የሚፈወሱ በርካቶች ናቸው። ይህም ምሳሌነቱ ከወንጌል የተገኘ ነው። በወንጌል ተጽፎ እንደምናገኘው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተራቡት ምእመናን እንጀራውንና ዓሣውን ባርኮ በሰጣቸው ሰዓት ጥቂቱ ብዙ ሆኖ ተመግበው ብዙ ተርፎ ተነሣ።

> "... ባረከ እንጀራውንም ቆርሶ ከደቀመዛሙርቱ ሰጠ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ፣ ሁሉም በልተው ጠገቡ የተረፈውንም ቁርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ"
>
> ማቴ. ፲፬፥፲፫-፳፩ (14፥13-21)፣ ማቴ. ፲፭፥፴፮-፴፱ (15፥36-39) ማር. ፮፥፵፫ (6፥43) ሉቃ ፱፥፲፯ (9፥17)፣

ይህ በጌታችን የተባረከው እንጀራ ተርፎ እንዴ አሥራ ሁለት መሶብ ወይም ቅርጫት በሌላ ጊዜ ደግሞ የተረፈው ሰባት መሶብ ዝም ብሎ አልተጣለም፡ በማርያም መግደላዊት ቤት ተቀምጦ በዘመነ ደዌ ከፈውስ በዘመነ ቀጠና (ረሀብ) ከበረከት ይወስዱት ነበረ። ይህም ድውያን የሚፈወሱበት እንደሆነ ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች። እውነትም ያንን የተባረከ እንጀራ እየቀመሱ ድውያን የሚድኑ ሆነውበታል። ይህንኑ ነው ዛሬም በማመን የምናደርገው። ከምጻምን የሚያነጻ ጎባጣን የሚያቀና ዕውርን የሚያበራ ሕሙማንን የሚፈውስ ሙታንን የሚያነሣ ነው። የሥጋን ሕመም ብቻ ሳይሆን የነፍስንም ቁስል የሚፈውስ ነው። አምላካችን በኤማሁስ መንደር ከሁለቱ ደቀመዛሙርት እንጀራውን ባርኮ ቢሰጣቸው ዐይናቸው ተከፈተ። ይህም የሥጋቸው ዐይን ሳይሆን የነፍሳቸው፡ የልቡናቸው ዐይን ነበር። ሉቃ ፳፬፥፴-፴፩ (24፥30-31)

የዚህ የበረከት ዳቤ (እንጀራ) ንፍሮው የንፍሮው ውኃ ሁሉ የሥጋን ብቻ ሳይሆን የነፍስም መዳኛ ነው። ዋናው ግን ዘላለማዊ ሕይወት ለመውረስ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን መቀበል ለክርስቲያኖች ግደታ ነው።

# መሥዋዕት፣ አሥራት፣ በኵራትና ቀዳምያት

## መሥዋዕት

ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ስጦታ ነው። ይህም የሚደረግበት ምክንያት ከኀሰሐ፣ ከምስጋና፣ ከፍቅር እንዲሁም ከእግዚአብሔር መልስ ከማግኘት ነው። ከእግዚአብሐር የሚቀርብ መሥዋዕት ከእንስሳት አዕዋፍ ከእህልና ከመጠጥ ይሆናል። እግዚአብሐር በባሕርዩ ንጹሕ ነውና የሚቀርብለትም መሥዋዕት ንጹሕና እንከን የሌለበት ይሆን ዘንድ የተገባ ነው። በዚህም ምክንያት ነበር የአቤልን ንጹሕ መሥዋዕት ሲቀበል የቃየልን የተጸየፈው።

> "እግዚአብሐርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ ወደ ቃየንና ወደ መስዋዕቱ ግን አልተመለከተም።" ዘፍ. ፬፥ ፬ (4፥4)

በዘመነ ብሉይ የሚቀርቡ አምስት ዓይነት ዋና ዋና መሥዋዕቶች ነበሩ

የሚቃጠል መሥዋዕት

የእህል ቁርባን

የደኅንነት መሥዋዕት

የኃጢአት ሥርየት መሥዋዕትና

የበደል መሥዋዕት ናቸው።

እነዚህ የተለያዩ የመሥዋዕት ዓይነቶች በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪትም ሰዎች ከአምላካቸው አቅርበዋል በሕገ ወንጌልም በዘመነ ክርስትና በእማናዊነት ይቀርባሉ። በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት የነበረው ምሳሌያዊ ሲሆን በሕገ ወንጌል ከሚሆነው መሥዋዕታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌና መርገፍ ነው። ከምሳሌ ሕዝበ እስራኤልን በባርነት በግብፅ በነበሩበት

ዘመን በሥረኛው መቅሰፍት "›ሞተ በኩር" ሲታዘዝ ይህ የታካካቅ ልጆች ሞት ወደ እስራኤላውያን ቤት አልገባም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ባዘዛቸው መሠረት ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ጠቦት ሠውተው ቤቶቻቸውን በደሙ ቀብተው ነበር። ይህም የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው። እግዚአብሔርም እንዳለ ከሰው እስከ እንስሳ የግብፅን በኩር ሁሉ ሲገድል ደሙ ባለበት ቤት ግን መቅሠፍቱ ከጥፋት አልመጣም። ዘጸ. ፲፪፥፩-፲፬ (12፥1-14)

ይህ የእስራኤል በግብፅ የባርነት ታሪክና የመሥዋዕቱ ምሥጢር በዘመነ ሐዲስ ስለሚደረግልን የመዳናችን መሥዋዕት ምሳሌ ነው። የእስራኤል በግብፅ መኖር የሰው ልጆች ሁሉ በጨለማ ኃጢአት ሲኦል የመውደቃቸውና ፈርኦን እስራኤልን እንዳስጨነቀ እኛም በዲያብሎስ አገዛዝ ከመያዛችን ነውር የሌለበት ጠቦት ምሳሌም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑና በእርሱም መሥዋዕትነት ተፈውሰን ግብፅ ከተባለች ሲኦል ወጥተን ከነዓን ወደተባች ርስታችን ገነት የመመለሳችን ምስጢር ነው። ይህ ሁሉ የሆነው በጌታችን ደም ነው።

> "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚብሔር በግ" ዮሐ. ፩፥፳፱ (1፥29)

በሐዲስ ኪዳን በሕገ ወንጌል የሚቀርበው የሰዎች መዳኛ የአምካካችን ሥጋውና ደሙ ነው እንጂ እንደ ቅድመ ክርስትና ዛሬ በመቅደሱ የቀደመው ምሳሌያዊ መሥዋዕት አይቀርብም።

> "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና"፩ ቆሮ.፭፥፯ (5፥7)

ክብር ምስጋና ይግባውና አምካካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሁሉ ከሚዳን በቀራንዮ ተራራ በእንጨት መስቀል ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ራሱም ሠዊ (ካህን) ሆነ ስለእኛ ሞትን ቀመሰ። ያ በዘመነ ብሉይ የነበረ

መሥዋዕት በግ የሰዎችን ኃጢአት እንደሚሸከም (ዘሌ. 16፥21) ጌታችንም የእኛን በደልና ኃጢአት ተሸከመ (ኢሳ. 53፥6) በእርሱም ግርፋትና ቁስል ተፈወስን። ሞትንም ድል አደረገልን።

> "ከኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" ፩ ጴጥ. ፪፥፳፬ (2፥24)

## አሥራት

አሥራት የሚለው ቃል ዐሠረ ዓሥር አደረገ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ፍችውም ከ10(አሥር) አንድ ማለት ሲሆን ይህንንም ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው። አሥራት ሰው ጥሮ ግሮ ሠርቶ ከሚያገኘው ከላቡ ገቢ ለእግዚአብሔር ከአሥር አንድ እጁን ወይንም ከመቶ አሥር ክፍሉን ለእግዚአብሔር መስጠት ነው። አሥራት በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪትም ይሰጥ ነበር። ለምሳሌ በሕገ ልቡና አብርሃም አባታችን ለካህኑ ለመልከጼዴቅ አሥራትን እንደከፈለ በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጿል።

"አብርሃምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው" ዘፍ. ፲፬፥፳ (14፥20) አባታችን ያዕቆብም ቤቴል ብሎ በሰየማት በሎዛ ምድር እግዚአብሔር ቢገለጥለት በሥፍራው የእግዚአብሔር ቤት እንደሚታነጽና እሱም አሥራትን ለእምላኩ እንደሚሰጥ ቃል ኪዳን አደረገ።

> "ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ። " ዘፍ. ፳፰፥፳፪ (28፥22) እግዚአብሔር አምላካችን ሙሴን በሲና ተራራ ካዘዘው ትእዛዝ አንዱ አሥራትን ስለመክፈል ነው። ይህም በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፳፯፥፴-፴፫ (27፥30-33) ተጽፎ ያለው ነው።

ስለዚህ አሥራትን ማውጣት የአምላክን ሕግ መጠበቅና

መፈጸም ነው። ሰው እግዚአብሔር ከሰጠው አሥራትን ካልከፈለ እግዚአብሔር ሰርቃችሁኛል ይላል።

> "እናንተም፡- የሰረቅንህ በምድር ነው ብላችኋል። በአሥራትና በበኩራት ነው።" ሚል. ፫፥፯-፲፪ (3፥7-12) አሥራት የሚከፈለው ከካህናት መገልገያ በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር መንግሥት ማስፋፊያ ነው። ካህናት ሙሉ በሙሉ ጊዜያቸውን ሁሉ አምላካቸውን እንዲያገለግሉ ሕዝቡንም እንዲጠብቁ ነው።

> "ለሌዊም ልጆች እነሆ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ስለሚያገለግሉ የእስራኤልን ልጆች አሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቼሃለሁ።" ዘኍ. ፲፰፥፳፩ (18፥21)

ይህ ቃል በግእዙና በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ልዩነት አለው "ለደቂቀ ሌዊኒ ናሁ ወሀብኩዎሙ ዐሥራተ ዘደቂቀ እስራኤል ክፍሎሙ ሀየንተ ግብሮሙ ኩሎ ዘይገብሩ እሙንቱ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል"

"ለሌዊ ልጆችም በደብተራ ኦሪት ለሚሠሩት ሥራቸው ሁሉ የእስራኤል ልጆች የሚያመጡትን አሥራት ዕድል ፈንታ አድርጌ ሰጧቸው።" ትክክሉ ይህ ነው።

## የአሥራት አሥራት

> "ካህናትም አሥራት ከሕዝቡ ከተቀበሉ በኋላ እነሱም ከቤተመቅደሱ አገልግሎት የሚያውሉት ክፍል የአሥራት አሥራት ተብሎ ይጠራል።" ዘኍ. ፲፰፥፳፮ (18፥26) ነህ ፲፥፴፰ (10፥38)

አሥራትን አባቶቻችን በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት እንዳደረጉት ሁሉ በሕገ ወንጌል በዘመነ ክርስትናም ይፈጸማል። ክብር ይግባውና ጌታችንም እንዲህ ብሎ አዟል።

> "ሀቡ ዘቄሣር ለቄሣር ወዘ እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር"

"የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ" ማቴ. ፳፪፥፳፩ (22፥21)

በአሁን ጊዜ ግን ካህናትንም ይህን ባለ ማስተማራትን ሕዝቡም ባለመስማቱና ባለማንበቡ አሥራትን ጥቂቶቹ ሲፈጽሙት ይታያል። ይህ ግን በሚገባ ከታወቀ አሥራትንና ሙዳየ ምፅዋትን መለየት እንችላለን። ቤተክርስቲያናችንም ትግሬዋችን ለመርዳት ትችላለች። እንዲያውም አሥራት ከቤተክርስቲያን አገልግሎት/ለካህናት ሲሆን ሙዳየ ምፅዋት ደግሞ ለተመጽዋቾች ይውላል።

"በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሐር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።" ፪ቆሮ. ፱፥፮ (9፥6)

"ከእርሻህ በየዓመቱ ከምታገኘው ከዘርህ ፍሬ ሁሉ ዐስራት ታወጣለህ" ዘዳ. ፲፬፥፳፪ (14፥22)

## በኵራት

በኩራት የሚለው ቃል በኩር ከሚለው ብዙ ቁጥር ነው። በኩር ሲባል የመጀመሪያ ማለት ነው። በኩራት ማለት ደግሞ የመጀመሪያዎች ማለት ነው። ይህም ቃል የተሰጠው ከሰውም ሆነ ከእንስሳት የእናታቸውን ማኅፀን በመጀመሪያ ከፍተው ለሚወጡ ነው። እነዚህም በኩራት እንደ ሕግ መሠረት ከእግዚብሔር ይሰጣሉ።

"እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማኅፀንን የሚከፍት በኩር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ የእኔ ነው።" ዘጸ. ፲፫፥፩ (13፥1)

የሰው በኩር እግዚአብሔርን በመቅደስ ያገለግላል ከእንስሳት ወገንም የሆነው ለመቅደሱ አገልግሎት ለመሥዋዕትና ለካህናት ይሆናል። ከላይ እንደ ተመለከትነው

እንደ መሥዋዕትና አሥራት ሁሉ የእንስሳት በኵራት ለካህናት ይሰጡና ካህናቱም ለእግዚአብሔር የሚገባውን ንጹሕ እየመረጡ ይሠዉታል።

"ከሰው ወይም ከእንስሳ ቢሆን ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡት ሥጋ ሁሉ ማኅፀን የሚከፍት ሁሉ ለአንተ ይሆናል።" ዘኁ.፲፰፥፲፭ (18፥15)

ካህናቱም እግዚአብሔር ባዘዘው ሕግ መሠረት ይፈጽማሉ። ሕዝቡም የሚገባውን ሁሉ የበኵራት ሥርዓት ወደካህኑ ያመጡ ነበር። እግዚአብሔርም ይባርካቸው ይቀድሳቸውና ከጠላት ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ ይህን ትእዛዙን በመሐላ አጽንተው ይጠብቁት ነበር።

"በሕጉም እንደተጻፈ የልጆቻችንንና የእንስሶቻችንን በኵራት የበሬዎቻችንና የበጎቻችንን በኵራት በአምላካችን ቤት ወደሚያገለግሉት ካህናት ወደ አምላካችን ቤት እናመጣ ዘንድ ...ማልን" ነሀ. ፲፥፴፮ (10፥36)

ይህ በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት የነበረ የእግዚአብሔር ሕግ እንደየመልኩ ለዘላለም ይሠራበታል። እርግጥ ነው ዛሬ በቤተመቅደስ የእንስሳት በኵራት የሚሠዋበት ዘመን አይደለም። ክብር ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ስለሁላችን ቤዛ አንድ ጊዜ ለዘላለም ተሠውቷልና። እርሱም ስለሁላችን በኵር ነው። በእምነት አናታችንና አማላጃችን ከሆነችው እመቤታችን ድንግል ማርያም የበኵር ልጅ ነውና።

"የበኵር ልጇን ወለደች" ሉቃ. ፪፥፯ (2፥7)

እርሱ ጌታችን ከባሕርይ አባቱ ከአብም የበኵር ልጅ ነው። አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ይልና መላእክት ሁሉ የሚሰግዱለትን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ያዳነንን በኵር ብሎ ይጠራዋል። መዝ. ፪፥፯ (2፥7) ዕብ. ፩፥፭-፮ (1፥5-6) የሁላችን በኵር ጌታችን ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሞትን ድል ነስቶ በትንሣኤው

ገልጸታልና የትንሣኤያችን በኵር ተብሎ ይጠራል። "ቀዳሚ ክርስቶ ውእቱ ዘተንሥአ እሙታን" "መጀመሪያ ትንሣኤ የተነሣ ክርስቶስ ነው" ፩ቆሮ፲፭፡፳፫ (15፡23)

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው አንደኛ መሥዋዕት፣ ሁለተኛ አሥራት፣ ሦስተኛ በኵራትና፣ አራተኛ ቀዳምያት እንደየ ዘመኑና እንደ ሕጉ በሦስቱም ሕግጋት ይቀርባሉ። ምእመናንም ይህንን ስለሚያውቁ መባዓቸውን ይዘው ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ዘወትር ይገሰግሳሉ። ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ በጸሎት እንዲታሰቡ ቅዱሳን ሐዋርያት ሁል ጊዜ በቅዳሴው የሚጸለየውን ጸሎት ሠርተው አዘዙ።

> "... ንስእለከ ወናስተበቍዐከ በእንተ እለ ያበውኡ መባዓ... መሥዋዕተ ቀዳምያተ ዐሥራተ አኰቴተ..."

ይህም ጸሎት ሁሉን ከሚያዝና ከሚገዛ እምላካችን እግዚአብሔር ከሁሉም መባዕ ከሚሰጡ የበረከት ዋጋ እንዲሰጣቸው ይለመናል።

## ቀዳሚት

ቀዳሚት የሚለው ቃል በኵር ከሚለው ወይም የመጀመሪያ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ቀዳምያት ከሰውና ከእንስሳት ከይቶ ከእህል የምንጠቀምበት ሲሆን ይህም ገበሬው ከዘራውና ካመረተው እህል የመጀመሪያውን ከእግዚአብሔር ያመጣል። ይህ በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪት የነበረ ሕግ ሲሆን በሐዲስ ኪዳንም ይደረጋል። ከዚህ ነው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን "የመገበሪያ ስንዴ" ተሸክመው ወደ መቅደሱ የሚያመጡት። ከሁሉም የእህል ዘርና ከሌላውም የእጃቸው ፍሬ ከእግዚአብሔር የሚያቀርቡት። እምላክም ይቀበላቸዋል።

> "ወኵሉ ዐሥራታ ከምድር ዘእምዘርአ ምድር ወእመኒ ዘእምፍሬ ዕፀ ዘእግዚአብሔር ቅዱስ ውእቱ ከእግዚአብሔር"
>
> "ከምድር አዝመራ የተገኘ የምድር አሥራት ሁሉ እግዚአብሔር ካበቀለው ከእንጨት ፍሬም ቢሆን

የተገኘው ከእግዚአብሔር የተለየ ነው" ዘሌ፡፳፯፡፴ (27፡30)

በዚህ ቅዱስ ቃል መሠረት የቀዳሚት ሕግ አንደኛ ከምድር ከዘር ሁሉ ሁለተኛ ከዛፍ ፍሬ ሁሉ የመጀመሪያው ከአምካካችን ከእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው።

# ዜማ ቤተክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከመላው ዓለም በተለየ መልኩ እግዚአብሔርን የምታመሰግንበት ከራሱ ከእግዚአብሔር የተሰጣት ልዩ ዜማ አላት። ይህም ዜማ ካህናተ ሰማይ ሃያ አራቱ ሊቃናት በሰማይ ከሥላሴ ምስጋና የሚያቀርቡበት ነው። እነዚህ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ያለ ማቋረጥና ያለ እረፍት እግዚአብሔር አምላክን በማደሪያው በጽርሐ አርያም ያመሰግኑታል።

## <u>ቁጥራቸው ሃያ አራት (24) መሆኑ።</u>

አንደኛ ያለ እረፍት ሃያ አራቱን ሰዓት ቀንና ሌሊት ስለሚያመሰግኑ ነው።

> "ወአልቦሙ ዕረፍት መዐልተ ወሌሊተ እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ አማልክት ዘሀሎ ወይሄሉ"
>
> "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌትነት ያለው አምላክ" እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም። ራዕ ፬፥፰-፲፩ (4.8-11)

ሁለተኛ ሃያ አራት ሰዓት በፊቱ እየሰገዱ የሚጸልዩትና የሚያመሰግኑት መሐሪ አምላክ የሰው ልጆች በየሰዓቱ የሠሩትን ኃጢአት ይቅር ይላቸው ዘንድ ከመለመን ከማማለድ ነው።

እንግዲህ ይህንን የሰማያት ምስጋናና ዜማ ነው። ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የምንሰማው። ይህንም ዜማ ለእኛ የደረሰልን እግዚአብሔር አምላክ በመረጠው ቅዱስ በካህኑ በቅዱስ ያሬድ አማካኝነት ነው።

ቅዱስ ያሬድ ኅዳር ፭ ቀን ፩፻፴፬ (ኅዳር 5 ቀን በ534) ዓመተ ምሕረት አሮጽዮን የሚባሉ ሦስት ነጫጭ ወፎች ከሰማይ ከገነት ኤደም ተልከውለት እኒህም መላእክት ናቸው። ብሥራት ነግረውት ወደ ሰማይ ይዘውት እንደወጡ የቤተክርስቲያናችን ታሪክ፣ ገድሉ እና በተለያዩ አበው የተጻፉ የቤተክርስቲያናችን መጻሕፍት ይመሰክሩልናል። ቅዱስ ያሬድ በፊት የነበረው የዜማ ዓይነት

እንደንባብ ድጋም ያከ ማሕዘኒ የሚባል ነው። ዛሬም በቤተክርስቲያናችን ያለውን የንባብ ስልት የራሱ የሆነ ዜማ አለው።

በስማይም የሃያ አራቱን ካህናተ ሰማይ ዝማሬ መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት እስከ ዛሬ ከዘከዓከምም የቤተክርስቲያናችን ሀብትና አምላክን ማመስገኛ ሆኖ ይኖራል።

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን የምንገለገልበት ዜማ ምንጩ እግዚአብሔር ሆኖ በመረጠው በቅዱስ ካህን በያሬድ አማካኝነት ለእኛ የተሰጠና የተደረሰ ነው። ስለዚህም በቤተክርስቲያናችን የምናመሰግንበት የዜማ ስልት ከቅዱስ ያሬድ ሦስቱ የዜማ ስልቶች አይወጣም። እነዚህም፡-

1. ግዕዝ

2. ዕዝል

3. አራራይ ናቸው።

እነዚህ ሦስቱ የቤተክርስቲያናችን ዜማዎች እያንዳንዳቸው ትርጉምና ምሳሌነትም አላቸው። ትርጉማቸው፡-

<u>ሀ. ግዕዝ</u>፡- ማለት ተቀዳሚ የመጀመሪያ ዜማ ማለት ነው። በራሱ ግዕዝ ማለት የመጀመሪያ ማለት ነውና።

<u>ለ. ዕዝል</u>፡- ማለት በበዓልና በደስታ ቀን የሚዜም በግዕዝ ላይ ታዝሎ የሚዜም ማለት ነው። ለምሳሌ በጾም ጊዜ በአብዛኛው ግዕዝ ይቀደሳል በዓለ ንግሥ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ቅዳሴው ዕዝል ይሆናል። በቅዳሴ ጊዜ ወደ ዕዝል የሚገባው ወንጌል ከተነበበ በኋላ መሆኑንም አስተውሉ።

<u>ሐ. አራራይ</u>፡- ማለት ልቡናን የሚያራራና የሚመስጥ ዜማ ማለት ነው።

ምሳሌነታቸው፡- ቅዱስ ያሬድ ከሰማይ መላእክት ባገኘው መሠረት እነዚህን ሦስት የዜማ ዐይነቶች በሚያዜምበት ሰዓትና ለእኛም ሲያስተላልፍ ምሳሌነቱን በመገለጽ ነው። ምሳሌነታቸውም እንዲህ ነው።

ግዕዝ - የአብ

ዕዝል - የወልድ

አራራይ - የመንፈስ ቅዱስ

ስለዚህ ከዚህ እንደምንረዳው ይህ የእግዚአብሔርን የአንድነቱንና የሦስትነቱን ምሥጢር ያዘለ ነው።

ሦስትነቱ፡- ከላይ እንዳየነው ሦስቱ የዜማ ስልቶች ግዕዝ፣ ዕዝልና አራራይ የአብ፣ የወልድና መንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ናቸው። በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ይሆናሉ።

አንድነቱ፡- ሦስቱም አንድ ዜማ በመሆናቸው ነው ይህም በመለኮት፣ በአዘዝ በአገዛዝ አንድ መሆኑን ከመግለጽ ነው።

# ፯ቱ (7) አጽዋማት

ቅድስት ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአዋጅ የወሰነቻቸው አጽዋማት በቁጥር ሰባት ናቸው። እነዚህም፡-

ዐቢይ ጾም

ጾመ ነቢያት

ጾመ ድኅነት

ጾመ ነነዌ

ጾመ ገሃድ

ጾመ ሐዋርያት

ጾመ ፍልሰታ

## ዐቢይ ጾም

ይህ ጾም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ከአኖም አብነት የሆነበትን የነፍስና የሥጋ ቁስል መፈወሻ የምናስብበት ጾም ነው። ማቴ. ፬፡፩-፲፩ (4፥1-11)

ዐቢይ ጾም መባሉ

ሀ. የፍጥረት ባለቤት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው በመሆኑ

ለ. ታላላቅ ኃጢአቶች የደቀቁበት በመሆኑ እነዚህም

ስስት

ትዕቢት

ፍቅረ ንዋይ ናቸው እነዚህ ሦስቱ አርእስተ ኃጣውዕ ይባላሉ።

በአገራችን ምእመናን የሁዳዴ ጾም ይባላል። ይህም ትልቅነቱንና በረከቱን ከመግለጽ ነው። ሁዳዴ የሚለው ሁዳድ ከሚለው ቃል

የመጣ ነው ትርጕሙም በጣም ሰፊ የእርሻ መሬት ማለት ሲሆን ከሰፊ እርሻ ብዙ ምርት ይገኛልና ከዚህም ከሁዳደ ጾም ብዙ መንፈሳዊ ፍሬ ይገኝበታል።

## ጾመ ነቢያት

የነቢያት ጾም መባሉ ነቢያት ጌታ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል እመቤታችን ተወልዶ መጥቶ ያድነናል ብለው የሚጾሙት ስለነበር ነው። ይህ ጾም የሚጾመው ከጌታችን ልደት በፊት ባሉት ቀናት ሲሆን ጊዜውም ከህዳር 15 ቀን እስከ ታህሳስ 28 ቀን ነው።

እኛ የምንጾምበት ምክንያት

ሀ. ከነቢያት ጋር ያለን አንድነት ስለሚገለጽበት

ለ. የጌታችን መወለድን እያሰብን ሁሌ በልባችን ይህ ይገባ ዘንድ

## ረቡዕና ዓርብ (ጾመ ድኅነት)

ሀ. ረቡዕ የምንጾመው፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል አይሁድ የተሰማሙበት ቀን ስለሆነ ይህችን ዕለት በጾም እናሳልፋታለን።

ለ. ዓርብ የምንጾመው፡- በዚህች ቀን የሁላችን ቤዛ መድኃኔዓለም ክርስቶስ እኛን ለማዳን በቀራንዮ ኮረብታ በመስቀል በሥጋ መሞቱም በመሞቱም መዳናችንን እያሰብን እንጾማለን። በአጠቃላይ እነዚህን ዕለታት የፈጣሪያችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መከራ በማሰብ እንጾማለን። ከነዚህ 2 ቀናት ምሥጢር በተጨማሪ ጾመ ዮዲትና ጾመ አስቴርን እናሳባን።

## ጾመ ነነዌ

የነነዌ ጾም መባሉ፡- ነነዌ በምትባል አገር የነበሩ ሰዎች ስለጾሙት ነው። ታሪኩ በትንቢተ ዮናስ የተጻፈ ነው። ሕዝቡ ኃጢአት አብዝተው እግዚአብሔር በቁጣው ሊቀጣቸው

በቀረበ ጊዜ ነቢዩ ዮናስን ልኮ ቢነግራቸው ለሦስት ቀን ከእህል ከውኃ ተከልክለው ቢጾሙ ቢዘንብባቸው ከነበረው እሳትና ዲን ድነዋል። ት.ዮናስ ፫፥፭-፮ (3፥5-6)

የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ ለጾም አዋጅ ነገሩ ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ማቅ ለበሱ ቁጥር ፳፱ (29) ... እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተፀፀቶ አላደረገውም።

የነነዌን ከተማ በኃጢአት ምክንያት ሊያጠፋ የነበረ እግዚአብሔር በመጾማቸው በምሕረት ተመልሶላቸዋል። ስለዚህ እኛም ይህን ጾም ስንጾም ከምናውቀውም ከማናውቀውም መከራ እንሠወራለን። እንድናለን። ስለዚህም እንጾማለን። ይህም ጾም እንደ ሁኔታው በጥርና በየካቲት ሲውል ሁል ጊዜ ሰኞ ይጀመርና እስከ ረቡዕ ይጾማል ሐሙስ ይፈታል፡ ለሦስት ቀን ብቻ ይጾማል።

## ጾመ ገሃድ

ገሃድ ማለተ ቃሉ የግእዝ ሲሆን ትርጉሙ ተለዋጭ ማለት ነው። ይህ ጾም የጌታችን ልደትና ጥምቀት በዕለተ ረቡዕ ወይም ዓርብ ሲውል በዋዜማው ማክሰኞና ሐሙስ ይጾምና በዕለተ ረቡዕ ወይም ዓርብ ይፈስካል።

"ገሃድ ዘውእቱ ተውላጠ ረቡዕ ወዓርብ"

"ገሃድ ይኸውም የረቡዕና የዓርብ ለዋጭ"

## ጾመ ሐዋርያት

ይህንን ጾም መጀመሪያ ሐዋርያት ስለጾሙት በስማቸው ተሰይሟል። የሰኔ ጾም እየተባለም ይጠራል። አንዳንዶቹም የቁሶች ጾም ብለው ይጠሩታል ይህም በመጀመሪያ ቁሶች ሐዋርያት ስለጾሙት እንጂ የክርስቲያን ሁሉ ጾም ነው።

# ጾመ ፍልሰታ ለማርያም

ይህ ጾም የእመቤታችን ፍልሰቷን ትንሣኤዋን ዕርገቷን የምናስብበት ነው። የሚውለውም ከነሐሴ ፩ (1) ቀን እስከ ፲፭ (15) ይሆንና በ16 ይፈስካል። ነሐሴ 16 ቀን ረቡና ዓርብ ቢውል የፍስክ ምግብ አይበላም።ይህንን ጾም በመጀመሪያ የጾሙት ሐዋርያት ናቸው። ዮሐንስና ቶማስ የእመቤታችንን ትንሣኤና ዕርገቷን አምላክ ስለገለጠላቸው መላው ሐዋርያትም ይህን ይገልጽላቸው ዘንድ ሁለቱን ሱባዔ ጾመዋል። ፍልሰቷን፣ ትንሣኤዋንና ዕርገቷን አይተዋል።

> ቅዱስ ዳዊት "አሁን ግን ጣልኸን አሳፈርኸንም ከሠራዊታችንም ጋር አትወጣም።" መዝ ፵፬፡፱ (44: 9)

በአጠቃላይ ሰባቱም አጽዋማት በረከት የምናገኝበት መላእክትን የምንመስልበት የሰይጣንን ቀንበር የምንሰብርበት ከአምላካችን የምንገናኝበት ነውና እንጾም ዘንድ ታዟል። ስንጾምም ከጥሉላት ምግቦች እንከለከላለን። እነዚህም ሥጋ ቅቤ እላ ወተት እንቁላል የመሳሰሉት ሲሆኑ በአጠቃላይ ከወንድና ከሴት ሩካቤ የሚገኙትን ነው። እግዚብሔር በቸርነቱ ሁላችንን ይጎብኘን አሜን!

# የንስሐና የፈቃድ ጾም

ከሚችል ሁሉ ዓመቱን ሁሉ ቢጾም በረከት ይወርሳል እንጂ አይጎዳም። ነገር ግን ሁሉ እንደአቅሙ ነውና የቤተክርስቲያን ሥርዓትም በመንፈስ ቅዱስ ተሰርቷልና። ሰባቱ አጽዋማት የአዋጅ ክርስቲያን ሁሉ የሚጾማቸው ሲሆን በተጨማሪ ምእመናን እንደ መንፈሳዊ ዕድገታቸው የበለጠ በረከትን ከማግኘት የሚጾሟቸው የግላቸው የንስሐና የፈቃድ አጽዋማት አሉ።

የንስሐ ጾም ካህኑ የነፍስ አባታቸው የሚያዘው ሲሆን የፈቃድ ጾም ደግሞ እንደ ዘመኑ ጽጌና ጳጉሜ ወር የሚጾመው ዓይነት ነው። ይህ የግል ወይም የፈቃድ ጾም እንጂ የግዴታ የአዋጅ አይደለም።

# ጸሎትና ሥርዓቱ

> "ጸሎትሰ ይእቲ ተናግሮተ ሰብእ ኀበ እግዚአብሔር ከሡከ እንዘ የአኩቶ ወይሴብሖ ወይትአመን በእግዚእናሁ ወበተአምኖ በአበሳሁ ወኀሚሥ አምኑሁ በዘያሠምሮ ቦቱ።"

> "ጸሎትስ ሰው ከልዑል እግዚአብሔር ጋር የሚነጋገራት ነገር ናት። ፈጽሞ እያመሰገነ ጌትነቱን አምኖ በደሉን አምኖ እርሱን ደስ የሚያሰኝበትንም ሽቶ" ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፬ በአንተ ጸሎት

በዘፍጥረት ፪፥፯ (2፡7) እንደተጻፈ እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ብሎት ሕያው ነፍስ ያለው ሆኖአል። ይችት ሕያው ነፍስ እግዚአብሔርን ስትፈልግ ትጠማለች መገናኛዋም ጸሎት ነው። ጸሎት ብዙ መንፈሳዊ ነገሮችን ይጠቀልላል። ከነሱም መካከል፡- ፈጣሪ እንዳለ ማመን፣ ከእርሱም ጋር መነጋገር፣ ይህም መገናኘት ነው። የአባትና የእናት ግንኙነት ከልጆች ጋር እንዳለ አባ ብለን እንጠራለን፣ በራሳችን መታመንን በመተው በእግዚአብሔር መደገፍ ከዚያም ምስጋናን በማስቀደም ልመና፣ ምልጃ፣ ተስፋ፣ ንስሐ፣ ይቅርታ፣ ደስታ ሁሉንም ከእምላክ በረከት ማግኘት ነው።

ክብር ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጸሎትን አስፈላጊ መሆን እንዲህ ነግሮናል።

> "ለምኑ ይሰጣችሁማል ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችሁማል።" ማቴ ፯፥፯ (7፡7)

## ስለዚህ ሦስት ዓይነት ጸሎት አለ

፩. <u>የኅብረት ጸሎት</u>፡- ይህም በቤተክርስቲያን በጋራ የሚደረግ ጸሎትና ሌሎችም በኅብረት የሚደረጉ የአገልግሎት ጸሎቶችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ፡- ማሕሌት፣ ሰዓታት፣ ቅዳሴ፣ ክርስትና፣ ፍትሐት፣ የማዕድ ጸሎት በኅብረት የሚጸለዩ ናቸው።

፯. የቤተሰብ ጸሎት፡- የክርስቲያን ቤተሰብ የጋራ ጸሎት አንድ ላይ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህም ከቤተሰቡ ለካምን የሚለጥና ልጆችም ወላጆቻቸውን አብነት በማድረግ እግዚአብሔርን መፍራት ይገበያሉ።

፰. የግል ጸሎት፡- ሁሉም ክርስቲያን በቤተክርስቲያን እንዲሁም ከቤተሰብ ከጓደኛ ጋር ከሚያደርገው ጸሎት ጋር የበለጠ በግሉ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ጸሎት ያስፈልገዋል። ይህም የግል ጸሎት ነው።

> "በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው። እንደፈቃዱ እንዳችብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን።" ፩ዮሐ ፭፡፲፬-፲፭ (5፡ 14-15)

## ጸሎት በቀን ሰባት ጊዜ

የሰው ልጅ እንደመላእክት ያለማረፍና ያለማቋረጥ የመጸለይ ብቃት ስለሚያንሰው አርግጥ እንደመላእክት የሆኑ ቅዱሳን ባይጠፉም ከምእመናን ግን በቀን ሰባት ጊዜ እንዲጸልዩ ሕግ ቤተክርስቲያን አለ። እነዚህም በሰዓት የተወሰኑ ናቸው። የሚችል ሁሉ በነዚህ ሰዓቶች ይጸልያል። ከዚያ ውጪ ግን አይጸለይም ማለት አይደለም። በነዚህ ሰዓቶች ቢያንስ አባታችን ሆይ የሚለውን ይጸልይ ዘንድ ይገባል።

> "ኩሎ አሚረ እባርከከ ወእሴብሕ ለስምከ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም" መዝ ፻፵፬፡፪ (144፡22)

በዚህም ዓለም በሚመጣውም ዓለም ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ ማለት ነበረ በቅዱስ ኪዳንም "ሀበነ ዘወትር ጸሎተነ" እሰበ ጸሎታችንን ስጠን አንድም አብዝተን እንድንጸልይ አድርገን ብለን እንለምነዋለን። ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው የሰባቱ ሰዓታት ጸሎት ምሳሌና ምሥጢር ነው።

"ሰብዓ ከዕለትየ እሴብሐከ"

በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሀለሁ" መዝ ፻፲፰:፻፷፬ (118:164)

**፯. በነግህ**:- ነግህ ወይም ማለዳ የሚለው ከጠዋት ሰዓት ነው። በብሉይም በሐዲስም የነበሩ ያሉ ምእመናን በዚህሰዓት ይጸልዩ ነበር አኛም እንድንጸልይ ታዘናል። ይህች ሰዓት አባታችን አዳም የወደቀባት መድኃኒታችንም ከውድቀት ያነሳን ዘንድ ከጲላጦስ ፊት የቆመባት ናት።

> "አቤቱ ወደ አንተ እጸልያለሁና በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ ከአንተም እታያለሁ።" መዝ ፭:፫ (5:3)

**፰. በሠለስት**:- ይህ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ነው። ቅዱሳን በዚህ ሰዓት ከጸሎት ይተጋሉ። ከምሳሌ ዳንኤል በየዕለቱ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ይጸልይ ነበር የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ ይላል ትክክለኛው ግን በግእዙ "በጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ሰገደ ዳንኤል ወጸለየ ወተጋነየ ለእግዚአብሔር በከመ ያለምድ" ይህም ሲተረጎም ከጠዋት በሦስት ሰዓት እንዳሰለመደ ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር ሰገደ፣ ጸለየ አመሰገነም ይላል። ዳን ፮:፲፩ (6:11)

ይህችም ሰዓት አባታችን አዳም እናታችን ሔዋን ገነት የገቡበት እመቤታችን ብሥራተ ገብርኤልን የሰማችበት፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጸነሰበት፣ በሰቅለቱ ቀን በዕለተ አርብ የተገረፈበት፣ ኋላም በጽርሐ ጽዮን ከመቶ ሃያው ቤተሰብ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ልዩ ሰዓት ነው።

**፱. በቀትር**:- ይህ እኩለ ቀን ነው፡፤ ከቀኑ ስድስት ሰዓት

> "በማታና በጥዋት በቀትርም እናገራለሁ" መዝ ፶፬:፲፯ (54:17) ይህች ሰዓት የክብር ባለቤት የሁላችን ቤዛ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለባት ሰዓት ናት።

"ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ" ሉቃ ፳፫:፵፬ (23:44)

፱. በተሰዓቱ፡- ይህ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ነው። ይህ ሰዓት በብሉይ የነበሩ አበውና እማት ኋላም ሐዋርያት የጸለዩበት ሰዓት ነው። በዚህች ሰዓት የሁሉ ፈጣሪ በቀራንዮ መስቀል ላይ ሆኖ ነፍሱን የሰጠባት ሰዓት ናት።

> "በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፡- ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም ማለት አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው.... ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱም ተወ። " ማቴ ፳፯፡፵፮፡፶ (27፡46-50)
>
> አሰረጅ፡- የሐዋ ፫፡፩ (3፡1)

፲. በሠርክ፡- ይህም ወደ ማምሻው አሥራ ሁለት ሰዓት ነው።

"ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ እጅ መንሣቴም እንደ ሠርክ መሥዋዕት ትሁን።" መዝ ፻፵፡፪ (140፡2) ክቅዱስ ዳዊት ቃል እንደምንረዳው ይህች ሰዓት የሠርክ መሥዋዕት የሚቀርብበት የኪመና ሰዓት ነች። ስለ ሁላችን መሥዋዕት የሆነው ጌታችን በዚህች ሰዓት ነበር ወደ መቃብር የወረደው ማቴ.፳፯፡፶፯-፷፩ (27፡57-61)።

፲፩. በንዋም፡- ንዋም ማለት በግእዝ እንቅልፍ ማለት ነው። ይህም ሰዓት ከምሽቱ በሦስት ሰዓት ነው። ከጠዋቱ የንጋት ሰዓት እንዲያደርሰን ጨለማውንም እንዲገፍልን የምንጸልይበት ሰዓት ነው። ይህች ሰዓት ጌታችን ሥርዓተ ጸሎትን በተያዘባት ሐሙስ ምሽት ያሳየባት ናት። የተያዘባትም ሰዓት ይህች ናት።

፲፪. በመንፈቀ ሌሊት፡- ይህም እኩለ ሌሊት ነው። ስድስት ሰዓት ነው።

"በእኩለ ሌሊት እመሰግንህ ዘንድ እነሣለሁ" መዝ. ፻፲፰፡፷፪ (118፡62)

> "በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር" የሐዋ ፲፮፡፳፭ (16፡25)

ይህች ሰዓት የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአመቤታችን የተወለደባት፣ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከሞት የተነሣባት ዳግም ዓለምን ከሚሳለፍ የሚመጣባት ሰዓት ናት።

ሰባቱ ጊዜያት ከላይ ያየናቸው ሲሆኑ የሰው ልጅ ከዚህም በላይ ይጸልይ ዘንድ ይገባዋል፡፤ መታከትም እንዳይገባ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፰፡፩-፰ (18፡1-8) ተገልጿል። ከዚህም ተጨማሪ አንድ ክርስቲያን ሥራውን ሲጀምር፣ ምግብ ከመመገቡ በፊትና ከተመገበ በኋላ ይጸልይ ዘንድ ይገባዋል።

አንባቢ ሆይ፡- በቤተክርስቲያናችን ሕግ የጠዋትና የማታ ጸሎት በቤተክርስቲያን ሄዶ እንዲጸለይ ታዟል።

## ከጸሎት ወደ ቤተክስርስቲያን መሄድ

አንዳንድ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ለምን ያስፈልገናል እግዚአብሔር በሁሉ ሥፍራ አለ። ስለዚህ በቤት መጸለይ እችላለሁ ሲሉ ይሰማሉ። በቤት መጸለይ አይከለከልም ግን ወደቤተ እግዚአብሔር መሄድ ደግሞ ግዴታ ነው። ለምን?

፩ኛ. ቤተክርስቲያን ከቤታችን ይለያል በቤታችን ብንጸልይም የእኛ መኖሪያ ነው ቤተክርስቲያን ግን የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው።

> "በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ።" ዘጸ ፳፭፡፰ (25፡8)

> "...ከዘላለምም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ዐይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ።" ፩ነገ ፱፡፫ (9፡3)

፪ኛ. ቤተክርስቲያን የማምከኪያና የመጸለያ ቦታ ብቻ ነው። የተሠራውም በጸሎት እግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ነው።

"ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች" ማቴ ፳፩፥፲፫ (21፥13)

፫ኛ. ቅዱስ ሥጋውን ለመብላት ክቡር ደሙን ለመጠጣት የምንችለውና የዘላለም ሕይወት ልንወርስ የምንችልበትን ክብር የምናገኘው ቤተክርስቲያን በመሄድ ነው። መሥዋዕት ባገኙት ሁሉ ሥፍራ አይሠዋምና።

> "የሚቃጠለውን መሥዋዕትህን በሚታይህ ስፍራ ሁሉ እንዳታቀርብ ተጠንቀቅ" ዘዳ ፳፩፥፲፫ (21፥13)

በተገኘ ስፍራ ሁሉ የእግዚአብሔር መሥዋዕት መሠዋት እንዳይቻል በብሉይ መሥዋዕት እንኳ እንዲህ ከተባለ በሐዲስ ደግሞ የጌታችን ሥጋና ደም በመቅደሱ እንደት ባለ ክብር ሊሰጥ እንደሚገባው እንመለከታለን። ሥጋውና ደሙ እንደሌለው ምግብ አይደለምና። በቤታችን የሥጋችንን ምግብ እንመገባለን በመቅደሱ ደግሞ የጌታችንን። ማንም ይህን ማመሳሰል አይገባውም።

> "የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን" ፩ቆሮ ፲፩፥ ፳፪ (11፥22)

፬ኛ. በቤተመቅደሱ የእግዚአብሔር ታቦት ስላለ።

> "ታቦቱን ወደ ማደሪያው አገባ የሚሸፍነውንም መጋረጃ አድርጎ የምስክሩን ታቦት ሸፈነ" ዘጸ ፵፥፳፩ (40፥21)

፭ኛ. አባቶቻችን ነቢያትና ሐዋርያት በእግዚአብሔር ተመርተው በመቅደሱ እየተሰበሰቡ እንዳመለኩት እኛም እነሱን አብነት አድርገን ሕጉንም ተቀብለን በመቅደሱ በአንድነትና በሕብረት እናመሰግነዋለን። ይህም የምንመኘውና ደስ የምንሰኝበት ነው።

> "በሌሊት በቤተመቅደስ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ እግዚአብሔርንም አመስግኑ" መዝ ፻፴፫፥፪ (133፥2)

"ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ" መዝ ፻፳፩፡፩ (121፡1)

"እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርሱዋንም እሻለሁ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ" መዝ ፳፮፡፬ (26፡4)

፲፫. ቤተክርስቲያን ከሰማያዊት መቅደስ ከመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናትና። በዚህ መሰብሰባችን በሰማይ ከመሰብሰባችን እምሳል ነውና።

"በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው መሰብሰባችንን አንተው" ዕብ ፲፡፳፭ (10፡25)

"ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እኖራለሁና።" ማቴ ፲፰፡፳ (18፡20)

"ወነበሩ በቤተመቅደስ እንዘ ዘልፈ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር" "ዘወትር እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑት ሲያገለግሉ በቤተ መቅደስ ኖሩ" ሉቃ ፳፬፡፶፫ (24፡53)

"ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር።" የሐዋ ፫፡፩ (3፡1)

"....እንዳያረክሱት ሰንበትን የሚጠብቁትን ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ሁሉ ወደ ተቀደሰ ተራራዬ አመጣቸዋለሁ በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላልና።" ኢሳ ፶፮፡፮-፯ (56፡6-7)

## በጸሎት የሚደረጉ ሥርዓታት

ጸሎት በሚጸለይበት ጊዜ ሊደረጉ የሚገባቸው ሥርዓቶች አሉ። እንኳን በእግዚአብሔር ፊት በሰው ፊት ለመቆም ሁሉም ሥርዓት አለው። ከመጸለይ በፊትና በጸሎት ጊዜ

እንዲሁም ሲያልቅ ከምንፈጽማቸው የሚከተሉት ዋና ዋና ሥርዓቶች አሉ።

፩. አለባበስ የተስተካከለ መሆንና ፊታችን የታጠበ መሆን። በተለይ በእኩለ ሌሊት ጸሎት ውኃ እንኳ ባይኖር በምራቅ ፊትን ማበስ ይገባል።

፪. ቀጥ ብሎ መቆም

"በጽባሕ እቀውም ቅድሜከ" "በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ" መዝ ፭፥፫ (5፥3)

፫. ፊትን ወደምሥራቅ መመለስ፡- በዚህም የምናስበው ምሥራቅ ከተባለች ፀሐየ ጽድቅ የተባለ ጌታችን መወለዱን ሕዝ ፵፬፥፩-፫ (44፥1-3) በምሥራቅ በኩል ማረጉን ዳግመኛም ከፍርድ መምጣቱን ማቴ ፳፬፥፳፯ (24፥27) ዮሐ ፩፥፱ (1፥9)

፬. ማማተብ

፭. የሚጸልዩትን አውቆ መጸለይ ሕሊናንም መሰብሰብ

፮. በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የጸሎቱን ቃላት ማንበብ

፯. ከጸሎት በፊትና በኋላ እንዲሁም ስግደትን የሚገልጽ ቃል በሚኖርበት መስገድ

፰. እጆችን በመስቀል አምሳል መዘርጋት (፩ጢሞ ፪፥፰ (2፥8)

፱. ዓይኖችን ወደሰማይ ማቅናት (መዝ. ፻፳፥፩ (120፥1)

፲. በተለይ በንስሐ ጊዜ ደረትን መድቃትና ማልቀስ

እነዚህን ከመፈጸምና ከማሰብ ጋር ዋናው ዐቢይ ነገር ንጹሕ ልብ ከቂም ከበቀል የነጻ መያዝ ይኖርብናል። ጸሎታችን ተሰሚ መሥዋዕታችን ጉዳይ ፈጻሚ እንዲሆን ጌታችን ያዘዘን ይቅር ባይነትን ነው።

"ከጸሎትም ዘቆማችሁ ጊዜ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፤ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ

ይቅር በሉት። እናንተ ግን ይቅር ባትሉ አይላችሁም።" ማር ፲፩፥
፳፭ - ፳፮ (21:25 - 26)

# ስእለት

ስእለት የሚለው ቃል ከግእዝ ግሥ "ሰአለ" ከሚለው የወጣ ነው። ሰአለ ማለት ለመነ "ስእለት" ደግሞ ልመና ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ስእለት ከእግዚአብሔር መልስ ለማግኘት መለመን ሲሆን ስለዚህም እግዚአብሔር ከሰጠው ስጦታን ለእግዚአብሔር ከመስጠት ጋር ነው። አንድ ሰው ስእለት ተሳለ በምንልበት ጊዜ እግዚአብሔር ልመናውን ሰምቶ እንዲፈጽምለት ወደ መቅደሱ ሊያመጣ ወይም እንደ ስእለቱ ሊፈጽም ቃል ገባ ማለት ነው። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው ስእለትና ልመና ልዩነት እንዳላቸው ነው።

ልመና ወይም ጸሎት፡- በየእለቱ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ነው። ስእለት ግን ሰዎች በአንድ በሆነ አስቸጋሪ ሰዓት ልመና ወይም ጸሎት ሲያደርጉ በተጨማሪ ለአምላክ ስጦታ ለመስጠት ቃል ኪዳን የሚገቡት ብፅዐት ተብሎ የሚጠራው ነው።

> "ለልዑልም ስእለትህን ስጥ በመከራ ቀን ጥራኝ እድንህማለሁ አንተም ታከብረኛለህ" መዝ. ፵፱፥፲፭ (49፥15)

ስእለት ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ ለእግዚአብሔር የሚገቡት ቃል ኪዳን ነው። በራስ ፈቃድ ቢሆንም ሕግና ሥርዓት አለው። ይህም በሕግ መጽሐፍ ተዘርዝሯል።

> አስረጅ፡- ዘሌ. ፳፯ (27) ዘኁ. ፴ (30)

ሰዎች ስእለት ከተሳሉ በኋላ መፈጸም ይኖርባቸዋል። አለዚያ ግን በደል ይሆንባቸዋል።

> "ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ፈጽሞ ይሻዋልና ኃጢአት ይሆንብሃልና መክፈሉን አታዘግይ። ባትሳል ግን ኃጢአት የለብህም። በአፍህ የተናገርኸውን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በፈቃድህ ተስለሃልና ከከንፈርህ የወጣውን ታደርግ ዘንድ ጠብቅ" ዘዳ.

፳፫፥፳፩-፳፫ (23፥21-23)

ይህንን የፈጣሪን ትእዛዝ ጠቢቡ ሰሎሞንም በስብከቱ ከገለጸው በኋላ እንዲህ ይላል። "ተስለህ የማትፈጽም ብትሆን ባትሳል ይሻላል" መክብብ ምዕራፍ ፭፥፩-፯ (5፥1-7)። ከመሳል በፊት መጠንቀቅና ማስተዋል የሚገባው በገለዓዳዊው በኃያሉ ሰው በእስራኤል መስፍን በዮፍታሔ የደረሰው እንዳይገጥመን ነው። እንዲህ ነበር የሆነው ዮፍታሔ አሞናውያንን ሊወጋ በሄደ ጊዜ ከእግዚአብሔር ስእለትን ተሳለ ስእለቱም ከእግዚአብሔር ጠላቶቹን በእጁ አሳልፎ ከጣለለት ወደ ቤቱ ሲሄድ መጀመሪያ የሚቀበለውን ሊሰዋ ነበር። በትርጓሜው እንደምንረዳው ዮፍታሔ ወደቤቱ በሚመጣ ሰዓት ሁልጊዜ የሚቀበለው ነጭ በግ ነበር። የዮፍታሔ ሐሳብ ይህን በግ ከመሠዋት ነበር። ድል አድርጎ ሲመለስ ግን የተቀበለችው አንዲት ልጁ ነበረች። "እንደተሳለውም ስእለት አደረገባት" መሳ. ፲፩፥፳፱-፵ (11፥29-40)። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፭፥፩-፲፩ (5፥1-11) ተጽፎ እንደምናየው ቸኩሎ መናገር ከተናገሩም ማስቀረት አይገባም። በዚህ ታሪክ ባልና ሚስት የነበሩት ሐናንያና ሚስቱ ሰጲራ ከሐዋርያት ሊሰጡ ቃል የገቡትን የመሬት ሽያጭ ገንዘብ ግማሹን ደብቀው ከተናገሩት አስቀርተው ቢያመጡ የሞት ሰዎች ሆኑ።

> "ሰው በችኮላ፡- ከእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው ብሎ ቢሳል ከተሳለም በኋላ ቢፀፀት ወጥመድ ነው" ምሳ. ፳፥፳፭ (20፥25)

ወጥመድ ሆኖብን ከእምላካችን እንዳይለየን በመከራ ቀን በጭንቀታችን ቀን አስበን ተስለን ልንፈጽመው ይገባናል።

የተናገሩት መፈጸም ቃል ኪዳንን መጠበቅ እንጂ የስእለቱ መብዛትና ማነስ መጠን ከፈጣሪ ትርጉም የለውም ሁሉ የእርሱ ነውና።

"በመከራዬ ጊዜ በአፌ የተናገርሁትን ከንፈሮቼም ያሉትን ስእለቴን ከአንተ አፈጽማለሁ" መዝ. ፷፭፥፲፬ (65፥14)

በታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ ከእኛ ትምህርት ይሆኑ ዘንድ በሕጉ እንድንመራ ከሕቱቱም እንድንጠበቅ ብዙ ምሳሌ እናገኛለን። ከምሳሌ የአባታችን የቅዱስ ያዕቆብ ስእለት። አባታችን ያዕቆብ ቤቴል ብሎ በሰየመው በፍኖተ ሎዛ የእግዚአብሔርን የማዳን ተግባር ከድንግል ማርያም የመወለዱን ምሥጢር በሕልም በመሰላል ቢያሳየው እንዲህ ብሎ ስእለትን ተሳለ

> "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን በምሄድበትም በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል። የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል። ከሰጠኸኝም ሁሉ ከአንተ ከዐሥር እጅ አንዱን አሰጥሃለሁ" ዘፍ. ፳፰፥፲-፳፪ (8፥10-22)

በአጠቃላይ ስንመለከት የሰዎች ስእለት በነዚህ ዋና ዋና አስፈላጊ በሆኑ በአባታችን ያዕቆብ ስእለት ውስጥ የተካተቱ ሆነው እናገኛቸዋለን።

፩፥ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፡- ይህ ሁሉ የሚበልጥ ነው በሃይማኖት መኖርን ይገልፃል። አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። ማቴ. ፮፥፴፫ (6፥33)

፪፥ በምሄድበት በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ፡- ይህ አጠቃላይ የሰው ልጅ ኑሮን እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ያሳያል። በኑሮዬ ሁሉ ቢጠብቀኝ ከክፉ ከሚያስፈራ አደጋ ሁሉ ቢጠብቀኝ ማለትም ነው።

፫፥ የምበላውን እንጀራ የምለብሰውን ልብስ ቢሰጠኝ፡- ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር መሆኑን መረዳትን ያሳያል። ለክ ቤት ትዳር ምግብ ልብስ ወይም ሥራ ይገልጻል።

፬፥ ወደ አባቴ ቤት በጤና ብመለስ፡- በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባት።

ሁሉን ገልጾ እግዚአብሔር ይህን ቢፈጽምልኝ

የእግዚአብሔርን መቅደስ አሠራለሁ። እንደገናም ከስጦኝ አለ። ሁሉን የሚሰጥ ፈጣሪ ስለሆነ ስለዚህም ካሥር አንድ እሰጣለሁ ብሎ ስእለቱን ተሳለ። ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን የሚፈጽሙት ይህንኑ ነው። አባታችን ነቢዩ ዳዊትም ከእግዚአብሔር ታቦት መቅደስ ማደሪያ ሳልሠራ አልተኛም ብሎ እንደተሳለ መዝ. ፻፴፩፥፩-፭ (131፥1-5)።

- ስእለትን በምንሳልበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ኪሆን ይችላል። ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር ነውና።
- ስእለት በብሉይ ዘመን እንደነበረ ሁሉ በአዲስ ኪዳንም የቀረ አለመሆኑን በብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ፣ በጵርስቅላና በአቂላ እንማራለን።

"ከዚህም በኋላ ጳውሎስ እጅግ ቀን ተቀምጦ ወንድሞቹንም ተሰናብቶ በመርከብ ወደሶርያ ሄደ፡ ስለትም ነበረበትና ራሱን በክንክራኦስ ተላጨ ጵርስቅላና አቂላም ከእርሱ ጋር ነበሩ" ሥራ ፲፰፥፲፰ (18፥18)

- ስእለታችን በምሥጢርም በግልጽም ልንሰጥ እንችላለን። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ለሌሎችም ጽናት እንዲሆን በሰው ሁሉ ፊት ብናደርገው እግዚአብሔር ይከበርበታል።

"ወእሁብ ብፅዐትየ ለእግዚአብሔር በቅድመ ኩሉ ሕዝብ"

"በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቱን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ (እሰጣለሁ)" መዝ. ፻፲፭፥፭ (115፥5)

- እግዚአብሔር የማይከብርበት ጥቅም የሌለው ከንቱ የሆነ ቃልን ከመናገርና ከመሳል መጠንቀቅ ይገባል። አፍ እንዳመጣም ከመሳል አለቦ ኢሆን ይገባዋል።

"እግዚአብሔር በሰማይ አንተም በምድር ነህና በአፍህ አትፍጠን በእግዚአብሔርም ፊት ቃልን ይናገር ዘንድ ልብህ አይቸኩል ስለዚህ

ቃልህ ጥቂት ይሁን" መክ. ፭፥፪ (5፥2) ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው የስእለት ሥርዓት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብቻ ይገኛል።

# የሠርግ ሥርዐት

ከስባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ "ምሥጢረ ተክሊል" እንደሆነ የታወቀ ነው። ይህም በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ የሚሆን ቅዱስ ሥርዓት ነው። ይህም የሚፈጸመው በጸሎትና በዝማሬ በቤተ ክርስቲያን ሲሆን የሠርግ ሥነ ሥርዓት ግን በቤት ውስጥ ይደረጋል።

የመጀመሪያ ተጋቢዎች አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ነበሩ። በዚህም ሠርግ የታደሙት እንደኛ ቅድስት ሥላሴ ሁለተኛ ቅዱሳን መላእክት ነበሩ። እነዚህም ዛሬ ካለው የሠርግ ሥርዓት ምሳሌነታቸው የሸማግሌዎችና የምዜዎች ነው። እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ባልና ሚስት ይሆኑ ዘንድ ፈጠረ። በመዋዕለ ሥጋዌውም ከጥምቀትና ከአርባው ጾም በኋላ የመጀመሪያውን ተአምር ሲያደርግ በሠርግ ቤት አደረገ።ዮሐ. ፪፡፩፡፲፩ (2፡1-11)

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ንጹሕ እንደ ሆነ ይገልጽና ይህም ምሥጢር ታላቅ ነው ይላል።

> "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን" ዕብ. ፲፫፦፬ (13-4)
>
> "ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ።" ኤፌ ፭፦፴፩-፴፪ (5፡31-32)

ቅዱስ ኤፍሬምም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሙሽራ እመቤታችንን ደግሞ በንጹሕ የሠርግ ቤት ይመስላታል። "ከብካብ ንጹሕ ዘመርዓዊሃ ቅዱስ" ሙሽራዋ ንጹሕ የሚሆን ንጹሕ የሠርግ ቤት ይላታል- ከላይ እንዳየነው ቅዱስ ጳውሎስ ሙሽራን በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በሙሽሪት ይመስላል። ንጹሕ

መቅደስ ንጹሕ ቤተ ክርስቲያን አመቤታችን ነችና።

በዚህ የቅዱስ ኤፍሬም ቃል የአባቶቻችን ትርጉም በረቡዕ ውዳሴ፡ እንደተገለጸው በሠርግ ቤት አራት ነገሮች ይደረጋሉ በንጽሕት አመቤታችንም ዓራት ነገሮች ተደርገዋል። በሠርግ ቤት አራት ነገሮች፡ -

1ኛ. ዘፈን ጨዋታ

2ኛ. መብል መጠጥ

3ኛ. የመርዓዊና የመርዓት (የሙሽራና የሙሽሪት ተዋሕዶ)

4ኛ. አዝማደ መርዓዊና አዝማደ መርዓት (የሙሽራውና የሙሽሪት ዘመዶች) አንድ ይሆኑበታል።

በንጽሕት አመቤታችን የአምላክ ቤተመቅደስ ደግሞ፡-

1. እንደ ዘፈንና እንደ ጨዋታ፡- ተአምራት

2. እንደ መብልና እንደ መጠጥ፡- ትምህርት።

3. እንደ መርዓዊና መርዓት ተዋሕዶ፡- ትስብእትና መለኮት ተዋሕዶባታል።

4. አዝማደ መርዓዊና አዝማደ መርዓት አንድ እንደሚሆኑ በአመቤታችንም፡-

ሀ. ሰውና እግዚአብሔር

ለ. ሰውና መላእክት

ሐ. ነፍስና ሥጋ

መ. ሕዝብና አሕዛብ አንድ ሆነዋል።

በአጠቃላይ የሠርግ ሥርዓት በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል የተፈቀደ ሥርዓት ነው። ምሥጢሩም ታላቅ ስለሆነ ዝምብሎ የታይታ ሳይሆን የበረከት ዕለት ነው።

# ቀብርና ከቅሶ

ክርስቲያኖች በሚሞቱበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚሄዱ ናቸውና ሞታቸው የተከበረ ነው። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ እንደተናገረው "ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር" "የጻድቅ ሞት በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው" መዝ ፻፲፭፡፮ (115፡6)።ምክንያቱም ጌታችን በወንጌሉ እንዳስተማረው በትንሣኤ እንደ መላእክት የምንሆንበት ነውና። ማቴ ፳፪፡፴ (22፡30)

የቀብር ሥርዓት ራሱን የቻለ ሃይማኖታዊ ምሥጢር አለው፤ በመጀመሪያ ሬሳው ይታጠብና ይገነዛል።

> "... ታመመችና ሞተች አጥበውም በሰገነት አኖሩአት" ሥራ ፱፡፴፯ (9፡37)

የክብር ባለቤት ጌታችን ለእኛ ሲል ሞትን በተቀበለ ጊዜ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ እንደገነዙት በመጽሐፍ ተመዝግቧል።

> "... በድኑን ለዮሴፍ ሰጠው። በፍታም ገዝቶ አውርዶም በበፍታ ከፈነው በዓለትም በተወቀረ መቃር አኖረው።" ማር ፲፭፡፵፭ (15፡45)

የሙታን ግንዘት ሲፈጸም መገነዣው ከፈን አዲስ የሆነ ነጭ ነው። ይኸውም በሰማይ የሚጠብቀን የክብር ልብስ ምሳሌ ነው። ብንሞትም ትንሣኤ እንዳለን ይመሰክራል።

"ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው" ራዕ ፮፡፲፩ (6፡11)

## አቀባበር

የአቀባበር ሥነሥርዓት በሳጥንም ይሁን በሰሌን ቢቀበር ሬሳው በጀርባው እንደተኛ ይደረጋል። ወደመቃብርም ሲገባ ራስ ወደምዕራብ እግር ወደ ምሥራቅ ተደርጎ አፈር ይለብሳል። የሚቀበረውም በቤተክርስቲያን ቅጽር ነው።

፮. አፈር የሚለብስበት፡- እግዚአብሔር አምላክ አዳምና ሔዋንን ሞትን ትሞታላችሁ ባላቸው ጊዜ "አ አዳም መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት" አዳም ሆይ አፈር (መሬት) ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ስላለው ካህኑ ይህን ብሎ አፈሩን ወደ መቃብሩ ይበትናል። በጉድጓድም መቀበሩ ይህን ነው። ምሳሌውም በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ሲኦል እንደነበረበት ከሚጠየቅ ነው። ይህም ማለት በሥጋ ሞት የነፍስ ሞት መቃብር እንደመውረድ ወደሲኦል መውረድ ነበረብንና ነው።

፯. ራስ ወደ ምዕራብ እግር ወደ ምሥራቅ ተደርጎ የሚቀበርበት ምክንያት አዳም ባመጣው ሞት ሁላችንም ብንሞት በክርስቶስ ትንሣኤ ሁላችን ከመቃብርና ሲኦል ወጥተን ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት እንደምንገባ እሙን ነውና ይህም የሚሆነው ጌታ ከፍርድ ዳግመኛ ወደዚች ምድር ሲመጣ ነው። አመጣጡም በወንጌል እንደተነገረው፡-

> "መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል" ማቴ ፳፬፡፳፯ (24፡27)

በቅዳሴያችንም ላይ እንደተጻፈው ሁልጊዜ "ውስተ ጽባሕ ነጽሩ" ወደምሥራቅ ወደ ፀሐይ መውጫ ተመልከቱ የሚባልበት አንዱ ትርጉም ምጽአትን አስቦ ማለት ነው።

ስለዚህም የጌታ አመጣጡ በምሥራቅ ነውና ራሳችን ወደምዕራብ ሆኖ ፊታችን ወደምሥራቅ የሚሆነው ጌታ ሲመጣ ፊት ለፊት እናየው ዘንድ የተመሰለ ነው። የጥንት ክርስቲያኖች ዛሬም ቢሆን የመተኛ አልጋ እንኳ ራስጌ ወደምዕራብ ያደርጋሉ እናደርጋለን።

> "በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረዘይት ላይ ይቆማሉ።" ዘካ ፲፬፡፬ (14፡4)

እንባቢ ሆይ፡- ማስተዋል ያለብን ይህ ሥርዓቱ መሆኑንና ነገር ግን በየትኛውም ዓይነት አሟሟት የሞተውም

የተቀበረውም ያልተቀበረውም በትንሣኤ ዘጉባዔ ሥራው ተከትሎት እንደሚነሳ ነው።

## የለቅሶ ሥርዓት፡

በሞት ለተለየ ሰው ማልቀስ ይገባል። ወደ ኀዘንተኞችም ቤት ሄዶ ማጽናናት ይገባል።

> "ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ ወደ ልቅሶ ቤት መሄድ ይሻላል።....የጠቢባን ልብ በልቅሶ ቤት ነው..." መክ ፯፡ ፪-፭ (7፡2-5)

ከዚህም አብነት ይሆን ዘንድ ጌታችን ወደማርያምና ማርታ ቤት ስለ ወንድማቸው ኀዘን እንደሄደ ስለሞተውም ኋላ ስለሚያስነሳው አልዓዛር እንዳዘነለት በወንጌል ተጽፏል።

> "ገብረ በመንፈሱ" በልቡናው አዘነ። ዮሐ ፲፩፡፴፫ (11፡33) በመጽሐፍ እንደተጻፈ ለሞቱ ሰዎች ሁሉ ሲያለቅሉ በብዙ ቦታዎች እናገኛለን።
>
> "የእስራኤልም ልጆች በሞዓብ ሜዳ ሠላሳ ቀን ለሙሴ አለቀሱለት" ዘዳ ፴፬፡፰ (34፡8)

በዚህም የተነሳ እስከ ወር መጨረሻ እስከ አርባ ቀን ድረስ ኀዘንተኞች ለከሙታን ያስባሉ። የሚደረግም የመታሰቢያ የጸሎት ሥርዓት አለው። ዋናው ለቅሶ ግን ሦስት ጊዜ ነው።

፩. ነፍስ ስትወጣ

፪. የሙት ሬሣ ከቤት ሲወጣ አይመከሉበትምና

፫. ወደ መቃብር ሲወርድ አፈር ሲገባ

## እጅ መታጠብ፡-

ሰዎች ከቀብር ሲመለሱ እጅ መታጠብ አለ። ይህ ምግብ ከመብላት ወይም ከንፍሮና ቆሎ ሳይሆን ሌላም ሥርዓት አለው። ይህም አገራችን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት ሥርዓት የነበረች በመሆኗ ከብሉይ ሕግ

የመጣ ነው። ሬሳውን የነኩም ያልነኩም በውኃ ይታጠባሉ።

> "የሞተውን ሰው በድን የነካ ሁከመናውን ባያጠራ የእግዚአብሔርን ማደሪያ ያረክሳል ያ ሰው ከእስራኤል ዘንድ ተለይቶ ይጠፋል በእርሱም ላይ የሚያነጻ ውኃ አልተረጨምና ርኩስ ይሆናል" ዘኁ ፲፱፥፲፫ (19፥13)

ይህም የመንጻት ሕግ ነው። በውስጡም የጤና ነገር አለበት ከሚተላለፍ በሽታም ሆነ ከሌላ ሰው ይጠበቅ ዘንድ መታጠብ አለበት።

## ሣልስት፡-

ከቀብር በኋላ ሦስተኛው ቀን ሣልስት ይባላል ይህም የግእዝ ቃል ሲሆን ሦስተኛ ማለት ነው። በሦስተኛው ቀን ወደመቃብሩ ስፍራ መሄድ ይገባል። ይህም የሞተ ሰው ትንሣኤ እንዳለው እንደሚነሳ ለመመስከር ነው፤ ይህም ከሦስተኛው ቀን የጌታ ትንሣኤ የመጣ ነው።

> "ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደመቃብር መጡ" ማር ፲፮፥፪ (16፥2)

> "... ገብተው የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም" ሉቃ ፳፬፥፩-፬ (24፥1-4)

## ነጭ ከር፡-

ኀዘን የደረሰባቸው በአንገታቸው ነጭ ከር ያስራሉ ይህም ምንም በሥጋ ሞት ቢኖር ትንሣኤ እንዳለ የሚመሰክር ነው። ነጭ ከር ደግሞ የሚታሰረው ክርስቲያኖች በቤታቸው ኀዘን ሲደርስ ከዘመዶቻቸው የዚህን ዓለም ሞት ሲሞቱ ምንም እንኳ በመለየታቸው ቢያዝኑ ቢያለቅሱ በነፍሳቸው ግን ወደ እግዚአብሔር በመሄዳቸው በኋላም በትንሣኤ ዘጉባዔ እንደሚነሱ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዳላቸው ስለሚያምኑ ነጭ ከር (ማዕተብ) በኀዘኑ ሰሞን ያስራሉ። ይህም ትንሣኤ እንዳለ ለመግለጽ ነው። በወንጌል ተጽፎ እንደምናየው መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ ጌታችን በተቀበረ

በሦስተኛው ቀን ወደ መቃብሩ ቢሄዱ ጌታችን ከሞት ተነሥቶ በመቃብሩም ሥፍራ ነጭ ልብስ የለበሰ መልአክ አዩ። የትንሣኤ ምልክት ነው።

> "ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ ጎልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ። እርሱ ግን አትደንግጡ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ ተነሥቷል በዚህ የለም" ማር ፲፮፡፭ 916-5)

## ሐውልት፡-

ከሞቱ ሰዎች ሐውልት መሥራት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናገኘዋለን። ይህም የሙታን አጥንት እጅግ የተከበረ መሆኑን ይገልጣል። አባታችን ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍን ቅዱስ ዮሴፍም ልጆቹን ስለአጥንታቸው ያሰጠነቀቁአቸውና ዝም ብለው በግብፅ እንዳይቀብሩአቸው ያማሏቸው ከዚህ የተነሳ ነው።

አሰረጅ፡- ዘፍ ፵፯፡፳፯-፴፩ (47፡ 27-31)፤ ዘፍ ፶፡ ፳፭ (50፡25)

ይህም ቃል ምሥጢሩ ትንሣኤን የሚያሳይ ነው፡፤ ከግብፅ ወጥቶ ከነዓን መግባት ከሲኦል ወጥቶ ወደ ገነት መሻገርን ያመለክታል። ስለዚህም በመቃብር ላይ ሐውልት የሚሠራበት ምክንያቱ ልክ አባታችን ያዕቆብ ከሚወዳት ሚስቱ ከራሔል እንዳደረገው ነው።

> "ወዐቀመ ያዕቆብ ሐውልተ ላዕለ መቃብረ ራሔል ወይእቲ ተሰምየት ሐውልተ ራሔል እስከ ዮም"

> "ያዕቆብም በመቃብርዋ ላይ ሐውልት አቆመ እርሱም እስከ ዛሬ የራሔል የመቃብርዋ ሐውልት ነው።" ዘፍ ፴፭፡፳ (35፡20)

ስለ ጌታችንም መቃብር ስንመለከት የአርማትያስ ባለፀጋ የነበረው ዮሴፍ ከጲላጦስ የጌታን ሥጋ ለምኖ ወስደ በአዲስ

መቃብር ከኒቆዲሞስ ጋር ከቀበሩት በኋላ ታላቅ ድንጋይ በመቃብሩ ላይ አደረገ። የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም በአንድነት ወደ ጲላጦስ መጥተው በሦስተኛው ቀን እንዳይነሳ ደቀመዛሙርቱ እንዳይሰርቁት በሚል ሰበብ መቃብሩ እንዲጠበቅ እንዲሁም ድንጋዩ እንዲታተም አደረጉ (ማቴ ፳፯፥፶፯-፷፮ (27፥57-66)። አምላካችን ግን ሙስና መቃብርን አጥፍቶ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በታላቅ ግርማ ተነሳ። ዛሬም ሐውልት መሥራቱ ምሥጢሩ ይህ ነው። ክርስቶስ የትንሣኤያችን በኩር ነውና። ሁላችንም ከመቃብር ወጥተን እንነሣለን፡፤

> "እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል።" ዮሐ ፭፡፳፭ (5፥25)

> "... እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።... እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።" ፩ተሰ. ፬፥፲፫፡፲፰ (4፥13-18)

## ፍትሐትና ተዝካር

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ለሕያዋን ዕቅበት (በምድር የሚኖሩ የሰው ልጆች ሁሉ ተጠብቀው እንዲኖሩ) ለሙታን ሥርየት (የሞቱ ሁሉ እንዲድኑ) ያለማቋረጥ ጸሎት ይደረግባታል። ለሁሉም ትጸልያለች። ከቤተክርስቲያን መጻሕፍት አንዱን ቅዳሴን ብንመለከት "በእንተ ቅድሳት" የሚለውን ጸሎት ቤተክርስቲያን የሁሉ እናት ስለሆነች ፍጥረት ሁሉ ድኅነትን ያገኝ ዘንድ ጌታዋን ትማልዳለች። እዚያ ውስጥ አንዱ ለሞቱ የክርስቲያን ወገኖች የሚደረገው "ጸሎተ ፍትሐት" ነው

### ፍትሐት

ለምእመናን በሕይወት እያሉ ከሞቱም በኋላ በካህናት የሚደረግ ሥርዓት ነው። የሚፈጸመውም ጌታችን በሰጠው ሥልጣነ ክህነት ነው። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ከጴጥሮስና ከደቀመዛሙርቱ ከእነሱም በኋላ እስከ ምጽአት ከሚነሡ ካህናት እንደ እርሱ ያለውን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል ሰጥቶናል እንዲህ ብሎ፡-

"አማን እብለከሙ ዘእሰርክሙ በምድር ይከውን እሱረ በሰማያት ወዘፈታሕክሙ በምድር ይከውን ፍቱሐ በሰማያት"

"እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል" ማቴ. ፲፰፥፲፰ (18፥18)

በዚህ እምላካዊ ቃል መሠረት ቤተክርስቲያናችን እንደኛ ሰዎችን በሕይወት እያሉ ከታሠሩበት የኃጢአት ወጥመድ በትምህርት እየፈታች የክርስቶስ ታደርጋለች። እነሱም በንስሐ እየታጠቡ ከልቡና ሽባነት እየተፈቱ የመንግሥተ ሰማይ ዜጋ ቅዱሳን ልጆች ይሆናሉ። በቤተ መቅደስ በር ላይ ቁጭ ብሎ ይለምን የነበረ ሽባ በቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከተፈታ ከዳነ በኋላ መቅደስ ሊገባ እንደቻለ ሁሉ ዛሬም ከተያዝንበት የኃጢአት ትብትብ በሐዋርያቱ ሥልጣን ስንፈታ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደምንገባ የታመነ ነው።ሥራ ፫፥፩-፰ (3፥1-8)

ይህ ጌታችን የሰጠው ሥልጣነ ክህነት ታላቅ ነውና ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ያስገባል። ይህም በካህናቱ ሥልጣን ይፈጸማል የእግዚአብሔር መንግሥት ቁልፍ በእጃቸው ነውና።

"ወእሁበከ መራኁተ ዘመንግሥተ ሰማያት"

"የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ" ማቴ. ፲፮፥፲፱ (16፥19)

እንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከእምነት ማነስ የተነሳ የእግዚብሔርን ኃይል ሲጠራጠሩ ይሰማል። ሰው ከሞተ በኋላ ጸሎት ቢደረግለት ምን ይጠቅመዋል ብለውም ይናገራሉ። በውኑ እልዓዛር ከሞት በኋላ ሲጠራ እንደት ሰምቶ ተነሣ ዮሐ. ፲፩፥፵፫-፵፬ (1143፥44)። የእምላካችን ኃይሉ ታላቅ ነው። በሰው ጥበብ የማይቻል በእምላካችን ይፈጸማል።

ይህንንም አምነን ነው ዛሬ በሥጋ ሞት ከእኛ ከተለዩ ፍትሐት ጸሎት የምናደርግላቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ነበር ያለን "ከእኔም ተማሩ" ማቴ. ፲፩፥፳፱ (11፥29)። ጌታችን ካስተማረን አንዱ ከሞቱ ዘመዶቻችን መጸለይን ነው። ኢያኢሮስ ስለሞተች ልጁ ጸለየ። ልብ በሉና አስተውላችሁ እዩ የጸለየችው የሞተችው ልጁ አይደለችም አባቷ ኢያኢሮስ ነው ወደ ጌታ ሄዶ አባክህ ልጀ ሞተች አጅህን ብትጭንባት በሕይወት ትኖራለች ብሎ ለመነ ጌታችንም ሄዶ የሞተችውን አስነሣት ለዘላለሙ ክብር ይግባው። ይህንን ቃል ተመርኩዘን የሞቱትን ዘመዶቻችንን ጌታ ሕይወት እንዲሰጥልን ከሲኦል እንዲያድንልን በፍትሐተ ጸሎት ስንማጸነው ክብር ይግባው፣ ይፈጽመዋል ያድናቸዋል። ማቴ. ፱፥፲፰-፳፭ (9፥18-25)

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን የፍትሐት ሥርዓት የሚደረግበት መጽሐፍ "መጽሐፈ ግንዘት" ይባላል።

## ተዝካር

ቃሉ የግእዝ ነው ተዝካር ማለት "ዘከረ" አሰበ ከሚለው ግሥ የወጣ የተገኘ ሲሆን። በዚህ ርዕስ የምንመለከተው የሞተውን ሰው በጸሎት ማሰብን ይመለከታል። የሚታሰበውም በቤተክርስቲያን ሲሆን በቅዳሴ በጸሎት ነው። ይህም እግዚአብሔር የሞተውን ሰው በመንግሥቱ እንዲያኖረው በሱ ስም ጸሎት በቤተክርስቲያን በማስደረግ ከተራቡ በማብላት፣ ከተጠሙ በማጠጣት፣ ከታረዙ በማልበስ በመሳሰሉት ነው። ችግረኞችንና ምንዱባንን ሳይረዱና ሳይጎበኙ ከደላውና ካለው ብቻ በማብላት በማጠጣት ተዝካርን ማድረግ ከጠቀሜታው ጉዳቱ ያመዝናል። አንዳንድ ሰዎችም ይህንን ይመለከቱና ይስቱበታል። ለሰውም መሰናክል ከመሆን ሕጉን ማወቅ ቤተክርስቲያንን መርዳት ማለከፈት የሚያስፈልገውን መባእ ማቅረብ የወደቁትን ማሰብ ትእዛዙ የአምላካችን ነውና። ይህን ከፈጸሙ ግን ነፍስ ይማር ይሉ ዘንድ የደላውንም ቢሆን ጸበል ጸዲቅ እንዲቀምስ ቢደረግ ይህም በረከት ነው።

"የሞተ ሰውስ ዐረፈ ነገር ግን ነፍሱ ታርፍ ዘንድ

ተዝካር አውጣለት"

"ከዚህ በኋላ ከቅሶህን ተው " ሲራክ ፴፰፥፳፫ (38፥23)

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሕይወት የሚኖሩና የሞቱ ሰዎች የእምነት ግንኙነት አይቋረጥም።

እኛ ታላቅ እምነት አለን ለምኑ ይሰጣችኋል ያለው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ ነው የሚሳነውም የለም ለዘላለሙ ክብር ይግባው።

## የሙታን መታሰቢያ ቀናት

፩. ሣልስት፡- ትንሣኤ እንጸለ የሚታወቅበት ጌታ የተነሣበት ሦስተኛይቱን ቀን በጸሎት እናስባታለን።

፪. ሰባት፡- በዚህም ዕለት መታሰቢያና ጸሎት ይደረጋል።

፫. ዘጠኝ፡- በዘጠነኛውም ቀን መታሰቢያ ይደረጋል።

፬. አሥራ ሁለት፡- በአሥራ ሁለተኛውም ቀን ላይ ይደረጋል።

፭. በአሥራ አራት፡- በዚህም ቀን የመታሰቢያ ጸሎት ይፈጸማል።

፮. ሠላሳ፡- በወሩ መጨረሻ በቀደሙት ሰዎች አምሳል እንደነ ሙሴ መታሰቢያ ይደረጋል።

፯. አርባኝ፡- በዚህም ዕለት መታሲያ ይደረጋል።

፰. ስድስት ወር፡- በመንፈቅም መታሰቢያ ይደረጋል።

፱. ዓመት፡- ይህም ሙት ዓመት ይባላል። በዚህም ቀን የመታሰቢያ ጸሎት ይደረጋል፡፤

፲. በየዓመቱ፡- በየዓመቱም መታሰቢያ ይደረጋል።

እነዚሀ ቀናት በብሉይና በሐዲስ ሕግጋት የተወሰኑ ሲሆኑ ክርስቲያኖችም እንደየ አቅማቸው ለሟቹ ዘመዶቻቸው

ሊፈጽሙላቸው ይገባል። ይህም ለሙታን በተከርስቲያን አስከፍቶ ጸሎት ማስደረግ ቁርባን ማስቀረብ ነው፤ ይህም ማለት ከሌላ ያለፈ ድግስ እየደገሱ ማለት አይደለም። ቁም ነገሩ ከሙታንም የሚጠቅመው በቤተክርስቲያን ጸሎት ማስደረጉና ለነዳያን መመጽወቱ ነው። ከላይ የተወሰኑትን ቀናት ብናይም ለሚችል ሰው ግን አርባውንም (40) ቀናት ከቀብር ቀን ጀምሮ መጸለይና ማጸለይ ነው፤ ፍትሐ ነገሥቱም በአንቀጽ ፳፪፡ ፯፻፺፭ (22፡795) እንዲህ ይላል

> "ወፈድፋደስ እመ ተከሀሎሙ ያዕርጉ ቁርባናተ ፵ ዕለተ እምዕለተ ተቀብረ ወየሀቡ ለነዳያን ወዘወሰከ ላዕለ ዝንቱ ሎቱኒ ወለዘሞተኒ ይፈድፍድ ዓስቦሙ በአምጣነ ጻሕቀ ወፍሥሐሁ ከምውት ይከውን በዝንቱ።
> "

"ይልቁንም ቢቻላቸው ከተቀበረበት ቀን ጀምሮ ፵ቀን ቁርባን ያስቀርቡ ለነዳያንም ይስጡ በዚህም ላይ የጨመረ እንደትጋቱ መጠን የአርሱም የሟቹም ዋጋቸው ይበዛል። የሟቹም ተድላ ደስታ በዚህ ይሆናል።"

# ምጽዋት

ክርስቲያኖች ኃጢአታችን ከሚደመሰስበትና ድኅነት ከምናገኝበት መልካም መንፈሳዊ ሥራዎች አንዱ ምጽዋት ነው። ይህም ለችግረኞች የሚያስፈልጋቸውን መስጠት ነው። ልበ አምላክ ዳዊት ለነዳያን የሚሰጥ የዘላለም ጽድቅ አለው ይለናል፤

"ዘረወ ወወሀበ ለነዳይ ወጽድቁኒ ይነበር ለዓለም።"

"በተን ለችግረኞችም ሰጠ ጽድቅ ለዘላለም ዓለም ይኖራል።" መዝ ፻፲፩፡፱ (111፡9)

ምጽዋት በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የታዘዘ ሕግ ነው።

"ድሆች ከምድሪቱ ላይ አያልቁምና ስለዚህ እኔ በሀገርህ ውስጥ ካለው ድሀ ለተቸገረውም ወንድምህ እጅህን ትከፍታለህ ብዬ አዝዝሃለሁ።" ዘዳ ፲፭፡፲፩ (15፤11)

"ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ ገንዘብህንም የሚወስድ እንዲመልስ አትጠይቀው።" ሉቃ ፮፡፴ (6፡30)

ይህንን የእግዚአብሔር ሕግ በመቀበል የእግዚአብሔር ሰዎች ለነዳያን በመመጽወት መንፈሳዊ በረከትን አግኝተዋል። ሐዋርያትም ይህን ያስተምሩና ያደርጉት እንደነበር በመጽሐፍ ተጽፎልናል።

"መቄዶንያና አካይያን በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወደዋልና።" ሮሜ ፲፭፡፳፮ (15፡26)

"ይህንም እላለሁ፡- በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል።" ፪ቆሮ ፱፡፮ (9፡6)

ምጽዋት በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ስም ይሰጣል። ይህም በቤተክርስቲያናችን ምእመናን የተለመደ ሃይማኖታዊ ሕግ ነው፤

"ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም።" ማቴ ፲፥፵፪ (10፥42)

በመመጽወት የሚገኝ የማይጠፋ ዋጋ ብዙ ሲሆን ሦስት ዓበይት የምናገኛቸው ጥቅሞች፡-

**፩. ከኃጢአት መደምሰሻ፡-** ምጽዋት ከነዳያን መመጽወት የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል፣ ይደመስሳል። ነቢዩ ዳንኤል የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን የመከረው ከዚህ የተነሳ ነው።

"ንጉሥ ሆይ ስለዚህ ምናልባት የደኅንነትህ ዘመን ይረዝም እንደሆነ ምክሬ ደስ ያሰኝህ ኃጢአትህንም በጽድቅ በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር።" ዳን ፬፥፳፯ (4፥27)

"የምትነድ እሳትን ውኃ ያጠፋታል፤ እንደዚህም ሁሉ ምጽዋት ኃጢአትን ታስተሠርያለች" ሲራክ ፫፥፳፰ (3፥28)

**፪. የእግዚአብሔርን ረድኤት ለማግኘት፡-** ምጽዋት ለተቸገረ ሰው የሚለግሱ ክርስቲያኖች ችግር በገጠማቸው ጊዜ እግዚአብሔር ፈጽሞ ይረዳቸዋል። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው፥ እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል...እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል።" መዝ ፵፥፫ (40፥3)።

ጠቢቡ ሲራክም እንዲህ ይለናል።

"ምጽዋትን ለሚሰጥ ሰው በፍጻሜ ዘመኑ እግዚአብሔር ዋጋውን ያስብለታል በመከራም በተሰነካከለ ጊዜ የሚድንበትን ረድኤት ያገኛል።" ሲራክ ፫፥፳፱ (3፥29)

**፫. የዘላለም ሕይወት ለመውረስ፡-** ዋናው የምጽዋት

ጥቅሙ መንግሥተ ሰማያትን ከማግኘት ነው። ይህም የዘላለም ሕይወት ነው። ድሆች አጅና እግር የላቸውም ለሚረዷቸው ግን በሰማይ ቤትን ይሠራሉ።

> "የዐመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ።" ሉቃ ፲፮፥፱ (16፥9)
>
> የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት ፍርድንም ለማድረግ የክብር ጌታ ሲመጣ የሚጠይቀን ከምጽዋት ጋር የተገናኙ ስድስት ጥያቄዎች ናቸው። በማቴዎስ ምዕራፍ ፳፭፥፴፩-፵፮ (25፥31-46)

ይህን ሁሉ ክብር እናገኝ ዘንድ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን መመጽወት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት እንደሆነ ታስተምራለች። "ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።" ዕብ ፲፫፥፲፮ (13፥16)

# ማኅሌትና ሰዓታት

ማኅሌት፡- በየወርና በየዓመት በዓላት በከበሮ፣ ጸናጽልና፣ መቋሚያ እየታጀበ የሚቀርብ የቤተክርስቲያናችን አገልግሎት ነው። የሚመራውም የአቋቋም ትምህርት በተማሩ መርጌታዎች ሲሆን የቃሉ ትርጉም "ኀለየ" ዘመረ፣ አመሰገነ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን ማኅሌት መዘመር ምስጋና ማለት ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት በዓል በሆነበት ዕለት ስቡሕ ወውዱስ ተብሎ እየተመረገደ ወደ ነግሥ ይሸጋገርና የበዓሉ ነክ ማለትም የዕለቱ ተስማሚ ተመርግዶ የዕለቱ በዓል መልክና ዚቅ እንደሥርዓቱ ይዘመራል፣ ይወረባል። ሁሉም ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳኑ የሚቀርብ ምስጋና ነው።

ማኅሌት ከሕገ ልቡና ጀምሮ ሰዎችን ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ዝማሬና ምስጋና ቢሆንም ከላይ ባለው ሥርዓት በተቃና የዜማ ስልት በቤተክርስቲያናችን የምንጠቀመውና በቀዳማዊነት ቅዱስ ያሬድ ያዘጋጀው ሲሆን ሌሎችም አበው በየጊዜው መልክ እየሰጡት ዛሬ ድረስ የምንገለገልበት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ልዩ መንፈሳዊ ምልክታችን ነው።

ሰዓታት፡- ያከበሮና ጸናጽል በአብዛኛው በዓቢይ ጾምና በፍልሰታ በዜማ የሚቀርብ ጸሎት ነው። በአንዳንድ ገዳማት ዓመቱን ሙሉ ሰዓታት ይቆማል። የስሙ ትርጉም ከቃሉ እንደምንረዳው የተሰየመው ከጊዜ ሁኔታ ጋር ነው። በየሰዓቱ የሚደርስ ጸሎት ነውና ሰዓታት ተብሏል። ይህም የሰዓታት ጸሎት በኢትዮጵያዊው ሊቅና ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ የሌሊትና የመዓልት (የቀን) ተብሎ በሁለት ከፍል የተዘጋጀ ነው። ይዘቱ ከእኛ ጋር አንድ ባይሆንም በሌሎች ሀገሮችም የሰዓታት ጸሎት አላቸው።

የሰዓታት ጸሎት ብዙ ምሥጢር ያለበት መንፈሳዊ ድርሰት ነው። በሌሊቱ ከፍል አሌትብ ወእትነሣእ ብሎ ይጀምርና ሚካኤል ሊቀ መላእከት የሚለው ተቁሞ ከኖኅ ሐመሩ

ሰብሐተ ፍቁር ይባላል። በዚህ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን ስለመፍጠሩና ስለማዳኑ ስለክብርት እናቱ ስለ ቅዱሳን መላእክትና ሰዎች ክብር ይነገርበታል። ከምስጋና በመቀጠል በሰዓታት ጸሎት ቤተክርስቲያናችን ለሰው ልጆች ስለ ዓለም ሁሉ ይጸልይበታል።

“ግነዩ ለእግዚአብሔር ወጸውዑ ስሞ ሃሌ ሉያ ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ”

# የማኅሌት ንዋያት

በማኅሌትና በዝማሬ ጊዜ ቤተክርስቲያናችን የምትጠቀምባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡና እግዚአብሔር የፈቀዳቸው የዝማሬ ንዋያት እነዚህ ናቸው፡-

ከበሮ

ጸናጽል

መቋሚያ

በሥርዓተ ማኅሌት በእነዚህ ንዋያት እየተዘመረ በሽብሸባ በእልልታና በጭብጨባ ይመስገናል። ከእነዚህ ውጪ በሥርዓተ ማኅሌት በሕዝብ ዘንድ ያሉ ለዝማሬ አገልግሎት የተፈቀዱ ንዋያተ ቅድሳት እንኳን አያገለግሉም። በማኅሌት ጊዜ የማንጠቀምባቸው ግን ለምእመናን ለዝማሬ የሚያገለግሉ የሚከተሉት ናቸው።

መሰንቆ

በገና

መለከት

ክራር

ዋሽንት

እንዚራ

እንቢልታ

ከእነዚህ ከተመለከትናቸው ውጪ ቤተክርስቲያናችን ሌሎችን አትጠቀምም ለሃይማኖት ምሥጢርም ምሳሌነት የላቸውም። በመጽሐፍም በቃልም አባቶቻችን እና እናቶቻችን እንደነገሩን ከተዘረዘሩት የተወሰኑትን ምስጢራት እንመልከት።

## ከበሮ

ከበሮ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ ከእግዚአብሔር

ምስጋና የሚቀርብበት የተቀደሰ የዝማሬ ንዋይ ነው። እስራኤል ከግብፅ ባርነት እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን ከፍሎ ባሻገራቸው ጊዜ ከእግዚአብሐር ምስጋናን በዝማሬ ሲያቀርቡ የሙሴና የአሮን እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮን ትመታ እንደነበረ ተጽፏል።

"የአሮን እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮ በእጇ ወሰደች"

መዝሙረኛው ልበ አምላክ ዳዊት በብዙ ስፍራ እግዚአብሔርን በከበሮ አመስግኑት እያለ ያስተምረናል።

"በከበሮ ወበመዝሙር ይዜምሩ ሎቱ" "በከበሮና በመሰንቆም ይዘምሩለት" መዝ. ፻፵፱፥፫ (149፥3)

"ሰብሕዎ በከበሮ ወበትፍሥሕት"

"በከበሮና በደስታ አመስግኑት"

መዝ ፻፶፥፬ (150፥4)

በሥርዓተ ቅዳሴም ቅድመ ወንጌል እንዲህ ይላል።

"ንሥኡ መዝሙረ ወሀቡ ከበሮ"


"መዝሙርን ያዙ ከበሮንም ስጡ"

## የከበሮ አሠራርና አመታት ትርጉም

የከበሮ አሠራር ቅርጽ በቀኝ እጅ የሚመታው ክፍል ሰፋ ያለ በግራ እጅ የሚመታው ክፍል ጠበብ ያለ ሲሆን ዙሪያውን በጨርቅ ተሸፍኖ በጠፍር እየተጠላለፈ ይታሠራል ማንገቻም ይደረግለታል። አመታቱም በማንገቻው አንገቶ ከትንሹ ጠባብ ክፍል ተጀምሮ በሰፊው ክፍል ይመታል። ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራም እያሸበሸቡ ይመታል። እንደየ ሥርዓቱም

ከመሬት ቀጭ ተደርጎም ይመታል። ይህ ሁሉ ምሳሌ አለው። ይህም ምሳሌነቱ ከአዳነን ከአምላካችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣


ይህ ስፋው የከበሮ ክፍል የመለኮት ምሳሌ ሲሆን ስፋቱ የማይወሰን የመለኮቱን ስፋት በሁሉ የመላ መሆኑን ያመለክታል
ከበሮው የሚለብሰው ሐሬርቅ አመቤታችን በቤተልሔም በሐሬርቅ የጠቀለለችበትን ኋላም አይሁድ ሲሰቅሉት ልብሱን ገፈው ቀይ ከለሜዳ (ሐሬርቅ) ያለበሱትን የሚያስረዳ ነው፡፡
ይህ ማንገቻ ጌታችንን በገመድ አስረው እንደጎተቱት የምናስብበት ነው፡፡
ይህ ጠፍር እንደኛ ጌታችንን በገረፉት ጊዜ የወጣውን ሰንበር እንደገናም አጥንቱ እስኪታይ መከራ መቀበሉን የሚያሳይ ነው፡፡
ይህ ጠባቡ ክፍል የትስብእት ምሳሌ ነው፡፡ አምላካችን በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት መወሰኑን ያመለክታል፡፡



## የከበሮ አመታት እንደየዜማው የራሱ ስልት አለው።

ከላይ እንደተመለከትነው ይህም የሚገልጸው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ መከራና ስቃይን ነው። ጠባቡና ትንሹ የከበሮ ክፍል በትንሹ ሲመታ ትልቁ ክፍል ከፍ ባለ ኃይል ይመታል። ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በያዙት ጊዜ በትንሹ መመታቱ መጀመሪያ ዓይኑን እየሸፈኑ ማነው የመታህ? እንዳሉት በትልቁ መመታቱ በኋላም በግልጽ የመቱት ምሳሌ ነው። ሉቃ ፳፪፥፷፫ (22፥63) በሁለቱም ክፍል መመታቱ ጌታችን በሁለቱም ጎን ትንጮቹን መመታቱን ያሳስበናል።

በመጀመሪያ ቀስ ተብሎ መመታቱ በኋላ በፍጥነት ቶሎ ቶሎ መመታቱ ጌታችንን አስቀድመው ቀስ እያሉ እንደመቱትና በኋላም መከራ እንዳጸኑበት ግርፋት እንዳበዙበት የሚያሳይ ነው። ከበሮ የሚመቱ ግራና ቀኝ ቀኝና ግራ እያሉ ማሽብሸባቸው የጌታን መንገላታት የሚያሳይ ነው፤ በገመድ አስረው ብዙ መከራ አድርሰውበታልና። እንደ ዝማሬው

ሁኔታ ከበሮው ተቀምጦ መመታቱ ጌታችን ከመከራው ጽናት የተነሳ በተዋሐደው ሥጋ ሥቃይን ስለእኛ ሲቀበል ከመሬት መውደቁን ከፋዎችም ተነሥ እያሉ እንደወደቀ ማንገላታታቸውን የምንመለከትበት ምሥጢር ነው።

## ጸናጽል

፩ ጸናጽል ፲፭፥፲፱ (15፥19) "መዘምራንም ኤማንና አሳፍ ኤታንም በናስ ጸናጽል ከፍ አድርገው ያሰሙ ነበር" ፩ ዜና መዋዕል ፲፭:፲፱ (15፡19)

ጸናጽል በቤተክርስቲያናችን ካሉ የዜማ ዕቃዎች አንዱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራ እግዚአብሔርን በጸናጽል አባቶቻችን እና እናቶቻችን እንዳመሰገኑት እኛም እነሱን መስለን አምላካችንን እናመሰግንበት ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ታዘናል።

"ሰብሕዎ በጸናጽል ዘሠናይ ቃሉ"

"ሰብሕዎ በጸናጽል ወበይባቤ"

"ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት"

"እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት" መዝ. ፻፶፥፭ (150፥5) ተብሎ ተጽፏል።


አባታችን ቅዱስ ዳዊት ይህንን የሚለን እሱ በጸናጽል አምላኩን አመስግኖ ለተጠቀመና የእግዚአብሔርን ክብር ስላየ እኛም ይህን በረከት እንወርስ ዘንድ ነው። መዝሙረኛው ልበ አምላክ ዳዊት ከመረጣቸው ካህናትና አገልጋዮች ዘማሪያን ጋር በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ፊት በሚዘምሩበት ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር በደመና ይገለጽ ነበር።

በ፪ኛ ሳሙ. ፮፥፭ 2ኛ ሳሙ. (6፥5) እንደተጻፈው በኮረብታውም ላይ ከነበረው ከአሚናዳብ ቤት

የእግዚአብሔር ታቦት ሲመጣ ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ኹሉ በቅኔና በበገና በመሰንቆም በከበሮም በነጋሪትና በጸናጽል በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይዘምሩ ነበር። ይህም ሥርዓት ከትውልድ የሚተላለፍ ነውና ጥበበኛው ሰሎሞን እንደአባቱ እንደ ነቢዩ ዳዊት እርሱና መዘምራኑ ከእግዚአብሔር በታቦቱ ፊት በዜማ ዕቃዎች ይዘምሩ ነበር።

> "መዘምራንም የነበሩት ሌዋውያን ኹሉ አሳፍና ኤማን ኤዶትምም ልጆቻቸውም ወንድሞቻቸውም ጥሩ በፍታ ለብሰው ጸናጽልና በገና መሰንቆም እየመቱ በመሠዊያው አጠገብ በምሥራቅ በኩል ቆመው ነበር። ... በመለከትና በጸናጽል በዜማም ዕቃ ኹሉ እግዚአብሔርን ባመሰገኑ ጊዜ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው።" ፪ ዜና ፭፥፲፩-፲፬ (5፥11-14)

የጸናጽል ጥቅሙ ዝማሬውን በልዩ ውበት ማጀብ ሲሆን አሠራሩ ግን ልክ እንደሌሎቹ የዜማ ንዋያት የሃይማኖትን ልዩ ምሥጢር የያዘ ነው። ይኸውም እንዲህ ነው፡-



ይህን ኹሉ ምሥጢር የያዘ ጸናጽል በዜማ ጊዜ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደቀኝ እንዲንደም ወደ ላይና ወደታች እየተደረገ ሲዜምበት ልክ እንደክበሮው ያምካካችንን ስለእኛ መከራ መቀበሉና መንገላታት የሚያስታውስ ነው።

## መቋሚያ


መቋሚያ በማኅሌት ጊዜ ቤተክርስቲያናችን የምትጠቀምበት አንዱ የዜማ ዕቃ ነው። መቋሚያ ከሙሴ የተሰጠውን በትር እንድም ያዕቆብ ይይዘው የነበረውን ዘንግ ያመክከታል።

> "አንተም በትርህን አንሣ እጅህንም በባሕሩ ላይ ዘርጋ ክፈለውም" ዘጸ ፲፬፥፲፮ ዘጸ. (14፥16)
>
> "ወንዙንም የመታህባትን በትር በእጅህ ይዘሃት ሂድ" ዘጸ. ፲፯፥፭ ዘጸ. (17፥5)

"ያዕቆብ ሲሞት በእምነት የዮሴፍን ልጆች እያንዳንዳቸውን ባረካቸው በዘንጉም ጫፍ ተጠግቶ ሰገደ" ዕብ. ፲፩፥፳፩ (11፥21) የሙሴ በትር የያዕቆብም ዘንግ ምሳሌነታቸው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ነው። ስለዚህም መቋሚያ የመስቀሉ ምሳሌ ነው። በዝማሬም ጊዜ አጠቃቀሙ የጌታን ሕማምና መከራ በመስቀል የሆነውንም የማዳኑን ነገር ያሳየናል።

መዘምራን በዝማሜና በወረብ ጊዜ መቋሚያውን በትከሻ የሚሸከሙበት አለ ይህም ጌታችን መስቀሉን ከመሸከሙ ምሳሌ አንድም የሚወደኝ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ ያለውን በግልጽ ያሳየናል። ማቴ. ፲፮፥፳፬ (16፥24)። እንደ ከበሮና ጸናጽል መቋሚያም የጌታችን ሕማም የሚገልጥ ነውና መዘምራን በዝማሜ ጊዜ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ሲያደርጉት በምሥጢር የጌታችንን ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ እንዲሁም ከቀያፋ ወደ ሐና ከሐና ወደ ቀያፋ የመንገላታቱ ምሳሌ፡- በትከሻ ላይ የሚደረግበት ጊዜ ጌታችን የተሸከመውን መስቀል ያሳየናል። ወደ ላይ ከፍ አድርገው

ከመሬት እንደመትከል የሚያደርጉት ጌታችንን ብዙ መከራና እንግልት ካደረሱበት በኋላ በማእከለ ምድር በቀራንዮ የመስቀላቸው ምሳሌ ነው።



ይህ ቅርጽ ዮሐንስ መጥምቁ "ነዋ በግዓ ከእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም" የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ያለውን ቃል ይዞ በንጹሕ በግ የተመሰለውን ጌታ ያውም ቀንድ አያከው የሚይዋጋ የተባለውን ያመለክታል ዮሐ. ፩፥፳፱ ዮሐ. (1፥29)

## **እልልታ**

እልልታ በግእዙ ይባቤ ተብሎ ይጠራል።

"ሠናየ ዘምሩ ወየብቡ ሎቱ"

"በእልልታም መልካም ዝማሬ ዘምሩ" መዝ. ፴፪፥፫ (32፥3)

ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ብሎ ይጣራል "ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን ከአምላክ ከመድኃኒታችን እልል እንበል" መዝ. ፺፬፥፩ (94፥1)። ከዚህም ነው ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን የእልልታ ድምፅ የሚያስተጋባው።

"የእልልታና የመድኃኒት ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ነው"

መዝ. ፻፲፯፥፲፭ (117፥15)

## እልልታ

በቤተመቅደስ ውስጥ በማኅሌትና በዝማሬው አብሮ ከእግዚአብሔር የሚቀርብ መሆኑንም ከዚህ እንረዳለን። ቅዱስ ዳዊት የጌታችንን ዕርገት በተነበየበት መዝሙሩ እንዲህ ይገልጸዋል።

"ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ፡ ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ" መዝ. ፵፮፥፭ (46፥5)

"አምላክ በእልልታ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ" መዝ. ፵፭፥፭ (45፥5)

እግዚአብሔር በሰጠን አንደበት ለእሱ ምስጋናን ባቀረብን ጊዜ ሁሉ በረከትን ከሰማይ እንወርሳለን። ከየትኛውም ዓለም በላይ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችን ከፈጣሪ ምእመናን እልልታን ያቀርቡበታል።

"ብፁዕ ሕዝብ ዘየአምር የብቦ።"

"እልልታ የሚያውቅ ሕዝብ ምስጉን ነው።" መዝ. ፹፰፥፲፭ (88፥15)

## ጭብጨባ

ከከበሮውና ከጸናጽሉ ከመቋሚያውና ከእልልታው እንዲሁም ከሽብሸባው ጋር ከእግዚአብሔር ምስጋና በማኅሌቱና በዝማሬው በጭብጨባም ልዑል እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይመሰገናል። የእግዚአብሔር ቃል በቅዱስ ዳዊት አድሮ እንዲህ ይላል።

"ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ

ወየብቡ ለእግዚአብሔር በቃለ ትፍሥሕት"

"አሕዛብ ሁላችሁ እጆቻችሁን አጨብጭቡ

በደስታ ቃልም ለእግዚአብሔር እልል በሉ"መዝ. ፵፮፥፩ (46፥1)

ጭብጨባ የድል የደስታ ምልክት ነው። እግዚአብሔርን እንኳን ለምስጋና የተፈጠሩ መላእክትና ሰዎች ቀርቶ ግዑዛን ፍጥረታት ለሰሙ ክብር ይሰጣሉ። በምሥጢሩ ተራሮችና ኮረብቶች የተባሉ (ነገሥታት መኳንንት አንድም ነቢያት፣ ደቂቀ ነቢያት) ያመሰግኑታል እያለ ኢሳይያስ ነቢይ እንዲህ ብሎ በመንፈስ ቅዱስ ተናግሯል።

"እናንተም በደስታ ትወጣላችሁ በሰላምም ትሸኛላችሁ ተራሮችና ኮረብቶች በፊታችሁ እልል ታ ያደርጋሉ የሜዳም ዛፎች ሁሉ ያጨብጭባሉ" ኢሳ. ፶፭፥፲፪ (55፥12)

የነቢዩ የአባታችን የኢሳይያስ ትንቢት የእስራኤልን ከምርኮ መመለስ እግዚአብሔርም እንደታረቃቸው ለሰሙም ምስጋና እንደሚቀርብ ነው። ዛሬ እኛም ከሲኦል ወደገነት መመለሳችንን እያመንን በቅን ከሚፈርደው እንዘምራለን። እርሱም በቀኙ ቀድሶናል በክንዱም ማዳንን አድርጎልናል። ከነቢዩ ከኢሳይያስ ጋር በአንድ መንፈስ የተናገረ ልበ አምላክ ዳዊት ወንዞችና ተራሮች ፍጥረት ሁሉ እንደሚያመሰግኑት ገለጸ።

"ወንዞችም በአንድነት በእጅ ያጨብጭቡ ተራሮች ደስ ይበላቸው። በምድር ሊፈርድ ይመጣልና።" መዝ. ፺፯፥፰ (97፥8)

በጭብጨባ ጊዜ የምናስበው፡- በዝማሬ ጊዜ በምናጨበጭብበት ጊዜ የምናስባቸው ሃይማኖታውያን ምሥጢራት አሉ። ይህም በመጀመሪያ እኛነታችንን ለሠራ ለፈጣሪያችን በፈጠረልን እጅ ለእሱ የምንሰጠው ክብርና ምስጋና ሲሆን ዳግመኛም በዚህ ምስጋና ውስጥ አምላካችን እኛን ለማዳን የደረሰበትን መከራና በጥፊ መመታቱን

እናስባከን። ስለዚህም በሙሉ ኃይላችን እናጨበጭባከን። በዚህ ጊዜ በትንሿ የሕመም ስሜታችን የማይገለጸውን የጌታችንን ሕማምና መከራ መቀበል ሁልጊዜ እናስታውሳለን።

"ወታደሮቹም ከእሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ አኖሩ ቀይ ልብስም አለበሱት እየቀረቡም፡- የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን ይሉት ነበር። በጥፊም ይመቱት ነበር።› ዮሐ. ፲፱፥፪ (19፥2)

## ሽብሸባ

ሽብሸባ በእጅና በእግር እንቅስቃሴ ከዝማሬው ጋር የሚቀርብ ነው። በማኅሌትና በዝማሬ ጊዜ ይልቁንም በወረብ ጊዜ ጸናጽል በቀኝ እጅ መቋሚያ በግራ እጅ ተይዞ በእግር እየተመላለሱ ይሸበሸባል። ምእመናንም እጆቻቸውን ከከበሮው ስልት ጋር እያስማሙ በእጃቸው ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ ያሸበሽባሉ።

የዚህ ሽብሸባ ምሳሌ አንደኛ ሰውና መላእክት በአንድነት የማመስገናቸው ምሳሌ ሉቃስ ፪፡፰-፲፬ (2፡8-14)

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ታቦተ ሕጉ በሚከብርበት ጊዜ በኪዳውንቱ የሚቀርበው ሽብሸባ በሰማይ ካሉ የመላእክት ዝማሬ ጋር አንድ ነው። ይህም ቅዱስና ነቢይ ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔር ታቦት ከአቢዳራ ቤት በመጣ ጊዜ ከመዘምራኑና ከሕዝቡ ጋር እያሸበሸበ የዘመረው ነው። ፪ሳሙ ፮፡፲፪-፲፮

ይህም ምሳሌ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መከራ መስቀል ይዞ የቀራንዮን ተራራ ሲወጣ እንቅፋት ሲመታው ሲወድቅ ሲነሳ የነበረውን በእግር ሽብሸባ ይገለጻል። እጆች ወደ ቀኝና ወደ ግራ መሸብሸባቸውን እንደ ወደ ሄሮድስ እንደ ወደ ጲላጦስ እንደ ወደ ሐና እንደም ወደ ቀያፋ መንገላታቱን እናስብበታን።

# ምእመናን ለዝማሬ የሚጠቀሙባቸው

## መሰንቆ

መሰንቆ መዝ ፻፶፥፫ (150፥3)

ምእመናን ለመዝሙር ከሚጠቀሙባቸው አንዱ የዜማ ዕቃ መሰንቆ ነው። መሰንቆ በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተክርስቲያን መጻሕፍት በብዙ ተጠቅሷል።

> "ዳዊትም በዜማ ዕቃ በመሰንቆና በበገና በጸናጽልም እንዲያዜሙ ድምጻቸውንም በደስታ ከፍ እንዲያደርጉ መዘምራኑን ወንድሞቻቸውን ይሾሙ ዘንድ ከሌዋውያን አለቆች ተናገረ።" ፩ ዜና ፲፭፥፲፮ (15፥16)

> "በከበሮና በመሰንቆም ይዘምሩለት" መዝ. ፻፵፱፥፫ (149፥3)

> "ለእግዚአብሔር በመሰንቆ በመሰንቆና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩ" መዝ. ፺፯፥፭ (97፥5)

በታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ እነዚህን የተወሰኑ ከተመለከትን በመቅድመ ወንጌል በቅዳሴያችን እንዲህ የሚል እናገኛለን።

"ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድአነ ወየብቡ ለአምላከ ያዕቆብ ንሥኡ መዝሙረ ወሀቡ ከበሮ መዝሙር ሐዋዝ ዘምስለ መሰንቆ" (ዋናው ቃሉ የዳዊት ነው።) በረዳን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ የያቆብንም አምላክ አመስግኑ መዝሙሩን ያዙ ከበሮንም ስጡ መዝሙር ከመሰንቆ ጋር የተስማማ ነው።

የሀገረ እስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ታላቁ ሊቅና ቅዱስ አባት አትናቴዎስም በቅዳሴ ድርሰቱ ይህንኑ ከምሥጢሩ ጋር ያነሣዋል። እንዲህ ብሎ፦

> "መዝሙር ሐዋዝ ዘምስለ መሰንቆ"

ከዚህ የምንማረውና የምንመለከተው ምእመናን

እግዚአብሔርን ያመሰግኑበት ዘንድ መሰንቆ የተመረጠ የዜማ ዕቃ መሆኑን ነው።

ምሳሌነቱ፡- መሰንቆ ምሳሌ እንዲከው ይህ አባታችን ቅዱስ አትናቴዎስ መሰንቆ ያልሁት ሃይማኖትን ነው ብሏል።

"መሰንቆሰ ይእቲ ሃይማኖት እንተ ከብሰዋ ሰማዕታት"

"መሰንቆሰ ሰማዕታት የለበሷት ሃይማኖት ናት"

ስለዚህ ምእመናን ይህን በመረዳት ምሥጢሩን ከዝማሬውና ከመሰንቆው በማዛመድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይፈጽማሉ። ትእዛዙም ይህ ነው።"ግነዩ ለእግዚአብሔር በመሰንቆ"

"እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት" መዝ. ፴፪፥፪ (32፥2)

## በገና

"ሰብሕዎ በበገና ወበመሰንቆ"

"በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት"መዝ.፻፶፥፫ (150፥3)

አባታችን ቅዱስ ዳዊት አምላካችንን በበገናና በመሰንቆ በጠቀስናቸው የመዝሙር ዕቃዎች ሁሉ ያመሰግን እንደነበር ሌሎችም አባቶቻችን እና እናቶቻችን እንደርሱ ለእግዚአብሔር ይዘምሩ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ከምስጋናው ተጨማሪ በዚህ ዓይነት ዝማሬ አጋንንትና ርኩሳን መናፍስት ደዌና ሕማም ሁሉ ከሰው ልጆች ይርቁ እንደነበር ዛሬም እንደሚርቁ ተጽፎልናል። ቅዱስ ዳዊት አባታችንን ባሰብን ጊዜ ሁሉ በገናው አብሮ ይታሰበናል። እርሱም በመቶ ሃምሳ እንደኛው መዝሙር እንዲህ ነበር ያለው። ከዕውቀት እንዲሆናችሁ በሌላው ዓለም ይህ መዝሙር አይታወቅም ነበር፡ አሁን ግን በምርምር ከተገኘ በኋላ ብዙዎች ይጠቀሙበት ጀምረዋል። በእኛ ቤተክርስቲያን ግን ከቀድሞ ጀምሮ ተጠብቆ ያለ ቃል ነው። ይህም "በእንተ ርእሱ" ስለ ራሱ የተናገረው ይባላል።

"አደሙየ ይገብራ መስንቆ ወአጻብዕየ ያስተዋድዳ መዝሙረ"

"እጆቼ መሰንቆ ይመቱ ነበር ጣቶቼም በገና ይደረድሩ ነበር"

አባታችን ነቢዩ መዝሙረኛው ዳዊት በገና እየመታ የእግዚአብሔርን ስም ከማመስገን ጋራ በነቢዩ ሳሙኤል በተቀባ ጊዜ ከተሰጡት ከስባቱ ሀብታት አንዱ ሀብተ ፈውስ ስለሆነ ንጉሥ ሳኦል የሚያስጨንቅ ርኩስ መንፈስ ሲያሠቃየው በበገናው ዝማሬ ይፈውሰው ነበር።

"እንዲህም ሆነ ... ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር።

ሳኦልንም ደስ ያሰኘው ያሳርፈውም ነበር ክፉ መንፈስም ከርሱ ይርቅ ነበር።" ፩ ሳሙ. ፲፮ ፥፳፫ (16፥23)

ቅዱስ ዳዊት ለእግዚአብሔር በሚዘምርበት ጊዜ በሙሉ ኃይሉና ክብሩ ነበር። ያልታደለች ሜልኮል እስኪምትቀልድበት ድረስ ለእግዚአብሔር ታቦት ካባው ከላዩ እስኪወድቅ በተመስጦ ይዘምር ነበር።

ይህም በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ ምዕራፍ ስድስት (2 ሳሙ.6) ዛሬም እንደሜልኮል ሰዎች እንዳይደፍሩ የታቦቱንም ዝማሬ እንዳይንቁ ቢንቁ ግን የሚደርስባቸውን ቀድመው እንዲያውቁት እግዚአብሔር ነገሮናል። ሜልኮል የዳዊትን በእግዚአብሔር ፊት መዘመር በናቀች ጊዜ እግዚአብሔር ማህፀኗን ዘጋ። ቅዱስ ዳዊት ግን አሁን ከሆንኩት በላይ ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ በሰው ፊትም እከብረዋለሁ አለ። ዘወትርም እንዲህ እያለ ያመሰግን ነበር።

"በገና ሆይ ተነሥ መሰንቆም እኔም ማልጄ እነሣለሁ" እቤቱ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ መዝ. ፻፯፥፪ (107፥2)

<u>ኢሠራሩና ምሳሌነቱ</u>፡- ራዕ. ፭፥፰ (5፥8) "መጽሐፉንም

በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ" ብሏል።

የበገናን አሠራር ስንመለከት ሁለት ቋሚ ምሰሶዎችን እናያለን የነዚህ ምሳሌነቱ ከሁለቱ ኪዳናት ከብሉይና ከሐዲስ ነው። በነዚህ በሁለቱ ቋሚ ምሰሶዎች መኻከል የምንመለከታቸው ዐሥሩ አውታሮችን ነው። የበገናችን አሠራር ልክ እንደ ቅዱስ ዳዊት በገና ዓይነት ነው። የአውታሮቹ (የጅማቶቹ) ቁጥር ዐሥር ነው።

"ወበመዝሙር ዘዐሠርቱ አውታሪሁ ዘምሩ ሎቱ"

"ዐሥር አውታርም ባለው በበገና ዘምሩለት" መዝ. ፴፪፥፪ (32፥2)

ቅዱስ ዳዊት ዐሥር አውታር ባለው በበገና ዘምሩለት ብቻ ማለት ሳይሆን እርሱ ራሱ ያመሰግንበት የነበረው በገና አሥር አውታሮች የነበሩት ነው።

"እግዚኦ ስብሐተ ሐዲስ እሴብሐከ ወበመዝሙር ዘዐሠርቱ አውታሪሁ እዜምር ለከ"

"አቤቱ አዲስ ቅኔ እቀኝልሃለሁ"

ዐሥር አውታር ባለው በገና እዘምርልሃለሁ መዝ. ፻፵፫፥፱ (143፥9) የእነዚህ ዐሥር አውታሮች ምሳሌነት ከዐሠርቱ ትእዛዛት ነው። ዐሥር አውታሮች በሁለቱ ቋሚ ምሰሶዎች መጽናታቸው። ዐሠርቱ ትእዛዛት በሁለቱ ኪዳናት በብሉይም በሐዲስም ጸንተው ከመኖራቸው ምሳሌ ነው። (ዐሠርቱ ትእዛዛት የሚለውን ይመልከቱ)

በሌላም መልኩ የሚገለጽ ምሳሌነት እንዳለው ከመጽናት በተጨማሪ ዐሠርቱ ትእዛዛት በሁለቱ ትእዛዛት ይጠቃለላሉ። እነዚህም ሁለቱ ሕግጋት ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ናቸው። በትርጓሜ እግዚአብሔርን መውደድና ሰውን መውደድ። ከዚህም የተነሣ በበገናው አሠራርና ምሳሌ ሁለቱ

ቋሚ ምስሶዎች በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ ሲመሰሉ በዐሥር አውታር የተመሰሉት ዐሠርቱ ትእዛዛት በነዚህ በሁለቱ ለመጠቃለላቸው የሚገለጽ ምሥጢር አለው።

"ኦሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ" ማቴ. ፳፪፥፵ (22፥40) ከዚህ ምሥጢር የተነሣ በአኛ ዘንድ ምእመናን እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚሠሩት በገና ምንም እንኳን አንዳንዴ በሰምንት አውታሮች የተሠራ በገና እንዳለ በመጽሐፍ ቢገኝም (1 ዜና ፲፭፥፳፩ (15፥21)) በኛ ዘንድ ግን የሚሠራው ባለዐሥሩ ልክ እንደ ዘማሪው ዳዊት ያለ ነው።

"እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው

ልዑል ሆይ ለስምህም ዝማሬ ማቅረብ

በማለዳ ምሕረትን

በሌሊትም እውነትህን ማውራት

ዐሥር አውታር ባለው በበገና

ከምስጋና ጋርም በመሰንቆ" መዝ. ፺፩፥፩-፫ (91፥1-3)

## መለከት

እግዚአብሔርን በዝማሬ ከሚገለገሉ ሰዎች ከሚጠቀሙባቸው የዜማ ዕቃዎች መካከል መለከት አንዱ ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ነው።

ጠቢቡ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን መቅደስ ካነጸ በኋላ ካህናቱ ታቦቱን ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ሲያስገቡ ከዘመሩበት የምስጋና ዕቃዎች አንዱ ስለሆነው ስለ መለከት እንዲህ ተጠቅሷል።

> "... መቶ ሃያ ካህናት መለከት ይነፉ ነበር። ካህናቱም ከመቅደስ በወጡ ጊዜ መለከቱንም የሚነፉ መዘምራኑም በአንድነት ሆነው እግዚአብሔርን

> እያመሰገኑና እያከበሩ፡- እግዚአብሔር ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ እያሉ በአንድ ቃል ድምፃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመለከትና በጸናጽል በዜማም ዕቃ ሁሉ እግዚአብሔርን ባመሰገኑ ጊዜ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው።" ፪ ዜና ፭፥፲፩-፲፬ (5፥11-14)

የኢያሪኮን ቅጽር መውደቅ ስንመለከት ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው መለከት እየነፉ ሰባት ጊዜ ሲዞሩ ነበር እግዚአብሔር ድልን የሰጣቸው።

> "ሕዝቡም ጮኹ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ነፉ ሕዝቡም የቀንደ መለከቱን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ታላቅ ጩኸት ጮኹ ቅጥሩም ወደቀ" ኢያሱ ፮፥፳ (6፥20)

ዛሬም እኛ ከአምላካችን በዚህ ሥርዓትና ሕግ ስንዘምርለት የኃጢአት ግንብ ይፈርሳል እስራኤል ኢያሪኮን ፈጽመው እንዳጠፏት እኛም በጠላታችን ሰይጣን ላይ ከዘላለም ድልን እናገኛለን።

መለከት ከዝማሬ በተጨማሪ የአዋጅ መንገሪያ ሆኖም ያገለግላል ሕዝቡም የመለከት ድምፅ ሲሰሙ ይሰበሰባሉ።

> "ሁለቱም መለከቶች በተነፉ ጊዜ ማኅበሩ ኹሉ ወደ አንተ ወደመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ይሰብሰቡ" ዘኍልቍ ፲፥፫ (10፥3)

ዘኍልቁ ምዕራፍ አሥርን በምናነብበት ጊዜ መለከት መቼ እንደሚነፉ እግዚአብሔር ከሙሴ እንዳዘዘው እንመለከታለን። ይህም ትእዛዝ ከቁጥር አንድ ጀምሮ እስከ ዐሥር ድረስ ተዘርዝሯል።

መለከት በሚነፋበት በመለከት በሚዘመርበት ጊዜ የምናስበው ምሥጢር አለ። ዝማሬው ድልን ይገልጻል። ይልቁንም ትልቁ ድላችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሣ ሁሉ እኛም በእሱ ኃይል

ሞትን ድል አድርገን በትንሣኤ ተነሥተን አሉን እንደምንለብስ መለከቱ ሲነፋ እስራኤል ወደ ሙሴና ወደመገናኛው ድንኳን እንደተሰበሰቡ እኛም በትንሣኤው መላእከት መለከቱን ሲነፋ በክብር ተነሥተን ወደ አዳኛችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደምንሰበሰብ የዘላለም ቤታችን የሆነችውን ከእርሱ ጋር አንድ ሆነን የምንኖርባትን ሰማያዊ ቤታችንን እንደምንወርስ የሚያስረዳ ነው። ስለዚህ የመለከቱ ድምፅ ሙታንን ሁሉ የሚያስነሣ የአዋጅ ጥሪ ነው። በኢያሪኮ ግንብ መውደቅ ጊዜ የመለከቱ ድምፅ ከእስራኤል ደስታና ኃይል ለኢያሪኮአውያን ኀዘንና ሞት እንደሆነ ሁሉ በጌታ ምጽአትም ጊዜ ከጻድቃን የምስጋና /የዝማሬ/ ከኃጥአን ግን የልቅሶና የዋይታ ድምፅ ይሆናል።

"ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእከትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና" ፩ ተሰ. ፬፥፲፮ (4፥16)

"... መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ ..." ፩ ቆሮ ፲፭፥፶፪ (15፥52)

የሥሩግ ኤጴስ ቆጶስ ቅ/ያዕቆብ እንዳለው፡-"ይከውን ንፍሐተ ቀርን ፫ተ ጊዜ" "ሦስተ ጊዜ የመለከት መነፋት ይሆናል"

በመጨረሻም ልናስተውለው የሚገባን በመለከት መዘመር ለጦርነት መዘጋጀት ነው። ጦርነቱም ከጨለማ አበጋዞች ከርኩሳን መናፍስት ኃይል ጋር ነው። የመለከቱም ድምፅ ከዝማሬው ጋር ሲወጣ ኹልጊዜ ድሉ የክርስቲያኖች ነው።

"የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ... ከከፋት መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።" ኤፌ. ፮፥፲፩ (6፥11)

## ከራር

ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ከመስጠት ከሚዘምርባቸው

አንዱ የዜማ ዕቃ ክራር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተወሰኑ ቦታዎች ተገልጿል። ሰዎች እግዚአብሔርን በዝማሬ እንደሚያመሰግኑበት በምሳሌ የገለጸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው።

"ነፍስ የሌለበት ነገር እንኳ ዋሽንትም ክራርም ቢሆን ድምፅ ሲሰጥ የድምፁን ልዩነት ባይገልጥ በዋሽንት የሚነፋው ወይስ በክራር የሚመታው መዝሙር እንዴት ይታወቃል?" ፩ ቆሮ. ፲፬፥፯ (14፥7)

ይህ የሚገልጽልን በክራር ከእግዚአብሔር ዝማሬ ይቀርብበት እንደነበር ነው። የሌለን ነገር ሐዋርያው አይጠቀስምና። የክራር አሠራር ስድስት አውታሮች (ጅማቶች) አሉት። እነዚህም ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን እንደሚመስሉ የሚናገሩ አበው አሉ።

## ዋሽንት፣ እንዚራ፣ እምቢልታ

በመጽሐፍ ቅዱስና በሌሎችም መጻሕፍት አገላለጽ ዋሽንት፣ እንዚራና እምቢልታ አንድ ዓይነት የዜማ ዕቃዎች ይመስላሉ፡ ተመሳሳይነት አላቸው።

"›ሰብሕዎ በአውታር ወበእንዚራ›

"በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት" መዝ. ፻፶፥፬ (150፥4)

ከዚህ የቅዱስ ዳዊት ቃል እንደምንረዳው እንዚራ የተባለው እምቢልታ ከመሆኑ ግልጽ ነው። አሠራሩም በአብዛኛው ቀርከሃ (መቃ) ከተባለ እንጨት ነው። ይህ ደግሞ ከዋሽንት ጋር አንድ አይነት እንደሆነ ይገልጽልናል። ዛሬም ምእመናን ታቦተ ንግሥ በሚሆንበት ጊዜ እምካከን ያመሰግኑበታል። ይህም በመጽሐፍ የተገለጸ እግዚአብሔርም የሚወደው ነው።"እንዲሁ እስራኤል ሁሉ ሆ እያሉ ቀንደ መለከትና እምቢልታ እየነፉ ጸናጽልና መሰንቆ በገናም እየመቱ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት አመጡ።" ፩ ዜና ፲፭፥ ፳፰ (15፥28)

መለከትና እምቢልታ እየነፉ የሚለው ሐረግ እምቢልታ የሚነፉ የዜማ ዕቃ እንደሆነ ይገልጻል። ይህም የመጠን ልዩነት ይኑረው እንጂ ከዋሽንትና ከእንዚራ ጋር አንድ መሆኑን ያሳያል።

እንዚራ በትንፋሽ እየነፉ የሚያመሰግኑበት የዜማ መሣሪያ ከመሆኑ አባታችን አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ኢትዮጵያዊው በሰዐታት ድርሰቱ እንዲህ ብሏል።

> "ወእስተንፍሲ ውስተ አፉየ ከመ እኩን ዕንዚራሁ ለበኩርኪ."

ከራርን በተመለከትነበት አንቀጽ እንዳየነው ቅዱስ ጳውሎስ ዋሽንትን ጠቅሶ አስተምሮናል። ይህም በ፩ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ፲፬ ቁጥር ፯ የተገለጸው ነው። በመዝሙር ፺፯፥፭ (97፥5) እንዲህ ይላል "በመለንቆና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩ በዋሽንትና በመለከት ድምፅ"

**እነቃቅቶ ካስጀመረኝ፣ አተጋግቶ ካስፈጸመኝ፣ ከልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።**

# ዋቢ መጻሕፍት

ሃይማኖተ አበው፡ 1986 ዓ.ም፡ ትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

መጽሐፈ ሄኖክ አንድምታ ትርጓሜ፡ 2003 ዓ.ም፡ ትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

መጽሐፈ መነኮሳት፡ ማር ይስሐቅ፤ 1982 ዓ.ም፡ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት ፤ አዲስ አበባ

መጽሐፈ መነኮሳት፡ ሁለተኛ መጽሐፍ ፊልክስዮስ (ገብረ ክርስቶስ) ንባብና ትርጓሜው፡ 1982 ዓ.ም፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

መጻሕፍተ መነኮሳት፡ ሦስተኛ መጽሐፍ አረጋዊ መንፈሳዊ ንባብና ትርጓሜው፡ 1982 ዓ.ም፡ በተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

መጻሕፍተ ብሉያት፡ ፩ቱ እሙ እሙንቱ አሪት ዘፍጥረት (ዘፀደት) ኦሪት ዘፀአት አንድምታ ትርጋሜ፡ 1999 ዓ.ም፡ ትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

መጻሕፍተ ብሉያት፡ ሠልስቱ እሉ እሙንቱ ኢያሱ፡ መሣፍንት፤ ሩት ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

መጻሕፍተ ብሉያት፡ ፫ቱ እሉ እሙንቱ ፤ኦሪት ዘሌዋውያን ፤ ኦሪት ዘሁልቁ ኦሪት ዘዳግም አንድምታ ትርጓሜ፡ 1999 ዓ.ም፡ ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት

መጽሐፈ ስንክሳር፡ ግእዝና አማርኛ ከመስከረም-የካቲት፡ 1994 ዓ.ም፡ትንሳኤ ማተሚያ ቤት

መጽሐፈ ስንክሳር፡ ግእዝና አማርኛ 1993 ዓ.ም፡ መጋቢት-ጳጉሜ፡ ትንሳኤ ማተሚያ ቤት

መጽሐፈ ኩፋሌ፡ አንድምታ ትርጓሜ፡ 2006 ዓ.ም፡ ትንሳኤ

ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

መጽሐፈ ቅዳሴ፡1989 ዓ.ም፡ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

መጻሕፍተ ነገሥት አርባዕቱ በአንድምታ ትርጓሜ፡ 2000 ዓ.ም፡ ትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

መጽሐፈ ዲድስቅልያ (ዘአበዊነ ሐዋርያት)፡ 2004 ዓ.ም፡ ትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

መዝሙረ ዳዊት ዘምስለ ነግሥ፤ 1987 ዓ.ም፡ ተሰፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፡1982 ዓ.ም፡ተሰፋ ገብረሥላሴ፡አዲስ አበባ

መጽሐፈ ግጻዌ፡ 1977 ዓ.ም፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መጻህፍት፡ 1980 ዓ.ም ፡ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

መሐሬ ትርፌ (ኪቀ ኪቃውንት)፡ 1989 ዓ.ም፡ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ፡ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

ሰዓታት፡ ዘሌሊት ወዘነግህ፡ 1989 ዓ.ም፡ ተሰፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፡ 1988 ዓ.ም፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው፡ 1988 ዓ.ም፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ

ያሬድ (ቅዱስ) 1998 ዓ.ም ፤ መጽሐፈ ድጓ ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡ ትንሳኤ አሳታሚ፡ አዲስ አበባ

ያሬድ (ቅዱስ) 1986 ዓ.ም፤ ዝማሬ መዋስዕት ፤ ትንሳኤ

ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

ዳንኤልና አስራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት፡ 1998 ዓ.ም፡ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

ድርሳነ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንባብና ትርጓሜ፡ 1987 ዓ.ም፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

ውዳሴ ማርያም ንባብና ትርጓሜው፡ 1983 ዓ.ም፡ ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው፡ 1990 ዓ.ም፡ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፡ አዲስ አበባ

መጽሐፈ ባሕረ ሐሳብ (አቡሻኽር)

መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

# መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት

ይህ መጽሐፍ መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት ተብሎ ተሠይሟል። አሚን ማለት ሃይማኖት ሲሆን ሥርዓትም ሃይማኖት የሚገለጽበትን ሕግጋት ያመለክታል። ከቀድሞ አበውና እማት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የትርጓሜ ስልትና የእምነት ሥርዓት እንዲሁም ትውፊት ሳይቀር እየጠቀመ ይነግረናል።

መጽሐፈ አሚን ወሥርዓትን ያነበበ ሰው ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነቱ በቂ የሆነ መረጃ ያገኛል። ለሚነሱም ጥያቄዎች መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት የተዘጋጀ መልስ ነው። በሌላ እምነት ያለ ሰው ይህን መጽሐፍ ካነበበ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሥርዓተ አምልኮን በሚገባ ይረዳል። የእምነቲቱንም እውነተኛነት ያውቃል።

መምህር ዶ/ር ዘበነ ለማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መምህረ ሃይማኖት የቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ከንባብ እስከ ትርጓሜ ሥርዓተ ቅዳሴን ከታላቁ ብጹዕ አባት አቡነ ሰላማ እና ከታላቁ ሊቅ ከመጋቤ ምስጢር አለቃ መሠረት ተሰማ የተማሩ፤ በነገረ መለኮት ትምህርት ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በዲግሪ በመጨረስ ከዚያም በአሜሪካን ሀገር በዋሺንግተን ዲሲ በሚገኘው በታወቀው የሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ በማስተርስ ስለ ዓለም እምነቶች ጥናትና በፍልስፍና እንዲሁም በዶክተሬት ዲግሪ በሥነ አመራርና አንትሮፖሎጂ ጠናትበከፍተኛ ማዕረግ ተመርቀዋል። በአንደኝነት ደረጃም አጠናቀዋል። በቡዊ ስቴት ዩኒቨርሲቲ በአጃንክት ፕሮፌሰርነትና በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ ገስት ፕሮፌሰርነት ያገለግላሉ። በአሜሪካን ሀገር በደብረ ገነት መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የደብሩ አለቃ ናቸው። ኑሯቸውም በአሜሪካን ሀገር በቨርጂኒያ ግዛት ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ኅሊና ታደሰ ጋር ነው።